ድል ነሺ ሕይወት

በዎች ማን ኒ

ተርጓሚ ነብዩ ኢሳይያስ

አሳታሚ፡- ሕይወት ሥነጽሑፍ አገልግሎት
ፖ·ሣ·ቁ· 698 ስልክ 13 15 70
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ጥቅምት 1990 ዓ/ም

የመጀመሪያ ዕትም ጥቅምት 1990 ዓ/ም
ሁለተኛ ዕትም ሚያዝያ 1990 ዓ/ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
First Edition October 1990 (1997)
Second Edition April 1990 (1998)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
The Life that win's by Watch Man Nee
copyright 1986
Christian Fellowship publishers, Inc.
New York. U.S.A
ከሚለው መጽሐፍ ነው ።

Published - by Heywet Literature services
P.O.Box 698 Tel 13 15 70
Addis Ababa, Ethiopia
October 1997

ማውጫ

መቅድም

ገጽ

1. ልምምዳችን 7

2. የክርስቲያን ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው..... 20

3. የድል ሕይወት ባህርይ.....35

4. ወደ ድል ሕይወት እንዴት እንደሚገባ 53

5. መተው 70

6. እምነት 84

7. የእምነት ፈተና 99

8. ማደግ.....112

9. የድል ድምፀት 129

10. መለየት.....141

መቅድም

ድል ነሺ ሕይወት ምን ዓይነት እንደሆነ ታውቃለህ? ስለምትኖረው የክርስትና ሕይወት ዓይነት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ታፍራለህ? በክርስትና ሕይወት ኑሮህ ውስጥ ድል ለመንሣት ስትጥር በሚያሳዝን ሁኔታ ወድቀህ እንደ ጳውሎስ «እኔ ምንኛ ጕስቋላ ሰው ነኝ፣ ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ብለህ ጮኸኻል? ሮሜ 7:24። እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ በኩል አመስግን። ድል ነሽ ሕይወት በጥረትና በትግል የሚገኝ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። ሮሜ 7:25

ድል ነሺ ሕይወት ከጌታ ለአማኞች የተሰጠ ነው። ይህ በጥቂቱ የተለወጠ ሳይሆን ፈጽሞ የተቀየረ ሕይወት ነው። ድል ነሺ ሕይወት ያለፈውን ባህርይ በመጫን የሚመጣ ሳይሆን አዲስ የሚገለጥ ሕይወት ነው። ድል ነሺ ሕይወቅ በውስጥህ በሚኖረው በክርስቶስ እንጂ በራስህ ጥረት የሚገኝ አይደለም። በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምን እግዚአብሔር የሰጠህ አንተም የተቀበልከው እንዲህ ያለ ሕይወት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ኅብረትን የሚፈጥር ኃጢአትን ድል የነሣ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት እርካታና ሰላም እንዲሁም ኃይል የሞላበት ሕይወት ነው። ይህ በአንተ ውስጥ ሆኖ መገለጥን የሚጠብቀው ሕይወት እንዴት ይመጣል ብትል በምትከህ ክርስቶስ እንዲኖር በመፍቀድ ነው። ይህ እምነት የሚጠይቅ ጎዳና ነው እምነቱም ለመዳን ያመንከውን ዓይነት ነው። ከዚህ በኋላ በወደደህ በእርሱ ከአሸናፊዎች ትበልጣለህ። ሮሜ 8:37

ይህን ድል የሚነሣ ሕይወት አማኞች እንዲለማመዱት ይረዳቸው ዘንድ ዎችማን ኒ «ድል ነሽ ሕይወት» በሚል ርዕስ ላይ በርካታ ተከታታይ መልእክቶችን እ.ኤ.አ. 1935 ዓ.ም. በመስከረምና በጥቅ ምት ወሮች በቻይና ውስጥ ሻንጋይ በምትባል ከተማ በተደረገው ኮንፍራንስ ላይ ተናግረዋል። ዎችማኒ እንደ ወትሮው ሰፊና መንፈሳዊ

ጥልቀት ባለው ትምህርታቸው በቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ በዚህ ቋሚ ርዕስ ላይ ሙሉ በሙሉ አስተምረዋል።

ዎችሚ በዚያ ከንፍራንስ በሚያሳፍር ሁኔታ ከሚገባው በላይ በዘቀጠው በአማኙ የግል ልምምድ ላይ ነው ትምህርታቸውን የጀመሩት። ከዚያ በኋላ በንፅፅር ከእግዚአብሔር ለአማኙ የተሰጠውን የክርስትና ሕይወት አስረዱ፣ ቀጥሎም ወደዚህ ሕይወት የምንገባበትን መንገድ ከግሣየታቸው በፊት የዚህን ሕይወት ምንነት በበለጠ አስተማሩ፣ ዘረዘሩም። የድል በር ግጥረሚ መንገዶች ለምን እንደሚሰውሩብን ምክንያቶችን አብራሩ። በመቅጠልም ስለ እምነት መፈተን ለእድግሎታቸው አስጠነቀቁ። አማኞች በእግዚአብሔር ጸጋ እንዲያድጉ መከሩ፣ የድል ድምጽ የሆነው ምስጋና እንዲኖርም አጽንተው ገለጡ። በመጨረሻም ከድል በኋላ የመጀመሪያና የመጨረሻ ድርጊት በሆነው የመቀደስ ወይም የመለየት ውጤት ደመደሙ። አሁን እነዚህ መልእክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ተተርጉመው ለአንባቢያን ቀርበዋል።

የክብር አምላክ የራሱን ሕይወት በኛ ውስጥ በማናሩ ይክበር።

«ሁሉ ከእርሱና በእርሱም ነውና ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን» ሮሜ. 11–36

ተርጓሚው

ስለ መጽሐፉ

በሐገራችን የክርስቲያን ሥነጽሑፍ ረድፍ የትርጉም ሥራዎች ያዋሉት አስተዋጽኦ የሚያስመሰግን ሲሆን፣ ከታላት ገበያው ጀምሮ የሃጉብ ተዋረድን በመጠበቅ በሁለት ሕብረተሰብ መሐከል ያለውን የባህልና የአገላለጽ ልዩነቶችን በግጥበብ፣ የመጽሐፉን ለዛ ሣያዛንፉ ለውጤት መብቃት በራሱ የሚያስተምነው ዋጋ ሚዛኑ ይደፋል። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚም ለሃገራችን አንባቢ በሚስማማ መልክ ይህን መጽሐፍ ለማቀነባበር ያደረገው ጥረት እድካሚ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስትናን ሕይወት በራሣችን ጥረት እንደማንኖረው፣ በራስ ትግልም ቅድስና እንደማይቃና አጥርቶ ቢያስተምርም እውነታውን ደጋግመን የምን ስተው ጥቂቶች አይደለንም። የጨለማው አለቃ ሰይጣን ሰዎችን የሚሸነግልበት፣ የሚከስበትና የቅጥፈት ብልጣብልነቱን የሚያሣይበትና በዓለማችን ያሉ የበርካታ ሃይማኖቶች አንደኛው መታለልም ቅድስናን በእኛነታችን ትግል ለማግኘት የሚደረገው ግብግብ ነው።

ሰዎች ከእውነታው ተራርቀው ጥረት ባጀበው ምግባረ ሰናይነት እግዚአብሔርን ለማክበርና ለማስደስት ከሞከሩ ውጤቱ ተስፋን ማጨጠጥ ይሆናል። ይህ መጽሐፍም እግዚአብሔር ያዘጋጀልን ድል ነሺ ሕይወት በትንቅንቅና መፍጨርጨር የሚገኝ ሣይሆን እንደ ደህንነታችን ሁሉ በእምነት የምንቀበለው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን ባማከለ መልኩ ያብራራል።

መለኮታዊው የእግዚአብሔር ፈቃድ ከመጀመሪያውም ሆነ ዛሬም ሰዎች በእግዚአ ብሔር ላይ ብቻ በመታመን እንድንኖረው ተደርጉ የተቀናጀ ነው። በዓለም ዙሪያ በመጽሐፍቶቻቸውና በትምህርቶቻቸው ታዋቂና ተወዳጅ የሆኑት አገልጋይና የበርካታ መጽሐፍት ፀሐፊም የሆኑት ዎች ማንኒም ሊያሣዩን የሚወዱት ይህንኑ የቀላል ሕይወት እውነታ ነው።

ነብዩ ኢሣይያስ ለትርጉም የመረጠው ይህ መጽሐፍ የክርስትና ሕይወት አብይ ጭብጥ የያዘና በብዙ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ስኬታማ ሥር ነቀል ለውጥን የሚያመጣ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም።

ተርጓሚው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት እንዳደረገ በተደጋጋሚ ያስተምራቸው ከነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና ይህን መጽሐፍም በአርታዒነት ስሠራለትም ለመረዳት ችያለሁ። በትርጉም ሥራው ውስጥ ያሣየው ጥረት የሚያበረታ ታና ሌሎችንም የሥራ ውጤቶችን እንዲያቀርብልን ይላመድህ የሚያሰኘው ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ደረጀ አበበ

ምዕራፍ አንድ

ልምምዳችን

«እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድር ብኝ ሕግን አገኛለሁ።» ሮሜ 7:21 «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጕደ ኵአቸ ዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል፤ እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።» ሮሜ. 3:23

ለክርስቲያኖች የተሰጠ ሕይወት

ቅዱሳት መጻህፍት እንደሚነግሩን ለክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሕይወት ፍፁም ደስታና ዕረፍት ያለበት፤ ከእግዚአብሔርም ፈቃድ ጋር ፍፁም የተዋሐደ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ሕይወት ዓለምን የማይራብና የማይጠማ ከኃጢአት ውጭ የሚራመድና ሁሉን ነገር ሰን ጥቆ የሚያልፍ ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ቅዱስ፤ ኃይለኛ፤ ድል ነሽና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅ ከእርሱ ጋር የማያቋርጥ ግንኙት የሚያደርግ ሕይወት ነው።

እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የሰጠው ሕይወት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር በእግዚአብሔር ውስጥ የተሰወረ ነው። ይህን ሕይወት ምንም ነገር አይነካውም፤ አይጐዳውም፤ አያናውጠውም። ክርስቶስ ሁሉን አልፎ እንደሚሄድ እኛም ሁሉን አልፈን እንሄዳለን። ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት እንደሆነ እኛም በእርሱ ፊት ነን። ስለዚህ እንደክግለን፤ እንሸነፋለን የሚል ነገር ሁለተኛ በሃሣባችን አናስተናግድ፤ መድከም ወይም መሸነፍ የሚባል ነገር የለም። ምክንያቱም በቆላ. 3:4 ላይ እንደተፃፈው «ክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወታችን ነውና»። ክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን ያል ፋል፤ በምንም ነገር ሊሸነፍ፤ ሊያዝ አይችልም። የክርስቶስ ሕይወት ይህ ነው። ሃሌሉያ!

የተሰጠን ሕይወት ዕረፍት፣ ደስታና ኃይል የሞላበትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም የሚችል ነው። እስቲ ዛሬ ምን ዓይነት ሕይወት እንደምንኖር እንጠይቅ። ሕይወታችን እግዚአብሔር እንድንኖረው የሰጠን ዓይነት ካልሆነ ድል ምን እንደሆነ እንደሚገባ ማወቅ ይኖር ብናል። ስለዚህ ልምዳችንን በተመለከተ አንዳንድ እውነቶችን ከዚህ በታች አብረን እንድንመለከት እፈልጋለሁ። እነዚህ እውነታዎች ለአንዳንዶቻችን ላይስማሙ ይችላሉ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል እውነትነታቸው ልንቀበላቸው ይገባል። ጉድለታችንን ተረድተን ጸጋን ከእግዚአብሔር መለመንና መቀበል እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን።

በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ያሉ ስምንት ዓይነት ውድቀቶች

ምን ዓይነት ሕይወት ነው የምትኖረው? በኃጢአት ባርነት ሥር? ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7:18 ላይ እንዲህ ይላል «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፣ ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም» ይህ በእኛ በአማኞች ልምምድ ውስጥ እውነት ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ የከበረ ድል አድራጊ ሕይወት ሰጥቶን ሣለ እኛ ግን በሽንፈት ሕይወት እንኖራለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደ ተፃፈውና በልምምዳችንና በምርምሮችም እንደተረጋገጠው በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ስምንት ዓይነት ውድቀቶች ወይም ኃጢአቶች ይገኛሉ ብለን መደምደም እንችላለን።

1. የመንፈስ ኃጢአቶች

ትዕቢት፣ ቅንዓት፣ አለማመን፣ ስህተት ፍለጋ፣ የጸሎት ማነስና ራስን ለእግዚአብሔር አደራ አሣልፎ አለመስጠት፣ እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ኃጢአቶች ናቸው። ምንም እንኳ አንዳንድ አማኞች በመንፈሣዊ ሕይወታቸው ድል አድራጊዎች ቢሆኑም ሌሎች ደግሞ በእነዚህ ኃጢአቶች የተሸነፉ ናቸው።

በአንድ ወቅት የትዕቢት ኃጢአት አስቸግሮኝ ነበር። ኩሩዎች ሁሉ የዚህን የመንፈስ ኃጢአት ፈጽመዋል። ኩሩ ሰው ሌሎች ከእርሱ ሊበ

ልጡ እንደሚችሉ ማየት አይችልም። ይህ በዓለማውያን ብቻ ሣይሆን በክርስቲያኖችም ላይ የሚታይ ነው። ሌላ ሰው የሚበልጠው ሲመስለው ሁልጊዜ ስህተት ይፈልጋል። ዝቅ ሊያደርገውም ይሞክራል።

ቅንዓት በሥራም ሆነ በመንፈሣዊ ነገሮች ቢከሰት ኃጢአት ነው። አንዳንዶች ደግሞ ባለማመን ክፉ ልብ ተሞልቶዋል። አንድ አማኝ በእግዚአብሔር የሚያምን መሆኑን ቢጠየቅ የሚያምን መሆኑን ይመልሳል፤ ነገር ግን በአጸደፈታው በተስፋ ቃሉች ላይ በእውነት የሚያምን መሆን አለመሆኑን ቢጠየቅ የማያምን ሆኖ ያገኛል። በጣም ትንሿ ፈተና ታና ውጠዋለች። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሉች ሊያምን አልቻልምና ነው። በአንድ ወቅት ማርቲን ሉተር በጣም አዝኖ ስለነበረ ሚስቱ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሉች ለማመን ተሸንፎ ስላየችው የሐዘን ልብስ ለበሰችና፤ «ዛሬ የሐዘን ልብስ ለብሻለሁ ምክንያቱም ልክ እምላ ከሀ እንደ ሞተ ያህል በጣም ተጨንቀሃልና» ስትል ተናገረችው በእኛም ዘመን ይኸው እውነት ነው።

ብዙዎች በእግዚአብሔር ተማምነው አይኖሩም። ከእርሱም ጋር መልካም ግንኙት የላቸውም፤ በግድ የለሽነትም ይኖራሉ። ብዙ ቀናትም ያለ ጸሎትና ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ያሳልፋሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ማምንቱን ሙሉ ሣይገናኙ ቀን በቀንም ጌታን ሣይፈሩ ይመላለሳሉ። ይህም በእግዚአብሔር ፊት የማይኖሩ መሆናቸውን ያሣያል። እንዲህ ዓይነት አማኞች የተትረፈረፈ ሕይወት የላቸውም። ራሰንም መግዛት በሚጠይቅ ነገር ላይ የተገዛ ማንነት የላቸውም፤ ፈጽሞም ራሣቸውን አልካዱም።

ችፎ በምትባል ቦታ ውስጥ አብረው የሚኖሩ ሁለት ወንድሞች በማይረባ ነገር ተጣልተው እንደነበረ ትዝ ይለኛል። አብረው በበሉ ቁጥር አንደኛው ወንድም ከምግቡ ውስጥ ደህና ደህናውን ሥጋ እያነሣ ይጨላ ነበር። ሌላው ወንድም ይህንን ድርጊቱን ተመለከተና አንድ ሁለት ማምንት ዝም አለው። ከሁለት ማምንት በኋላ ግን ከዚህ በላይ ነገሩን መታገስ አልቻለምና ራሱን ከዚህ ወንድም ለየ። እዚህ ላይ በትልልቅ ነገሮች ሣይሆን በትንንሽ ነገሮች የሰዎች ማንነት ሊገለጥ እንደሚችል መመልከት እንችላለን። በዚህ ረገድ ያነበብኩትን የሀድሰን ታይለርን

የሕይወት ታሪክ አስታውሳለሁ። ይህ ወንድም ወንጌል ለመስበክ በሚዘዋወርበት ቦታ ሁሉ የማይረባ ክፍልና አልጋ ይደርሰዋል፤ ይህም ቢሆን ግን ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለአንድም ቀን እንኳ በፍፁም ተግሮና አጉረምርሞ አያውቅም። ይህ ቀላል ነገር ቢሆንም የአንድ ሰው ስሜት በትንሽ ነገር ሊጐዳ ይችላል። ሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ምን ዓይነት እንደሆነ ያሳየናል።

2. የሥጋ ኃጢአቶች

የመንፈስ ብቻ ሣይሆን የሥጋም ኃጢአቶች አሉ። እነርሱም ዝሙት፣ ቅብዝብዝነት እንዲሁም ተገቢ ያልሆነ ወዳጅነትና ግንኙነቶች የመሳሰሉት ናቸው ብዙዎች በእነዚህ ኃጢአቶች ይወድቃሉ። አንዳን ዶች ዝሙትን በመፈፀም በገዛ ሰውነታቸው ላይ ኃጢአትን ይሠራሉ። እንዲሁም ሌሎች በዓይናቸው ኃጢአትን ይሠራሉ። ብዙዎች ደግሞ ከማያምኑ ጋር ተገቢ ያልሆነ ጓደኝነት ይመሠርታሉ።

ዓይኖችህን ተቆጣጥርህ ታውቃለህ? በዚህ ዘመን በዓይን ብዙ ነገር የማየት ሉጋጣሚ እንዳለ አውቃለሁ። ዓይኖቻቸውን መቆጣጠር ባለመ ቻላቸው ወደ ድል መምጣት ያልቻሉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ይህን በተመለከተ ግን በእግዚአብሔር ፊት አንድ ነገር ማድረግ አለብን። ወዳጅነትም እንዲሁ ሊታሰብበበት የሚገባ ነገር ነው። በአንድ ወቅት አንድ ወንድም ከማያምን ሰው ጋር አጥብቆ ወዳጅነት ያዘ። ይህ ሁኔታ በዓለም አመለካከት እንደ ኃጢአት አይታይም። ክርስትያኖች ለሆንን ግን ኃጢአት ነው። አንድ ሚሲዮናዊን አንዱ ቀርቦት ከሁሉ በላይ ጓደኛዬ ላድርግህ እንዳለው መስክሮልናል። ከተገቢው በላይ ከማያምኑ ጋር ወዳጅነት መመሥረት የተከለከለ ነው። 2ኛ ቆሮ. 6:14

3. የአእምሮ ኃጢአት

ብዙዎች የመንፈስ ኃጢአት ላይፈጽሙ ይችላሉ። ሥጋቸውም ተገ ዝቶ ሊሆን ይችላል። በአእምሯቸው ግን ድል የላቸውም። ሃሣባቸው ከኃ ጢአት ነፃ አይደለም፤ ወጣ ይላል፤ ይነሆልላል፤ ይበተናል። ንፁሕ አይ ሆንላቸውም፤ ይቆሸሽባቸዋል፤ ወይም ደግሞ በጣም ግምታዊና በጥር

ጣሪ የተሞላ አለትጥ ለማወቅም የሚጓጓ ይሆንባቸዋል፤ ባወቁት አይረ ኩም። የማይታወቀውን ለምን አይታወቅም ይላሉ። እንዲህ ዓይነት አእ ምሮ ያላቸው ሰዎች ወደ ድል ነሽ ሕይወት አይገቡም።

እንደ እውነቱ ከሆነ በአእምሯቸው ድልን የሚለማመዱ አማኞች በጣም ጥቂቶች ናቸው። በአንድ ወቅት ሃጣቢ ለምን እንደሚነሆልልባት ያልገባት አንዲት እህትና ሃጣቡ ሁልጊዜ እንደሚቆሽሽበት የመለከረ አንድ ወንድምም አጋጥመውኛል። መንፈሳዊውን ሕይወት ለመኖር በዚህ አካባቢ መፍትሔ ማግኘት አለብን።

ግምትና ጥርጣሬ ብዙ ክርስቲያናችን ጐድቷል። ለምሳሌ ፊቱ የጨ ፈገገ አንድ ወንድም በመንገድ ላይ ብታገኝ ወዲያውኑ የምትገምተው ምንድነው? በእኔ ላይ ደስተኛ አይደለም ነው የምትለው፤ ነገር ግን ቤቱ አብረኸው ብትሄድ ባለፈው ሌሊት ደህና እንቅልፍ እንዳልተኛና ራሱን እንዳመመው ይነግርሃል። ነገር ግን በአንተ ላይ አንድ ደስ ያላለው ነገር እንዳለ ገምተሃል! እውነቱ ግን ያ አይደለም።

በግምት ምን ያህል ተጐድተናል? ያም ሆኖ ግን ራሳችንን እንደ መርግሪ አድርገን እንቆጥራለን። ኩላሊትንና ልብን የሚመረምር ጌታችን ብቻ መሆኑን እናስታውስ። ራዕይ 2:23 ብዙዎች በስህተት እገሌና እገሊት እንዲሆና እንዲያ ናቸው ይላሉ። እንዲህ በማድረግ በአእምሯ ችንም ኃጢአት ሠርተናል። ለራሳችን ጥቅም ለማምጣት በሰዎች ላይ ብዙ ፈርደናል! ብዙም ገምተናል። ስለ አእምሯችን በእግዚአብሔር ፊት መፍትሔ ማግኘት አለብን፤ ያለበለዚያ በምን ተአምር ነው ወደ ድል ነሺ ሕይወት የምንመጣው?

አንድ ወንድም ልክ በሌለውና ባልተገራ የማወቅ ፍላጐት ተሞልቶ ነበር። የሁሉንም ነገር ምክንያት ማወቅ ስለነበረበት ሁሉን ተነተነ፤ መረ መረ አእምሮው ግሰብ ከሚገባው በላይ ስላወቀ በመጨረሻ በጥርጣሬ ተሞላ።

4. የሰውነት ወይም የአካል ኃጢአት

በአካል ላይ የሚፈጽሙ አንዳንድ ድርጊቶች በዓለም ችላ ሊባሉ ይችላሉ። ለመንፈሣዊ ነገር ራሱን ላስገዛ ክርስቲያን ሕይወት ግን ኃጢ

አቶች ናቸው። አንዳንድ አማኞች ለመብል፣ ለመጠጥ ወይም ለመሸቀርቀርና ለእኔነታቸው ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። በእግዚአብሔር ዓይን እነዚህ ኃጢአቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

ብዙ ክርስቲያናች የግድ መብላት አለባቸው። ክርስቲያን ከሆኑ አንስቶ ያመው አያውቁም። ከእነርሱም ጋር በመብላት ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ አበላላቸው ወዲያውኑ ይነግርሃል። ቢላዋና ሹካ ሲያነሱ እነማን እንደሆኑ ታውቃቸዋለህ። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ያገኘሁት ወንድም የምግብ ፍላጐቱ ከመደበኛው የሰው የምግብ ፍላጐት ምን ያህል ትልቅና ልዩ እንደሆነ ነግሮኛል። በአመጋገብ ላይ ራስን ያለመግዛት ኃጢአት ሊሆን እንደሚችል ሣልናገር አላልፍም።

አንዳንዶች ከተለመደው የመኝታ ሰዓት ጥቂት አሣንሰው ከተነሱ ወዲያውኑ ሐዘንተኞች ይሆናሉ። ከዚህ የተነሣ በሥራ ላይ ይጣደፋሉ፣ ንግግራቸው የተምታታ ይሆናል፤ ይህም ኃጢአት ነው። አንዳንዶች ማጌጥ በጣም ይወዳሉ። ይህ ሁሉ ምንድነው? እኔነትና የራስን ሕይወት መውደድ አይደለምን? ጥቂት መከራ መታገስ ወይም ወደ በሽተኛ በጣም ፡ ፡ቅረብ እስክ ማይችሉ ሕይወታቸውን የሚወዱ ብዙዎች አሉ። በግልጽ ለማስቀመጥ ለሰውነታቸው ባርያዎች ናቸው። ጳውሎስ ግን እን ዲህ ብሏል፣ «ሥጋዬን እየጐሰምሁ አስገዛዋለሁ» 1ኛ ቆሮ 9፥27። ሰውነታችን እንዲገዛን ከፈቀድንለት ያ ኃጢአት ነው። ሰውነታችን ከእኛ በታች እንጂ በላይ መሆን የለበትም። ብዙዎች መተኛት ስለሚፈልጉ የማለዳ ጸሎትን ችላ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ መብላትና መሽቀርቀር ስለሚወዱ እግዚአብሔርን ማገልገል አልቻሉም። ስእነዚህም የሰውነት ፍላጐቶች ምክንያት ራስን አለመግዛት ኃጢአት ነው።

5. የባህርይ ኃጢአት

ባህርይ ማንነትን የሚያመለክት ነው። ሁሉም ሰው የተወለደው በተለ ያየ ዓይነት ባህርይ ነው። በተለያየ ዓይነት ባህርይ መወለዳችን በማንነ ታችን ውስጥ ልዩ ባህርይን ይፈጥራል። ሆኖም ግን ጌታ ከባህርያችንና ከኃጢአታችን ሊያድነን መጥቷል። አንዳንድ ሰዎች በግትረኝነትና በቀላሉ በሚገነፍል ባህርይ የተወለዱ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በጽድቅ

አመለካከት ተወልደዋል። ይህ የኋለኛው ዓይነት ባህሪይ ያለው ሰው በሁሉም ዓይነት ጉዳዮች ለሁሉም ሰዎች በማንኛውም ጊዜ እንደ ጠቅ ላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ይሆናል። በጣም ፃድቅና ቅን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በወንድሞች መካከል በሚያደርገው ነገር ጣፋጭነት ይጐድለዋል። ሁልጊዜ ትክክለኛ ነው። ነገር ግን ኃይለኛ ነው። ይህም ደግሞ ኃጢአት ነው እላለሁ።

ኮሰታራ ከሆነው ፃድቅ ሰው ተቃራኒው ደግሞ በጣም ደካማ የሆነ ሰውና በሁሉ ነገር የሚፈራ ሰው ነው። እንዲህ ላለ ሰው ሁሉ ነገር ትክክል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ፃድቅ መሣይ ሰው ሰዎች ሁሉ እንደ ፃድቅና ቅዱስ ሊቆጥሩት ይችላሉ። ነገር ግን ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ እያን ዳንዳችን መጠየቅ አለብን። ባህሪያቸው ፃድቅና ቅዱስ ከሚመስሉት ሰዎች ውስጥ ምን ያህሉን ሰዎች እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል? የእግ ዚአብሔር ልጅ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ እንደነዚህ ፃድቅ ይመስል ነበረን? መልሱ በግልጽ አይደለም ነው። በእነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተገለፀው የባህርይ ኃጢአት መወገድ አለበት።

ሌላም ደግሞ አለ። ግትር ወይም ለስላሳ ያልሆነ ባህርይ ያለው ሆኖም ግን በሁሉም ነገር ራስ መሆን የሚፈልግ ነው። እንዲህ ዓይነት ባህርይ ያለው ሰው በተገኘበት ቦታ ሁሉ ራሱን ማሣየት ይፈልጋል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ይሁን ሁልጊዜ መናገር ወይም የትኩረት ማዕከል መሆን እንዳለበት ያምናል። በሰዎች እስኪታይ አይረካም። እንዲህ ዓይነቱ የተደበቀ የእግዚአብሔር ሰው መሆን አይችልም። አሁንም ሌላው አማኝ በጣም ዓይናፋርና ሰዎችን ሁሉ የሚሸሽ ነው። በሄደበት ቦታ ሁሉ እርሱ ወይም እርሷ ጥግ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ። ወደ ፊት ወንበ ሮች መምጣትና መቀመጥ አይሆንላቸውም። ይህ ደግሞ መጥፎ ባህርይ በመሆኑ መስተካከል አለበት።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ቶሎ ተናዳጆች ናቸው በአንድ ወቅት አንድ ወንድም እንዲህ አለ፤ «እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ቶሎ እናደዳለሁ ቶሎም ከቁጣዬ እበርዳለሁ። ጠዋት ላይ እናደድ ይሆናል፤ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ግን ሁሉ አልፎአል፤ ቢሮም ስደርስ ሁሉንም እረሣለሁ»። በዚህ ወንድም ቁጣና ንዴት ሚስቱና ልጆቹ ቀኑን በሙሉ ሲረብሹ ነው

የሚውሉት። ነገር ግን ወደ ቤቱ ሲመለስ ሚስቴ ለምን አዘነች? ብሎ ይገርመዋል። እርሱ ደህና ሆኖ ሣለበቤተሰቡ ግዘን በጣም ይደነቃል። ይህ የባህርይ ኃጢአት ነው። በመሆኑም መወገድ አለበት።

አንዳንዶች በቀላሉ ሊሠራ የሚችልን ሥራ ለቀን ወይም ለአሥር ቀን ሊያቆዩት ይችላሉ። ይህ ስንፍና ነውና መወገድ አለበት። እያንዳንዱ ሰው የየራሱ ባህርይና ተፈጥሮ አለው። በቅዱሳን መካከል የተለያየ ባህርይ ያላቸው ሰዎች አሉ። አንዱ በጣም የሚቆጣ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሁሉ ነገር ጠንካራና ጥንቁቅ ነው። ሌሎችን ባያታልልም እርሱን ግን ግንም እንዲያታልለው አይፈቅድም። የሰውን ዓይን ወይም ጥርስ አይ መታም ሌሎች የእርሱን ዓይን ወይንም ጥርስ ሊመቱ ቢሞክሩ ግን ዓይን ስለ ዓይን ጥርስ ስለ ጥርስ ነው የሚያስከፍለው። ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት የሚለው ምን ማለት እንደሆነ አይገባውም። አንዳንዶች እንደዚህ ሰው አይደሉም። ነገር ግን መካከለኛ ይሆናሉ። ሰዎችን ፊት ለፊት አይዘር ፉም፤ ከሌሎች ግን አምስት ሣንቲም ጥቅም የሚያገኙበት አጋጣሚ ከተ ገኘ ወደ ኋላ አይመለሱም።

አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሯቸው ለፍላፊ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች ባሉበት ፅጥታ ሊኖር አይችልም። በጣም የሚያሳዝነው ሌሎችን ፀጥታ እስኪነሣ የሚያወሩት ስለ ሌላ ሰው ነው ውሸት የመናገር ሃጣብ ባይኖራቸውም ሁልጊዜ ግን ያጋንናሉ። ባህርያቸው ይህ ነው። እንግዲህ ሁላችንም ይህን እንረዳ። ድል ነሺዎች ለመሆን ከፈለግን በግል ባህርያ ችን ጉዳይ ላይ ጌታ እንዲሠራ እንፍቀድለት።

ለምን ስለነዚህ ነገሮች እንነጋገራለን? ብዙ ክርስቲያኖች የሚኖሩት ኑሮ የእግዚአብሔርን ሕይወት ስለማይመስል ነው። አንዳንድ ወንድሞች የሌሎችን ሰዎች ጉድለት ያያሉ መልካም ነገራቸውን ግን ማየት አይች ሉም። ሁልጊዜ ስለ ወንድሞቻቸው ጉድለት ይናገራሉ። አንድ ጊዜ በዚህ ነገር ላይ ድል ያገኘ ወንድም ድልን ከማግኘቱ በፊት ለምን ሁል ጊዜ በሌሎች ወንድሞች ላይ ስህተትን እንደሚፈልግ ምክንያቱን እንደ ማያውቅ መስክሯል። ወደ ወንድሙ ተመልክቶ ስድስት ወይም ሰባት ጉድለቶችን ያገኛል፤ ወደ ሌላኛውም ወንድሙ ተመልክቶ እንዲሁ።

በመጨረሻ ግን ይህን የሚያደርግበት ምክንያት እርሱ ራሱ እነዚህ ጉድለቶች ስላሉበት እንደሆነ ነገርኩት። የባህርይና የተፈጥሮ ጉድለቶች ስላሉበት እንደሆነ ነገርኩት። የባህርይና የተፈጥሮ ጉድለቶች ኃጢአቶች ናቸው፣ በመሆኑም ክርስቲያን ሁሉ ከእነዚህ ነገሮች በላይ በድል መኖር አለበት። በእነርሱ መሸነፍ የለበትም።

6. የእግዚአብሔርን ቃል የመጠበቅ ልብ ማጣት

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር በእግዚአብሔር ፊት የጐደለን ነገር ቃሉን የመጠበቅ ልብ ነው። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው። እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ፤ ምን ያህሉን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳነበብንና ትዕዛዙን እንደጠበቅን እንዳከበርን። ለምሳሌ ስንቶቹ ባሎችሚስቶቻቸውን ይወዳሉ? ስንቶቹ ሚስቶችስ ለባሎቻቸው ይገዛሉ? አንድ ጊዜ አንዲት እህት ለባሏ መገዛት እንዳለባት እንደምታውቅ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል በትክክል ተገዝታ እንደማታውቅ ተናግራለች።

ክርስቲያኖች ጭንቀት ምን ያህል ኃጢአት መሆኑን ያውቃሉ? በፊሊ.4:4 ላይ የእግዚአአብሔር ቃል «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ» ብሎ ያውጃል። ስንቶች ክርስቲያኖች ይህንን ትዕዛዝ አክብረዋል? ጭንቀትና መረበሽ ኃጢአት መሆኑን ማወቅ አለብን። መደሰትን የማይቀበሉ አማኞች ሁሉ ኃጢአትን ፈጽመዋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ለእኛ በአንዳች ነገር እንዳንጨነቅ ነው። /ፊሊ. 4:6/ በሰው ዓይን ፊት ጭንቀት እንደ ኃጢአት ባይቆጠር በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ግን ኃጢአት ነው። በሁሉ ነገር ማመስገን አለብን ይህ የእግ ዚአብሔር ትዕዛዝ ነውና በሁሉ ነገር «እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ፣ አባርካለሁ»፣ ብለን መፀለይ አለብን። ችግር ቢገጥመን እንኳ እንዲህ ማለት አለብን። ዘጠኝ ልጆች ስላሏት አንዲት እናት የተነገረ ታሪክ አለ «በአንዳች አትጨነቁ» የሚለው ቃል እንደ እርሷ ባለው እናት ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይገባ ትከራከራለች፣ ምክንያቱም አለ መጨነቅ ለእርሷ ኃጢአት ሆኗልና። በመጀመሪያ እስኪሞቱ ድረስ ባለማ ቋረጥ የተጨነቀችላቸው ሁለት ልጆች ነበሯት። ቀጥሎም አድገው ለአቅመ አዳም እስኪደርሱ ሰባት ልጆች ነበሯት፣ ያሳዝናል ይህች ሴት

መጨነቅ በእርግጥ ኃጢአት መሆኑን አላወቀችም። ጭንቀት ክርስቲያናዊ ግዴታ መስሏታል።

ሁልጊዜ ደስ እንድንሰኝ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው። 1ኛ ተሰ.5: 16 «በሁሉም ነገር እንድናመሰግን» የእርሱ ፈቃዱ ነው። ድል የነሱ ሁሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅ አለባቸው። ድል ያልነሱ ግን ፈቃዱን ሊጠብቁ አይችሉም።

7. ለእግዚአብሔር የሚገባውን አለመስጠት

እግዚአብሔር ራሳችንን ከቤተሰቦቻችን ጋር እንዲሁም ከሥራችንና ከሐብታችን ጋር አጠቃለን ለእርሱ እንድንሰጠው ይፈልጋል። ነገር ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የተወሰነ ነገር ለራሱ የሚያስቀር ይመስላል። ምንም እንኳ ብዙዎቹ ኪዳን ሰዎች አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር መስጠት ያለባቸው ቢሆንም የአዲስ ኪዳን አሰጣጥ ግን አሥር አሥረኛ ነው። እርሻችንን፣ ሚስቶቻችንን፣ ልጆቻችንንና እኛ ራሳችንንም ጭምር ለጌታ መስጠት አለብን። ሉቃ. 14÷25–26

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሚያስቸግራቸው እየመሰላቸው ይፈራሉ። በአንድ ወቅት ራሱን ለጌታ መስጠት የሚፈራ አንድ አማኝ እንዲህ አለ «ራሴን ለጌታ ብሰጥና እርሱስ እንድሰቃይ ቢያደርገኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?» ይህንን ወንድም ኮስተር ብዬ እንዲህ አልኩት፤ «እግዚአብሔር ግን መሰለህ? ወላጆቹን የማይታዘዝ ልጅ ከአሁን በኋላ እንደሚታዘዛቸው ቢነግራቸው ወላጆቹ ሆን ብለው እርሱን ለማሰቃየት የማይችለውን ሥራ እንዲሠራ የሚያዙት ይመስልሃል? እንዲህ ካደረጉ ወላጆች አይደሉም፣ ፈራጆች እንጂ። እነዚህ ሰዎች ወላጆች እንደመሆናቸው መጠን በተለየ ሁኔታ ለልጆቻቸው መሐሪ እንደሚሆኑ ጥርጥር የለኝም። ታዲያ እንዴት ብለህ ነው እግዚአብሔር ሆን ብሎ እንድ ትሰቃይ እንደሚያደርግህ አድርገህ ያሰብከው? አባትህ መሆኑን ረስተሃል?» አልሁት።

ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ሰው ብቻ ኃይል እንዳለው ለመግለጽ እወዳለሁ። ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ወላጆቹን፣ ሚስቱን፣ ልጆቹን፣ ሥራውን በሕያው አምላክ እጅ ያስቀምጣል። እግዚአብሔር የሰጠውን

ወስጾ ፈጽሞ በዓለም ውስጥ አያኩሣችም። በተቃራኒው ራሱንና ያለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጣል። ከዚህ ጋር አያይዤ የምናገረው ነገር ያለውን ሁሉ ግለትም ሰዎችን፣ ነገሮችንና እንዲሁም ጉዳዮችን በመለየት በእግዚአብሔር ፊት ለመጣል የሚፈራ ሰው ድል ነሽ ሊሆን አይችልም። ሰውያለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር በሰጠ ቁጥር የዚያ ሰው ኃይል ታላቅ ይሆናል። በፈቃዱ ለእግዚአብሔር የሰጠ ሰው ነገሮቹን ሁሉ በእርሱ እጅ ያስቀምጣል። ይህ ብቻ አይደለም፣ አሁንም የበለጠ እንዲወስድ እርሱን ብመጠየቅ ራሱን ለእግዚአብሔር በሞለየት ሕይወቱን ብርቱና ደስተኛ ያደርገዋል። ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ደካማ ነው። እንዲሁም ኃጢአቱኛና ሐዘንተኛ።

8. ያልተናዘዝናቸውን ኃጢአቶች ለመናዘዝ ፈቃደኛ አለመሆን

አንዳንድ ሰዎች ለብዙ ጉዳዮች መፍትሔ አግኝተዋል። ሆኖም በሕ ይወታቸው ኃጢአት መኖሩን ባለመቀበል አይናዘዙም። በመዝ. 66:18 ላይ «በልቤስ በደልን አይቼ ቢሆን» የሚለው ትርጉም ይህ ነው። የሰው ልብ አንድን ኃጢአት መፈለግ ብቻ ሣይሆን ያፈቅራል። በመሆኑም እርሱን ማስወገድ ያቅተዋል። በልብ ይህን ወይም ያንን ኃጢአት በም ስጢር የመውደድ ነገር ይኖራል። በእኛም ዘንድ እርሱን አውጥተን ለመ ናዘዝ ፈቃደኛ አለመሆን ይኖራል። ምንም እንኳ አንድ ሰው አፉን ሞልቶ ኃጢአት ወዳለበት፣ በአጠገቡም አላልፍም ቢልም ልቡ ግን እዚ ያው ነው። ኃጢአት በአብዛኛው የውጭ ባህርይ ጉዳይ ሣይሆን የውስጥ ፍላጐት ነው። በልቡ በደልን የሚያይ ድል ያስፈልገዋል።

ብዙዎች በልባቸው ኃጢአትን መውደድ ብቻ ሣይሆን ያልተናዘዙባ ቸው ኃጢአቶች አሏቸው። እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፣ ስንት ጊዜ በወንድማችሁ ላይ ኃጢአት አደረጋችሁ? ስለ እርሱ ባሰባችሁ ቁጥር የበደላችሁት መሆኑን ታውቃላችሁ? በልባችሁ ስለ እርሱ ክፉትን ይዛችሁ ውጫዊ ነገራችሁን በመለወጥ ሲወጣ አቅፋችሁ ትስሙታ ላችሁ? ወይም በቤታችሁ በችጋት ትቀበሉታላችሁ? ሰውጫዊ ገጽታ አመለካከታችሁ መለወጣችሁ ያማረ መንገድ እንደሆነ ልገልጽላችሁ እወ ዳለሁ። ነገር ግን ይህ ፈጽሞ የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም። የእርሱ

መንገድ ውጫዊ ባህርይን መቀየር አይደለም።እግዚአብሔር የሚጠብቀው ስለ ወንድማችሁ በልባችሁ ውስጥ ክፉ የሆነ የጥላቻ ኃጢአት እንድትናዘዙ ነው።

እዚህ ላይ ከመበዳደል ጋር በተያያዘ መንገድ ታሉ ምን እንደሚል እንይ። ኃጢአትን ስለ መናዘዝ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ የግድ በዝርዝር አያስተምርም። ኃጢአትን እንድንናዘዝ ብቻ ያስተምራል እንጂ ዝርዝር ታሪኩን በሌሎች ፊት እንድንተርክ አይደለም። ማቴ. 18:15 «ወንድምህ ቢበድልህ» ይላል። እዚህ ላይ አንድነገር እንመልከት! ወን ድም በብዙ ነገሮች ሊበድል ይችላል። ሊናዘዝ ወደ ተበዳዩ ወንድም ሲቀርብ ግን «ወንድሜ ሆይ በድዬሃለሁ» ማለት ብቻ ይበቃዋል። ያኔም ተበዳዩ ወንድም ይቅር ማለት አለበት ወደ ተበዳይ የመጣው ሰው የተደበቀ ታሪኩን ሁሉ ሊነግረው አያስፈልገውም። ለምን? የሰው ጆሮ ይህን ሁሉ ዝርዝር ሊሰማ የተገባ አይደለምና።

እስቲ ልጠይቃችሁ፣ በልባችሁ ውስጥ ምን ያህል ኃጢአቶች ትመለከታላችሁ? በሕይወታችሁስ እስከ አሁን ድረስ ስንት መተላለፎች አሉ? እንደዚህ ዓይነት ኃጢአቶች ካሉባችሁ ድል ያስፈልጋችኋል። ያለበለዚያ ያለድል ነሽ ሕይወት ልትኖሩ አትችሉም።

ድል ነሽ ሕይወት የሚቻልና አስፈላጊም ነው

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው እነዚህ ስምንት ዓይነት ኃጢአቶች ቢኖሩብህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖር ድል ያስፈልግሃል። ምናልባት ስምንቱም ዓይነት ኃጢአቶች ላይኖሩብህ ይችላል። ነገር ግን በአንዱ ወይም በሁለቱ ኃጢአቶች ከታሰርህ የኃጢአት ባሪያ ነህ። በሕይወትህ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ መኖር የለበትም። ምክንያቱም ምንም ዓይነት ኃጢአት ይሁን ከእግርህ በታች ነው። ድል የማይነሣ ከባድ ፈተና ስለሌለ እንዲሁም ለምንም ዓይነት ኃጢአት እጅ ትሰጥ ዘንድ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ኃጢአት ከጌታ በላይ ብርቱ ስላልሆነ ጌታን አመስግን። ሕይወት ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙት ያለውና ፈቃዱን የም ናደርግበት፥ እንዲሁም ከተቃራኒ ነገሮች የምንለይበት

ነው። ግንኛውም ክርስቲያን የመንፈስ፣ የሥጋ የአእምሮና የአካል ኃጢ አቶችን ድል መንሣት ይችላል። እግዚአብሔር ይመስገን ይህ የማይገኝ ምናባዊ ሕይወት አይደለም፣ እያየን ያለነው ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሕይወት ነው። የድል ሕይወትን ልንለማመደው የምንችለው ነው።

ድል ለማግኘት ከልብ ግልጽ መሆንና ራስን አለማታለል

ራሣችንን ከማታለል ነፃ እንዲያደርገን እግዚአብሔርን አጥብቀን መለመን አለብን። ምክንያቱም እርሱ የሚባርከው በፊቱ ቅን ልብ ያላቸውንና የማይዋሹትን ሰዎች ሁሉ ነው በታማኝነት «እግዚአብሔር ሆይ በፊትህ ዋሽቻለሁ፣ አውነ ግን ምህረትህን እለምናለሁ» ብትለው ወዲያውኑ ይባርክሃል።

ምናልባት እንዳልረካ ክርስቲያን ያረካህ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይ ቀህ ሊሆን ይችላል። ያልረካ ምንጊዜም የተራብ ሊሆን እንደማይችል በግ ልጽ ልንገርህ። አባካኙ ልጅ የአባቱን ቤት ትቶ ወጣ፤ ያለውንም ሁሉ አጠፋ። በኋላም አሣማዎቹ ከሚበሉት አሠር ሊጠግብ ተመኘ፤ ነገር ግን ማንም አልሰጠውም። ስለሆነም አለመርካት አንድ ነገር ነው፤ አለመ ጥገብ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ዘወትር ደካሞችና ያለማቋረጥ የምንሸነፍ ከሆነ እንዴት ልንረካ እንችላለን? አዎን ላንረካ እንችላለን ግን ከጠዋት እስከ ማታ እንዲህ ያለውን ሕይወት እንኖራለን። በዚህ ምክንያት ዝም ብሎ ካለመርካት መራብ ይሻላል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የተራ ቡትን ብቻ ስለሚባርክ አልረካሁም የሚለውን ግን የማርካት ግዴታ የለበትም።

ለብዙ ጊዜ ራሳችንን እያታለልን በእግዚአብሔር ፊት ስለዋሸን ዛሬ ውሸታችንን እናቁም በእርሱ ፊት ሁሉ ነገራችን ግልጥና እርቃኑን ሆኖ የሚታይ መሆኑን እንረዳ። ስለዚህ ከልባችን ግልጽ እንሁን፤ ኃጢአታ ችንን በሰዎች ፊት መናዘዛችን የእግዚአብሔርን ስም ያከብራል። ታማኝ የሆነ ሁሉ በእግዚአብሔር ይጐበኛል፤ ይረካልም።

ምዕራፍ 2

የክርስቲያን ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው

«በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ» ኤፌ 1:-3

የክርስቲያን የመሸነፍ ልምምድ

በመጀመሪያ ስንድን በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያትልባችን በደስታ ተሞልቶ ነበር። ለሕይወታችን ትልቅ ተስፋ ነበረን። ከአሁን በኋላ ኃጢአቶችን ሁሉ ከእግራችን በታች እንረታግጣለን ብለን አስበን ነበር። በዚያን ጊዜ የትኛውም ፈተና ይሸነፋል፣ የትኛውም ችግር ይፈታል ብለናል። በአጠቃላይ ኃጢአታችን ለመጀመሪያ ጊዜ ይቅር ስለተባለ ደስታ ሰላምን ስለቀመስን የወደፊት ዕድላችን ብሩህ ተስፋ የተሞላ ነበር። ከእግዚአብሔርም ጋር ያለን ግንኙት ድካም የሌለውና ጣፋጭ ነበር። በእውነትና በደስታም ተሞልተን ነበር። መንግሥተ ሰማይም በጣም የቀረበን መስሎ ተሰምቶን ነበር። የማይቻልም ነገር እንደሌለ ያህል ይመስለን ነበር። ዕለት በዕለት ድል ነሽ ሕይወት እንኖራለን ብለንም ሙሉ በሙሉ አምነናል።

በጣም ያሳዝናል እንዲህ ያለው ውብ ልምምድ ብዙም አልቆየም። ጨርሶ ተሸንፈዋል ብለን የቆጠርናቸው ኃጢአቶች ተመልሰው መጡ። አይነኩኝም ያልናቸው ኃጢአቶች ግልብጥ ብለው ተመለሱ፣ የድሮ ንዴትህና ትዕቢትህ፣ ቅናትህም ጭምር። በዚህ ጊዜ መፍትሔ ለማግኘት የእግዚአብሔርን ቃል ብዙ አነበብህ፣ ብዙም ጸለይህ፣ እርዳታ ግን አላገኘህም። ያም ሆኖ በመጀመሪያ የተዳሰስክበትና ከእግዚአብሔር ጋር የነበረህን የቅርብ ግንኙነት አጣህ፣ ስለ ጠፋት ነፍሳት የነበረህ ቅንዓት ቀነሰ፣

ፍቅርህም ቀዘቀዘ፣ ዕለት ተዕለት ሕይወትህም ከድል ይልቅ ብዙ ሽንፈ ቶችን መለማመድ ቀጠልህ፣ በመጨረሻም ትልቅ ጉድለት እንዳለህ ተረዳህ።

በመጀመሪያው ዘመን ከነበሩት ክርስቲያኖች ከነጳውሎስ፣ ጴጥሮስ ዮሐንስ ጋር ራስህን ስታስተያይ ከአንተ ምን ያህል የተለዩ እንደሆኑ አወ ቅህ፣ ይህ ብቻ አይደለም ሌሎችንም መርዳት አልቻልክም። የድል ታሪ ክህን ልትነግራቸው ትችላለህ፣ የመሸነፍ ታሪክህን ግን ደፍረህ አትና ገርም፣ ሁልጊዜም የድል ሕይወትህ አጭር እንደሆነና የመሸነፍ ሕይ ወትህ ግን ረዥም እንደሆነ ይሰማሃል። ከዚህ የተነሣ ዘመንህን በሐዘን ታሳልፋለህ። ይህ ብዙ ክርስቲያኖች የሚጋፉት ልምምድ ነው።

ስንድን ኃጢአታችን ተደምስሷል፣ ዳግመኛ አያገኘንም ብለን ገም ተን ነበር። እንዲሁም ያለን ሰላምና ደስታ ለዘለዓለም ከእኛ ጋር ይቆያል ብለን በእውነት አመንን። በአዲሱ የክርስትና ሕይወት ጅምሬ ላይ ይህ አመለካከታችን ትክክል ነው። ታዲያ ኃጢአትና ፈተና ይመለሳሉ ብሎ ማን ይገምታል? ከዳንንስ በኋላ ከብዙ ከፍታ ይልቅ ብዙ ዝቅታ ይኖራል ብሎ ማን ይጠብቃል? በመዳናችንስ ላይ ከደስታ ይልቅ ብዙ ሐዘን ይኖ ራል ብሎ ማን ያልማል? ነገር ግን ፈተና፣ ትዕቢት፣ ቅናት፣ ቶሎ መቆ ጣት ወይም ሌሎች ድክመቶች እንደገና ሲመለሱ በአብዛኛው ሁለት ነገሮች እናደርጋለን። በመጀመሪያ ያለ የሌለንን ኃይል በመጠቀም ኃጢአትን እናሸፍናለን፣ በሁለተኛ ደረጃ ግን ኃጢአትን ፈጽሞ ማሸነፍ አይቻልም የሚል አቋም እንይዛለን።

እነዚህ ኃጢአቶች ከዳንን በኋላ ወደ እኛ ሲመለሱ በአንድ በኩል እነርሱን ለመጫን ብዙ ጥረት እናደርጋለን። ይሕውም በውጭ ተገል ጠው እንዳይታዩብን ነው። በዚህ ጊዜ ኃጢአቱን ለመቆጣጠር ወይም ለመርገጥ የቻለ አማኝ ራሱን እንደ ድል ነሽ ይቆጥራል። በሌላ በኩል ግን በኃጢአት የተሸነፍን ሌሎቻችን የሕይወት ዘመናችንን በማሸነፍና በመሸነፍ ኃጢአትን በመሥራትና በመናዘዝ ከተናዘዝንም በኋላ ኃጢአ ትን በመሥራት እናሳልፋለን። ይህ ዓይነት ልምምድ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይጥላል። ስለዚህ ኃጢአትን ተቆጣጠርን ቢባል ለጊዜው መጨ ቆን ብቻ ነው የምናደርገው፤ ወይም መጨቆን ካልቻልን ኃጢአት

ሊወገድ የማይችል መሆኑን እናስባለን፤ ቀስ በቀስም ወደ ተስፋ መቁረጥ መዘፈቅና እጅ ወደ መስጠት እንመጣለን።

በግለግለው ጌታ ስም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ወደ መስቀል ሞት ሲሄድ ከዳንን በኋላ ያለን ሕይወታችንን ያየው ዛሬ እንደምንሄድበት ዓይነት አድርጐ ነበር? ኢየሱስ በመስቀል ሲሞት አሁን የምንኖረው ኑሮ ጠዋት ላይ ድሏ፤ ከሰ ዓት በኋላ ላይ ግን ውድቀት እንዲሆን ነው? ሙሉ በሙሉ በመስቀል ላይ የተጠናቀቁው የማዳን ሥራ በቅድስናና በጽድቅ እንድናገለግለው በቂ አይደለም? ጌታ ኢየሱስ ደሙን በመስቀል ላይ ያፈሰሰው የኃጢ አትን ኃይል ሳያይ የገሃነምን ፍርድ በመመልከቱ ብቻ ነው? ወይስ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደም የዛሬውን ስታያችንን ራሳችን እንድንሸከም እርሱ ግን ወደ ፊት ካለው ስቃይ ሊያድነን ብቻ ነው?

ጌታ በቀራንዮ ሁሉን አከናውኗል። አዳኛችን በመስቀል በነበረ ጊዜ ስለ ገሃነም ፍርድ ብቻ ሳይሆን ስለ ኃጢአትም ኃይል አስቧል። እርሱ በኃጢአት ኃይል ያለውን ስቃይና የኃጢአትን ቅጣት ከሩቅ አይቷል። እርሱ ራሱ በምድር ላይ እንደኖረ እኛም በምድር ላይ እንድንኖር የሚያ ስችል ደኅንነት ነው ያለው። በሌላ አገላለጽ በክርስቶስ የመስቀል ሥራና መቤዠት ለመዳን ብቻ ቦታና መብት ያዘጋጀ ሳይሆን ፈጽመን እንድንድን ቦታና መብት ያዘጋጀ ነው። ከአሁን በኋላ አሁን ከምንኖረው የተለየ ሕይወት ልንኖር እንችላለን። ክብር ለበጉ ይሁን! ምክንያቱም ዛሬ የምሥራች ድምጽ ለቅዱሳንም ሆነ ለኃጢአተኞች ስለሰማን ነው።

በእግዚአብሔር የተሰጠ የክርስቲያን ሕይወት

እስቲ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ ክርስቲያን ምን ዓይነት ሕይወት መኖር አለበት? ይሁ ጥያቄ ለእያንዳንዱ ዳግም ለተወለደ ክርስቲያን ሁሉ እንጂ የበሰሉ ክርስቲያኖችን ብቻ የሚመለከት አይደለም። አንድ ሰው መኖር የሚገባውን ሕይወት ለማወቅ ጉድለቱን መረዳት ይኖርበታል። የዚህን ሕይወት የተለያዩ ገጽታዎች የሚገልጽልን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንመልከት።

1. ከኃጢአት ነፃ የሆነ ሕይወት

«ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፤ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» ማቴ 1:21

በቼርና በፔኪንግ የሚኖሩ አንዳንድ ወንድሞች ኢየሱስን «በፊት ክርስቶስ እያልን እንጠራው ነበር፤ ከአሁን በኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንላለን፤ እርሱ የተቀባ ብቻ ሳይሆን አዳኛችንም ነው» አሉኝ። ለምን ኢየሱስ ተባለ? ሕዝቡን ሁሉ ከኃጢአታቸው ስለሚያድናቸው ነው። ኢየሱስ ማለት አዳኝ ማለት ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ተቀብለኸው ከሆነ የይቅርታን ጸጋ ላግኝተሃል፤ ይህ እውነት ነው። ለዚህም እግዚአብሔርን ልታመሰግንና ልትባርከ ትችላለህ። ለመሆኑ ኢየሱስ ለአንተ ምን አድርጓል? ጥያቄው አሁንም በኃጢአት ውስጥ ትኖራለህ ወይስ ከኃጢአት ወጥተሃል ነው። «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና» የሚለው ከእግዚአብሔር የተሰጠና በክርስቶስ የተከናወነ ነው።

የውሃ ዋና መከላከያ ጃኬት ከሕይወት አዳኝ ጀልባ (ላይፍ ቦት) የተለየ ነው። ሰው ባሕር ውስጥ ሲገባ የሚወረወርለትን የሕይወት አድን ጃኬት ይይዛል፤ ስለዚህም አይሰጥምም። በአንጻሩ ግን ከውሃውም አይ ወጣም፤ በሞትና በሕይወት መካከል ይቆያል። የሕይወት አደን ጀልባ (ላይፍ ቦት) ግን ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነገር ነው። በባሕር ውስጥ የወደቀ ሰው ከውሃ ውስጥ ወጥቶ በሕይወት ጀልባ ውስጥ ይቀመጣል። በተመሳሳይ አገላለጽ የጌታችን ማዳን እንደጃኬቱ ሳይሆን እንደጀልባው ሊመሰል ይችላል። ደስ ይበልህ፤ ጌታ በሞት መካከል አይተውህም። ይልቁንም «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» ምክንያቱም በኃጢአታችን አልተወንምና።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው (ደኅንነት) «ከኃጢአታቸው ሁሉ ያድናቸዋልና» የሚል ነው። ያም ሆኖ ግን ምንም በእውነት የዳንን ብንሆንም ስንቶቻችን በኃጢአት እንኖራለን? መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰት ሊሆን ይችላልን? በፍጹም! መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል፤ ልምዳችን ግን ስህተት ነው።

2. ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙት ያለው ሕይወት

«በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቷል... በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን» ሉቃ 1:69–75

እግዚአብሔር በዳዊት ቤት «የመዳንን ቀንድ» አስነስቷል፤ ይህንንም የመዳን ቀንድ በእጃችን አድርገናል። ይህ የመዳን ቀንድ ከጠላቶቻችን ምን ያህል ነፃ አድርጐናል? ከጠላቶቻችንስ ከዳንን ዛሬ ምን ዓይነት ሕይወት ልንኖር ይገባል? ያዳነንን ጌታ አልፎ አልፎ ብቻ በጽድቅና በቅድስና እናገልግለውን? አይደለም! «ዘመናችንን ሁሉ በቅድስናና በጽድቅ» እንድናገለግለው ይገባል። ይህ ነው ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙት ያለው ሕይወት።

ይህንን በድፍረት መቀበል አለብን፤ ይኸውም ምንም እንኳ ከጠላቶቻችን እጅ ብንድንም ዘመናችንን ሁሉ «በቅድስናና በጽድቅ» አላገለገልንለትምና ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ቃል እውነት ከሆነ የግል ልምምዳችን ስህተት መሆን አለበት።

3. ሙሉ በሙሉ በጌታ የረካ ሕይወት

«እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘለዓለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ ይሆናል እንጂ» ዮሐ 4:14 ብሏል።

ይህ ቃል እንዴት ድንቅ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወሰነ ክርስቲያን ወይም ልዩ ጸጋ የተቀበለ ለዘለዓለም የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ይኖረዋል አላለም፤ ጌታ ኢየሱስ ያለው ግንም ነው። በተጨማሪም ቃሉ በቀጥታ የተነገረው ፍጹም እንግዳ ለሆነች ሣምራዊት ነው። እንዲህ አላት። «ብታምኝ ለዘለዓም ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ይኖርሻል» መጠማት ምንድነው? አለመርካት ነው። በጌታ የሚሰጠውን ውሃ የሚጠጣ ግን ዳግመኛ አይጠማም። ከርስቲያን ሁሉ በቃኝን ብቻ ማወቅ ሳይሆን የዘለዓለምን እርካታ ያገኛል። በቃኝን ብቻ የሚያውቅ

ከሆነ ገና ሊያውቅ የሚገባው ነገር ቀርቶታል። እግዚአብሔር ለዘለዓለም እንድንረካ ያደርገናል።

በሻንጋይ፣ በቺንግአንና በሴንሴር የዕቃ መሸጫ መደብሮች አሉ። የከተማውን ዋና መንገድ ይዘው የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ ዕቃዎችን እያዩ ይመኛሉ። ይህ ወይም ያ ቢኖረን ሕይወት እንዴት ቆንጆ ይሆን ነበር ብለው ያስባሉ። ይህ መጠማት ነው። የትምህርት ቤት ጓደኛህ ወይም የሥራ ባልደረባህ ያለውን ስትመለከት ለማግኘት ትመኛለህ? ጌታ ግን እንዲህ አለ፤ «እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ ይሆናል እንጂ»። ምንም እንኳ ልምምዳችን የተለየ ታሪክ ቢነግረንም እርሱ የሰጠን ይህንን ዓይነቱን ሕይወት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ማግኘት ብቻ በቂ እንደሆነ ይነግረናል። እኛ ግን እርሱን ማግኘት ብቻ በቂ እንዳልሆነ ነው የምናስበው። አሁንም ሌሎች ነገሮች እንዲያረኩን እንፈልጋለን። ማነው የተሳሳተው? ጌታ የሰጠን ወይስ የእኛ ልምምድ? ከሁለት አንዱ ስህተት መሆን አለበት። በቂ ገንዘብ የሌለው ቸክ አይፈርምም። ጌታ እሰጣለሁ ያለውን ይሰጣል።

ጌታችን በእርሱ የሚያምን ሁሉ ለምን እንደማይጠማ ተናገረ? በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ አንድ አዲስ ነገር ስለሆነ ነው። ይህንን ልጠይቃችሁ፤ ጌታችንን ዕለት በዕለት በቅድስናና በጽድቅ ታገለግሉታላችሁ? የሌሎችን ሰዎች ጥማት የሚያረካ ከአንተ ውስጥ የሚመነጭ ነገር አለ? አለመርካት የሚሰማህ ከሆነ ያለ ምንም ጥርጥር የሕይወት ልምምድህ ስህተት ነው።

4. ኃይል ያለው ሕይወት

«ኢየሱስ ቆሞ– ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ»። ዮሐ 7:37–38

ከማን ውስጥ ነው የሕይወት ውሃ ወንዝ የሚፈልቀው? በአማኞች ዘንድ ልዩ ክርስቲያን ተብለው ከሚገመቱት ከነጳውሎስ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ብቻ አይደለም። በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ የሕይወት ውሃ ወንዝ

ከሆኑ ይፈልቃል። ከአንተና ከእኔ ግለት ነው። ይህም ከእኛ ጋር የተገናኙ ሰዎች ሁሉ እርካታ እንዲያገኙና ሁለተኛ እንዳይጠሙ ያደርጋቸዋል።

አንዲት ጓደኛ አለችኝ፤ ሰዎች ከእርሷ ጋር ሲገናኙ ወዲያውኑ ዓለምን በመውደዳቸው ራሳቸውን ይወቅሳሉ፤ ትልቅ ቦታ ለመድረስ ያላቸውን የመንጠራራት አሳስፈላጊነት ይረዳሉ። የመመኘትንም ክፉነት ያውቃሉ። እንድ ነገር የሚያረካ ነው ብለህ ታስባለህ፤ ግን አይደለም። ከዚህች እህት ጋር ጥቂት ጊዜ ያሳለፉ በጌታ መርካትን ያገኛሉ። ከእርሷም ጋር በመገናኘታቸው ያ ነገር ምንም እንዳልሆነ ይሰማቸዋል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆኑ ይፈልቃል»። ይህ ጌታ የሰጠን ሕይወት ነው። የሁሉም ክርስቲያን የጋራ ልምምድ መሆን አለበት። እኔ እዚህ የምናገረው የተለዩ ክርስቲያኖችን የሕይወት ልምምድ ሳይሆን ክርስቲያኖች በጋራ ሊለማመዱት የሚገባውን ነው። ራሳችንን ሰዎች እኔን ከተገናኙ በኋላ ጥማት ይናራቸዋልን? ብለን መጠየቅ አለብን። ሰዎች ወደ እኛ መጥተው ሕይወታችን ጉስቋላ፤ አሳዛኝና መፍትሔ ያጣ ነው ሊሉን እኛም በእሽታ ይሁን ብለን መቀበላችን ያሳዝናል። ይህም በበኩሉ የሕይወት ውሃ መሆናችን ቀርቶ እርጥቡን የሚያደርቅ፤ የለመለመውን የሚገድል የተራቆተ ሕይወት ያለን መሆኑን ያሳያል። እንዲህ ያለው ሁኔታ በተሳሳተ ልምምድ ውስጥ መሆናችንን ያረጋግጣል። እግዚአብሔር ግን ተሳስቶ አያውቅም።

5. ከኃጢአት ኃይል ነፃ የሆነ ሕይወት

«ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነስቶ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ ሰደደው።» ሐዋ 3:26

ይህን ቃል ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መመላለሻ ያስተላለፈው መልእክት ነው። ጌታ ኢየሱስ ያከናወነው ሥራ ሰዎችን ከኃጢአታቸው መመለስ ነው። የክርስቲያን የመጀመሪያ ልምምዱ ከኃጢአት ነፃ መሆን ነው። ክርስቲያን ኃጢአትን ሁሉ ድል መንሳት አለበት። እዚህ ላይ የምናውቃቸውን እንጂ የማናውቃቸውን ኃጢአቶች ድል እንድ

ናደርግ አልልም። ለብዙ ዓመታት አስረው የያዙንን ኃጢአቶች ሁሉ ድል መንሳት አለብን። በገላ 6:1 ላይ «ሰው በማንኛውም በደል ስንኳ ቢገኝ» ይላል። በዚህ ዓይነት ሕይወት የሚገኝ እንኳ ቢኖር ድል መንሳት አለበት ምክንያቱም ክርስቶስ ሕይወቱ ነውና። የብዙዎቻችን ልምምድ በአብዛኛው መሸነፍ አልፎ አልፎ ግን ማሸነፍ ነው። እንዴት የተበላሸ ልምምድ ነው።

በሮሜ 6:1–2 ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣ «እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት እንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?»

እኛ በጌታ በኢየሱስ ያመንን ለኃጢአት ሞተናል፤ ስለሆነም ግንም ክርስቲያን በእርሱ (በኃጢአት) መኖር የለበትም። ለኃጢአት መሞታችንን እንዴት እናውቃለን? ጳውሎስ በተከታዩ ጥቅስ መልሱን አስቀምጧል። «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?» ቁ.3 በሌላ አባባል የተጠመቁ ሁሉ ለኃጢአት ሞተዋል ምክንያቱም ጥምቀቱ በጌታ ኢየሱስ ውስጥ ነውና ማለት ነው። ቁ.4 «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፤ ከሞቱ ጋር አንድእንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብረን።» ይህ ክርስቲያን በየዕለቱ ሊኖረው የሚገባው ዓይነት ሕይወት ነው። የተጠመቁ ሁሉ በአዲስ ሕይወት መመላለስ አለባቸው። ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ ብአዕምሮው ያሉት አዲስ የተጠመቁ አማኞች እንጂ በሳልና ልዩ ክርስቲያኖች አይደሉም። ሁላችን ተጠምቀናል ስለዚህ በአዲስ ሕይወት መመላለስ አለብን። ይህ ለሁሉም ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ልምምድ ነው።

«ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።» ሮሜ 6:14

አ! ይህን ጥቅስ እንዴት እንደምወደው ልንገራችሁ። እስቲ ልጠይቃችሁ፤ ከጸጋ በታች የሆነው ጳውሎስ ነው ወይስ ጴጥሮስ? ወይስ ዮሐንስ? ወይስ ሙሪ? ወይስ ያመኑት ሁሉ? ክርስቶስን አምነው የተጠመቁ ሁሉ ከሕግ በታች ሳይሆኑ ከጸጋ በታች አይደሉምን? ዛሬ ስንቶቻችሁ

ከጸጋ በታች ናችሁ? በረከትና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን ሁላችንም ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለንም። ከላይ የተገለጸውን አባባል የሚገጥመው «ኃጢአት አይገዛችሁም» የሚለው ነው። እዚህ ላይ ኃጢአት ጌታችን መሆን እንደሌለበት ነው ሚናገረው። ድል የተወሰኑ ክርስቲያኖች ልምምድ አይደለም፤ ይልቁንም ሁሉም ክርስቲያኖች የሚጋሩት ልምምድ ነው እንጂ። ምክንያቱም የዳኑ ሁሉ ከጸጋ በታች ናቸውና። በመጀመሪያ ስድን በሮሜ 6:14 ላይ «ኃጢአት አይገዛች ሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና» የሚለውን ጥቅስ ልዩ ጥቅስ አድርጌ ወሰድኩት። ከዚያም ለብዙ ቀናት በኃጢአት ላይ ድል እንዳለኝ ተናገርኩ። ያም ሆኖ የተቆጣጠረኝ አንድ የተለየ ኃጢአትና ጥቂት ሌሎች ኃጢአቶች ሊረብሹኝ ደግመው ደጋግመው ይመጡ ነበር።

ኃጢአት የሚከተለን ይመስል ለምን ሁልጊዜ እንደሚያጋጥመን አናውቅም። ሆኖም ግን ያጋጥመናል። አንዳንዶች ቶሎ መገንፈል ይከተላቸዋል፤ አንዳንዶችን ትዕቢት ይከተላቸዋል፤ አንዳንዶችን ቅንዓት፤ አንዳንዶችን ከፉ አመል፤ አንዳንዶችን ራስ ወዳድነት፤ ሌሎችን ርካሽ ሐሳብና ያልፀዳ ስሜት ይከተላቸዋል። አንዱን ሰው ሁልጊዜ የሚከተለው የተለየ ኃጢአት አለ። እኔ ራሴ እግሬ ስር የሙጥኝ ብለው የሚከተሉኝ ኃይለኛ ኃጢአቶች ነበሩ። በኋላ ግን ድልን ለማግኘት ኃጢአት በእኔ ላይ ገዥነት ነበረው ብዬ ማመን ነበረብኝ። ከዚያ በኋላ ለጌታ «ኃጢአት አይገዛህም ብለኸኛል፤ ስለዚህ ስህተቱ በአንተ ቃል ላይ ሳይሆን በእኔ እንደሆነ አስግግለሁ» ብዬ ጸለይኩኝ፤ ድልንም መለመመድ ጀመርኩኝ።

የተሸናፊነት ሕይወት ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ ሕይወት እንደሆነ ታውቃለህ? እስከ አሁን ድረስ ኃጢአት የሚገዛህ ከሆነ ይህ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠህ መሆኑን በግልጽ መረዳት አለብህ። ቅዱስ ቃሉ በግልጽ «ኃጢአት አይገዛችሁም» ይላል።

በሮሜ 8–1 ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ፤ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም»። ኩነኔ የሚለውን ቃል በብዙ መጽሐፍቶቼ ላይ ገልጬዋለሁ። የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ ከመሬት

ተቆፍሮ በወጣ አንድ የድሮ ጽሑፍ ታሉ በአሪጅናል የግሪክ ጽንሰ ልዩ ልዩ ትርጓሜዎች አሉት ከእነኚህ አንዱ «ያለኃይል መሆን» ተብሎ ሊተረጉም ይችላል። በመሆኑም ይህንን ጥቅስ እንዲህ ብለን ልንተረጉመው እንችላለን፣ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ያለኃይል መሆን የለባቸውም» ይህ እንዴት አስደናቂ ነው። እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፣ ይህ ጥቅስ የማን ነው? የዌስሊይ ብቻ ወይስ የግርቲን ሉተር፣ ወይስ የሀድሰን ቴይለር ብቻ? መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ላይ ምን ይላል? «በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ከአሁን በኋላ ወይም ከእንግዲህ ያለኃይል አይደሉም» ይላል። እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? ክርስቲያናች ሁሉ ናቸው። ክርስቲያናች ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ እንደሆኑ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ማንም ያለ ኃይል ሊሆን አይችልም። በቁጥር 2 ላይ «በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና» ይላል። አሁንም መቶ ጊዜ ደግሞ እላለሁ፣ ይህ ለተለዩ ቅዱ ሳናች አይደለም። እያንዳንዱ በክርስቶስ ያለ ክርስቲያን ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ ሆኗል። ይህ እውነት ነው።

ያለ «ኃይል» መሆን ምን ማለት ነው? ለዚህ መልስ የሚሆነው በሮሜ 7 ላይ የተነገረው ነው። «ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም፤ የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና። ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም»። ከቁ. 18–19 በሉላ አነጋገር የሮሜ 7 ጠቅላላ አነጋገር የሚያመለክተው ኃይል የለኝም፤ ማድረግ አልችልም ነው።

የብዙ ክርስቲያናች ታሪክ በውሳኔና ውሳኔን በማፍረስ ሽክርክሪት የተሞላ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፣ እንባርካለንም፤ ታሉ ያለአንዳች መሳሳት ማናቸውንም ክርስቲያን ኃይል አልባ እንዳልሆነ ያውጃልናል።

ሕግ ምንድነው?

ሕግ በማናቸውም ቦታና በየትኛውም ሁኔታ በተመሣሣይ መንገድ ይሠራል፤ አንድ ዓይነት ውጤትም ያመጣል፤ የተደጋገመ ልምምድን

ይገልጣል። የማያጸድጥ ክስተትም ነው። ሁልጊዜም በተመጣጣይና በአንድ ዓይነት ውጤት ያበቃል። ለምሳሌ በምድር መሳከል የሰበት ኃይል አለ። አንድን ነገር ስንወረውር በስበት ኃይል ምክንያት የተወረወረው ነገር ሁልጊዜ ወደታች ተሰቦ ይወድቃል። ይህ የሰበት ኃይል የተፈጥሮ ሕግ ነው።

በተመጣጣይ የአንዳንዶች ቶሎ መቆጣት ሕግ ይሆናል። አንዱ ሰው አንድ የሚያስቆጣው ነገር ሲመጣ አንድ ሁለት ጊዜ ፈተናን ይቋቋም ይሆናል። ነገር ግን በሦስተኛውና በአራተኛው ጊዜ ጨርሶ ስሜቱን መቆጣጠር ያቅተዋል። ቁጣው ቶስ በቶስ ገንፍሎ ቦግ ይላል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በተተነኮሰ ጊዜ ይቆጣል፤ ያለ ምንም ለውጥም ሁልጊዜ ተመጣጣይ ውጤት ያስከትላል።

ሰውን ትዕቢት ሁልጊዜ በተመጣጣይ መንገድ ይከተለዋል። በመጀመሪያ በተሞካሸህበት ቃላት እንዳልተነካ ልትሆን ትችላለህ። ሁለተኛውን የማሞካሻ ቃል ስትሰማ ግን ፊትህ በትዕቢት መለወጡ የድግግሞሹ ሥርዓት ተመጣጣይ ውጤት የሚያስከትል ሕግ ይፈጥራል።

ደጋግሚ የምገልፀው ከኃጢአት ሕግ ነፃ የሆኑት የተመረጡ፣ ልዩ የሚባሉ ክርስቲያኖች አይደሉም። ይልቁንም ከአሁን በኋላ ማንም ክርስቲያን ያለ ኃይል አይደለም። የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እውነታዎች እንጂ ትዕዛዝ አይደሉም። ስለዚህ እነርሱ ሁሉ የሁሉም አማኞች ልምምዶች መሆን ይገባቸዋል። የልምምዳችን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አለመጣጣም ምንኛ አሳዛኝ ነው።

6. ሁኔታዎችን ድል የሚነሳ ሕይወት

«ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት፥ ወይስ ረሃብ፥ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን?... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» ሮሜ 8:35–37

በወደደን ጌታ በሁሉ ነገር ከአሸናፊዎች እንድንበልጥ ተደርገናል። ይህ በእርግጥም ማንም ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባ ልምምድ ነው። መከራና ሰይፍን ትተን የአንድ ሰው ፊት ትንሽ መለወጥ የክርስቶስን

ፍቅር ምንነት እንድንረሳ ያደርገናል። ነገር ግን ጳውሎስ በእነዚሁ ሁሉ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ብሎ አወጀ።

ድል የክርስቲያን ጤነኛ ልምምድ መሆን አለበት። እንደ እግዚአ ብሔር ፈቃድ ግንኙውም ክርስቲያን በግናቸውም ዓይነት ሁኔታ ከግሸ ነፍ በላይ መሆን አለበትና መከራ ወይም ጭንቀት ወይም ስደት ወይም ረሃብ ወይም ራቁትነት ወይም ፍርሃት ወይም ሰይፍ ቢሆን ግሸነፍ ብቻ ሳይሆን ከአሸናፊዎች መብለጥ አለበት። የችግር መባባስ ለውጥ አያመ ጣም። ዓለም ክርስቲያኖችን እንደ እብድ ይመለከታቸው ይሆናል። ታዲያ ምንድነው እንደ እብድ ብንቆጠርስ! በክርስቶስ ፍቅር ስለነዚህ ነገሮች ግድ አይሰጠንም! ምክንያቱም ከግሸነፍም በላይ እንሆንባቸዋለ ንና። ከእግዚአብሔር ለክርስቲያን የተሰጠው ሕይወት እንዲህ ያለ ነው። ግን ልምምዳችን ምን ይመስላል? እያዘንኩ እላለሁ እንደ አግባቡ አልኖ ርንም። ባጋጠመን ትንሽ መከራ ምን ያህል ተሰቃየን ብለን እናግር ራለን። ነገር ግን በአግባቡ ብንኖር በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

«ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሳቱ ለሚያዘረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን።» 2ኛ ቆሮ 2:14 የክርስቲያን ሕይወት አንዳንድ ጊዜ የሚሸነፍ፣ አን ዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚያሸንፍ አይደለም። ሁልጊዜ ድል የሚነሳ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛ አለማሸነፍ እንደ እንግዳ ነገር የሚቆጠር ሲሆን ግሸነፍ ደግሞ እንደ ተለመደ ነገር የሚቆጠር ነው።

7. መልካም የሆነውን ነገር የሚያደርግ ሕይወት

«እኛ ፍጥረቱ ነንና፣ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።» /ኤፌ 2:10/

ይህ ጥቅስ በጣም ከታወቁትና ድንቅ ከሆኑት ከቁጥር 8 እና 9 ጥቅሶች የቀጠለ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። በቀዳሚዎቹ ጥቅሶች ላይ የተጠቀሰው በጸጋ መዳናችን ነው፤ በቁጥር 10 ላይ ግን እንዲህ ይላል፤ እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።»

ይህ የተወሰኑ ክርስቲያኖች ልዩ መግለጫ አይደለም። ይልቁንም በሁሉ አማኞች ዘንድ የሚደረግ የጋራ ልምምድ ነው፤ ግለትም እግዚአብሔር ሁላችንንም ያዳነን መልካሙን ሥራ እናደርግ ዘንድ ነው።

ጥያቄው፣ እግዚአብሔር ለኛ ባዘጋጀው መሠረት መልካም ሥራ ታደርጋለህ? ወይም በአንድ በኩል መልካም ሥራ እያደረግህ በለላ በኩል ታጉረመርማለህ? ለምሳሌ ወለል ትወለውላለህ እንበል፤ ስትወለ ውል አንተና ሌላው ወንድም ብቻ ይህንን ሥራ እንደምትሠሩ እያሰብህ ታብላላለህ? ሌሎቹ ወንድሞች ለምን እንደ እኔ አይወለውሉም? እያልክ በሃሳብህ ስታወጣ ስታወርድ ወይ በራስህ፣ ወይም ደግሞ በሌሎች ላይ ታንጐራጉራለህ። ይህ መልካም እንደመሥራት ተደርጐ ሊታይ አይች ልም። እያንዳንዱ ክርስቲያን በልቡ ደስ እያለው መልካም ግድረግ አለ በት። በጐ ፈቃድ በማጣት ወይም ጉልበቱን በመቆጠብ ምንም ማድረግ የለበትም። ራስ ወዳድ መሆን የለበትም። ይልቁንም የራሱን ሕይወት እንኳ በሙሉ ፈቃዱ ለሌሎች ማፍሰስ አለበት። ጥሩ ክርስቲያን የሚ ባሉት ብቻ መልካምን ሥራ የሚያደርጉ ከሆነ ነገሩ ምንኛ አሳዛኝ ነው!

8. በብርሃን የተሞላ ሕይወት

«ደግሞም ኢየሱስ– እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።» ዮሐ 8:12

ይህም እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የሰጠው ሕይወት ነው። ለተወሰነ ክርስቲያን ብቻ አይደለም በሕይወት ብርሃን ውስጥ መመላለስ የሚቻለው፣ ክርስቶስን የሚከተሉ ሁሉ በጨለማ መመላለስ የለባቸ ውም። የሕይወት ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል። በብርሃን የተሞላ ክርስ ቲያን ጤናማ ክርስቲያን ሲሆን ብርሃን የሌለው ግን ያለ ጥርጥር በሽተኛ ነው፤ ጤናማ አይደለም።

9. ሙሉ በሙሉ የተቀደሰ ሕይወት

«የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም፣ ሥጋችሁም፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።» 1ኛ ተሰ 5:23

ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ያለው ጸሎት ነው። «ሁለንተናችሁን ይቀድስ» በማለት ስለጸለየ ሙሉ በሙሉ መቀደስ የሚቻል መሆኑ ግልጽ ነው። «ፍጹም ያለ ነቀፋ መጠበቅም» የሚቻል ነው። እግዚአብሔር እኛን አማኞችን ፍጹም ሊቀድሰንና ያለ ነቀፋም ሊጠብቀን ይችላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ጌታ ለክርስቲያኖች የሰጠውን ሕይወት ያሳያሉ። «ማዳኑ» አማኞች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተጣረጠ ግንኙት እንዲኖራቸው የሚያደርግና ኃጢአትን ሁሉም ድል አድርገው ከእግራቸው በታች መርገጥ የሚያስችላቸው ነው። ስለዚህ ይህ ጌታ ለእኛ የሰጠው ሕይወት ነው። ይህ ተራ ሐሳብ ሳይሆን የተረጋገጠ ሕይወት ነው።

የእግዚአብሔርን ሙሉ ማዳን መለማመድ አለብን

ዛሬ ልምምድህ ምን ዓይነት ነው? ልምምድህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተገለጸው ካልሆነ ሙሉ ደኅንነት ያስፈልግሃል ማለት ነው። መዳንህ እውነት ነው፤ ነገር ግን ደኅንነትን ሙሉ በሙሉ አላገኘህም። ስለዚህ የምሥራች ላሰማህ? ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያከናወነው ተጋድሎ ከኃጢአት ፍርድ መዳን ብቻ ሳይሆን ከኃጢአት ኃይል አድኖሃል። ይህን ሙሉ ደህንነት ያዘጋጀው ዕለት በዕለት የድል ሕይወት እንድንኖርና የመጀመሪያውንም ደኅንነት እንድናገኝ ነው።

ድል ምንድነው? ድል በእርግጥ የጐደለንን የማሸነፍ ሕይወት የሚያጐናፅፈን ነው። ደኅንነትን ባገኘን ጊዜ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከእኛ በኩል አንድ ነገር ጐድሎ ነበር። እርሱ ውጣ ውረድ የበዛበት ደኅንነት አልሰጠንምና፤ ሙሉ ደኅንነት እንዲኖረን ይፈልጋል። ነገር ግን እኛ

በሚገባ ስላልተለወጥን ዛሬ መፍትሔ አስፈልጐናል። «እርሱም የድል ኑሮ ልምምድ ነው» በድል ኑሮ ደኅንነታችን ሙሉ ይሆናል።

እናንተ በክርስቶስ ኢየሱስ በግመን የዳናችሁ ወገኖቼ! እግዚአብሔር አድኖን መልሶ ደግሞ ኃጢአትና ንስሐ እየተፈራረቁብን እንድን ናር ይፈቅዳልን? የእግዚአብሔር ልጅ ሞቶልን ሳለ በኃጢአት ልንቀጥል እንችላለንን? ከዳንን በኋላ ኃጢአት ሊገዛን ይገባልን? ኃጢአትና እግዚአብሔር ምንኛ እርስበርስ የሚቃረኑ ናቸው! ታዲያ እግዚአብሔር ኃጢአት በእኛ ውስጥ የበላይነት እንዲኖረው ይፈልጋልን? ኧረ በፍጹም! አካላዊም ይሁን ስነ ልቦናዊ ወይም ባህሪያዊ ኃጢአት ኃጢአት ነው።

ጌታን እንዲህ እንበል! «ጌታ ሆይ እባርክሃለሁ! አመሰግንሃለሁም! ምክንያቱም በመስቀል ላይ የሠራኸው ሥራ ከኃጢአት ኃይልና ከቅጣቱም አድኖኛልና! ጉድለቴን አሳየኝና ድልን እንድፈልግ አድርገኝ።» ብለን እንጸልይ። ልምምዳችን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር የማይ ስማማ ከሆነ ያለ ጥርጥር ድል ያስፈልገናል። ፍጹም የሆነ ድልነሺ ሕይወት ልናር አልችልም እያልን ራሳችንን አናታል።

ለመሆኑ በክርስቶስ መስቀል ምን ምን ተከናውኗል? ብለን በእውነት እናስባለን? አንዳንዶቻችን የመስቀሉ ተጋድሎ ጥቂት ይሆንብን ይሆናል ብለን እንገምታለን! በዚህም ራሳችንን እንዋሻለን። በእንዲህ ዓይነቱ ሕይወት አንመካ! እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ድልን አይሰጠንም። የክርስቶስ ድል ባህሪው ኃጢአትን ጨርሶ ማስወገድ ነው። ክርስቶስ ሲሞት ኃጢአት ከእግሩ በታች ተረግጧል! ጌታ ይመስገን! ሆኖም ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት ያላገኘንና ኃጢአትን ድል ለመንሳት ኃይል የሌለን ድል ያስፈልገናል። ለዚህ እያንዳንዳችንን እግዚአብሔር ይርዳን!

ምዕራፍ 3

የድል ሕይወት ባሕርይ

«የእሥራኤል ኃይል እንደ ሰው የሚጸጸት አይደለምና አይዋሽም አይጸጸትምም አለው።» 1ኛ ሣሙ 15:29

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ድል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1ኛ ሣሙ 15: 29 ላይ ተገልጿል። በዚህ ክፍል ላይ ድል (ኃይል) ልምምድ ወይም ከስተት አይደለም። ሰው ነው። እርግጠኛ ነኝ ያ ሰው ግን እንደ ሆነ ሁላችን እናውቀዋለን። እርሱም ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ዛሬ እቅ ጩን ልንገ ራችሁ፤ ድል እኛ ዘንድ አይደለም ያለው፤ የኛ ልምምድም አይደለም። እንደ ችግሩ አንተ ድሉም አይደለህም፤ ድል የክርስቶስ ማንኑት (ሰውነት) ለአንተ መኖር ማለት ነው! በዚህ ምክንያት የምና ገኘው ድል አይዋሽም፣ አይጸጸትም። እግዚአብሔር ይመስገን! ድላችን ክርስቶስ ራሱ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ቃል የድል ነሽ ሕይወት ገጽታ ባለብዙ መልክ ነው። እኛ ግን ከብዙ ባሕርያቱ አምስቱን እንገልጻለን። የዚህ ሕይወት ትርጉም በጥቂቱ የተለወጠ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ፍፁም የተለወጠ ነው።

ወንድሜ ሆይ! ከሁሉ አስቀድሞ እባክህ ድል ፍፁም የተለወጠ እንጂ ነካ ነካ የተደረገ ሕይወት ብቻ እንዳልሆነ ተረዳ። ድል ማለት ፍፁም ተለወጥሁ ማለት ነው። ገላ 2:20 እንዲህ ይላል፤

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ። እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖ ርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወ ደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖርው ነው» ይህ ጥቅስ ምን ማለት ነው? አንድ ትርጉም ብቻ አለው። ይኸውም በዚህ ላይ የተነገረው ሕይወት የተለወጠ ሕይወት መሆኑ ነው። ዋናው ነገር «እኔ አይደለሁም ነው።» እኔ ስለ እኔ የሚባል

ነገር ፈጽሞ የለም። መጥፎ እኔ፣ ጥሩ እኔ ወይም ቆሻሻው እኔ፣ ወደ ንጹሕ እኔ የሚለወጥ ነገር አይደለም። ይህ ባጭሩ «እኔ አይደለሁም» ነው። ዛሬ ሰዎች ድል ደረጃ በደረጃ የሚደረስበት ውድቀትም ቀስ በቀስ ወደ ኋላ የሚሄድ ነገር ነው በማለት ትልቅ ስህተት ይፈጽማሉ። አንድ ሰው ስሜቱን መቆጣጠር ከቻለ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙት ካደረገ ድል ነሽ ነው እየተባለ ይተረጐማል። ነገር ግን እንዲህ አይደለም። ይህን አንድ ነገር እንያዝ፤ «ድል ከግንነታችን ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም።»

አንድ ወንድም እያለቀሰ፣ ድል ሊያደርግ እንዳልቻል መሰከረ፣ እኔም በግልጽ ጨርሶ በልምምዶቹ ኃጢአትን ሊያሸንፍ እንደማይችል ነገርኩት፣ እንዲህም አልኩት፤ እግዚአብሔር አንተ በራስህ ድል እንድትነሳ አንዴም ፈልጐ አያውቅም። ይህ ብቻ አይደለም። ከፉ አመ ልህን ወደ መልካም፣ ሻካራነትህን ወደ ጨዋነት ወይም ሐዘንህን ወደ ደስታ እንድትለውጥ ጨርሶ ጠይቆህ አያውቅም። በቀላሉ የእግዚአ ብሔር መንገድ ሕይወትህን በኢየሱስ ሕይወት እንድትለውጥ ነው። ይህ ከአንተ ጥረት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙት የለውም አልኩት።

እንዲሁም አንዲት እህት ለሌሎች ድል መንሣት ቀላል ሆኖ እንደ ሚታይ ለእርሷ ግን እንዲህ ግድረግ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ በምሬት ገለጸች። ስሜቷ ከሌሎች ሰዎች የባሰ መጥፎ ስለሆነ፣ በሐሳቧም ያልፀዳች ስለሆነች፣ በባሕሪዋ ከብዙዎች በላይ ብልጣብልጥ በመሆኗ በምንም ዓይነት ራሷን መቆጣጠር እንደማትችል ተናገረች። የእኔ መልስ እንዲህ የሚል ነበር፤ በእውነቱ ለአንቺ ማሸነፍ ከባድ ሳይሆን አስከማ ይቻል ድረስ በጣም ከባድ ነው። አንቺ ተፈጥሮሽ ከማንም የተሻለ ታማኝ፣ ስሜትሽም ጥሩ፣ ሐሳብሽም ንጹሕ ቢሆን ድል መንሣት ቀላል ሊሆንልሽ እንደሚችል ታስቢያለሽ፤ ነገር ግን እንዲህ ብሎ ነገር የለም። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ምንም ያህል ጨዋና ቅዱስ እንዲሁም ትክ ክለኛ ሰው ቢሆን የራሱን ማንነት ካልለወጠና በምትኩም ክርስቶስ እንዲ ገባ ካልፈቀደ ድል ሊነሣ አይችልም። እንዲሁም ያልተቀደሰና በሁሉም የጐደለ ሰውም ራሱን ከራሱ ሲያስወጣና ክርስቶስን ሲያስገባ ብቻ ድልን ሊለማመድ ይችላል። ክፉ ባሕሪይ ያለውና ሞራሉም ፈጽሞ የተበላሸ

ሰው ደኅንነትን ለማግኘት በኢየሱስ ማመን እንዳለበት እንዲሁም መል ካም ባሕሪ ያለውና ጥሩ ሰውም በኢየሱስ ማመን አለበት። እንደዚሁም ለቅድስና መልካም ባሕሪ ያለውና በሞራሉም መልካም የሆነ ሰው፣ አመለ ጥፉ እንደሆነውና ሞራሉም እንደተበላሸው ድል ያስፈልገዋል ብዬ ነገርኳት።

ድል ክርስቶስ ራሱ ነው። ከእንተና ከእኔ ጥረት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ይህንን እወቅ።

አንድ ጊዜ በሻንጋይ ከፍለ ሀገር ካሉት እህቶች መካከል ድል መን ግት በእጅጉ ያቃታትን አንዲት እህት አገኘሁ። ከልጅነቷ አንስቶ እስከ ሃምሳ ዓመቷ ድረስ ያሳለፈችውን ጉድለቶችና ውድቀቶች ለእኔ ለመንገር ሁለት ሰዓት ፈጀባት። ጌታን ከተቀበለችበት ከልጅነቷ ጊዜ አንስቶ ትዕቢቷንና ነጭናጫነቷን ለመለወጥ ምንም መንገድ አላገኘችም። በየ ጊዜው ጉዳት በሞላበት ሕይወት ትሰቃያለች። እንደ እውነቱ ከሆነ እንደ እርሷ ድል የሚያስፈልገው ሰው ጨርሶ አጋጥሞኝ አያውቅም። በአንጻ ሩም እንደ እርሷ ዓይነት ልዩ የሆነ ድል ያገኘ ሰው አላየሁም። ይህች እህት በውድቀቷ ሁልጊዜ በጣም ታዝን ነበር። እንዲሁም ከነበረባት ጉድለት የተነሣ ራሷን ለማጥፋት አስባለች። ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ ራሷን ረዳት አልባ ሆና እንዳገኘችው ነገረችኝ። ታሪኳን እያጫወተችኝ ሳለ መሳቅ ጀመርኩ። «ዛሬ» አልኳት «ዛሬ ጌታ ኢየሱስ ሊፈውሰው የሚችል እውነተኛ በሽተኛ አግኝቷል!» ብዬ ነገርኳት። ይህቺ እህት ሙሉ በሙሉ በኃጢአቷ ሐሳብ ተውጣ ነበር።

ድል ምን ማለት መሆኑን ካላወቅህ ያስተቀር ስለ ትዕቢቷና መነጫ ነጯ በምትነግርህ ነገር ያለ ጥርጥር ትመረዛለህ፣ ምን አልባትም ለዚህ ተስፋ ላይኖር ይችላል ብለህ ከሷ ጋር ልትስማማ ትችላለህ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል ታላቅ ደስታ የሚል የምስራች ቃለ። ድል መንሣት በአንተ ላይ የተጣለ ቢሆን ኖሮ ምን ጊዜም ድል ማድረግ አትችልም ነበር። ድል ክርስቶስ ስለሆነ ግን ፈጽሞ ችግር የለውም። ጥያቄው በአንተ ሆኖ ድል የሚነሣው ማነው? አንተ ወይስ ክርስቶስ? የሚለው ነው። ክርስቶስ ከሆነ በተፈጥሮህ ምንም ዓይነት ሰው ሁን ችግር

የለውም። ከሌሎች አሥር እጅ የማትረባ ብትሆን እንኳ ክርስቶስ በአንተ ምትክ ከሆነ ድል መንሣት ትችላለህ። ሃሌ ሉያ!

ልጠይቅህ፤ ድል ምንድነው? ድል ክርስቶስ ለአንተ አሸናፊ ሆነ ማለት ነው እንጂ አንተ አሸናፊ ነህ ማለት አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ዓይነት ድልን ብቻ ያስተምራሉ፤ ይኸውም ገላ 2:20 የሚያውጀውን ነው፤ «እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል።» በደቡብ ቻይና የሚኖሩ ፍክኒዞች «በሞትም ቢሆን መለወጥ የለም» የሚል አባባል አላቸው። ይህን ነገር በፔኪንግ ላሉ ወንድሞች ነገርኳቸው። እኛም በሞትም ቢሆን መለወጥ የለም ማለት አለብን አልኩ። ባለመለወጤ ጌታ የተመሰገነ ይሁን፤ ነገር ግን በእርሱ ተለውጫለሁ!

አንዲት እህት ራስን በመለወጥና በክርስቶስ በመለወጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ስትል ጠየቃችኝ። እኔም መልሱን ለመስጠት ተከታዩን ግብራሪያ ተጠቀምኩ፤ ለምሳሌ ያህል እንበል አንድ አሮጌ መጽሐፍ ቅዱስ ይገዛለሁ። ልለውጠው የፈለግሁ ቢሆን አዲስ ሽፋን አለብሰዋለሁ፤ በሙጫም አያይዘዋለሁ፤ በሽፋኑ ላይም በወርቃማ ፊደሎች «መጽሐፍ ቅዱስ» ብዬ እጽፍበታለሁ። በተጨማሪም በገጾቹ ውስጥ የጠፉ ፊደሎች ቢኖሩ በብዕር እጽፍበታለሁ፤ ግልጽ ያልሆነ ፊደል ከተገኘም አደምቀዋለሁ። ይህ ሂደት ግን ምን ያህል ጊዜ እንደ ሚፈጅብኝ አላውቅም። በዚህ ሂደት ስንቱ በትክክል ተሰርቶ እንደ ሚወጣም እርግጠኛ አልሆንም። በአንጻሩ ግን አሮጌውን በአዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ለመተካት ብወስን ይህ በሰከንድ ውስጥ ይከናወናል። በዚህ ኛው ሁኔታ አሮጌውን መጽሐፍ ቅዱስ ለመጽሐፍት ሻጩ ሰጥቼ እርሱ በአዲስ ይለውጥልኛል። በመንፈሳዊ ሕይወታችንም እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር ልጁን ለአንተ ስለሰጠ ኃይልህን ማጥፋት የለብህም። በቀላሉ አሮጌውን ሕይወትህን፤ ለእርሱ ስጥ፤ የልጁን ሕይወት በምትኩ ለመቀበል ነው። ይህ በራስ የሚገኝ መለወጥ ሳይሆን በክርስቶስ የሚገኝ ፍፁም ለውጥ ነው።

ሌላ ግብራሪያ ልጠቀም፤ ከብዙ ዓመታት በፊት ለሁለት ዓመታት ዋስትና የተሰጠው አንድ ሰዓት ገዛሁ። ግን እንዲህ ሆነ፤ ሰዓቱ በእኔ እጅ

ከቆየበት ጊዜ ይልቅ ኩባንያው ዘንድ የቆየበት ጊዜ በለጠ። ይሽውም ከገዛሁት ከጥቂት ጊዜ በኋላ በትክክል መቁጠሩን አቆመ። በዚህ የተነሳም ለጥገና ወደ ኩባንያው ብዙ ጊዜ መመላለድ ነበረበት። አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ፣ እስከ አሥር ጊዜ ወደዚያ መሮጡ ሰለቸኝ። ከዚህም በላይ ሰዓቱ እንደተበላሸ ቀረ። ስለዚህም ኩባንያው ሰዓቱን በሌላ ሰዓት ይቀይርልኝ ዘንድ ጠየቅሁት። እነርሱ ግን ይህን የሚፈቅድ የኩባንያ ደምብ ስለሌ ላቸው መለወጥ እንደማይችሉ መልስ ሰጡኝ ነገር ግን ሰዓቱ የሁለት ዓመት ዋስትና ሰላለው በዚህ የዋስትና ጊዜ ውስጥ የጥገና ሥራ እንደ ሚሠሩ ተነገረኝ። ይህ ሁኔታ ለማምንት፣ ለወር ያህል ቀጠለ፣ ሆኖም አልተስተካከለም በመጨረሻም እጅግ ስለሰለቸኝ ሰዓቱን ኩባንያው ዘንድ ትቼው ሄድኩ። ይህ ማብራሪያ የሰው መንገድ ሁልጊዜ የጥገና ሞሆኑ ለማሳየት ያገለግላል። ሕይወት ዋስትና በተሰጠው ዘመን ሁሉ ጥገና፣ ጥገና ጥገና ብቻ ነው። ልመለወጥ ሰው ቆራሁ መንገድ የለውም።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ቢሆን የእግዚ አብሔር መገሄድ መጠገን ወይም ማደሰ አልነበረም፣ ፍፁም መለወጥ እንጂ። ለምሳሌ ይህን ከፍል አስተውል፣ «እግዚአብሔር ለክብሩ የተከ ላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ፣ ለጽዮን አልቃሾች፣ አደርግላቸው ዘንድ በአመድ ፈንታ አክሊልን፣ በለቅሶም ፈንታ የደስታን ዘይት፣ በሐ ዘንም መንፈስ ፈንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ እስጣቸው ዘንድ ልኮ ኛል።» ኢሳ 61፡3 መተካት የእግዚአብሔር መንገድ ነው። አመዱ አይለወጥም፣ ይልቁንም በምትኩ በአመዱ ፈንታ አክሊልን ይሰጣል እንጂ ወይም ለቅሶን የማሻሻል ሥራ አይሠራም። ለልቅሶ የደስታን ዘይት ይሰጣል እንጂ እንዲሁም በሐዘን መንፈስ ፈንታ የምስጋና መጐና ጸፊያ ይሰጣል። ማሻሻል የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም። ምንጊዜም የእርሱ መንገድ መለወጥ ነው።

ባለፍኩባቸው ዓመታት ሁሉ ራሴን መለወጥ አልቻልኩም። ነገር ግን እግዚአብሔር ለዋውጦኛል። ይህ ቅድስና ነው፣ ይህ ፍጹምነት ነው፣ ይህ ድል ነው፣ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት ነው። ከዚህ በኋላ የክ ርስቶስ ጨዋነት የእኔ ጨዋነት ነው፣ የክርስቶስ ቅድስና የእኔ ቅድስና ነው፣ የክርስቶስ የጸሎት ሕይወት የእኔ የጸሎት ሕይወት ነው፣

የክርስቶስና የእግዚአብሔር ግንኙት የእኔም ግንኙት ነው። ድል የማል ነሣው ከባድ የሚባል ኃጢአት የለም፤ የማላሸንፈው ኃይለኛ ፈተና የለም፤ ምክንያቱም ድል የሚነሣው የክርስቶስ ሕይወት እንጂ እኔ አይደ ለሁምና ነው። እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፤ ክርስቶስ ትልቅ ኃጢ አትን ሊፈራ ይችላልን? ለትልቅ ፈተናስ ይንበረከካልን? ኧረ በፍጹም! እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! ከአሁን በኋላ አልፈራም ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ክርስቶስ እንጂ እኔ አይደለሁምና።

የዚህ ሕይወት መርህ ስጦታ እንጂ ዋጋ አይደለም

በዚህ ሁሉ አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር አለ፤ ይኸውም ድል ነፃ ስጦታ እንጂ የሥራ ዋጋ አለመሆኑን ነው። ስጦታ ምንድነው? በሥራ የምታገኘው ደሞዝ (ዋጋ) አይደለም። በአንጻሩ ከተቀባዩ የሚሟላ ነገር እንዲኖር ሳያስፈልግ እንዲሁ በነጻ የሚሰጥ ነገር ነው። እንዲሁ የድል ነሽ ሕይወት የአንተን ጥረት የማይጠይቅ ነፃ ስጦታ ነው። ሃሌ ሉያ! «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግ ዚአብሔር ምስጋና ይሁን» /1ኛ ቆሮ 15:57/ ድል እግዚአብሔር ለእኛ ሊሰጠን ያዘጋጀው ነገር ነው። የእኛ ድል በግል ጥረት የተገኘ ሳይሆን በነፃ የተገኘ ነው።

ብዙውን ጊዜ አማኞች እጅግ የተዛባ አስተሳሰብ አለን፤ ይኸውም ደኅንነትን በነፃ አገኘን እያልን ድል መንሣትን ግን በእኛው በራሳችን ይገኛል እንላለን። ደኅንነትን ለማግኘት መልካም ሥራ እንደማንጨ ምር እናውቃለን። በቀላሉ ወደ መስቀሉ መጥተን ጌታ ኢየሱስ እንደ ግል አዳኛችን መቀበል ነው፤ ወንጌል ይሄ ነው። በሥራ እንደማንድን እናው ቃለን። ነገር ግን ከዳንን በኋላ ለመቀደስ በበጐ ሥራችን መተማመን እንዳለብን እናስባለን። ይህም በሥራህ መዳን ባትችልም ድል ለመንሣት በሥራህ መተማመን አለብህ እንደማለት ነው።

ቁርጥ ያለ አንድ ነገር ልንገርህ፤ በሥራህ እንዳልዳንህ ሁሉ በሥራ ህም ድል መንሣት አትችልም። መልካም ማድረግ እንደማትችል እግዚአ ብሔር ተናግሯል። ክርስቶስ ስላንተ በመስቀል ላይ ሞቶአል፤ አሁንም

በውስጥህ ለአንተ ይናገራል። ከሥጋ የሆነ ሥጋ ነው። ከእርሱ የሚመጣውን ሁሉ እግዚአብሔር ፈጽሞ አይቀበለውም፤ ያም ሆኖ ደህንነት በክርስቶስ መስቀል ላይ ያለቀ መሆኑን እያወቅን በሕይወታችን ድል ለማግኘት መልካም ለመሥራት ግሰብና መልካም ነገሮችን ማድረግ አለብን እንላለን። አንድ ነገር በደምብ እንረዳ ምንም መልካም ነገር በራሳችን ማድረግ አንችልም። ድል ከእግዚአብሔር በነፃ የሚሰጥ ስጦታ ነው።

ከ1ኛ ቆሮ 15:57 በፊት ያለው ጥቅስ ስለ ኃጢአትና ሞት ይናገርና በቁጥር 57 ላይ እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ድል ያመራል። ድል ግልት በሞት እንዲሁም በሕማና በኃጢአት ላይ ባለውጤት መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር የፈጸመው ቤዛነት ኃጢአትን ብቻ ሳይሆን ሕማንና ሞትንም ድል ይነሣል። በመከከላችሁ ሆኜ ለእያንዳንዳችሁ ተራ በተራ እግዚአብሔር ድልን ለማን ሰጥቷል የሚለውን ወንጌል ብነግራችሁ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር።

እንዴት ብዬ ነው ፈተናን የማሸንፈው? ትዕቢቴንስ እንዴት አስወግደዋለሁ? ቀናተኛነቴንስ እንዴት ድል እመታዋለሁ? ብላችሁ እንደምታስቡና በዚህ ነገር ጌታችንን እንደምትጠይቁ ጥርጥር የለኝም። ኃጢአት ኃይሉን በአናንተ ላይ በገለጸ ጊዜ ከኦጢአት ለመዳን ጌታን ምንኛ ጠራችሁ? ያም ሆኖ ግን ተስፋ ቢል መቁረጥ ምን ያህል ድል እስከምታገኙ ቆማችሁ ይሆን? ዛሬ ግን አንድ የምንገራችሁ የምስራች አለ! አሁም ይኸ ነው፤ በጌታ ኢየሱስ ያለው ገርነት፤ ቅድስናና የጸሎት ሕይወት ጌታን እንደገል አዳኛችሁ ከተቀበላችሁበት ጊዜ ጀምሮ በነፃ ተሰጥቷችኋል። በክርስቶስ ያመንክ ወንድሜ ሆይ ጌታን ስትቀበለው የእርሱ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው። ይህ የምስራች ካልሆነ እንግዲያውስ የምስራች ምንድነው?

ከፈለግህ መጽሐፍ ቅድስን ለማንበብና ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ሕንኙነት ለማድረግ ምን ያህል ሰዓትና ኃይል እንዳጠፋህ አስላ። እንዲሁም ኃጢአትንና ቶሎ መናደድን ለማሸነፍ ምን ያህል ጥረት እንዳደረግህ እውጣና አውርድ። በዚህ ሁሉ ግን ኃጢአትን ካለማድረግ ይልቅ ኃጢአትህን መናዘዝ ትችል ይሆናል። ቢሆንም በአብዛኛው ኃጢአትን ካለማድረግ ልትቆጠብ አልቻልክም። ስለዚህ ባለማቋረጥ ትሸነፋለህ።

ይህንንም ልታስወግድ ጥረት ብታደርግ መዋሸትህን ትቀጥላለህ፤ በዚህም ተስፋ ትቆርጣለህ። በአንድ ወቅት አንድ ቦታ ሳገለግል ላለመዋሸት ቢሞክሩም ከመዋሸት ግን ራሳቸውን ሊለውጡ ያልቻሉ መሆናቸውን የነገሩኝ በርካታ ወንድሞችና እህቶች አጋጥመውኛል። በእውነት ዛሬ የምስራችን የሚያበስር ወንጌል ለአንተ አለኝ! እግዚአብሔር የጌታ ኢየሱስን ቅድስና፣ ትዕግሥት፣ ፍጹም ፍቅርና ታማኝነት በነፃ ሰጥቶሃል! ለሚፈልግ ሁሉም በነፃ ሰጥቷል። በኢየሱስ እንዳለው የተቀደሰ ኑሮ ውበት ያለው የቀረበ ሕብረት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ሰጥቶሃል። በራሴ አሸንፋለሁ ብለህ የምትንጠራራ ከሆነ ግን ከሃያ ዓመት ድካምና ጥረት በኋላም ክፉ ዓመልህን ወይም ትዕቢትህን ልትለውተ አትችልም። ከሃያ ዓመት በፊት እንደነበርኸው ሆነህ ትቀራለህ።

እግዚአብሔር ለአንተ ፍጹም ደኅንነት አለው። የክርስቶስ ትዕግሥትና ቅድስና የአንተ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር የክርስቶስን መልካም ነገር ሁሉ የአንተ እንዲሆን አድርጓል። ይህ ነው እግዚአብሔር የሰጠን ደኅንነት ፡

በሥራ ራሱን ሊያድን የሞከረ ኃጢአተኛ አይተህ ታውቃለህ? እኔ ጥቂቶች አጋጥመውኛል። እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ስታገኛ «ክርስቶስ ሁሉን ስላደረገ አንተ ለደኅንነት ምንም ዓይነት መልካም ነገር መፈጸም (መሥራት) አያስፈልግህም፤ እግዚአብሔር እንድትድን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሰጠህ ማድረግ ያለብህ እሱን መቀበል ነው።» ብለህ ትነገረዋልህ። በተመሳሳይም ድልን በሚመለከት «ክርስቶስ ሁሉን ስላደረገው አንተ ምንም ማድረግ አያስፈልግህም። ደኅንነት ያለ አንተ ሥራ ከእግዚአብሔር ነፃ ጸጋ እንደተገኘ ሁሉ በኃጢአት ላይ ድልም ያለ አንተ ሥራ የእግዚአብሔር መልካም ስጦታ ነው። ደኅንነት የአንተን ጥረት አይሻም፤ ድልም እንዲሁ ጥረትህ አያሻውም። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንተ መስጠት ብፈልግ በመጀመሪያ ማወቅ ያለብህ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት ቃላት የአንተ አይደሉም፣ ሽፋኑም በአንተ አልተሸፈነም፣ ርዕሱም በወርቃማ ፊደሎች በአንተ አልተጻፈም። እነዚህ ሁሉ በሌሎች የተደረጉ ናቸው። ይህን እንደ ስጦታ ብሰጥህ አንተ ያልደከምህበትን ነው ያገኘኸው። የድልም ነገር እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር

በነፃ የሚሰጥህ ስጦታ ስለሆነ ወደ ድል፣ ቅድስናና ፍፁምነት በራሳችን ጥረትና ሥራ ቀስ በቀስ አንመጣም፤ በፍጹም እንደዚህ አይቻልም። ግንም ድል የነፃ ቢኖር ድሉ በጌታ ኢየሱስ የተገኘ ነው።

ትዕቢቷንና ቁጡነቷን ለማስወገድ ከሃያ ዓመት በላይ ሞክራ ሳይሳካላት መቅረቱ ብቻ ሳይሆን ፍጹም የተስፋ መቁረጥ ስሜት የተሰማት አንዲት እህት ለምክር አገልግሎት ወደ እኔ መጣች። የመከርኳትም እንዲህ ብዬ ነበር፤ «ትዕቢትንና ቁጡነትሽን አስወግዳለሁ ብለሽ የምትጥሪ ከሆነ ሌላ ሃያ ዓመት ቢጨመርም አይሆንልሽም። «የእግዚአብሔርን ስጦታ» ከተቀበልሽ ግን ዛሬውኑ ከኃጢአትሽ ነፃ ትሆኛለሽ። ይህ ስጦታ በራሱ በእግዚአብሔር የተሰጠ ነፃ ስጦታ ነው፤ እሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስን አዳኝሽ አድርገሽ እንደተቀበልሽው የድልሽም መሪ አድርገሽ ብትቀበይው ድል ይኖርሻል።» ብዬ መከርኳት። ይህን እንደሰማች እግዚአብሔር የሰጣትን ይህንን ድል ኢየሱስን ድሏ በማድረግ በእምነት ተቀበለች። እስቲ የሥራህን ከንቱነትና በሕይወትህም ያጋጠመህን ውድቀት ተገንዘብ።

በሮሜ 6፡14 ላይ «ኃጢአት አይገዛችሁምና፣ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና» ይላል። አሁንም ይህን ጥቅስ እስቲ ደግመን እንየው። ለምንድነው አማኞችን ኃጢአት የማይገዛን? ከሕግ በታች ሳይሆን ከጸጋ በታች ስለሆንን ነው። መልሱ ይህ ከሆነ ከሕግ በታች መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ምንም እንኳ ደጋግሜ ብገልጸውም ከሕግ በታች የሚለው አባባል ሰው በእግዚአብሔር ፊት በድካሙና በጥረቱ እንዲመላለስ መጠየቁን ያመለክታል። እንዲህ ከሆነ ከጸጋ በታች መሆን ማለትስ ምን ማለት ነው? ከጸጋ በታች መሆን እግዚአብሔር ስለ ሰው መሥራቱን ያመለክታል። እንግዲህ በእግዚአብሔር ፊት በጥረታችን እንገኝ ካልን ኃጢአት ይገዛናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ እኛ በጸጋው ከሠራ ኃጢአት በእኛ ላይ ጌትነት አይኖረውም። እግዚአብሔር ስለ እኛ ሲሠራ ኃጢአት አይገዛንም። እንግዲህ የእኛን ጥረት የሚጠይቅ ሁሉ ድል አይደለም። ኃጢአትን ለማሸነፍ የምናደርገውን ትግል ስናቆም እግዚአብሔር ስለ እኛ እየሠራ ድል በነፃ ወደ እኛ ይመጣል።

እንበል ክርስቲያን የሚለውን መጠሪያ ስም እስከታጣ ድረስ ኃጢ አት ያሸንፈህ ሰው ትሆናለህ። ልንገርህ ይህንን የእግዚአብሔርን ስጦታ አሁን ብትቀበል ወዲያውኑ የድል ሰው ትሆናለህ። የድል ማርህ የስጦታ መርህ ነው፤ የሥራ ዋጋ ግን አይደለም። ይህን የእግዚአብሔር ስጦታ በመቀበልህ ሕይወትህ ባለ ድል ይሆናል። ሁሉም ይስተካከላል።

የድል ሕይወት በስጦታ እንጂ በጥረት የሚገኝ አይደለም።

የድል ሕይወት የሚገኘው በነፃ እንጂ በጥረት አይደለም። በነፃ ማግኘ ትና በጥረት ማግኘት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? በነፃ ማግኘት ማለት አንድን ነገር ያለ ጥረት ማግኘት ሲሆን በጥረት ማግኘት ደግሞ ቀስ በቀስ ብዙ ነገር አድርገህ ወደ አለምከው ግብ ለመድረስ በውጣ ውረድ የምትሠራው ሥራ ማለት ነው። የክርስቲያን ድል ግን ቀስ በቀስ የሚደረስበት ጉዳይ አይደለም።

በአንድ ወቅት ወደ ኪሊንግ ተራራ እወጣ ነበር። በጌታ ወንድም የሆነ ሲንግ ሊያንግ ዮ፤ ከእርሱ ጋር ተራራውን እንድወጣ ጠየቀኝ። ያንን ረጅም ተራራ እየወጣን ሳለ በዚያው ልክ እየደከመኝ መጣ። የተወ ሰነ ርቀት እንደሸፈንን ወንድም ዮን ከዚህ በኋላ ምን ያህል እንጓዝለን ብሎ ጠየቅሁት። ከተራራው ጫፍ ለመድረስ ምንም ያህል አልቀረንም ብሎ መለሰልኝ። ቀስ እያልን መውጣቱን ተያያዝነው፤ ያም ሆኖ ግን አሁንም አልደረስንም። ወንድም ዮን በጠየቅሁት ቁጥር በመደጋገም የሚ ሰጠኝ መልስ አሁን ትንሽ ነው የቀረን የሚል መልስ ነበር። በመጨረሻም ግን በወላንሳ ይዘውኝ ወደ ተራራው ጫፍ ከወጣን በኋላ ኪሊንግን አገኘሁት። እዚህ ላይ ልነግራችሁ የምፈልገው የእኛ ነገር በድካም ነው የሚገኘው፤ ከጌታ ዘንድ የምንቀበላቸው ድሎች ሁሉ ግን ያለምንም ውጣውረድ የሚገኙ ናቸው።

«በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ ይልቁን፥ የጸጋን ብዛ ትና የጽድቅን ብዛት ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።» ሮሜ 5:17

በዚህ ጥቅስ ላይ ጳውሎስ ድል ስጦታ ነው በግለት ይናገራል። ስለ ዚህ ድል ቀስ በቀስ የምታገኘው ነገር ሳይሆን የተሰጠህ ስጦታ ነው። ድልን ለማግኘት የምታደርገውን እንቅስቃሴ አቁም። የአንተን ሥራ አይ ጠይቅም። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱሴን ልሰጥህ ፈለግሁ። ለመቀበል ጥረት ማድረግ አለብህ እንዴ? በፍጹም። እጅህን ትዘረጋለህ፥ በስኮንድ ውስጥ ታገኘዋለህ። ስጦታ እንደመሆኑ መጠን እቤትህ ገብተህ መጸም እንዲ ሁም በቀን ሦስት ጊዜም ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም አዙረህ ተንበርክከህ መጸለይ የለብህም። ይህ ሁሉ አስፈላጊ አይደለም። ከአንተ የሚጠበቀው መቀበል ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለመቀበል ምን ዓይነት ሥነ ሥር ዓት መፈጸም ያስፈልጋል? በእጅህ መቀበል እንጂ ምንም ዓይነት ሥነ ሥርዓት አያስፈገውም። ድልም እንዲሁ ነው። በነፃ የምታገኘው ስጦታ እንጂ በጥረት የምታገኘው አይደለም።

«ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረ ገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።» 1ኛ ቆሮ 1:30 ሁላችንም ይህን ጥቅስ በሚገባ እናውቀዋለን። እዚህ ላይ ስለ ጥበብ አጠ ቃላይ ሐሳብ ምንም መናገር አያስፈልገኝም። እንዲሁ አልፈዋለሁ። ነገር ግን ጽድቅ፣ ቅድስና ቤዛነት በሚለው ላይ እናተኩር እስቲ አሁንም በድጋሚ ልጠይቃችሁ፤ እግዚአብሔር ክርስቶስን «ቅድስናችን» ያደረ ገው መቼ ነው? ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮና እር ሱን አዳኛችሁ አድርጋችሁ በእምነት ከተቀበላችሁበት ጊዜ አንስቶ እን ደሆነ በእርግጠኝነት ትመልሱልኛላችሁ። እርሱን እንደ ጽድቃችሁ ከመ ቀበላችሁ በፊት ሦስት ቀን ግልቀስ አላስፈለጋችሁም፤ እንዲሁም ያስቀ የማችኋቸውን ሰዎች ይቅርታ መጠየቅም አላስፈለጋችሁም፤ እግዚአብ ሔር የተመሰገን ይሁን! የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እያንዳንዳችን ሞቷል፤ በእምነት ጽድቅን ብቻ ሳይሆን ቅድስናንም ተቀብለሃል። ጌታ ኢየሱስን እንደ ፅድቅህ አድርገህ እንደተቀበልኸው ሁሉ እንደ ቅድስናህም አድ ርገህ በመቀበሉ ጉዳይ ላይ መቸገርህ ነው። ስለዚህም አብዛኛውን ጊዜ ኃይልህን በማጥፋት በራስህ ዙሪያ ትዞራለህ። በክርስትና መንገድ ቀስ በቀስ ተጉዞ አንድ ቀን ቅድስናን አገኛለሁ ብለህ ካቀድህ ዘበት ነው፤ መቼም አታገኝም። የራሱን ጽድቅ ለመፈጸም የሚያስብ ሁሉ

እንደማይድን በተመሳሳይ ቅድስናን አገኛለሁ ብሎ የሚያስብም በምንም ዓይነት ባለ ድል አይሆንም።

በነፃ በመቀበልና በጥረት በማግኘት መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው? የጊዜ ልዩነትን እናያለን። አንዱ ወዲያውኑ የሚከናወን ሲሆን ሌላው ደረጃ በደረጃ የሚገኝ ነገር ነው። አንድ የዶሮ ሌባ በሳምንት ሰባት ዶሮ ይሰርቅ ነበር። በኋላ ላይ ግን ይህን ባሕሪውን ለመልወጥ አሰበ። ከስድስት ሳምንት በኋላ ጨርሶ መስረቅን ለማቆም በማሰብ በየሳ ምንቱ አንዳንድ ዶሮ እየቀነሰ መስረቅ ጀመረ ይባላል። ይህ ታሪክ እውነ ትነት ሊኖረው ይችላል። የጌታ ድል ግን ወዲያውኑ የሚገኝ ነው።

ቼር በነበርኩ ጊዜ ቁጣው በጣም አስደንጋጭ የሆነ አንድ ወንድም አገኘሁ። ቁጣው ሲገነፍል ሚስቱና ልጆቹ ይርበደበዳሉ። በልብስ ጥልፍ ሥራ ሱቁ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች፣ ከርስቲያን ወንድሞች እንኳ ይፈሩና ይንቀጠቀጡ ነበር። አንዳንዴም በስብሰባ ስፍራዎች ሁሉ ሁከት ይፈጥር ስለነበር አንድ ቀን ይህን ስሜቱን ለመቆጣጠር ምንም መንገድ እንዳላገኘ ነገረኝ። እኔም ጌታን እንደ ድሉ ቢቀበል ወዲያውኑ ድል ሊያገኝ እንደ ሚችል ነገርኩት። ወዲያውም ተቀበለ! ድልንም መለማመድ ጀመረ።

ጥቂት ከቆየ በኋላ ድል ማግኘት ከጀመረ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነው ጠየቀኝ ቀኑን አብረን ስንቆጥር አንድ ወር ገደማ ሆኖታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ አንድ ቀን ሚስቱ ለሞት እስክምትደርስ በጣም ታማ እንደነበረ ነገረኝ። እንዲህ ያለው ነገር በፊት ቢከሰት ኖሮ በጣም ተጨንቆ ፊቱን በማጨማደድ እየተብሰጨ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ይወጣና ይገባ እንደ ነበር አጫወተኝ። በዚህ ጊዜ ግን ሚስቱ ስትታመምና የልብ ትርታዋ ሲቀንስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን እንዳለ በተረጋጋ ስሜት በለስላሳ መንፈስ ነገረኝ። አስፈሪ ቁጣው ፈጽሞ ተወገደ። ሚስቱም ታክማ ተሻላት እርሱም የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ይጠነቀቅላት ነበር።

ቼርን ትቼ ስሄድ ሊሸኘኝ መጣ። ባለፉት ጊዜያት የሌላ ሰው እንጂ የሱ የራሱ ሚስት ያልታመመች ያህል ምንም ዓይነት ጭንቀት እንዳልነበ ረበት አጫወተኝ። በዚህም ጊዜ በሱቁ ውስጥ የጥልፍ ሥራ የሚሠሩ ሴት ሰራተኞቹ ለቁጥጥር በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። በተጨማሪም ባለ ፈው ወር በሱቁ ውስጥ ብዙ አሳዛኝ ነገሮች የተፈጸሙ መሆኑን ነገረኝ።

ቀድሞ ቢሆን በጣም ይበሳጭ ነበር። አሁን ግን የእርሱ ችግሮች እንዳል ሆኑ አድርጉ ወሰዳቸው። ቁጣው ስለጠፋ እንዲያውም እየሳቀ ለምን እን ዲህ ያለ ነገር ያደርጋሉ ማለት ጀመረ። ይህ ድል ስጦታ ነው። በጥረት የማግኘት ነገር ቢሆን ናሮ ከሃያ ዓመታትም ጥረት በኋላ ድል አይቀ ዳጅም ነበር።

አንድ ጊዜ አንዲት ሚሲዮናዊት ወደ ሕንድ ሄደች። በጉዞዋ ክፉ አመሏን እንጂ ከእሷ ጋር ምንም ነገር ይዛ አልሄደችም ነበር። ይህች ሚሲዮናዊት እህት ሁልጊዜ ትናደዳለች። መንፈሳዊ ጓደኛዋ እሷ መታ ገስ ከቻለች መላው ዓለም መታገስ ይችላል ስትል መስክራለች። የድል ሕይወትን ምስጢር ታውቅ ስለነበርም ለዚህች ሚሲዮናዊት ይህ ህይወት እንዴት እንደሚገኝ በደብዳቤ ነገረቻት። ይህች ሚሲዮናዊት ደብዳቤ ውን ተቀብላ እንደሚለው አደረገች። ከሦስት ወር በኋላም ከሚሲዮናዊቷ የመጣው የመልስ ደብዳቤ ዋና ሐሳቡ ይኸ ነበር፤ «ደብዳቤሽን እንዳነብ ብኩ ወንጌል ይህ እንደሆነ አወቅኩ! ክርስቶስ ትዕግሥት ነው፤ እርሱን የእኔ ድል አድርጌ በተቀበልኩት ጊዜ ብስጭት በነነ። በቅርብ ጊዜ ባጋጠ ሙኝ ከባድ ውድቀቶች ምክንያት ግን ለሦስት ወር ያህል ሃሳብሽን እስካ ጣጥመው ድረስ ለመናገር አልደፈርኩም። እነዚህ ሕንዳውያን አገልጋ ዮች ዝግተኞችና ድብቆች ናቸው። የቤቴን መዝጊያ በዘጋሁ ቁጥር በእነ ርሱ ላይ ያለኝን ቅሬታ ለመግለጽ አላትመው ነበር። ይሁንና ደብዳቤሽ ላይ በገለጽሽልኝ የድል ሕይወት ምስጢር መኖር ስጀምር አንዴም በሩን አላላተምኩም፤ የቅሬታም አመለካከት አልነበረኝም።» ብላ መልስ ጽፋለች።

በጋጢአት ላይ ድል ያለ ጥርጥር በጌታ ይከናወንልሃል፤ ስለሆነም ምንም ዓይነት ጥረት ማድረግ አያስፈልግም። እደግመዋለሁ ! ድል በነፃ የሚገኝ እንጂ በጥረት የሚመጣ አይደለም።

የድል ሕይወት ማግኘት እንደ ተዓምራት ይቆጠራል

«የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ ስለ በጐ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግ ንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» ፊልጵ 2:12–13

ጳውሎስ የራሳችንን መዳን እንደ እግዚአብሔር በጉ ፈቃድ የምንፈጽምበት ምክንያት በቀላሉ እርሱ እንድንፈጽም ስለሚያስችልን ነው ብሎ ይነግረናል። በውስጣችን ተንቀሣቅሶ ቅዱስ መሆን የሚያስችለን እግዚአብሔር ነው። እርሱ ሁሉን በእኛ ውስጥ ፈጽሞ ስለሠራ ቅዱሳን እንሆ ናለን እንጂ እኛ ብርቱ ጥረት ስላሣየን አይደለም። ምክንያቱም ይህ የቅድስና ሕይወት ፈጽሞ ጌታ ራሱ ያከናወነው ሥራ እንጂ የጥረታችን ውጤት አይደለም።

በምድር ላይ ብዙ ሰዎች ያለ ተዓምራት ብልሹነታቸውን ሊያስወግዱ አይችሉም ብዬ ያለማመንታት እናገራለሁ። አንዳንድ ሰዎች ውድቀታቸውን አያውቁም፤ ድካማቸውን አያዩም። ሌሎች ደግሞ በትዕቢተኛ ባሕሪያቸው ላይ ልጓም ሊያደርጉ እንደማይችሉ ይገነዘባሉ። ተአምራት ከሌለ ግናቸውም ወደ ድል አይመጡም። ግነው ኃጢአትን ሊያሸንፍ የሚችል? የሰው መንገድ ኃጢአትን መጨቆን ነው። እግዚአብሔር ሥራውን ሲሠራ ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ አሮጌው ሰውነታችንንና ኃጢአታችንን አስወግዶ ንጹሕ ልብን ይሰጠናል። የእግዚአብሔርን ልብ ብንረዳ ምንኛ ደስተኞች በሆንን ነበር!

ከብዙ ሰዎች ይልቅ ስሜቷ እጅግ ኃይለኛ የነበረ አንዲት እህት ነበረች። ባለቤቷና ልጆቿ እንዲሁም የሚያውቋት ሁሉ ይፈሯት ነበር፤ ነገር ግን ክርስቲያን ነበረች። ይህን ስሜቷን ታዲያ ምን ታድርገው? ከብዙ ዓመታት በኋላ ጌታን እንደ አዳኛዋ እንደተቀበለች ሁሉ እንደ ድሏም አድርጋ ተቀበለችው። ልክ ይህንን እንዳደረገች በግሥቱ ፀጉሯን ልታበጥር ወደታችኛው ፎቅ ከመውረዷ በፊት ከባድ ፈተና ገጠማት። ባለቤቷና ሰራተኛው ታችኛው ፎቅ በጣም ውድ የሆነ አምፑል ሊሰቅሉ ሲሞክሩ በንዝህላልነት ሳይሆን አይቀርም አምፑሉን ጣሉትና ደቀቀ፤ ልክ ያን ጊዜ እነርሱ ወዳሉበት ክፍል ወረደች። ባለቤቷ እንዳያትም በቁጣ ትናደዳለች በሚል ፍርሃት በድንጋጤ ተሳቀቀ። ነገር ግን ግንም ከሚጠብቀው ውጭ ረጋ ብላ የደቀቀው አምፑል ተጠርጐ ይነሣ ስትል ሠራተኛውን አዘዘች። ባለቤቷ በጣም ተደነቀ። ወትሮ ትንሽ ስኒ ወይም ሣህን ቢሰበር ትጣላ ነበር። እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ሲያይ ያን ሌሊት በደንብ ተኝታ መሆን አለመሆኗን ወይም ታማ እንደሆን

ጠየቃት። መልሷ እንዳልታመመችና ጌታ አርጌ ማንነቷን እንዳሰመ ገደ ላት ነበር። ባለቤቷ «ይህ ተዓምር ነው! ይህ ተዓምር ነው» በማለት ጮኸ። በእርግጥም ተዓምር ነበረ። እግዚአብሔር ይመስገን!

ሚስተር ቻርለስ ጂ ትርምቡል በዘመኑ የሰንደይ ስኩል ታይምስ ዋና አዘጋጅ ሲሆን በጣም መንፈሳዊ ነበር። ይህ ወንድም የድል ሕይወት ተዓምራት መሆኑን በሚገባ ተቀብሎታል። በአንድ ወቅት ለአንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ጌታ ኢየሱስን ወደ ሕይወቱ ስለተቀበለው አንድም ጊዜ ተናድዶ አንደግያውቅና የሚናደድ ዝንባሌም ጨርሶ እንደሌለው መሰከረለት። የቤተክርስቲያን ሽማግሌውም «የቀድሞው ኃጢአተኛ» ሁሉ አሁን የሉም ለማለት ፈልገህ ነውን? አለው። ሚስተር ትሩምቡልም «አዎን እንደዚያው ነው» በማለት መለሰ። ሽማግሌውም «ደህና ይህ በእንተ ሕይወት እውነት እንደሆነ አምናለሁ። ለእኔ ግን እውን ሊሆን አይችልም» አለ። ሚስተር ትሩምብል ሽማግሌው አብሮት ይጸልይ ዘንድ ጠየቀው። በዚያን ተገም ብዙ ጸለዩ በመጨረሻም ሽማግሌው አሁን ደይሆንም ያለው እንደሚሆን ተቀበለ። በሌላም ቀን ሽማግሌው ሚስተር ትሩምቡልን አግኝውና እንዲህ ሲል መሰከረለት! «ያን ምሽት ከአንተ ጋር ጸልዩ እንዳገኘሁት ያለ ነገር በሕይወቴ ጨርሶ አግኝቼ አላውቅም። በእርግጥ ተዓምር ነው። ድልን ለማግኘት መታገልና ኃይልን ማፍሰስ አያስፈልግም። በእውነት ይህ አስደናቂ ተዓምር ነው» አለው። ከዚያም በኋላ ትንሽ ቆየት ብሎ በሚሠራበት ቦታ በቦርዱ አባላት መካከል ከፉ ተፅዕኖ እንዳለበት ነገር ግን መታገሥ እንደምለ ለሚስተር ትሩምቡል ጻፈለት። እንዴት ያለ ተዓምር ነው!

ወገኔ ሆይ! መፍታት ያቃተህ ችግር ወይም ልትተወው ያስቸገረህ ኃጢአት ካለ ጌታ ኢየሱስ በእንተ ሕይወት ተዓምር ይሠራል። ለዓመታት ተስፋ ያስቆረጠህን ጉዳይ በእንዲ ይፈታዋል። ምንም ዓይነት ኃጢአት ይሁን የመንፈስ ወይም የሥጋ ወይም የሐሳብ ወይም የአካል ወይም የባሕርይ ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማድረግ ወይም አለመለየት ወይም ለመናዘዝ መቸገር ይሁን ጌታ የኃጢአቱን ምንነት ሳይመለከት ተዓምር ይሠራልሃል። ራስህን ለእግዚአብሔር ልትቀድስ አትችልም፤ እርሱ ግን እንድትቀደስ ያደርግሃል። በራስህ መታገሥ

አትችልም! እርሱ ግን ታጋሽ ያደርግሃል። እግዚአብሔር በተዓምራቱ ማንኛውንም ኃጢአት ድል መንሣት ይችላል።

የድል ሕይወት የተሸፈነ አይደለም

የድል ሕይወት ውጤት የሚታየው ተገልጦ እንጂ ተሸፍኖ አይደለም። በራሳችን የሚገኝ ድል ሁልጊዜ ራሳችንን በመጨቆን የሚገኝ ነው። ትክክለኛው የድል ሕይወት ግን በነፃ ስጦታ የሚገኝ ነው። እኔ በምናርበት አካባቢ አንዲት በዕድሜ ጠና ያለች ሴት ነበረች። ይህችም ሴት የሚያሳዝናት ነገር ሲያጋጥማት የውስጥ ስሜቷን ጨቁና ላይ ላዩን ፈገግ ያለ ፊት ታሳይ ነበር። እንዲህ ያለውን የተጨቆነ ሕይወት ለተወሰነ ጊዜ ከኖረችበት በኋላ በውስጧ ታምቆ ደም መትፋት ጀመረች። ይህች ሴት በስተመጨረሻ ለምን ደም መትፋት ጀመረች? ችግሩ በውስጧ ታምቆ ስለቀረ ነው። በክርስቲያን ሕይወት ያለው እውነተኛ ድል ግን የተገለጠ እንጂ የታመቀ አይደለም። የተገለጠ ሕይወት ጌርሶ የተገኘውን ነገር የመግለጥን ነገር ያመለክታል። ይህ በፊሊጲስዩስ 2፡12 «ደኅንነታችሁን ፈጽሙ» በማለት የተነገረውን ያሣያል። ቀደም ሲል ራሳችንን ለመሸፈን በኃይል ጥረናል፤ አሁን ግን በእኛ ውስጥ የሚደረገውን የክርስቶስን ድል እንገልፃለን። ክርስቶስ በእኔ ስለሚኖር በዓለም ፊት እርሱን እገልጣለሁ።

ሚስስ ፔን ሌዊስ ግጥም የመግጠም ችሎታ ያላትና ሕፃናትን ወደዚህ የድል ሕይወት በመምራት የተካነች አንዲት ወጣት ጓደኛ ነበራቻት። አንድ ቀን ሚስስ ፔን ሌዊስ ሕፃናቱን እንዴት እንደምትይዛቸው ለማየት ወደዚች ወጣት ሄደች። በዚያን ቀን ይህች ወጣት ከአሥር የሚበልጡ ሕፃናትን ምግብ ጋብዛ ነበር። ልክ በልተው ጠረጴዛ ከመፅዳቱ በፊት ፔን ሉዊስ በሥፍራው ደረሰች። ወጣቷም ሕፃናቱን «ይህን ቆሻሻ ምን ማድረግ ይቻላል?» አለቻቸው። እነርሱም ለመምህራቸው በንጹሕ የጠረጴዛ ልብስ እንዲሸፈን ሐሳብ አቀረቡ። እርሷም እንደተባለችው አደረገች። እንግዳ ሆና ሕፃናቱን እንዴት እንደምትይዛቸው ለመገንዘብ የመጣችው ፔን ሉዊስ ከሄደች በኋላ ወጣቷ ልጆቹን እንግዳዋ በጠረጴዛው ላይ ያለውን ፍርፋሪና የተንጠባጠበውን ወተ ማየት አለማየቷን

ጠየቀቻቸው። እነርሱም አላየችውም በማለት መለሱ። በመቀጠልም ልጄ ቸን እንዲህ በማለት በጥያቄ ያዘነቻቸው፤ «ምንም እንኳ እንግዳዋ ፍርፋሪውንና የተንጠባጠበውን ወተ ያላየች ቢሆንም ጠረጴዛው ንጹሕ ነው ትላላችሁ?» መልሳቸው ግን «እንግዳዋ ምንም ነገር ያላየች ቢሆንም ጠረጴዛው ግን ቆሻሻ ነበር» የሚል ነበር።

እዚህ ላይ ብዙ ሰዎች ውጫቸውን እንጂ ውስጣቸውን ንጹሕ ለማድረግ የተነሱ እንዳልሆኑ መናገር እፈልጋለሁ። ማለው የልብ ሐሳብ ስሜቱን መግለጥ የሚደፍር፣ ይህም ሆኖ ራሳችንን እንደ ድል ነሽ እንቆጥራለን። ሰዎች እንዲያመሰግኑን ጨኖና አንገት ደረ ለመሆን እንሞክራለን። ታጋሽ ለመሰል ታጋሽ አለመሆናችንን በሽሩን እንደብቃለን። እዚህ ላይ በግልጽ እናገራለሁ። በውስጥ የተጨቆነ ነገር ሁሉ ድል አይደለም፤ ከእኔነታችን ስንወጣና በምትካችን ክርስቶስ ሲገባ ያኔ ድል ይኖረናል። በዚህ ጊዜ የሚገለጥ ሁሉ ድል ነው።

ለምሳሌ አንድ ፍራፍሬ እያዞረ የሚሸጥ ሰው ወደ አንተ መጥቶ ፍራፍሬ እንድትገዛው ይጠይቅሃል እንበል። ነገር ግን ምንም ላትገዛው ትመልሰዋለህ። እንደገና ሁለት ሦስት ጊዜ መጥቶ ሲጠይቅህ ፍራፍሬውን አይተህ አልገዛም፣ አመሰግናለሁ ብለህ በመለስከው ቁጥር ብስጭቱን በውስጡ ጭምቅ ያደርጋል። ይህ ድል አይደለም፤ የንግድ ዘዴ እንጂ። የክርስቶስ ድል ግን ልብን እንኳን ያነፃል። በእጥፍ ድል ንጹሕ ልብ ነው።

በቼር ውስጥ የሚኖር ዕድሜው ከሃምሳ ዓመት በላይ የሆነ አንድ ወንድም አውቃለሁ። ይህ ወንድም የኮንፊሽስን እምነት ሥነ ጽሑፎች ወይም የቻይና የፍልስፍና አስተማሪዎችን ሥነ ጽሑፍ በዕድሜው ሙሉ አጥንቷል። በጌታ ካመነ ሦስት ዓመት ቢሆነውም የደሰሰውን ደምና ከኃጢአት የማንፃት ኃይሉን ብቻ ነው የሚያምነው። ጌታን ከተቀበለ በኋላ ባለው ሦስት ዓመት ውስጥ በኮንፊዩሽያኒዝምና በክርስትና መካከል ያለውን ዋና ልዩነት ፍጽሞ አላወቀውም። የኮንፊሽስ ተከታይ ስለሆነ በትዕግሥት ለመሥራትና ራሱን በመቆጣጠር ለመሻሻል ይሞክራል። በዚህም ጥረቱ ውጤት ካመጣ «የልምምድ ጠቢብ» የሚል ስያሜ ያገኛል። ይህ ወንድም ክርስቲያን ከሆነ በኋላ እነዚህን ልምምዶች ያደርግ

ክር።ትልቁን ችግር እንደ ትንሽ መቁጠር፣ አነስተኛውንም ነገር እንደ ምንም በመቁጠር የክንፈሽሰን አመለካከት ይዞ ቀጠለ። በጓላ ላይ የክር ስቲያን ድል የሚገኘው ራስን በመጨቆን ሳይሆን ክርስቶስን ድላችን አድርጉ በመቀበል እንደሆነ ሲገባው የድልን በር አቋረጠ። ከዚህ በፊት የክርስቶስ ድልም በሕይወቱ እንዳልነበረ መሰከረ። ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ሲተያይ ምንኛ ሰፊ ልዩነት አለው። በመስቀል ላይ በክርስቶስ ሞት የተመሰከረው ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ልዩ እንደ ሆነ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስም በእኛ ስለሚኖር ክርስትና ከሌሎች ሃይማኖቶች ልዩና ውብ ነው። ስለዚህም የደኅንነትን መንገልና በተለይም በድል እንድንኖር በእኛ ምትክ የሚኖረውን ክርስቶስን እንሰብካለን። ቀደም ሲል ይህ ወንድም በራሱ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ታማኝ የሆነ የክንፈሽሰስ ደቀ መዝሙር ነበር። አውነ ግን ራሱን ከራሱ አስወጥቶ ክርስቶስ በእርሱ ምትክ እንዲኖር ፈቅዷል? ያለ መጨቆንና ያለ ሽንፈት።

ከላይ ያሉት አምስት ነጥቦች ድል የሚነሣውን የዚህን ሕይወት ባሕርይ ይገልፃሉ። በመደምደሚያ ሙልክ ግን ትንሽ ታል ጨምራለሁ። ይህንን አስታውስ! ልክ እንደ ደኅንነት ድልም የምዝገባ ቅፅ አለው። በአንድ በሆነ ዓመት፣ በአንድ በተወሰነ ወር በአንድ በሆነ ቀን ድነሃል። ይህን ስል አንዳንድ ሰዎች ቀኑን ሊረሱ ወይም እርግጠኛ ላይሆኑ እንደሚችሉ ግን እገነዘባለሁ። ልክ እንደዳንከበት ዓመት፣ ወርና ቀን ወደ ድል የገባህበትም ዓመት፣ ወርና ቀንን መመዝገብ አለብህ። ምክንያቱም ድል ወደ አሸናፊነት ሕይወት የምትገባበት በር ስለሆነ ነው። ግንም ሰው ለመዳን ምንም ያህል አልቀረውም አይባልም። ዳነ ከተባለ ዳነ ነው። እንዲሁም ግንም ድል ሊነሣ ትንሽ ነው የቀረው አይባልም። ድል ድል ነው። ለማሸነፍ ምንም አልቀረውም ግለት እንደ አውነቱ ከሆነ ማሸነፍ አለመቻል ነው። ስለዚህም ሁላችንም ይህን የድል በር ግለፍ አለብን።

ምዕራፍ 4

ወደ ድል ሕይወት እንዴት እንደሚገባ

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም። ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁን በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለእኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።» ገላ 2፡20

ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሕይወት ምን እንደሚመስል፣ እንዲሁም በራሳችን የምንኖረው ኑሮ ተሸናፊነት ያለበት እንደሆነ አይተናል። የእግዚአብሔር ቃል የድልን መንገድ ቀላልነት የሚያሳየን ሲሆን ድል ወደሚነሣ ሕይወት እንያዥ እንደሚገባ እንግራለን።

ገላ 2:20 ላይ ያለው ጥቅስ ድል ወደሚነሣ ሕይወት እንዴት እንደሚገባ ያሳየናል። በመጀመሪያ «እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» የሚለውን እንወያይበት። በአሉታ «እኔም ሕያው ሆኜ አልኖርም» ማለት እንችላለን። በአዎንታ ግን «ክርስቶስ በእኔ ይኖራል» ማለት እንችላለን። ጳውሎስ ይህንን ልምምድ በሚገባ ስለያዘው ስገላትያ መልእክት ላይ እንደዚህ ለማለት ችሏል። ወደ እርሱም ጨርሶ ገብቷል። ጳውሎስ በገባበት መንገድ እኛም እንገባለን። እርሱ የገባበት መንገድ «እኔም ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» ከሚለው በፊትና በኋላ ላይ ተቀምጧል። ወደዚህ ሕይወት ለመግባት የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ እንዲህ በሚል ቃላት ተገልጧል። « ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» ሁለተኛውም የመግቢያ ሁኔታ እንደሚከተለው ይገኛል፣ «አሁን በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» ጳውሎስ እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች በሕይወቱ ስላሟላ ክርስቶስ ድሉ ሆኖ አገኘው። እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች በደንብ እንመልከታቸው።

ራስን መስጠት – ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፣

የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» የሚለው ነው። የድል ነሽ ሕይወት ከግኅኘት በፊት ለምን ከክርስቶስ ጋር መሰቀል ይኖርብኛል? አሁንም ሌላ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ፣ ክርስቲያን እንደመሆናችን መጠን በእኛ ውስጥ ስንት ሰዎች ይኖራሉ? ምን አልባት ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ አታውቁምን? በጌታ እንዳመንን ወዲያውኑ ጌታ በእኛ ውስጥ ሊኖር ይመጣል። ጌታ በእኛ መኖሩ የተረጋገጠ እውነት ነው። ግን ምን ያደርጋል የሚያሳዝነው ክርስቶስ በእኛ ቢኖርም አሁንም እኛ በእኛ ውስጥ እንኖራለን። ክርስቶስ በእኛ ውስጥ እንዲኖር ከስፈለገ እኔነታችንን ከራሳችን ውስጥ ማውጣት አለብን። እኛ ስንወጣም ድል ነሽውን ሕይወት እናገኛለን።

ለምሳሌ ሁለት ቤተሰቦች በአንድ ታዛ ስር ይኖራሉ እንበል። በመካከላቸው ችግር ቢፈጠር አንዱ ቤተሰብ ለቅቆ ቢሄድ ሁኔታው ያለ ጥርጥር ይለወጣል።ዛሬ አከራካሪው ነገር ክርስቶስ በአንተ ውስጥ የመኖሩ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም ካመንክጊዜ አንስቶ በአንተ ይኖራልና ነው ።አንቲ ግን ሙሉ ለሙሉ ሥፍራውን ለእርሱ መልቀቅ አለብህ። አንተ ኃጢአተኛው ኃጢአት ከሌለበት ከእርሱ ጋር ከመኖር ራስህን ስታገልል ሁሉ ወርቅ ይሆናል። ስለሆነም የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ አንተ ውጣ የሚለው ነው።

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ»

የአኅዚአብሔር ቃል ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀልን ያውጃል። እኛ ስለዚህ ቃል ምን እንላለን? ብዙ ጊዜ ራሳችንን ለመገደል እንሞክራለን። ያም ሆነና ግን አሁንም እንኖራለን። ብዙ ጊዜ የሞትን እንመስላለን። ሆኖም አልሞትንም፣ ራሳችንን ለመስቀል እንሞክራለን፣ መሞት

ግን ያቅተናል። ችግሩ እንግዲህ ምንድነው? ይህንን ጉዳይ በበለጠ ጥልቅነት እንመርምር።

1. አልችልም

ሁላችንም የመስቀሉን ምንነት እንደተገነዘብን አስባለሁ። ጌታ ለእኛ ሲሰቀል ኃጢአታችንን ብቻ ሳይሆን የተሸከመው እኛን ራሳችንን ከእርሱ ጋር ወደ መስቀሉ ወስዶናል። የሮሜ ስድስት ትምህርት ብዙዎቻችን ለዓመታት እናውቀዋለን። የኃጢአታችን ዋጋ በመስቀል ላይ በክርስቶስ እንደተከፈለ፣ አርጌው ሰውነታችንም ከእርሱ ጋር ተሰቅሏል። ስለዚህም ከእርሱ ጋር በመሰቀላችን ምክንያት የኃጢአት ጉዳይ መፍትሔ እንዳገኘ እውቀቱ አለን። ሮሜ 6፥6 ከክርስቶስ ጋር መሰቀሌ ጥርጥር የለውም፣ ግን ለምን የአብሮ መሰቀልን ውጤት አልለማመደውም? ጌታ ወደ መስቀል ወስዶኛል ሆኖም ግን እኔ አልሞትኩም። እስከ አሁን ድረስ በኃጢአት የታሰርኩ፣ ደካማ ተሸናፊና ኃይል አልባ ነኝ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለሃል፣ ይላል ታዲያ ለምን እስከ አሁን ያለ ኃይል እሆናለሁ? ብዙ የዳኑ ክርስቲያኖች ለዚህ በክንቱ ይደክማሉ፣ አንድ ቀን ድል እናገኛለን ብለው። ነገር ግን ድል ከእኛው እጅ የራቀ ነው። ምግብ ማዘጋጀት አንድ ነገር ሲሆን መብላቱ ደግሞ ፈጽሞ የተለየ ሌላ ነገር እንደሆነ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ለእኛ የፈጸመልንን ደኅንነት ማወቅ አንድ ነገር ሲሆን መቀበሉ ደግሞ ሌላ ነገር ነው።

ሮሜ 6 እያንዳንዳችን ለኃጢአት እንደሞትን ይገልጥልናል። ሮሜ 7 ግን እንደ ክርስቲያን ለኃጢአት የሞትን ሆነን ሳለ ለምን ግን እስከ አሁን እንዳልሞትን ይነግረናል። የሞትኩት እኔ ለምን አሁንም በሕይወት እኖራለሁ? መልሱ ሮሜ 6 ላይ ያለው እውነት ነው። ሮሜ 7 ግን ልም ምጹን ያሳየናል። ዛሬ ክርስቲያኖች ሮሜ ስድስትን ጠንቅቀው ያውቃሉ፣ ማለትም ለኃጢአት ባሪያዎች እንዳልሆኑ፣ ከሕግም ነፃ ወጥተዋል። እንዲህ በመሆኑም በየቀኑ ለኃጢአት የሞቱ እንደሆነ መቁጠር አለባቸው።

የገላትያ 2:20 ትምህርትና እኔ ወዲያና ወዲህ ነን። « ትምህርቱ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» የሚል ቢሆንም እኔ ግን አሁንም ሕያው ነኝ

እላለሁ። ትምህርቱ ከአሁን በኋላ የኃጢአት ባሪያ አይደላችሁም ቢልም እኔ ግን ኃጢአት ከእኔ ጋር ነው እላለሁ። ትምህርቱ ከሕግ ባርነት ነፃ ወጥታችኋል ቢልም እኔ ግን ዛሬም ከሕግ በታች ነኝ እላለሁ። በእውነት ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? በሮሜ 7 ላይ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔር ያደረገውን አምን ትክክል ነው ብለን አልተስማማንም፣ ፍርዱንም አልተቀበልነውም። ስለዚህ ሮሜ 7 በውስጣችን የተሸፈነ መወለድ እንዳለ ይገልጣል። ለምንድነው እግዚአብሄር እኛን የሰቀለው? ከልጁ ጋር ሊሰቅለን ፈጽሞ የማንጠቅምና ተስፋ የሌለን ከመጠ ገንና ከሞሻሻል ውጭ መሆናችንን አይቶ አይደለምን? ስለዚህ ከመሰቀል ውጭ ለምንም አንጠቅምም፣ ተስፋም የለንም። ስለሆነም መሰቀል የእኛ መለኪያ ሆኖ ቆሟል። የመሰቀሉ መለኪያ አንተና እኔ ሞት ብቻ የሚገባን መሆኑን የሚነግረው ነው። ይህ እግዚአብሔር ለአንተና ለእኔ ያለው ግምት ነው። በእውነት መሰቀሉን እንደ መለኪያችን አድርገን ብንቀበል ያን ጊዜ በእርግጠኝነት ፈጽሞ የማንጠቅምና ምንም መልካም ነገር እንደሌለን እናውቃለን። ከክርስቶስም ጋር መሞት የሚገባን መሆኑን እንረዳለን። እግዚአብሔር አንተና እኔ ካልሞትን በስተቀር ምንም ተስፋ እንደሌለን በትዳስ ቃሉ ተናግሯል። ይህን ብንረዳ መልካም ስራዎችን ልመሥራት እናስብ ይሆን?

የቻይና መንግሥት «አቲየም» ግጠሰን የሚከለክል አዲስ ሕግ አወጣ። ሕጉ ከወጣም በኋላ «ሲያጠኩ የተገኙ ሁሉ ይገደላሉ» አለ። እንበል ሕጉ ከወጣ በኋላ አንዱ ሲያጨስ መንግሥት ቢይዘው ያ ሰው ምን ያደርጋል ብለህ ትገምታለህ? ከመሞቱ በፊት ግጠስ እንዲያቆም መርፌ እንዲወጋው ዶክተር ያማክራል፣ እንዲህ ቢያደርግ ትርጉም የለሽ ነው የሚሆነው። ለምን? ምክንያቱም ጨርሶ የተፈረደበት ወንጀለኛ ነውና ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ስመሥራትና ለመሻሻልም መሞከር የለበትም። ሞቱን ብቻ ይጠባበቃል። ቢተመሰሳይ አነጋገር እግዚአብሔር ሞት የሚገባንና ከመሰተካከልና ከመሻሻል ውጭ መሆናችንን ከነገረን በእኛ ላይ ያስተላለፈው የሞት ፍርድ ትክክል ነው። ታዲያ ጥሩ ሥራ በመሥራት ራሳችንን ለማሻሻል ለምን እናስባለን?

ደኅንነት ከማግኘታችን በፊት መስተካከልና መሻሻል ጥቅም እንደ ሌለው የተቀበልን ቢሆንም ምናልባት እግዚአብሔርን ደስ እናሰኝ ይሆ ናል በሚል ግምት ከዳንን በኋላ እነዚህን ነገሮች ለማድረግ እንሞክ ራለን። ስንት ጊዜ መንፈሳዊ ሰዎች ለመሆን በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳኖች ገባን? ቃልኪዳኖቻችን ብዙዎች ነበሩ። በእውነት ግን ስንቶቹን አሟላን? በአንድ ወቅት ከምዕራቡ ዓለም የመጣች አንዲት እህት ሰላሣ የተለያዩ ቃልኪዳኖችን ለመፈጸም ለእግዚአብሔር ቃል እን ደገባች ነገረችኝ። ነገር ግን አንዱንም ለማሟላት አልቻለችም።ይህ እግዚአብ ሔር ለእኛ ያለውን መለኪያ እንዲሁም በእኛ ላይ ያሳለፈውን ፍርድ አለ መቀበላችንን ብቻ የሚገልጽ ነው። እንድንሞት ነው የተወሰነብን፣ ነገር ግን እኛ ሐኪም ስንፈልግና ስንጨነቅ ነው የምንገኘው። እባካችሁ መስ ቀሉ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ያለውን ቁጣ የሚገልጽ መሆኑን እንረዳ!

እኛን መስቀል ብቻ ጨጤጆጂ ሌላ ነገር አያስተካክለንም ወይም አያሻሽ ለንም። ይህ እውነት ሆኖ እያለ የማንረባ መሆናችንን በመረዳት ስቅላት የሚገባን እንደሆንን ካወቅን በኋላ ሠናይ ምግባር ያለን ሆነን ለመገኘት እንፍጨረጨራለን። በየጊዜው እንምላለን፣ ውሳኔዎችን እንወስናለን፣ ነገም ደግሞ የበለጡ ውሳኔዎችን እንወስናለን። «እግዚአብ ሔር ሆይ ከአሁን በኋላ አልበሳጭም፣ ምን አልባት ያለፈው ውሳኔም ጽኑ አልነበረም ይሆናል፣ ከአሁን በኋላ የበለጠ አጸናዋለሁ፣» እንዲህ በማድረግም ውሳኔ በውሳኔ እንሆናለን። በእርግጥ ጳውሎስ የተከተለው መንገድ ይህንን ነበረ። በሮሜ 7:18 ላይ እንዲህ ይላል፣ «ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።» በጳውሎስ ሕይወት ሁል ጊዜ መወሰንና ሁልጊዜ መውደቅ እንደሆነ ይናገራል። ይህ ዛሬ የብዙ ዎቻችን የጋራ ችግር ነው። እግዚአብሔር ለእኛ የሚለውን ለአንዴና ለመጨረሻ በአንክሮ እንስማ፣ የማንጠቅምና ተስፋ የሌለን በመሆናችን ሞት የሚገባችሁ ናችሁ ይለናል።

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» ማለት እግዚአብሔር በእኔ ተስፋ ቆርጧል፣ ልክ እንደ ጳውሎስ ራሴን ሰልችቻለሁ ማለት ነው። እግዚአ ብሔር አገላብጦ አይቶኛል። ጥቅም ወይም ተስፋ እንደሌለኝ ያውቃል። እኔም ራሴን ተስፋ እንደሌለኝ ቆጥሬ በፍጹም እግዚአብሔርን ላስደስት

አልችልም ብዙ አምኛለሁ። በሥጋ ያሉ ጨርሶ ተስፋ የላቸውምና ሞት የሚገባቸው ናቸው።

አንድ ሰሞን ብዙ ቅዱሳንን ቤታቸው በመሄድ እጎበኛቸው ነበር። ከጎበኘኋቸው አንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ አባወራዎች ታመዋል። በሌሎቹ ደግሞ ሚስቶች፣ አሁንም በሌሎቹ ቤተሰቦች ልጆች ታመዋል። ከጎበ ኘኋቸው ውስጥ ብዙዎቹ ተስፋ ስለቆረጡ «በእግዚአብሔር ፈቃድ በሰ ላም እረፍት ወደጌታ ቢቶሉ መሰብሰብ ይሻላል» ይሉኝ ነበር። ለምን እንዲህ ይናገራሉ? ተስፋቸው የመነመነ ነው። ዘመዳቸው ተስፋ የሌለው ከሆነ ቶሎ መሞቱ ይመረጣል። እግዚአብሔር ምንም ማድረግ ስላል ቻለና ተስፋ እንደሌለን ስላየ መሰቀል ብቻ እንዳለብን አልነገረንም? እኛስ በራሳችን ተስፋ ከሌለን መሰቀል አይሻለንም? ችግራችን ይኸ ነው። በአንድ በኩል የሮሜ ስድስትን ውሳኔ በደንብ እናውቃለን፣ በሌላ በኩል የሮሜ ሰባትን ሕይወት እንኖራለን እስከ አሁን ራሳችንን ጥሩ ነገሮች እንዳሉን እንቆጥራለን ለእግዚአብሔርም ቃል እንገባለን። ሮሜ 6 ጳውሎስ በራሱ ምንም እንደማይጠቅም ፍርድ የሰጠበት ነው።

ሮሜ 7 ደግሞ ጳውሎስ በራሱ ለምንም እንደማይጠቅም ሳይወድ በግዱ የተቀበለበት ክፍል ነው። እግዚአብሔር እኛን ከሥር መሰረታችን በደንብ ተመልክቶን በራሳችን የድልን ሕይወት እንደማንኖር ያውቃል። በእኛ ጥረት እንደማንበቃ ተረድቷል። ስለዚህም በራሳችን ለውጤት እን ደማንበቃም ተናግሯል። ታዲያ በመልሳችን ምን ማለት ነው ያለብን? እኛም በራሳችን ተስፋ ቆርጠናል ማለት ነው ያለብን። ማናችንም በራ ሳችን ውጤት እንደማናመጣ ብናስብ ወዲያውኑ ነፃ እንወጣ ነበረ። እግዚ አብሔር አንተና እኔ በራሳችን እንድንፍጨረጨር ሁሉንም ነገር የለቀ ቀልን እነዚህና ሌሎች ኃጢአቶች ተስፋ አስቆርጠውን በመጨረሻ ፈጽሞ አቅቶናል እንድንል ነው። እኛ በየአለቱ ኑሮአችንን በየጊዜው ቆይ አሁን እራሴን እለውጣለሁ በሚል ተስፋ በውሳኔ ላይ ውሳኔ እንወስናለን። በሮሜ 7 ላይ የጳውሎስ ልምምድ ይኸ ነበር።

ግንም ፈጽሞ ብልሹ መሆኑን ቢመስክር እኔ ሃሌሉያ! አሜን! እላ ለሁ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል የማንጠቀም መሆናችንን ይናገራ ልና እኔ ዎችማን ኒ ከሥር መሠረቴ ብልሹ ነኝ። ጳውሎስ በዘመኑ ተስፋ

ወደ መቁረጥ ገብቷል ለብዙ ዓመታት ተሰቃይቷል ለመሰቀል የሚገባ ሆኗል። አንተም ዛሬ ጥቅም የሌለህ መሆንህን ብታውቅ ያኔ ፈጥነህ ነፃ ትወጣለህ። ይህ ፈጽሞ እውነት ነው። መልካም ለመስራት የሚሞክሩ ኃጢአተኞች ሁሉ አይድኑም። እንደዚሁም በተመሣሣይ መልካም ለማ ድረግ የቆረጡ ቅዱሣን ሁሉም በፍጹም ድልን ሊለማመዱ አይችሉም። የክርስቶስን መስቀል በስህተት እንዳልተረጉምን ፈጥነን እንገንዘብ። ለእኛ የተሰጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ፍርድ በደስታ እንቀበል ትናንት የምጠቅም አልነበርኩም፣ ዛሬም አልጠቅምም ነገም የማልጠቅም ነኝ፣ ለዘለዓለም አልጠቅምም።

ለምንድን ነው እግዚአብሔር የመስቀሉን ትርጉም እንድንቀበል የሚ ፈልገው? ትርጓሜውን ባመቀበል በመጨረሻ ጌታ ቅድስናችን ፣ ፍጹም ነታችንና ድላችን እንደሆነ ለመቀበል ፍቃደኞች እንደምንሆን ያውቃልና ነው። ትንሽም የራሳችንን ተስፋ በውስጣችን ከሸሸግን የመስቀሉን ኃይል ለመቀበል እስከንችል ድረስ እግዚአብሔር በዝምታ ይጠብቀናል። አለመ ቻላችንን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንድንገነዘብና እንድንቀበለው እግዚአ ብሔር እኛን ወደ ሮሜ 7 ልምምድ ግምጣት አለበት።

እጅግ በሚገርም ሁኔታ ብዙዎች አለመቻላቸውን ቢረዱም ነገር ግን አሁንም ድልን አይለማመዱም። ይኼ ለምን ይሆናል? የዚህ ምክን ያቱ እግዚአብሔር በራሳችን ምንም እንደማንችል በመገንዘብ በእርሱ ላይ እንድንታመን ስለሚፈልግ ነው።

2 ወደፊትም አልችልም

ትናንትና አንዲት እህት አግኝቼ የአስርት ዓመታት የውድቀት ታሪኳን ለእኔ ስትነግረኝ ሁለት ሠዓት ፈጀባት። እየተናገረች ሣለች እኔ ሣቅሁ። «ከእንግዲህስ በአሸናፊነት ለመኖር ተስፋ አለሽ?» ብዬ ጠየቅኳት፤ እሷም ጨርሶ ችሎታው እንደሌላት በእውነትም መሠከረች፣ ነገር ግን አንድ ነገር ይጐድላታል። አለመቻላችንን መረዳታችን ብቻ ድልን አይ ሰጠንም አቅም እንደሌለን መረዳት አንድ ነገር ነው፣ ችሎታን ጨርሶ መተው ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ይህችን እህት ችሎታ እንደሌላት መረዳቷ መልካም እንደሆ ነገርኳት ግን አሁንም ለማሸነፍ

የምትጥር መሆኗን ተገንዝባለች፣ አለመቻሏን ካወቀች የራሷን ጥረት መተው አለባት። ያም ሆኖ ግን አሁንም በራሷ መከራ ማድረግ እንደ ምትችል ተስፋ ታደርጋለች። ይህች እህት ብዙ ጥራለች በመሆኑም ልታሸንፍ አልቻለ ችም። አንድ ጊዜ እንደገና ይቺን እህት መስቀሉን ለመሸከም፣ አቅም እንደሌላት እንድትረዳ እንዲሁም መሞከሯን እንድ ታቆምና ድልን አንድትጠብቅ አበከሬ አሳሰብኳት። ስለዚህ ምን ማድረግ እንደሚገባት ጠየቀችኝ እኔም አንዳች ማድረግ እንዳለባት ከተሰማት ምንጊዜም እንደምትወድቅ መለስኩላት። ለጥያቄዋ የእሷ መደምደሚያ ግን ይህ ነበር «አዎ ብሠራ የምወድቅ መሆኔን አቀበላለሁ፣ ሆኖም በራሴ ጥንታቄ ካላደረግኩ ግን ውድቀቴ የበለጠ አይሆንም?» አለች። በእውነትም የብዙ ሰዎች ችግር እዚህ ላይ ነው። በራሳቸው ምንም እንደማይችሉ በግልፅ እያወቁት በብርቱ መታገላቸውን ይቀጥላሉ፣ በዚህ ምክንያትም ድል የላቸውም።

ስለዚህ ድል ሁለት መሠረታዊ ገጽታዎች አሉት በመጀመሪያ እግ ዚአብሔር አንተን በአግባቡ እንደገመገመህ ማወቅ ሁለተኛ ስለድል ማሰ ብን አንኳን ማቆም። አንድ ወንድም ግን አላምንም አለኝ። ማመን አለመ ቻልህን ለእግዚአብሔር ንገር አልኩት እርሱ አለማመንህን እንድትናዘ ዝለት ብቻ ነው የሚፈልገው።

«በእምነት ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» ብሎ መናገር ከዚህ በኋላ ስለ ድል ወይም ማሸነፍ አይገደኝም ምክንያቱም ሁሉን ነገር በክርስቶስ እጅ ጥያለሁና ማለት ነው። ድል በመንግት ጉዳይ ላይ እጄን አንስቻ ለሁ፣ ስለድልም መጨነቅን አቁሚያለሁ ማለት ነው።

ከአሁን በኋላ ራሴን ለእርሱ አሳልፌ እሰጣለሁ፣ ድልም የእርሱ እንጂ የእኔ ጉዳይ አይደለም ብዬ ለእግዚአብሔር እናገራለሁ። አንድ ወንድም እንዴት ወደ ድል እንደሚገባ ጠየቀኝ።የእኔም መልስ «መተው» የሚል ነበር። መተው ማለት የእኔ ሥራ አይደለም ማለት ነው።

በእርግጥም ለእግዚአብሔር ምንም ማድረግ አልቻልኩም፣ እናደዳ ለሁ ስሜቴንም መቆጣጠር አቅቶኛል። መተው ወይም አሳልፎ መስጠ ትም አልችልም። ከአሁን ጀምሮ ግን የራሴን ነገር ጨርሶ አቆማለሁ

የሚል የልብ አመለካከት ሊኖረን ይችላል። ሆኖም በሚያሳዝን ሁኔታ ምንም እንኳን ወደ እግዚአብሔር መጥተን አልችልም ወደፊትም አልሞ ክርም ብንልም ከእርሱ ዘወር እንዳልን ራሳችንን እንተካለን ወይም ወደ ራሳችን እንመለሳለን።

ኦ! ወደ እግዚአብሔር ያመጣነውን ራሳችንን ስንሄድ ለእርሱ ጥለን መሄድ እንዳለብን እንግር። ራሱን በእግዚአብሔር ላይ የጣለና እርሱም ጋር ትቶ መሄድን ያወቀ ነፃ ይወጣል።

አንድ ወቅት አንድ ጽሑፍ በታይኘ ይጻፍልኝ ዘንድ ወደ አንዲት እህት አመጣሁ። ነገር ግን ከእርሷ ስለይ ሳላውቅ ጽሑፉን ይዤው ወደ ቤት ተመለስኩ። ታይኘ ለማድረግ ብትፈልግ ጽሑፉን ግግኘት አልቻ ለችም። ዛሬ እኛ ብዙ ጊዜ የምንጸልየው እንደዚህ ነው። በአፋችን«እግ ዚአብሔር ሆይ ፣ እባክህ እርዳኝ»እንላለን ፣ከጸሎት በኋላ ግን ወደ ራሳ ችን እንመለሳለን። ስንጻልይ «እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ ግሸነፍ አል ችልም፣ለግሸነፍም አልመኝም፣ አልሞክርምም ማለት አለብን። መተው ለእኛ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነውና። ይህ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ትርጉም ነው። እንዴት ያለ ድንቅ አባባል ነው።

ጠዋት በግለዳ ሰይጣን አውንም ያው ስለሆንክ ምንም አልተሻሻ ልክም ብሎ ይከስሃል። መጨነቅ ትጀምራለህ ግለት ነው? በፍጹም ፣ ከብዙ ጊዜ በፊት ጨርሶ ብልሹ መሆኔን አውቃለሁ፣ ስለዚህም ተስፋ ቆርጫለሁ፣ በምንም ዓይነት መንገድ ራሴን ላሻሽል አልችልም ካልከው ብቻ ወዲያውኑ ከተጫጫነህ ነገር ነፃ ትሆናለህ። ይህ እንዴት የሚያ ስደንቅ ነው፣ ምክንያቱም እውነተኛው ለውጥ የሚጀምረው ከዚህ በመ ሆኑ ነው። በቀላሉ እግዚአብሔር ያጠናቀቀውን ነገር ያዝ። መልካም ነገር ቢኖርህ ኖሮ እግዚአብሔር ባልሰቀለህም ነበር። ግን ጨርሶ ብልሹ የግትረባ በመሆንህ ምክንያት ሰቅሎህ ክርስቶስን በውስጥህ አስቀመጠ። ስለዚህ ራስህን ከራስህ ግስወጣት አለብህ። ታዲያ እንዴት ነው ይህን በተግባር የምታውለው? ይህን ብቻ ግለት አለብህ፣ «እግዚአብሔር አም ላኪ ሆይ መልካም ግድረግ አልችልም፣ መልካም ለግድረግ አልሞክ ርም። ጌታ ሆይ ከዚህ በኋላ የበኩሌን ጨርሻለሁ፣ ሙሉ በሙሉ የግል

ችል ነኝ፣ ለመቻልም እንኳ አልሞክርም ማለት አለብህ። እንደዚህ ራስህን ከራስህ ልታስወግድ ትደፍራለህ?

አንድ ሰባ ዓመት የተጠጋው አዛውንት ሐኪም ሲጋራ የማቆም ችግር ነበረበት። አንድ ቀን በጥባኤ ላይ ሲጋራ ማጤስን ለማቆም የሚያደርገውን ትግል ገለጸ። እግዚአብሔርን የሚያውቅ አንድ ወጣት በዚያ ነበር። እኔ አንተን ብሆን ኖሮ እንዲህ አላደርግም ብሎ ነገረው። አዛውንቱም ለወጣቱ በትግሌ ማሸነፍ እንዳልቻልኩ ታውቃለህ? ትግሉን ጨርሶ ባቆምማ እንዴት ከፍ ያለ ችግር ይኖርብኝ ነበር አለው። ወጣቱ እንዲህ አይደለም በማለት መለሰ፣ እኔ አንተን ብሆን እግዚአብሔርን እግዚአብሔር ሆይ ማጤስን ከእኔ ውሰድ እለው ነበር አለው። ሐኪሙም የወጣቱን ምክር በአድናቆት ተቀበለና ከልቡም እንዲህ በማለት ጸለየ «እግዚአብሔር ሆይ ማጤስን የማቆምበት መንገድ የለኝም። አሁን ለማቆም የማደርገውን ትግል አቆማለሁ ጌታ ሆይ ይህንን ለአንተ አተዋለሁ። ምንም አላደርግም ግን ማጨስን ከእኔ እንድትወስድ እጠይቅሃለሁ» ብሎ ጌታን ጠየቀው። ይህ ሐኪም ለሃምሳ ዓመት በቀን ከአስራ ሁለት እስከ ሃያ ሲጋራ አጭሷል። ለእግዚአብሔር ከሰጠበት ቀን በኋላ ግን በተከታዩ ጠዋት በሕይወቱ የማጤስን ፍላጐት ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ጠዋት እንደረሳ መሰከረ።

ቅዱስ መሆን እችላለሁ ብለህ የምታስብ ከሆነ ያለ ጥርጥር ትወድቃለህ፣ ታጋሽ መሆን እንደምትችል ብታስብ ፈጽሞ ትወድቃለህ፣ ፍጹም መሆን እንደምትችል ብታስብ በእርግጥ ትወድቃለህ። ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ከመስተካከልና ከመታደስ ውጭ እንደሆንክ ቆጥሯልና ነው። ሆኖም እንደጳውሎስ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» ፈጽሞ የተበላሸሁ ነኝ አልረባም፣ መሰቀል ይገባኛል ማለት ትችላለህ? ፔኪንግ ውስጥ አንድን ወንድም ድል ለማድረግ መሞከርን አቁሚያለሁ ወይ ብዬ ጠየቅሁት። «እግዚአብሔር ይመስገን አቁሚያለሁ። ማቆም ለድል መሠረታዊ ነገር ነው» ብሎ መለሰልኝ። በጉልበትህ የምትፍጨረጨር ከሆንህ በእግዚአብሔር ፊት ፈጽሞ ጥቅም እንደሌለህ እንዲሁም እንደማትስተካከልም ወይም እንደማትታደስ ማወቅ አለብህ። አንተ ልታደርግ የምትችለው እንዲህ ብሎ መጸለይ ብቻ ነው፣ «ጌታ ሆይ

ከዚህ በኋላ ሁሉን በእጅህ እተዋለሁ። ከአሁን ጀምሮ አንተ ሁሉን ነገር አድርግልኝ።

ነገር ግን ይህም መረዳት ናሮ «አንችልም፣ ተስፋ ቆርጠናል» ብለው የተናዘዙና ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀሉ የሚናገሩ ወንድሞችና እህቶች ራሳቸው በመሸነፍ ሕይወት ውስጥ ይገኛሉ። ለምንድነው እስከ አሁን ድረስ ድልን የማይለማመዱት? ይህ የሆነበት ምክንያት ለማሸነፍ ድልን ከመለማመዳቸው በፊት አንድ ነገር ስለሚቀራቸው ነው። ድል ለመንሣት ይህ ሁለተኛ ሁኔታ ነው።

1.ማመን

«በሥጋ የምኖርበት ኑሮ...»

እስካሁን የተባለውን ጠቅለል ባለ መልኩ እንየው። እግዚአብሔር ፍጹም የተበላሸህ ነህ ይለኛል፣ እኔም ፍጹም የተበላሸሁ ነኝ እላለሁ፣ እግዚአብሔር ምስኪን ነህ ይለኛል፣ እኔም እቀበለዋለሁ እላለሁ፣ እግዚአብሔር ከሞት በስተቀር ምንም አይገባህም ይለኛል፣ እኔም እንዲሁ ሞት ብቻ ነው የሚገባኝ እላለሁ።

«እኔ ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል።» ይህ የተረጋገጠ እውነት ነው። እንደዚህ እንደተረጋገጠው እውነት ዛሬ ሕያው ሆኜ አልኖርም፣ ክርስቶስ ነው ለእኔ የሚኖረው። ለምንድነው እኔ ሕያው ሆኜ የማልኖረው? ከሁለት አንድ ሲቀነስ አንድ ነው። አዳማዊ ባሕርይ ከእኔ ሲቀነስ የሚቀረው ምንድነው? መልሱ ግልጽ ነው፣ ክርስቶስ ነው። ሁለቱም አብረው ይኖራሉ ግን አንዱ ተወግዷል ስለዚህ በውስጣችን የሚቀረው ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ እውነት ነው። ሆኖም ከማመን በስተቀር ይህን የምገልጽበት ሌላ መንገድ የለኝም።

ሀ.የእግዚአብሔርን እውነት ማመን

ወንጌል እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እንደሰጠን ይነግረናል። ኢየሱስ ጽድቃችን፣ ቅድስናችን፣ ቤዛችን፣ ሆኗል። 1ኛ ቆሮ 1:30ን ተመልከት። ክርስቶስ ኢየሱስን በእውነት ልንቀበለው ይገባል። ምክንያቱም እርሱ ሕይወታችን ሆኗልና። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ራሳችን እንደሆነ

በኤፌ 1:22፣ 4:15 ቆላ 1:18ላይ ይናገራል። የሰው ራስ ስለ አካል እንደሚሰማውና እንደሚጠነቀቅለት ሁሉ ከርስቶስም ከርስቲያን ለሆንን ለእኛ እንዲሁ ነው። ዛሬ እርሱ ራስ ነው። እኛም የአካሉ ብልቶች ነን። በአሉታዊነት ራሳችንን ሰጥተናል።አሁንም በአሉታዊ አባባል ይህንን እምነናል። የእግዚአብሔር ቃል ከርስቶስ ራስ እንደሆነ ይናገራል። ስለ አንተ እንደሚጠነቀቅ ታምናለህ?

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15:1–5 ላይ ከርስቶስ የወይን ግንድ እኛ ደግሞ ቅርንጫፎች እንደሆንን ይገልጥልናል። በዚህ ከፍል ላይ መንፈሳዊ ሕይወታችን ሲሻሻልና ከአሁኑ ሲልቅ እርሱ የወይን ግንዳችሁ እናንተ ደግሞ ቅርንጫፎቹ ትሆናላችሁ አይለንም። ባመንን ጊዜ እርሱ የወይን ግንዳችን ነው፣ እኛም ቅርንጫፎቹ ነን። ሕይወቱንና ፍሬ የማፍራት ኃይሉን ስለሰጠን እርሱ በመልካም ነገር እንደተሞላ ሁሉ እኛም ፍሬ ለማፍራት በመልካም ነገር መሞላት አለብን። ደኅንነትን በተቀበልን ጊዜ እርሱ ሕይወቱን ከፍጹምነቱ፣ ከቅድስናውና ከመልካም ነገሩ ሁሉ ጋር በእኛ ውስጥ አፍሷል፣ ይህን እናምናለን?

ኢየሱስን እንደ አዳኝህ አድርገህ ስትቀበለው ከእርሱ ጋር ተጣብቀሃል፣ ይህንንስ ታምናለህ? የወይን አትክልት ግንድ ከቅርንጫፎቹ ጋር ግንኙነት እንዳለው ሁሉ ከርስቶስም ከአንተ ጋር ያለው ግንኙነት ይህን እንደሚመስል ልታምን ትችላለህ? ገበሬው እግዚአብሔር ቀደም ሲል ጀምሮ አንተንና እሱን አንድ ዛፍ ስላደረጋችሁ እንዴት ነው ከእርሱ የምጣበቀው ብለህ ማሰብ አያስፈልግህም። አንተ አይደለህም ለእርሱ ፍሬ የምታፈራው።ይልቁንም እርሱ በአንተ ውስጥ አድሮ ፍሬን ያፈራል እንጂ።

እግዚአብሔር በቃሉ የከርስቶስንና የእኛን ሕብረት ልክ ምግብ ከእኛ ጋር እንዳለው ዓይነት ግንኙነት በዮሐ 6:51–58 ባለው ክፍል ላይ አመልክቷል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በቁ 54 ላይ «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው።» ስለሚል ከርስቶስ ኢየሱስ የምን ጠጣው ደምና የምንበላው ሥጋ ነው። ልክ የምንበላው ምግብ ያለንን ፍላ

ጎት እንደሚያሟላ፣ ያለ እርሱም እንደምንሞት ጌታ ኢየሱስም እንደ መንፈሳዊ ምግባችን ለእኛ እንደዚሁ ነው። ሕይወታችንን የሚያቆመው እርሱ ነው።

እግዚአብሔር በቃሉ ከክርስቶስ ጋር እንደተዋሐድን ያረጋገጠል ናል። ክርስቶስ ራሳችን፣ ጽንዳችንና ምግባችን ነው። ልጁ የሕይወታችን ኃይል እንዲሆን ተሰጥቶናል። እንደ ክርስቶስ እንድንኖር ኃይልን እንዲሰ ጠን እግዚአብሔርን መጠየቅ አያስፈልገንም። በፊት ባለግወቃችን ለእግዚአብሔር ከመገዛት ይልቅ ሁልጊዜ የራሳችንን ቅድስና ልንጠብቅና ልንፅናበት እናስብ ነበር። አሁን ግን በአሉታዊ መልክ ከራሳችን ትግል ተጸርጠናል። ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም። ልጁን ሕይወታችን አድርጉ አስከሰጠን ድረስ በአዎንታዊ መልኩ እርሱ ሕይወታችን እንደሆነ ማመን አለብን። ያንጊዜ እርሱንኑን ሁሉ በእኛ ውስጥ ይገልጣል። በየትም ቦታ ምንም ዓይነት ፍላጉት ይኑረን እርሱ ይሞላዋል። የእግዚአብሔር ቃል ይህን ይላልና እንመን።

የድል ምስጢር የሚገለጠው በራሳችን ጥረት የሚሆነውን የማሸነፍ ትግል ደረጃ በደረጃ በማቆምና በመተው ላይ ነው። ክርስቶስ ድላችን እንደሆነ በእምነት እናውቃለን። ድል ክርስቶስ በመሆኑ እምነትም የክርስቶስ የሆነውን ሁሉ በእኛ ውስጥ ያመጣል። እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስን በጸጋ ለእኛ ሰጥቶናል። የክርስቶስ ሕይወቱ፣ ኃይሉ፣ ገርነቱና ቅድስናው በሥጋችን እንዲገለጥ እግዚአብሔር የሰጠንን ሁሉ በእምነት እንቀበላለን?

ይህ የመዋሃድ ምስጢር የእግዚአብሔር ሥራ ነው። በእርሱ ከፍለጋ የሚያልፈው የክርስቶስ ባለጠግነት የእኛ ይሆናል። ይህን እናምናለን? የክርስቶስ የሆነው ሁሉ የእኛ ነው። እግዚአብሔር ቅድስናውን፣ ፍጹምነቱን፣ ሕይወቱን፣ ኃይሉንና ባለጠግነቱን ሰጥቶናል ብለን እናምናለን? ራሳችን፣ ግንዳችንና ምግባችን እንዲሆን እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር አጣብቆናል፣ አሁን ክርስቶስ ጽድቃችን፣ ቅድስናችንና ቤዛነታችን መሆኑን፣ እናምናለን? የእርሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ እንደሚኖር እናምና ለን? እግዚአብሔር ይህን እንድናምን ማባበል የሌለበትን ትዕዛዝ አዝዞ ናል። እኛ ከክርስቶስ ጋር ያለን ሕብረት እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር

ባለው ሕብረት ዓይነት የተቀረጸ ነው። ስለዚህ የእርሱ ትዕግሥት፣ ገርነት፣ ንጽሕናና መልካምነት ሁሉ የእኛ ነው። ልከ ደኅንነትን ስናገኝ በመጀመሪያ እርሱ ጽድቃችን መሆኑን እንዳመንን ዛሬም እርሱ ቅድስ ናችን መሆኑን እንመን። ይህም ሆኖ ግን ስንቶች በዚህ ረገድ ይወድቃሉ? ብዙዎች የእግዚአብሔርን የድል መንገድ ያውቃሉ ግን እምነቱ የላቸውም። አለመቻላቸውን ያውቃሉ፣ የክርስቶስን ችሎታ ግን አያውቁም። ሥጋቸው ፍጹም ዋጋ እንደሌለው ያያሉ፣ ግን የክርስቶስን ባለጠግነት እንደ እግዚአብሔር ስጦታ አያዩም።

ይህን ስጦታ እንዴት እንቀበላለን? በጥረታችን ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቃል እንዳመንን ይህን ስጦታ እንዲያው በእምነት መቀበል እንችላለን። ወንጌል ይህ ነው። መንፈስ ቅዱስም እምነታችንን የእግዚአብሔር ተዓምር በእኛ ውስጥ እንዲፈጸም መነሻ ነጥብ አድርጎ ይወስደዋል። የእግዚአብሔርን ብርቱ ኃይል ያልተለማመዱ ሰዎች ይህንን አጥብቀው ላይቀበሉት ይችላሉ። ለተለማመዱት ግን ይህ ድንቅ እውነት ነው። በጌታ ውስጥ ያለው ባሕርይ የእኛ እንደሆነ ስናምን መንፈስ ቅዱስ በእር ግጥ የእኛ እንዲሆን ያደርገዋል። ኦ ይህ ምን ዓይነት ወንጌል ነው! የክርስቶስ የሆነው ሁሉ በእምነት የእኛ ሆኗል። በእምነት ይህ የክርስቶስ ፍጹም ሕይወት ሙት በሆነው ሥጋችን ውስጥ በየዕለቱ ራሱን ይገልጣል። በእምነት ማለትም ያለብን ከእንግዲህ «እኔ ሕያው ሆኜ አልኖርም» ብቻ ሳይሆን «ክርስቶስ በእኔ ይኖራል» የሚለውንም ቃል ጭምር ነው።

ለ. እንደተቀበልክ አመን ፣ ታገኛለህ

እግዚአብሔር የማናምነውን ነገር እንድናምን አያደርገንም። አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን ጥረት እንዲተው ሲጠየቁ ይተዋሉ። ግን ተውት የተባሉትን ነገር ለማድረግ ሲፍጨረጨሩ ይታያሉ። እናምናለን ይላሉ ሆኖም አያምኑም። በእርግጥ የራስን ጥረት ማቆም አስፈላጊ ነው። ዋናው ነገር አሁን ጌታ ኢየሱስ የእራሱን ድል በውስጣችን ያኖራል የሚለውን ማመኑ ነው። እግዚአብሔር ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ መሞቱን የተናገረውን በማመን የዘለዓለምን ሕይወት እንቀበላለን። በተመሳሳይም

ጌታ ኢየሱስ በእኛ ይኖራል የሚለውን በማመንም የድል ሕይወት እንቀበላለን።

ብዙዎች ጌታ እነርሱን መኖሪያው እንዳደረገ ግመን አይችሉምና የሚሳሳቱትም እዚህ ላይ እንደሆነ አውቃለሁ። ከዚህ የተነሳ ጌታ ለእነርሱ ድል እንደሚነግ አያምኑም። አንድ ወቅት አንዲት እህትን ድል ለማግኘት የምታደርገውን የግል ጥረት ትታ እንደሆነ ጠየቅኋት ፤ እርሷም ትቻለሁ አለችኝ። በመቀጠልም እንዴት ተውሽ ስላት «በራሴ ፍጹም ቲስፋ እንደሌለኝና ጥረቱንም እንደማቆም ለእግዚአብሔር ነገርኩት» ስትል መለሰችልኝ። ቀጠለችና የጸለየችውን ጸሎት ነገረችኝ። «እግዚአብሔር ሆይ፣ ከዚህ በኋላ በሚሆነው ሁሉ ሁለንተናዬን ለአንተ ሰጥቻለሁ አለች።» ታዲያ ድል አገኘሽ፣ ብዬ ጠየቅኋት። አገኘሁ ግለት እንኳን አልደፍርም አለች። መልሼ ለምንድነው የማትደፍሪው ስላት «ድል እንዳደረግሁ አይሰማኝም፣ ምንም ዓይነት ውጤትም አላየሁም» አለችኝ። እኔም «በእግዚአብሔር እውነት ካመንሽና በውስጥሽ የሚኖረው ጌታ ኢየሱስም ድል መሆኑን ካመንሽ ወዲያውኑ ድል እንዳለሽ ግመን አለብሽ። ነገር ግን ውጤት ከጠበቅሽ ምንጊዜም አታገኚውም ስል እንደ እግዚአብሔር ቃል መከርኋት።

የድልን ጸጋ መቀበል በመልዋጥ ጊዜ የይቅርታን ጸጋ ከመቀበል ጋር አንድ ነው። ለአንድ በክርስቶስ ላለመነ ኃጢአተኛ ሰው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለ እርሱ ያዘጋጀውን የደኅንነት ጸጋ ቢቀበል ኃጢአቱ ሁሉ ይቅር እንደሚባልለት አትነግረውምን? ሰምቶ ካመነ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ኃጢአቱን ይቅር ይለዋል። ቀጥለህም ኃጢአቱ ይቅር የተባለለት መሆን አለመሆኑን ትጠይቀዋለህ። ይቅር አልተባልኩም ይልሃል። እንዲህ የሚልህ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? ሰዎች ኃጢአት ይቅር ከተባለ ደስታና ሰላም ይኖራል ሲሉ ሰምቷል፣ እርሱ ግን እስከ አሁን ይህ ደስታና ሰላም የለውም። እንዲህ በማለትም ይቀጥላል። ኃጢአቱ እንደተሰረየለት በድፍረት መናገር የሚችለው ሰላምና ደስታ ሲያገኝ መሆኑን ይነግርሃል። ይህ እስኪሆንለትም በጸሎት እንደሚቆይ ይነግርሃል። እንዲህ ያለውን አባባል ብትሰማ ደስታና ሰላም ለማግኘት ዓመቱን ሙሉ እንኳን ቢጸልይ እነዚህ ስሜቶች ሊኖሩት እንደማይችሉ አትነግረውም?

ደስታና ሰላምን ሁለቱንም የሚያገኛቸው ሲያምን ብቻ እንደሆነ ትነግረዋለህ። ከደኅንነት በኋላም የድልን ሕይወት የምንለማመደው እንዲሁ ነው። የድል ቅድመ ሁኔታዎች የምትላቸውን የራስህን ዝግጅቶችና ጥረትህን በመተውና በክርስቶስ ድል ነሺ ሕይወት እንዳገኘህ ማመን አለብህ። የእግዚአብሔር ልጅ ድሉን በእንተ ውስተ ሊያኖር እየጠበቀህ ነው። እመን ውጤቱም ይከተልሃል። የድልን ሕይወት ለማግኘት መልካም ሥራ እየሠራህ ውጤት ብትጠብቅ ለዘለዓለም ድል አታገኝም።

የድል ሕይወት አልኝ ከማለትህ በፊት ውጤቱን ስትጠብቅ አንተ ያመንከው የእግዚአብሔርን ቃል ሳይሆን የራስህን ልምምድ ነው። ነገር ግን ልክ በእግዚአብሔር ቃል እንዳመንክ በመቀጠል ልምምዱ ይመጣል፤ ከዚያ በኋላ ድልም ይከተላል። ጳውሎስ «የድልን ሕይወት ከመቀበሉ በፊት እንዳሸነፍኩ ይሰማኛል አላለም፤ እንዲያውም የተናገረው «አሁን በሥጋዬ የምኖረው ኑሮ ፣ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» ብሎ ነው። ቀዝቃዛና ደስ የማይል ስሜት የተሰማህ ቢሆንም «አሁን በሥጋዬ የምኖረው ኑሮ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት ነው»ብለህ እግዚአብሔርን ማመስገንና ማክበር አለብህ።

እኔን ራሴን በልዩ ሁኔታ እንደሚናገር ሰው አድርጋችሁ አትመልከቱኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ በየቀኑ የመታከት ሕይወት የምኖር ሰው ነኝ። በረጋ መንፈስ የተነሳሁበት የማለዳ የጸሎት ጊዜ የለም። ያለ እክል በመደሰት ያሳለፍኩት ጊዜ የለም። ሰይጣን ብዙ ጊዜ እየከሰሰኝ እንዲህ በማለት ወደ እኔ መጥቷል፤ «ደስ አትሰኝም፤ ሁልጊዜ በስሜትህ በጣም ቀዝቃዛ ነህ፤ ባለፉት ቀናት ቀዝቃዛና ስሜት አልባ ነበርክ፤ አሁንም ስሜት አልባና ቀዝቃዛ ነህ፤ ክርስቶስ በአንተ ይኖራል ማለት ነው? ይህ ነው የክርስቶስ ድል?» ሲለኝ እግዚአብሔር በቃሉ መልስ ይሰጠኛል። «እኔ ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» አለዋለሁ። የክፋውን ድምጽ ባስተናግድ ኖሮ እኔ እኖራለሁ፤ ሕያው አለመሆኔን ካመንኩ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው በእኔ የሚኖረው። ቀዝቀዝ ያለ ነገር በስሜቴና በሀዋሳቆቼ ይሰማኛል። የእግዚአብሔርን ልጅ በእኔ መኖርና ቅዱስ ቃሉ የሚለኝንም ዋጋር አምናለሁ። የመተውና የማመንን ቅድመ ሁኔታዎች ካሟላህ ያኔ ክርስቶስ ድሉን

በአንተ ውስጥ ያኖራል። በመሆኑም እንዲህ ብለህ ጸልይ «እግዚአብሔር ሆይ ስሜት ማለት ምንም ማለት ስላልሆን አመሰግንሃለሁ፣ አከብርሃለ ሁም። በዚህ ጉዳይ የሰይጣን ትልቁ ውሸት ስሜት ነው። ስሜት የዚህ ጠላት የቅርብ ወዳጅ ነው። ጌታ ሆይ ከስሜት ይልቅ ቃልህን በማመኔ አመሰግንሃለሁ። ምክንያቱም ቃልህ ብቻ እውነት ሲሆን ስሜትን ግን ልተማመንበት የማይገባ ነው።» ከዚያም በኋላ ቢሆን በስሜት መልክ ፈተና ሲገጥምህ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት እንደምትኖር በድፍረት ተናገር።

እራስህን ስትተውና በአምላክህ ስታምን የእግዚአብሔር ልጅ ስለ አንተ ሲዋጋ ታያለህ። ላንተ ድልን ያቀዳጃል። ክፉ አመልህን፣ ደንዳና ነትህን፣ ትዕቢትህን፣ ቅናትህን ያስወግዳል። ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ሰዓት በመላው ዓለም ሁሉ አንድ ድል ነሽ ብቻ ስላለ እግዚአብሔርን አከብር፣ ሁላችንም የተሸነፍንና የማንጠቅም ነን። ጌታ ብቻ ግን ድል ነሽ ነው። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

በአንድ በኩል ተው የተባልከውን በመተው በሌላ በኩል በእግዚአ ብሔር ልጅ ላይ አምነህ እነዚህን መሠረታዊ ሁኔታዎች በማሟላት ኑር። ክርስቶስ በአንተ ይኖራል የሚለውን የእግዚአብሔርን እውነት እመን። ይህንንም እንደተቀበልህ ተረዳ።ሁሉ በልጁ ስለ እኛ እርዳታ እንደ ተደረገ እግዚአብሔር እንዲያሳየን እንጠይቅ፣ ይህና ይህ ብቻ ድል ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ድል ይህ ነው፣ሁሉ በእርሱ ተደርጓል። ሃሌ ሉያ!

ምዕራፍ 5

መተው

«እርሱ ግን በለው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ።» /ሉቃ 18:27/

«ገና አንድ ነገር ይቀርሃል»

በሉቃስ 18:27 ላይ ላለው የማይቻለው ለእግዚአብሔር ይቻላል የሚል ቃል ተጽፏል። ይህንን ቃል የተናገረበትን ሐሳብ ሁላችንም እናውቃለን። በቁጥር 1 ላይ እንደምንመለከተው፣ «አንድ ጎበዝ ወደ እርሱ ቀርቦ የዘለዓለምን ሕይወት እወርስ ዘንድ ምን ማድረግ አለብኝ» ሲል ጠየቀው። ወጣቱ ጎበዝ የጠየቀው ምን ማድረግ እንዳለበት በመሆኑ ጌታ እንዲህ ሲል መለሰ፣ «ትዕዛዛቱን ታውቃለህ...» አለው። ጌታችን በሥራ የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ የሚያስገድዱና የማያስገድዱም ሕጉች እንዳሉ ለማሳየት እነዚህን አምስት ትዕዛዛት ጠቀሰ። ጎበዙ እነዚህን ትዕዛዛት ሁሉ ከልጅነቱ ጀምሮ እንደጠበቃ ተናገረ፣ ጌታ ግን ገና አንዲት ነገር ቀርታሃለች ሲል አሳሰበው። /ቁ 22/

ከዚህ ክፍል መማር የሚገባን ነጥብ አለ። ጎበዙ የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ እንደሚገባው ጌታን ሲጠይቅ ጌታችን አምስቱን ትዕዛዛት ብቻ ነው የነገረው። ለምን ሁሉንም አልነገረውም? አምስቱን ብቻ ከጠቀሰ በኋላ ለምን «አንዲት ነገር ቀርታሃለች» ሲል ጨመረ? አለመቻሉን ሊያሳውቀው ፈልጎ ነው። የዘለዓለም ሕይወት የእግዚአብሔር ጸጋ የሆነ ስጦታ ነው። በሰው ሥራ ሊገኝ አይችልም። ጎበዙ ግን አልገባውም፣ እንዲያውም «እነዚህን አምስት ትዕዛዛት ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄያለሁ» በማለት ተኩራራ። ጌታ ግን ይህን ጎበዝ ሊያደርገው የማይ ችለውን አንድ ነገር እንዳለ ያውቃል። በመሆኑም

«አንድ ነገር ይቀርሃል» ሲል ጨመረ። የታሪኩን ፍፃሜ እናውቃለን፣ ጎበዙ የዘለዓ ለምን ሕይወት በሥራ መውረስ አልቻለም።

የድልም ነገር በዚህ መርህ የሚሄድ ነው። አንዳንዶቻችሁ እንደ ብዙዎቹ ሌሎች ሰዎች ኩሩ ፣ቀኖተኛ ወይም ገታራ አይደለንም ትሉ ይሆናል። እርግጥ ነው ከሌሎች ሰዎች በብዙ መንገድ ትሻሉ ይሆናል። ግን በሕይወታችሁ ውስጥ አንድ ግሽንፍ ያልቻላችሁት ነገር እንዳለ እግዚአብሔር ያውቃል። ለእኛ ለሰዎች ይህ ነገር እንደማይቻል ሊያሳየን ፈልጎ ይህን አንድ ነገር በእኛ ውስጥ ትቷል። ዝሙት ስላልፈጸምህ፣ ስላልገደልህ፣ ስላልሰፈቅህ፣ በሐሰት ስላመሰከርህ ወይም አባትና እናትህን ስላከበርህ ሁሉን ነገር እንደምትችል አድርገህ ትገምታለህ። ምን አልባት አንድ ሰው ድል ነሥተህ መሆን አለመሆንህን ቢጠይቅህ በዚህ ነገር ድል የነሣህ በዚያኛው ደግሞ ድል ያላገኘህ እንደሆነ ትመል ሳለህ። ነገር ግን ጥያቄው ዛሬ ምን ያህል ድል ነሣህ አይደለም። ድል ልትነሣው ያልተቻለህ አንድ ነገር እንኳን አለ ወይ? ነው። እንደ ጎበዙ ከልጅነት ጀምሬ ጠብቄአለሁ የምትለው ነገር ቢኖርህ እንኳን ድልን በተመለከተ አለመቻልህን ሊያሳይህ እግዚአብሔር አንድ ነገር በሕይ ወትህ ያስቀራል።

እግዚአብሔር ማንነታችንን ገላልጦ ስለሚያውቅ በእኛ ላይ ያሳለ ፈው ፍርድ ስቅላት መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። ኃጢአትን እንደማ ናሸንፍና መልካም ነገር እንኳን ልናደርግ እንደማንችል ያውቃል። እርሱ በግልጽ ተመልክቶን ሳለ እኛ ግን ራሳችንን በድንግዝግዝ እያየን መል ካምና ጠቃሚዎች አድርገን እንቆጥራለን። ምንም ያህል መልካም ነን ብለን ራሳችንን ብንቆጥርም ለእያንዳንዳችን እግዚአብሔር «ገና አንዲት ነገር ቀርታሃለች» ይለናል። አንዳንድ ሰዎች በቁጡ ባሕሪያቸው ይቸ ገራሉ። ሌሎች ደግሞ በግትርነታቸው። አንድ ሰው ኩሩ ወይም ቀናተኛ ላይሆን ይችላል፣ ግትርነቱ ግን ሁልጊዜ ይከተለዋል። እንዲህ ከሆነ ድል ለመንሣት ገና አንዲት ነገር ቀርቶታል። ድል ያላደረገው አንድ ነገር መኖር አለበት። አንዱ ኩሩ ወይም ቀናተኛ ወይም ብስጩ ላይሆን ይች ላል። አፉ ግን ያለማቋረጥ ይሠራል፣ ሳይናገር መሥራት አይችልም። ይህንን፣ ያንን ወይም ሌላውን ኃጢአት ፈጽሜ አላውቅም ብሎ ሊናገር

ይችላል።ጌታ ግን እንዲህ ይለዋል፣ «ገና አንዲት ነገር ቀርታሃለች» ሌላው ደግሞ በገንዘብ ላይ እጁ የማይፈታ ይሆናል። በሕይወቱ ሁሉ የተጋነነ ኃጢአት ፈጽሞ አያውቅም፣ ይሁንና የስስት ኃጢአት ይፈጽማል። ገንዘብን መውደድ ተዋህዶታል። ስለሆነም ጌታ እንዲህ ይለዋል፣ «ገና አንዲት ነገር ቀርታሃለች።» ይህ አንድ የቀረ ነገር በዚህ ጉዳይ ድል የመንሣት ችሎታ እንደሌለው ያሳያል። ሰዎች ፍጹም የሆነ ሕይወት እንዲገለጥባቸው ይጠበቃሉ ግን በተቃራኒው በእነርሱ ላይ የሚመሰክር ባቸው አንድ ባህሪ አላቸው፣ስለሆነም የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ይህን አንድ ነገር ትዕቢትን ወይም ቅናትን ወይም ለፍላፊነትን ወይም የረከሰ ሐሳብን በራስ ጥረት ማሸነፍ አልችልም በማለት መናዘዝ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ለወጣቱ ነበዝ ማለት የፈለገው ነገር የዘለዓለም ሕይ ወት ጉዳይ ለሰው አይቻለውም ነው። ልክ እንዲሁ ድልና የተትረፈረፈ ሕይወት ለሰው በራሱ ሥራና ጥረት ማግኘት አይቻለውም። ጌታ ለጎ በዙ አለመቻሉን ሲነግረው ይህ ሰው ግን ሊያምን ፈቃደኛ አልነበረም። እንዴት ያለ ደፋር፣ ጠንካራና መመካት የሚታይበት ሰው ነው፣ ከከን ፈሩ የወጡት ቃላት «ከልጅነቴ አንስቶ እነዚህን ሁሉ ጠብቄአለሁ» የሚል ነበር። ይህ ሰው ሕይወቱን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር እንዳዋለ አስቦ ነበር። ጌታ ግን «ገና አንዲት ነገር ቀርታሃለች» ብሎ መለሰለት።

እነዚያ የጠቀስኳቸው ኃጢአቶች ማለትም ትዕቢት፣ ቅናት፣ ግት ርነት፣ የረከሱ ሐሳቦች ወይም ለፍላፊነት የለብኝም ብለህ ገምተህ ይሆ ናል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ደግሚ ላስተጋባልህ፣ «አንዲት ነገር ቀርታሃለች» ይልሃል። የጎደለህ ምን እንደሆነ ቤትህ ግባና አስብ።

እግዚአብሔር ሰዎች አለመቻላቸውን ያዩ ዘንድ ይወዳል

እግዚአብሔር ማንነትህን በደንብ አድርጎ ስለተረዳ አትችልም ብሎ ደምድሟል። አንተስ ምን ትላለህ? ከዳንህበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በኃጢአት አሁንም አሁንም እንድትወድቅ ለምን እንደሚፈቅድ ታውቃለህ? ብዙ ወንድሞችና እህቶች ድል መንሣት ባቃታቸው

ኃጢአት ያለቅሳሉ። ምናልባት አንተም እንዲሁ ታደርጋለህ። እኔ ግን ለዚህ ችሎታ ማጣት እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ይህን በማለቴ ግን አስሮ በያዘህ ኃጢአትና ባለብህ ሐዘን ስለ አንተ እንደማይሰማኝ አድርገህ አትቁጠር። ኃጢአትን በራስህ ማሸነፍ አለመቻልህን ታይ ዘንድ እግዚአብሔር ይወዳል። አለመቻልህንም ሊያሳይህ አንድ ነገር ብቻ በውስጥህ እንዲቆይ ይፈቅዳል። ከዳንህበት ጊዜ እስካሁን በምትሸነፍበት ኃጢአት አለመቻልህን ተረድተሃል?

አንዲት እህት ከመዋሸት በስተቀር ሁሉን ኃጢአት ማሸነፍ ችላ ነበር። ነገር ግን ድል ልትነሣ ያቃታት አንድ ኃጢአት ይህ መሆኑን ታውቃለች። ሌላዋ እህት ደግሞ በቀላሉ ትናደዳለች፤ ራሷን መቆጣጠር ይሳናታል። እንዲያውም በንዴቷ ጊዜ ክፉ ነገር ትናገራለች። ይህ ሕይወቷ በጣም ያሳፍራታል። ያም ሆኖ ታዲያ ምንም ልታደርግ አልቻለችም። ሌላ አንድ ወንድም ደግሞ አውቃለሁ። ይህ ወንድም ከማጤስ በስተቀር ሌሎችን ኃጢአቶች ድል ነስቷል። ነገር ግን ይህን ልማድ የሚተውበት መንገድ አላገኘም። ሌላይቱ እህት ያለማቋረጥ መመገብን ለማቆም ተሳናት እንጂ ብዙ ኃጢአቶች ላይ ድል ነበራት።

ለምንድነው ብዙ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለ የተለያየ ልምምድ የሚኖራቸውን? እግዚአብሔር አለመቻላቸውን የሚያሳይበትና ማንነታቸውን የሚገልጥበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር ችሎታ እንደሌለህ በሚገባ አሳይቶህ ሳለ አንተ ግን በራስህ በመተማመን ተስፋ አለኝ ትላለህ። እስቲ አንዳንድ ጥያቄዎችን ልጠይቅህ። ልብ የሚሰብር ውድቀትህና አሳፋሪ ሽንፈትህ የድልን ሕይወት በራስህ አለመቻልህን እግዚአብሔር የሚያሳይበት መንገድ እንደሆነ ትረዳለህ? እስከሚሰለችህ ወድቀሃል? እግዚአብሔር በራስህ አንድን ኃጢአት እንደምታሸንፍ አሳይቶሃል? አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ፣ አሥር ጊዜ፣ ሃያም ጊዜ እንኳ ወይም መቶ ጊዜ እንድትወድቅ ይፈቅድልሃል። በዚህም ስላለመቻልህ በቂ ማስረጃ ይሰጥሃል። «እግዚአብሔር ሆይ እኔ አልችልም» እስክትል ሽንፈትህን ሊያሳይህ ይወዳል። አንድ ሰው ለመዳን መጀመሪያ ራሱን ሊያድን አለመቻሉን መናገር ያስፈልገዋል። በተመሳሳይም ለማሸነፍ በራሱ አለመቻሉን ማወቅ አለበት። ስለሆነም አንድ ሰው ወደዚህ ነጥብ ሲመጣ

እግዚአብሔር ወዲያውኑ መሥራት ይጀምራል። በጣም የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር በሉቃስ 18:18–23 ባለው ክፍል ላይ የተጠቀሰው ጎበዝ አለመቻሉን ቢያውቅም እንኳ እያዘነ ሄደ።

እግዚአብሔር ሕግን ለሰዎች ለሁለት ሺህ ዓመት ሰጠ። ይሁን እንጂ ለእሥራኤል ልጆች አሥርቱን ትዕዛዛት ሲሰጥ ዓላማው ምን ነበር? እነዚህን የሰጣቸውን ትዕዛዛት እንዲጠብቋቸው ሳይሆን እንዲጥሷቸው ነው። ይህ እንዴት ይሆናል? ምክንያቱም ሰዎች ኃጢአተኞች በመሆናቸው ምክንያት እነዚህን ትዕዛዛት ሊጠብቁ እንደማይችሉ ያውቃል። ነገር ግን ሰዎች ራሳቸው ወድቀው ካላዩ እግዚአብሔር ያላለፈባቸውን ፍርድ አይቀበሉም። ያኔ ብቻ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ይናዘዛሉ። የሮሜ መጽሐፍ እግዚአብሔር ለሰዎች ሕግን እንዲጠብቁት ሳይሆን እንዲጥሱት እንደሰጣቸው ሲናገር «በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ» ይላል። 5–20 ሰዎች ሕግን መጠበቅ እንደማይችሉ ከተረዱ በኋላ ያኔ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላሉ። ሰዎች በራሳቸው ችሎታ እንደሌላቸው ተረድተው በክርስቶስ ይታመኑ ዘንድ እግዚአብሔር የ2000 ዘመን የሰውን ታሪክ ተጠቀመ።

ላለፉት 2000 ዓመታት ብዙ ኃጢአተኞች ድነዋል። አሁን የክርስቶስን ስም የምንጠራ ሁሉ የዳንን ኃጢአተኞች ነን። ስለዚህ ሙሉ በሙሉ መሰጠት አለብን። እኛ ግን ንዴታችንን፣ ትዕቢታችንን ወይም ለሌላ ሌላ ነገራችንን እውስጣችን በመጨቆን ለመሻሻል እንሞክራለን። በፊት ቁጣችን በውጭ ይታይ ነበር፣ አሁን ግን ድል ለማግኘት ስንል በውስጣችን ታፍኗል። ቀደም ሲል ትዕቢታችን በውጭ ይታይ ነበር፣ አሁን ግን ወደታች ተጭኗል፣ ግን ምንም ያህል ቢጨቆኑ ድል አልተመቱም። እንዲሁም እግዚአብሔር በመጨረሻ የእኛን ደካማነት ያሳየናል። ማንም ኃጢአቱን ሊያሸንፍና በራሱ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል ይነግረናል።

በራስህ ምንም ተሰፋ እንደሌለህ ስትረዳ ነፃ ለመውጣት ወደ እግዚአብሔር ና። በመጀመሪያ ደረጃ «እግዚአብሔር ሆይ አልችልም፣ ድል ለማግኘት በራሴ አልሞክርምም። ከአሁን በኋላ ለድል መፍጨር ጨረን አቁማአለሁ፣ ከአሁን በኋላ አልዋጋም» ብሎ ለራሱ መናገር

ነው። ይህ መሰጠት ነው። ነፃ ለመውጣት የመጀመሪያውን እርምጃ ያሰ ምራል። በፊት ትዕቢቴንና ንዴቴን፣ ተቆጣጥሬ ማሻሻል እችላለሁ ብያ ለሁ። ካሁን በኋላ ግን ጌታ ሆይ አልችልም በራሴ ለመለወጥ አልች ልም፣ ጨርሶ አቆማለሁ ማለት አለብኝ።

መሰጠት ማለት መተው ነው

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላንተ መሰቀሉን እንዳመንህ ምን ሆነ? ወዲያውኑ የሆነው ነገር በእምነት መዳንህ ተረጋግጧል። እንደዚሁም መሰጠት ማለት ወዲያውኑ ራስህን ለማሻሻል የምታደርገውን ጥረት ማቆም ነው። አንተ ድል ለማግኘት በምትቸገርበት ምትክ ጌታ በውስጥህ እንደሚኖርና ላንተ እንደሚያሸንፍ እመን። የራስህን ሥራ አቁመህ እግዚአብሔር ነፃ እንዲያወጣህ ፍቀድ፣ ድልን በነፃ ሊያጎናጽፍህ የሚች ለውን አምላክ «እግዚአብሔር ሆይ በፍጹም መልካም ልሆን አልች ልም፣ ካሁን በኋላ መልካም ለማድረግ አልሞክርም። ሁሉን ለመተው እጄን አንስቻለሁ» ብለህ ንገረው። ይህ መሰጠት ነው፣ ይህ መተው ነው። አንዳንድ አማኞች መተውን እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ያገኙታል። ፈተና በመጣ ቁጥር ሁልጊዜ ጦርነት ውስጥ ይገባሉ። ንዴት ሲመጣ ግጥ ሚያ ለማድረግ ይወስናሉ። የመጀመሪያ ውሳኔያቸው ሲወድቅ ለሁለተኛ ጊዜ የበለጠ ጠንካራ ውሳኔ ይወስዳሉ። በመጨረሻም በውሳኔያቸው ልክ ሽንፈታቸው ስለሚበዛ ሕይወታቸው በብዙ ቃልኪዳኖችና በብዙ ውድ ቀቶች የተሞላ ይሆናል። ሁለተኛው ውሳኔያቸው ምንም ያህል ጠንካራ ይሁን በሮሜ 7:18–19 ላይ ጳውሎስ «ፈቃዱ አለኝና መልካሙን ማድረግ ግን የለኝም» እንዳለው ነው።

እንዲህ አላደርግም ብለን ለእግዚአብሔር የምንገባው የትኛውም ዓይነት ቃልኪዳን ትክክል አይደለም። ምክንያቱም መሥራት አላቆም ንምና ነው። አሁንም ድረስ የራስህን ጉዳይ አንተ ራስህ ነህ የምትሠ ራው። ስለዚህ በድፍረት «እኔ ሕያው ሆኜ አልኖርም፣ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» ብለህ መናገር አትችልም። ሞት ማለት መተው ነው። ያንተ አለመቻል ሲጀምር በእግዚአብሔር ዘንድ የመቻል ነገር

ይጀምራል። ስለዚህ ላንተ የመጀመሪያው ወሳኝ እርምጃ እጅህን ማንሣት ነው።

ቴንጺን በምትባል ሰፈር የሚኖር አንድ ወንድም ድል ለማግኘት ሞክሮ ስላልተሳካለት አሸናፊ ሕይወት ለማግኘት የሚያደርገውን መፍጨርጨር መተው እንዴት እንደሚቻል ጠየቀኝ። እኔም ካደመጥኩት በኋላ ወንድም በምትሠራበት ኩባንያ ውስጥ የሥራ መደብህ ምንድነው ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም የልብስ ክፍል ኃላፊ ነኝ ብሎ ነገረኝ። መለስ እንበልና አለቃህ በሚቀጥለው ወር ከሥራ እንደሚቀንስህ ዛሬ ቢነግርህ ምን ታደርጋለህ? ብዬ ጠየቅሁት። እርሱ ሥራ አቆማለኋ አለ። በመቀጠልም በአንተ ቦታ ለተተካው ለአዲሱ የልብስ ክፍል ኃላፊ በእጅህ ያለውን ንብረት ሁሉ ካስረከብህ በኋላ ወዲያው አንድ የኩባንያው ወኪል መጥቶ ከሁለት ቀን በኋላ የዚህ ዓይነት ልብስ ዋጋ ሊጨምር ነው ቢልህ ምን ታደርጋለህ? በመቀጠልም ይህ ሪፖርት ቀደም ሲል መጥቶ ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ልብስ በመጋዘን ውስጥ አለን? ፍላጎታችንንስ ለማሟላት ብዛቱን ምን ያህል መጨመር አለብን? ብዬ እጠይቅ ነበር። በአሁኑ ሰዓት ግን የክፍሉን ሥራ ለአዲሱ ኃላፊ ስላስረከብሁ ምንም ኃላፊነት ስለማይጠበቅብኝ ሁኔታውን ሁሉ መመልከት ብቻ ስለሆነ ደስተኛ ነኝ በማለት መለሰልኝ። ይህ ስለመተው ድንቅ ምሳሌ ነው። «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ»ለሚለው እውነት መሰጠት ልክ እንደዚሁ ነው። የምተወው ስለቻልኩ ሳይሆን ባለመቻሌ ነው ብለህ ለጌታ ንገር።

ንዴቴ፣ ትዕቢቴ፣ ግትርነቴና ቅንዓቴ ከእኔ ጋር ናቸው። ግን ማድረግ የምችለው ምንም ነገር የለም። ከአሁን በኋላ ሁሉ በአንተ እጅ ነው። ድል በአንተ ማንነት የሚወሰን አይደለም። አንተ ፈጽሞ ሞተሃል፣ ክርስቶስ ግን በአንተ ይኖራል፣ ይህ ድል ነው።

በቼፎ ኮንፈረንስ ብዙ ወንድሞችና እህቶች የድልን በር አቋረጡ። አንዲት እህት ግን ባለቤቷና አማቷ ያሰቃዩዋት ስለነበረ እጅግ የሚያሳዝን ታሪክ ነበራት። ይህች እህት ከባለቤቷና ከአማቷ የሚመጣባትን ክፉ ነገር ችላ ተቀመጠች። ነገር ግን ድል አልነበራትም። በማስተምርበት ጉባኤ በድል ሕይወት ላይ ስናገር እውነቱን ተቀበለች። ከሁለት ቀን በኋላ አግኝታኝ ስለ መተው መንገድና እግዚአብሔር በውስጧ እንዲሠራ

ስለመፍቀድ ሁኔታ ያልገባትን ጠየቀችኝ። እኔም ጌታ ጥሩ የሆነ ግብረ ሪያ ይሰጠኝ ዘንድ ለመንኩት። ወዲያውኑ በታክሲ በመሄድ ጓደኛሽን ጠይቀሽ ታውቂያለሽ? አልኳት። አዎን ጠይቄአለሁ አለችኝ። መኪናው እጓደኛሽ በር ላይ ሲደርስ አንቺ ከቦርሳሽ ገንዘብ ስታወጪ ወዲያውኑ አብራሽ ያለችው ጓደኛሽ ፈጥና ትከፍልልሻለች። አንቺም የከፈለችልሽን ገንዘብ መልሰሽ ስትሰጫት እርሷ ግን ልትከፍልልሽ ወስናለችና መልሳ ሰጠችሽ። በአንቺ ልምምድ ውስጥ እንዲህ ያለ አጋጣሚ ነበረ ወይ ስላት አዎን ነበር ስትል መለሰችልኝ። እንበል ጓደኛሽ የታክሲውን ሳንቲም ከከፈለችልሽ በኋላ ሹፈሩ ገንዘቡን ይዞ ሄደ፣ አንቺም ጓደኛሽን ጠየቅሽ። ግን ይህም ሆኖ እርሷ ለአንቺ ገንዘብ እንድታወጣ ያልፈለግሽ በመሆኑ ልክ ልትሄጅ ስትይ ገንዘቡን መለስሽላት። ጉብኝትሽን አብቅተሽ እርሷም ስትሸኝሽ ፈጥና ገንዘቡን መልሳ በእጅሽ ላይ አኖረች። ገንዘቡ በሁለታችሁ እጅ ወዲያና ወዲህ ከተመላለሰ በኋላ በበሯ ላይ አስቀም ጠሽው ሄድሽ፣ ያም ሆኖ ታዲያ ገንዘቡን ጓደኛዪ ታነሣው ይሆን እያልሽ ታስቢያለሽ? ባታነሣውና መንገደኛ ቢያነሣውስ? ወይስ ሕፃን ልጅ አይቶ ቢወስደውስ? ስለዚህ ቀስ እያልሽ ጓደኛሽ ማንሣት አለማንሣቷን እየዞርሽ ታያለሽ? ያሳዝናል ግን አላነሣችውም። ልንገርሽ፣ ደጋግመሽ እየዞርሽ ብትመለከቺም እርግጠኛ ነኝ ጓደኛሽ ገንዘቡን አታነሣውም። ነገር ግን ገንዘቡን መንገድ ላይ ትተሽ አንሺ ብለሽ ነግረ ሻት ቢሆን ኖሮ ግንም ያነሳዋል ብለሽ ሳትጨነቂ ትጓጕለሽ፣ ጓደኛሽም ያለጥርጥር ገንዘቡን ታነሣለች። ይህን ብዬ እንደጨረስኩ ነገሩ ገባት። በዚህ መሠ ረትም ወደ ድል ሕይወት ገባች።

ያሳዝናል የላይኛው ምሳሌ ብዙ ሰዎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሚሰጡበት መንገድ ነው። በአንድ በኩል አንችልም ይላሉ፣ በሌላ በኩል እየተጨነቁ ይመለከታሉ። ለነገሮች ራስህ የምትጨነቅ ከሆነ እግዚ አብሔር ትጨነቅላቸው ዘንድ ይፈቅድልሃል እንጂ ጭንቀትህን አይወስደ ውም። ካልተጨነቅህ ግን እግዚአብሔር ስለ አንተ ይጠነቀቃል። ጠቅላ ላውን ኃላፊነትም ራሱ ይወስዳል። መሰጠትና መተው ማለት ገንዘብን አመንገድ ላይ ትቶ ወደ ኋላ ሳይገላመጡ እንደመሄድ ነው። ሕፃን ልጅ ሆነ ታክሲ ነጂ ወይም መንገደኛ ቢወስደው ባይወስደው ጉዳይህ

አይደለም። አንተ ለእግዚአብሔር ሁለንተናዬን ሰጥቼሃለሁ ብለሽው ከሆነ ከዚህ በኋላ መጥፎም ሆንክ ጥሩ የአንተ ጣጣ አይደለም። እንዲ ሁም ራስህን በመስጠት እግዚአብሔር በእርግጥ ያንተን ሸክም ይሸከ ግል። ለእርሱ ብትተው ሁሉ ውብ ነው።

አንተ ድል ለማግኘት መፍጨርጨርህን ብትተው ያኔ እግዚአብሔር የአንተን ነገር ይወስዳል። ለእርሱ ከመተውህ በፊት ግን ስለ አንተ ኃላፊ ነት እንዲወስድ ብትጠይቀው ኃላፊነቱን ከመውሰዱ በፊት እስክትተው ይጠብቅሃል።

ሁላችንም ከባድ የአለማመን ኃጢአት ያለብን ይመስላል። በየዕለቱ ስለ ራሳችን ራሳችን ኃላፊነቱን እንወስዳለን። ግን ወንጌልን ለአሕዛብ ሰን ሰብክ ክርስቶስ ስለሞተላቸው ስለ ምንም እንዳይጨነቁ እናስተምራቸ ዋለን። ከእነርሱ የሚፈለገው ግመን ብቻ እንደሆነና ይህም ሲሆን እንደ ሚድኑ እንነግራቸዋለን። በተመሳሳይም እኛ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለናል። አሁን እርሱ ነው በእኛ የሚኖረው ፤እግዚአብሔርን አክብር፤ አመስ ግን፤ አክብር ብንባል ከግመን እንዘገያለን። ክርስቶስ ራሳችን ነው፤ እኛም የእርሱ ብልቶች፤ ክርስቶስ የወይን ግንድ ነው፤እኛም ቅርንጫ ፍች፤ እርሱ ሕይወታችን ነው፤ እርሱ ሁለንተናችን ነው።ስለዚህ እኛነታ ችንን ከራሳችን ውስጥ እናስወግድ።ከክርስቶስ ጋር የተሰቀልን እኛ ስለ ምንም አንጨነቅ።ጌታ ኃላፊነታችንን ሁሉ መሸከም ይጀምር ዘንድ እንፍቀድለት።

ክርስቲያናዊ የደስታ ሕይወት ምስጢር «*The christian secret of a happy life*» በተሰኘ መጽሐፍ ላይ አንድ የተጻፈ ታሪክ አለ። አንድ ክርስቲያን ውሃ የሌለበት አንድ ጉድጓድ ውስጥ ይገባል። ወደ ውስጥ የገባውም በጉድጓዱ አፍ ላይ የታሰረውን ገመድ በግራና በቀኝ እጁ እያፈራረቀ በመያዝ ነው። ሲንሸራተትም በድንገት የገመዱ መጨረሻ ላይ ደረሰ። የጉድጓዱን ጥልቀት ስላላወቀ ወደ ጉድጓዱ አፍ ለመመለስ ቢያስብ ረዘመበት አቅምም አጣ። ገመዱን በሁለት እጁ ይዞ እርዳታ ያገኝ ዘንድ ጮኸ። ግን ምን ያደርጋል በረሃ መካከል ነው። እርሱም ከጉድጓዱ በታች ወርዷል። ምንም ያህል አብዝቶ ቢጮኽ ማንም ሊደርስለት አልቻለም። በመጨረሻ እጅግ ከመድከሙ የተነሳ

ገመዱን በዚህ ዓይነት ይዞ መቆየት አልቻለም። በመሆኑም «እግዚአ ብሔር ሆይ በአንተ እጅ ልውደቅ»ብሎ ጸለየ። እንዲህ ከጸለየ በኋላ እጆቹን ከገመዶቹ ለቅቆ ወደታች ወደቀ። የሚገርመው እንደፈራው ሳይሆን የቀረው ሶስት ኢንች ያህል ነበር። አልሞተም፣ በዘለዓለሙ ዓለት ላይ አረፈ እንጂ። እባክህ አንተም የራስህን ትግል አቁም። «ጌታ ሆይ አድነኝ» ማለት ብቻ ነው የሚያስፈልገው። በቀላሉ በአንድ ስንኝ ቃል ብቻ ጠይቅ። ይህ የአንተን እጅ ማንሣት ያሳያል። እየደጋገምህ «ጌታ ሆይ አድነኝ» በማለት መጮህ ከቀጠልክ ተሸንፈሃል ማለት ነው። እንዲህ ያለውን ጸሎት «በጸሎት መጽናት» አለዋለሁ። የዚህን ዓይነት ጸሎት አብዝተህ በጸለይክ ቁጥር የራስህን ጥረት እንዳልተውከና በነገሩ ላይ ተንጠልጥለህ እንዳለህ የበለጠ ያሳያል። ጸሎትን እንደ ድል ማግኛ መሣሪያ አድርገህ ትጠቀማለህ፣ የራስህን ድል ለመቀዳጀት ትጠቀምበታለህ። በዚህም ምክንያት ድል አይኖርም። ለማሸነፍ የምታደርገውን ትግል አቁም፣ ወደ ድል ትመጣለህ።

ቀድሞ ስሜትን የሚጐዱ ዘለፋዎችን ከሌሎች አንደበት ስትሰማ ትበሳጭ ነበር። አንድ ሰው ደጋግሞ በነገር ቢነካካህ ምንድነው የምታደርገው? እንዲህ ዓይነት ነገር ሲገጥምህ «ጌታ ሆይ ይህ የእኔ ጉዳይ አይደለም፣ ድል የአንተ ሥራ ነው። ስሜቴን ልትቆጣጠር እንደምትችል አውቃለሁ። ለሁሉም ነገር አንተ ኃላፊ ነህ» ብትለው ይሻል መተው ይባላል። ጌታም የእርሱን ትዕግሥት ለአንተ ያደርጋል። በዚህ ጊዜም እግዚአብሔርን ልታከብርና «ጌታ ሆይ በፍጹም አልጨነቅም»ልትል ትችላለህ። ግን መጮኸታተሉን እንደማትችል ይሰማህና «ጌታ ሆይ ራሴን መቆጣጠር ስለሚያቅተኝ አድነኝ »ብለህ ትጸልያለህ። አሥራ አምስት ደቂቃ አስራ አምስት ሰዓት ሆኖ ያልፋል። ምንም እንኳ ቁጣህ በውጭ ገንፍሎ ባይወጣም ውስጥህ ግን በግኗል ይህም ድል እንዳልነሳህ ያሳያል። ሰይጣን ቁጣህ ገንፍሎ እንዲወጣ አይፈልግም፣ በውስጥህ ከተቆጣህ ይበቃዋል። እንዲህ በማድረግም ያሸንፋል።

ድል ማለት አለመታገል ነው፣ ስለ ነገሩ ግምት አለመስጠት፣ አለ መጨነቅ ማለት ነው። ዝምታህ፣ እንደሞተ ሰው መሆንህ መተው ተብለው በትክክል ሊጠሩ ይችላሉ። በእግዚአብሔር ተቃዋሚ ኃይሎች

አትናወጥ። በሌጌዎኖች የሚገመቱ የጠላት ወኪሎች አሉ። ዕለት በዕለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድትተላለፍ ይፈታተኑሃል። አንተ ግን ራስ ህን ለክርስቶስ አሳልፈህ ሰጥተሃል። ካልተጨነቅህና ትግልህን ካቆምህ ይህ መተው ይባላል።

ሰይጣን ራስህን እንድታናውጥ ሊፈትንህ ይችላል።

አንድ ወንድም ሁልጊዜ የሚናደድበት ፈተና እንደሚገጥመው ተናገረ። ሌላው ወንድም ደግሞ በመደጋገም በጨካኝነት እንደሚፈተን ተናገረ። አሁንም ሌላው ወንድም ሁልጊዜ በስንፍና እንደሚፈተን ተናገረ። ሺህ ሰዎች ሺህ ዓይነት የተለያየ ፈተና ያላቸው ይመስላል። በዓለም ላይ ግን አንድ ፈተና ብቻ ነው ያለው። ለቁጣ፣ ለትዕቢት፣ ለስ ስት፣ ለዝሙትና ለመሳሰሉት የተለያዩ ፈተናዎች ቢቀርቡም ጠላት ግን ያለው አንድ ፈተና ነው፣ ይኸውም ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ቅዱሳንን ለፈተናው መልስ እንዲሰጡ ማነሳሳት ነው። ሰይጣን እንድትበሳጭ፣ እን ድትኮራ፣ ወይም እንድትሰስት አይፈትንህም። የሚፈትንህ ራስህን አንድ ነገር ታደርግ ዘንድ በማነሳሳት ነው። ይህን በማድረጉ ብቻ ድል ያገኛል። እኔ ዎችማኒ ራሴ በዚህ ነገር ብዙ አንብቻለሁ። ምንም ነገር ለማድረግ አትነሳ። አንድ ነገር ለማድረግ ከተነሳሳህ ወድቀሃል ማለት ነው። ኃጢአትን ለማሸነፍ ከሰይጣን ጋር ትግል ከጀመርክና በራስህ ለመ ሥራት ከተነሳሳህ እርሱ ድል አግኝቷል ማለት ነው። ድላችን ተመልካች በመሆን እንደሚገኝ ይህን ልብ አድርግ። ድል የምናገኘው የራሳችንን ሥራ በመተው ነው። እግዚአብሔር እኛን በማስወገድ ልጁን ስለኛ እንዲ ያሸንፍ ማድረጉን ብናይ ምንኛ ድንቅ ነው።

«መንፈስ በሥጋ ላይ...» ገላ 5:17

እዚህ ላይ ሥጋን ለማሸነፍ እንዋጋለን አይልም፣ ወይም ሥጋ እኛን ይቃወማል አይልም። በዚህ ፈንታ «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ» ይላል እንጂ እኛ የለንበትም። መንፈስና ሥጋ ናቸው እርስ በርሳቸው የሚቀ ዋወሙት። እኛ ምን ማድረግ ነው የምንፈልገው? ኃጢአት ማድረግን

እንፈልጋለን። መንፈስና ሥጋ እርስ በርሳቸው ስለሚቀዋወሙ እኛ መሆን ያለብን ምንም ማድረግ የማንችል ተመልካች ነው። ለመሣተፍ ስፍራ አልተሰጠንም። የእግዚአብሔር ነፃ ማውጣት ይኼ ነው። የመንፈስ ቅዱስንና የሥጋን መቀዋወም ለመመልከት ወደ ጐን እንቀመጣለን። ነፃ የመውጣት መንገዱ ይህ ነው።

አዲስ አማኝ ሆኜ አንዲት ትንሽ ልጅ እንዴት የደኅንነት ምስጢር እንደተረዳች በኪዝዊክ ጉባኤ ሰምቻለሁ። አንድ ወንድም ይህችን ልጅ ፈተና ሲገጥምሽ እንዴት ታሸንፊያለሽ በማለት ጠየቃት። «በመጀመሪያ ሰይጣን መጥቶ መዝጊያዬን ሲያንኳኳ፣ እንዳትገባ፣ አለዋለሁ። ይህ ግን ሁልጊዜ በሽንፈት ነበር የሚያበቃው። አሁን ግን ሰይጣን ባንኳኳ ቁጥር ወዲያው ጌታን «ጌታ ሆይ አንተ በሩን ክፈት» አለዋለሁ። ጌታም እንዲሁ ለማድረግ ይሄዳል። «ሰይጣንም ጌታን እንዳየው እንዲህ ይላል ይቅርታ በስህተት ሌላ በር አንኳኳሁ በማለት ተመልሶ ይሄዳል» አለች።

በፈተና ላይ ወድቀን እያለ«እረ ጌታ ሆይ! ይኸው ፈተና መጣ ብኝ፣ አድነኝ፣ አድነኝ» ብለን ብንጮኽ በሩ ከመከፈቱ በፊት ሰይጣን ይገባል። ሰይጣንን እንደፈቀደ ያደርገው ዘንድ ለጌታ ተውለት። የድል ነሽ ሕይወት የመጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ መተው ነው። አጥብቀህ የያዝከውን ነገር ለጌታ ስትለቅ ድል ትነሣለህ።

አንዲት እህት በመተውና በማመን ድል የሚነሣ ሕይወት እንዴት እንደሚገኝ የሚናገር መልዕክት ሰማች፣ ለመጸለይም ሁልጊዜ ወደ ተራራ ትወጣለች። ነገር ግን ወደ ድል የሚያወጣውን በር አልፋ መሆን አለመሆኗን ጠየቅኋት። እርሷም ዛሬ በተራራው ላይ አንድ ሌላ ጉድጓድ ቆፍራ ራሷን ቀብራ እንደተመለሰች ተናገረች። ከዚህ በኋላ ብዙ ጊዜ ጠይቄአታለሁ፣ የምትሰጠኝ መልስ ግን አንድ ነው። ከሕይወቷ ብዙ አስቸጋሪ ኃጢአቶችን እንዳስወገደች አውቄያለሁ፥ ያም ሆኖ ግን ጭንቀት አነብባታለሁ። ጸለይኩላት ግን በከንቱ ነበር። አንድ ቀን እንዴት እንደ ምረዳት አውቅ ዘንድ እግዚአብሔርን ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጠየቅሁት።

በዚያው ቀን ስትዘምር ሰማሁ። እንደገናም አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንደ ምትገኝ ጠየቅኋት። እንባዋ ዱብ ዱብ እያለ እንዲህ አለች፣ «ለብዙ ኃጢአት መፍትሔ አግኝቻለሁ፣ ግን ማሸነፍ ያቃተኝ አንድ ትንሽ ኃጢአት አለ። ይኸውም ከመጠን በላይ መመገብ መውደድ ነው።» ለሌሎች ይህ ችግር ምንም ላይሆን ይችላል። ለእርሷ ግን እንደ ቀላል ነገር አይታይም።

ችግሯን እየነገረችኝ ሳለ ፈገግ በማለት ይህ በጣም ድንቅ ነገር ነው፣ ከዚህ የተሻልሽ ልትሆኚ አትችይም አልኳት። ግን እርሷ እንዲህ በማለት ምሬቷን ገለጸች፣ «የድል ሕይወትን የማግኛ ቅድመ ሁኔታዎች አንደኛው መተው፣ ሁለተኛው ማመን ናቸው ብለሃል፣ ደግ እኔ ማመንም መተውም አልችልም» አዎን ማመንም መተውም የለብሽም ስል መለስኩላት። ግን የድል ቅድመ ሁኔታዎችን መተውና ማመን ናቸው አላልክም? ታዲያ ካልተውኩና ካላመንኩ ምን ማድረግ እችላለሁ? ስትል አጉረመረመች። እኔም ባትተይና ባታምኚ መልካም ነገር ነው በማለት ደጋገምኩላት። መተው ምንድነው? መተው ማለት የራስን ነገር ማቆም ነው። የራስን ጥረት ማቆም ማለት ምንም አለማድረግ ማለት ነው። ግን አንቺ መተውን ሥራ አድርገሽዋል። ማመንም እንዲሁ ምንም አለማድረግ ነው። ማመንንም ሥራ አድርገሽዋል። መተው ወይም ማመን አልችልም ብለሻል። ለመተው መጣር የለብሽም። የድል ቅድመ ሁኔታዎች መተውና ማመን ብቻ ናቸው። ግን መተውና ማመንኝ የሥራ ውጤቶች አድርገሽ ወስደሻቸዋል። ይህ ምንም የማይጠቅም ነው። ዝም ብለሽ ሁሉን ተይ። ምንም ነገር አታድርጊ፣ ከቻልሽ አመስግኚ፣ ካልቻልሽ ለማመስገን እንኳ አትሞክሪ። ወደ እግዚአብሔር ነይና ራስሽን በእጆቹ ላይ ጣይ። ካስፈለገ ወደ እቅፉ ለመሸሸግ ታገይ፣ መተው ማለት ይህ ነው።

አ! ምንኛ አስገራሚ ሰዎች ነን፣ እግዚአብሔር ምንም ነገር እንዳናደርግ ሲነግረን እኛ ግን ይህን ወይም ያንኛውን ለማድረግ እንፈልጋለን።

ብዙ ወንድሞችና እህቶች የራሳቸውን ጥረት ትተናል ይላሉ። መተዋ ቸውን ግን ሥራ ያደርጉታል። በመተውና ባለመተው ጉዳይ ላይ እስከ አሁን ድረስ ይታገላሉ፣ ኃይላቸውንም ያጠፋሉ። መተው ማለት በቀላሉ በእኔነቴ ምንም ማድረግ አለመቻል ማለት ነው። ይህ ድል ነው።

ይህች እህት በደንብ ካደመጠችኝ በኋላ ከተገለጠላት ታላቅ ብርሃን የተነሣ ለሶስት ቀናት ያህል ዓይናቿ ተጥበርብረው ነበር። ከዚያ ወደ ድል የሚወስደውን በር አቋረጠች፣ እግዚአብሔር ወደ ድልነሺነት አመጣት።

ድካማችንን ንቀን ልንተወው ይገባል።

ምዕራፍ 6

እምነት

«...አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው ቦእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።» ገላ 2/20

«እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።» ዕብ 11:1

ለድል ማመን

እስካሁን እንዳየነው አሸናፊ ሕይወት በራሱ በክርስቶስ ካልሆነ በቀር አይኖርም። የእኔ መንፈሳዊ ዕድገትና የልምምድ መሻሻልም የሚያስገኘው ወይም በራስ ጥረትና ጥንካሬም ክርስቶስን የምንመስልበት አይደለም። ድል ኢየሱስ በእኔ ውስጥ ሲኖር ስለ እኔም ሲያሸንፍ ነው። እኔ እንድድን በመስቀል ላይ እንደሞተ ሁሉ ዛሬም እኔ እዳሸንፍ በእኔ ውስጥ ይኖራል። ለድል የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች ተመልክተናል፣ አንደኛው ራስን መስጠት *(Yielding)* ሁለተኛው ማመን *(believing)* ናቸው። የእግዚአብሔር ልጅ በውስጣችን እንደሚኖር እናምናለን፣ እንዲሁም ደግሞ ራሱ ድሉን በሕይወታችን ውስጥ ያኖራል። በመጨረሻው ውይይታችን ካለፈው ይልቅ ራስን ስለመስጠት ተመልክተናል። አሁንም ደግሞ ጠለቅ ብለን ስለ እምነት እንመለከ ታለን። ብዙ ሰዎች ራሳቸውን ሰጥተዋል፣ ነገር ግን ድል የላቸውም። የዚህ ምክንያቱ አለማመናቸው ነው። ከእምነት ተለይቶ ራስን መስጠት ድልን ሊያመጣ አይችልም። ራስን መስጠትና ማመን እስካልተቀናጁ ድረስ ድል ሊገኝ አይችልም። ስለዚህ ከዚህ በታች ስለ እምነት ጠለቅ ብለን እንመልከት።

በቻይና ቼፎ በሚባል ቦታ የሚኖር አንድ ወንድም ከቤተ ክርስቲያን ስብሰባ በኋላ ወደ ቤቱ ሲመለስ ራሱን ቢሰጥም ድልን አለመ

ለማመዱን ያስብ ነበር። በሚቀጥለውም ቀን በዚሁ ሁኔታ ነበር፣ እንዲያውም በዚያ ቀን ተናዶ ነበር። ስለዚህ ራሱን መስጠቱ ብቻ ድልን ለማግኘት ዋስትና እንደማይሆነው ነገርኩት። ራሱን ከመስጠቱ በተጨማሪ በልቡ ማመን አስፈላጊ ነበር። እርሱም እውነታውን ተቀበለ፣ ድልንም አገኘ። ከስብሰባው በኋላ ተነስቶ እርሱ ምንም የሚኮራበት ነገር ሳይኖረው እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዳደረገለት በማወጅ እግዚአብሔርን አከበረው።

የሐዋርያው የጳውሎስ ልምምድ ምን ነበር? እንዴት ድል አድራጊ ሆነ? በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ራሱን መስጠት ነበር። «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ»ይህን አረጋገጠ። «እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም» የሚል ልምምድ ነበረው። «አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» እያለም ያውጅ ነበር። ለግለት የፈለገውም «የእግዚአብሔር ልጅ በእኔ ውስጥ እንደሚኖር አምናለሁ፣ እንደሚወደኝ፣ ራሱንም ለእኔ እንደሰጠ አምናለሁ።» ለግለት ነው።

እስቲ አሁን እምነት ምን እንደሆነና በእምነትና በድል መካከል ያለውን ግንኙነት እንጠያየቅ፣

በእግዚአብሔር እውነት ማመን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ነገሮች በሙሉ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረጋቸው ነገሮች ናቸው። እ.አ.አ. በጃንዋሪ 1934 በተካሄደው ኮንፍራንስ እንደጠቀስነው እግዚአብሔር ሶስት ነገሮች ሰጥቶናል፣ 1ኛ. ቃል ኪዳኑን፣ 2ኛ. ያከናወነልንን እውነታዎች፣ 3ኛ. ተስፋውን።

እግዚአብሔር ለእኛ የሰጣቸው ነገሮች በሙሉ በእነዚህ ሶስት ስጦታዎች ተጠቃለዋል። ቀደም ብሎ «የተሻለው ቃል ኪዳን »በሚለው መልእክታችን ስለ መጀመሪያው ቃል ኪዳናችን ረዘም ባለ ሁኔታ ተነጋግረናል። ስለሆነም አሁን ደግመን በዚህ ቃል ኪዳን ላይ አንነ ጋገርም። ስለ እግዚአብሔር ተስፋና ስለ እግዚአብሔር እውነታዎች *(God's fact)* ግን ጥቂት ነገሮች እንነጋገራለን። ተስፋ እግዚአብሔር ወደፊት

ሊያደርግልን ያለ ነገር ነው። እውነታ *(Fact)* እግዚአብሔር ሰርቶልን ያለው የተፈጸመ ነገር ነው።

ብዙ ሰዎች እውነታ ምን እንደሆነ አያውቁም። «ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለዓለም ሁሉ ሞተ »ይህ የእግዚአብሔር እውነታ ነው፣ ነገር ግን ምን ያህሉ ድነዋል? የዳኑት ያመኑት ብቻ ናቸው። ኢየሱስ ለዓለም ሁሉ ስለሞተ ዓለም ሁሉ ለምን አልዳነም? የዚህ ምክንያቱ በዓለም ያሉት ሁሉም የእግዚአብሔርን እውነታ በእምነት ስላልተቀበሉ ነው። ቢኮመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣ ቸው የመኖሩን የእግዚአብሔር እውነታ በእምነት አልተቀበሉትም። ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ሲሆን አማኞች ሁሉ ደግሞ አካል ናቸው። በአንድ ሰውነት ውስጥ ራስ ስሜት እንደሚሰማው፣ እንደሚቆጣጠር፣ እንደሚ መራና መልስ እንደሚሰጥ አንድ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ራሱ ግለት ክርስቶስ እንዲሰማው፣ እንዲቆጣጠርና አስፈላጊውን ምላሽ እንዲሰጥ መፍቀድ አለበት። የእግዚአብሔርን እውነታ በተመለከተ ስንቶች ክርስ ቲያኖች ይሆኑ በእርግጥ ክርስቶስ ራሳቸው እንዲሆን የፈቀዱለት? ዛሬ የሚሰሙት *(feelings)* እነርሱ ይሆኑ ወይስ ኢየሱስ ይመራቸ ዋል ወይስ በራሳቸው ይመራሉ? ኢየሱስ ይቆጣጠራቸዋል? ወይስ.. ራሳቸውን ይቆ ጣጠራሉ? ኢየሱስ ለአንድ ነገር ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል ወይስ ራሳቸው ይመልሳሉ? የት ይሆን ችግሩ ያለው? ችግሩ እምነት ማጣት ነው።

አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች ክርስቶስ መሪያቸው እንደሆነ ይናገ ራሉ፣ ነገር ግን እርሱ ለሁሉም ነገር ኃላፊ እንደሆነ አያምኑም። መጽ ሐፍ ቅዱስ፣ ጌታ የወይኑ ግንድ፣ እኛም ቅርንጫፎች እንደሆንን ይናገ ራል። ጌታ ግንዱ ይሆናል፣ እኛም ቅርንጫፎቹ እንሆናለን አይልም። እኛ አመንነውም ወይም አላመንነውም እርሱ የወይኑ ግንድ ነው። እኛም እንዲሁ ቅርንጫፎቹ ነን፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ምግብ ከግንዱ ወደ ቅርንጫፍ የሚያልፈው ለሚያምኑት ብቻ ነው፣ በውጤቱም ፍሬ ይሸከ ማሉ። ነገር ግን ለማያምኑት የጌታ ሕይወት በውስጣቸው አያልፍም፣ ስለሆነም፣ ፍሬ ለማፍራት በራሳቸው መድከም አለባቸው።

እምነት የእግዚአብሔርን እውነታ ያስረግጣል

ዕብ 11:1 ስለ እምነት አስፈላጊነት ይናገራል። ይህ ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እምነት ምንነት ገለፃ የሚሰጥ ብቸኛ ክፍል ነው። እምነት ተስፋ የሚደረጉ ነገሮችን የሚያስረግጥ ነው። እምነት በማይታዩ ነገሮች ላይ ያለ ጽኑ እርግጠኝነት ነው። እምነት የማይታይን ነገር እውነታ እንደሆነ የሚያስረግጥ ነው። ለምሳሌ በዚህ በተሰበሰብንበት አዳራሽ የአምፖሉን ቅርጽ፥ የግድግዳውን ቀለም እንዲሁም የኦርጋኑን ድምጽ እንረዳለን። ቅርጹን፣ ቀለሙንና ድምጹን እንዴት አረጋገጥን? ከሁለቱ ዓይኖቻችን በስተቀር የቀለሙን ዓይነት ያረጋገጠልን ነገር የለም እንበልና በሚያምሩ አረንጓዴ፣ ቀይና ቢጫ ቀለሞች የተሳለ ሥዕል አለ። ዓይኖች ባይኖሩ ቀለሞች ምንም ቢያምሩ በእኛ ልምምድ ቀለሞቹ በምንም መንገድ እውን ሊሆኑ አይችሉም። በተመሳሳይ ሁኔታ የኦርጋኑ ድምጽ ምንም ቢያምር የድምጹን ህልውና ለመረዳት ጆሮዎች ያስፈልጋሉ። ለአንድ ዶንቆሮ ለሆነ ሰው የሙዚቃውን ህልውና ለመረዳት ምንም ዓይነት መንገድ አይኖርም። ዓይንም ሆነ፣ የእጅ ዳሰሳ የድምጹን ህልውና ሊያረጋግጡ አይችሉም። ጆሮዎች ብቻ ናቸው የድምፅን ህልውና ሊያረጋግጡልንና አስደሳችም ሊያደርጉት የሚችሉት። እንዲሁም ደግሞ አንድ ነገር ቅርጹ አራት ማዕዘን፣ ክብ፣ ዝርግ፣ ሶስት ማዕዘን ወይም ቆልማማ ሊሆን ይችላል። የነገሩ እውነታ ሊታወቅ የሚችለው በአንድ ዳሰሳ ወይም በአንድ ዕይታ ብቻ ነው። ስለዚህ የአንድ እቃ መኖር አንድ ነገር ሲሆን ህልናውን ማረጋገጡ ሌላ ነገር ነው። በቁሳዊ ዓለም ውስጥ ብዙ ነገሮች አሉ ነገር ግን የእያንዳንዱን ነገር ህልውና ለመረዳት አንድ ችሎታ ያስፈልጋል። በመንፈሳዊ ግዛት ይህ ችሎታ እምነት ነው። አንድ ሥዕል አለ እንበል፣ ስዕሉ ቆንጆ የኮረብታ፣ የውሃ፣ የአበቦችና የዛፎች ትእይንት ይዟል። በዓይናችሁ የሥዕሉን ቆንጅናና ህልውና ልታረጋግጡ ትችላላችሁ እንበል፣ አንድ ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደ ሰው ምንም ዓይነት ቀለም አይቶ አያውቅም። እናንተም በሥዕሉ ውስጥ ስላለው ቀይ ቀለም ልትነግሩት ትሞክራላችሁ፣ እርሱ ግን ቀይ ምንድነው? ብሎ ይጠይቃችኋል፣ አረንጓዴ ደግሞ አለ ብላችሁ

ትነግሩታላችሁ። እርሱም አረንጓዴ ምንድነው? ብሎ ይጠይቃችኋል። እናንተ ልትመልሱለት የምትችሉት ነገር ቀይ ቀይ ቀለም እንደሆነ፣ አረ ንጓዴም አረንጓዴ ቀለም እንደሆነ ብቻ ነው። ሥዕሉ ቢያምርም እንኳ ዓይነሥውሩ ሰው ሊደሰትበት አይችልም።

አንዲት ፒያኖ በደንብ የምትጫወት እህት አለች እንበል። ሙዚቃን አዳምጦ የሚያጣጥም ሰው ሁሉ ይህቺ እህት የምትጫወተውን ሊያደንቅ ይችላል፣ ነገር ግን ደንቆሮ የሆነና ለሙዚቃም እንግዳ የሆነ ሰው የሙዚቃውን ጣፋጭነት ሊያረጋግጥ አይችልም። የእኛም እምነት እንዲሁ ነው። ሁሉም የእግዚአብሔር እውነታዎች እርግጠኛና እውነተኛ ናቸው። ነገር ግን ሊያረጋግጣቸው የሚችለው እምነት ብቻ ነው። እም ነት ተስፋ የምናደርገውን ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያ ስረዳ ነውና።

ዓይነ ሥውሩ ሰው በሥዕሉ ላይ ያለውን ውብ ትእይንት ሊያይ አይችልም፣ ይሁን እንጂ ለማየት አለመቻሉ በምንም ዓይነት የሥዕሉን ሀልውና ሊያስቀረው አይችልም። ሰውዬው አየም አላየም የሥዕሉ መኖር እውነታ ነው። የሚያምሩትም ቀለሞች ሳይለወጡ ይቆያሉ። ጥያቄው ሰውዬው በሥዕሉ መጠቀም ችሏልን? የሚለው ነው። ዓይን ያለው ሁሉ በሥዕሉ ይደሰታል፣ በዚህም ይጠቀማል። መንፈሳዊውም ዓለም እንዲሁ ነው። ጌታ ለሰው ልጆች ሁሉ ደሙን ማፍሰሱና በመስቀል ላይ መሞቱ እውነታ ነው፣ ይሁን እንጂ ይህን እውነታ ሊያረጋግጡና ሊጠቀሙበት የሚችሉት እምነት ያላቸው ብቻ ናቸው። ለማያምኑት ግን ጌታ በመ ስቀል ላይ መሞቱ እውነታ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሊለማመዱት ሊጠ ቀሙበት አይችሉም።

አሁን የእምነትን ምንነት ተገነዘባችሁ? ዓይኖቻችንን እጆቻችንን ጆሮዎቻችንን ቁሳዊን ነገር ለማረጋገጥ እንደምንጠቀምባቸው ሁሉ እምነትም መንፈሳዊን ነገር ለማረጋገጥ ይጠቅመናል። በሁሉም መንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥ በእርግጠኝነት እምነት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ጌታ ራስ ነው፣ እኛም የእርሱ የአካል ክፍሎች ነን። ይህ ሕብረት ሊለያይ የማይ ችል እውነታ ነው። እንደዚሁም ጌታ የወይን ግንድ፣ እኛም ቅርንጫፎቹ

የመሆናችን ነገር የማይለያይ እውነታ ነው። ይህን እውነታ በማመን እንጠቀምበታለን።

ብዙዎች ጌታ የወይን ግንድ ነው እኛም ቅርንጫፎቹ ነን ይላሉ። ነገር ግን ከወይኑ ግንድ መንፈሳዊ ምግብ የማግኘትም ሆነ ፍሬ የማፍራት ልምዱ የላቸውም። የዚህ ምክንያቱ እምነት ስለሌላቸው ነው።

እምነት ምንድነው? እምነት የአእምሮ መጨነቅ አይደለም። እምነት እውነታውን መመልከትና ማጽደቅ ነው። ከርስቶስ ለኃጢአት ይቅርታ በመስቀል ላይ እንደሞተና ደሙን እንዳፈሰሰ ሰምታችኋል፤ ስለሆነም ከርስቶስ ለኃጢአት ይቅርታ በመስቀል ላይ ሞቷል ትላላችሁ። ጌታ የወይኑ ግንድ እንደሆነና እኛም ቅርንጫፎቹ እንደሆንን ሰምታችኋል፤ እናንተም ደግሞ ጌታ የወይኑ ግንድ እኛም ቅርንጫፎቹ ነን ትላላችሁ። ጌታ ኢየሱስ ሕይወታችሁ እንደሆነና በውስጣችሁም እንደሚኖር ሰምታችኋል፤ ደግሞም ሕይወታችሁ እንደሆነና በውስጣችሁም እንደሚኖር ተናግራችኋል። ይሁን እንጂ እምነት ስለሌላችሁ እነዚህን እውነታዎች ልታረጋግጧቸውና በሕይወታችሁም ልትለማመዷቸው፤ ተግባራዊም ልታደርጓቸው አትችሉም። በተመሳሳይ ሁኔታ አለመቻላችሁንና ጥቅመ ቢስነታችሁን ስለተረዳችሁ በራሳችሁ ለመሄድ ወስናችኋል፤ ይሁንና ይህ የድል ተቃራኒ ጉዞ ነው። ከርስቶስን በሥራና በእምነት ልታረጋግጡ ይገባችኋል። ከርስቶስ የፈጸማቸው እውነታዎች ሁሉ በአንድ ደቂቃ ውስጥ እንዲያውም በአንድ ሴኮንድ ውስጥ በሕይወታችሁ ቢረጋገጡና ቢንጸባረቁ ይህ በጣም የሚያስደንቅ አይደለምን? ይህ በእምነት የሚረጋገጥ ጉዳይ ነው።

አንድ ሥዕል ውብ እንደሆነ በምን ታውቃላችሁ? ያወቃችሁት በሥጋዊ ዓይናችሁ ስላያችሁት ነው። የክርስቶስን ባለጸግነት እንዴት ተረዳችሁ? በመንፈሳዊ ዓይናችሁ ስላያችሁት ነው። ወደ ቆላስያስ በተጻፈው ደብዳቤ ውስጥ «በእርሱ (በክርስቶስ) ሆናችሁ ተሞልታችኋል።» (2:10) በማለት እግዚአብሔር አውጇል። ነገር ግን እንዴት በክርስቶስ ሙሉ ሆናችሁ መመራታችሁን አወቃችሁ? ያወቃችሁት በመንፈሳዊ ዓይናችሁ ስላያችሁት ነው። ወደ ራሳችሁ በተመለከታችሁ ጊዜ ፈጽሞ ሙሉ ያለመሆናችሁን ታውቃላችሁ። ይህም ቢሆን በክርስቶስ

ሙሉ መሆናችሁን ማወጅ ትችላላችሁ? በእምነት ዓይን ትች ላላችሁ። ጌታ ባለጸግነቱን ሰጥቷችኋል፤ በጸጋ ላይ ጸጋ አላችሁን? በአዕ ምሮ አችሁ ውስጥ ሰላለ አይደለም፤ ነገር ግን በልባችሁ ሰላመናችሁ ነው።

በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። (ኤፌ 1:3) በረከቶቹ በየትም ይሁኑ በእርግጥ በእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በረከቶች ሁሉ በሰማያዊ ሥፍራ እንደባረከን እናምናለን። አጠቃላዩ ጥያቄ የሚሸክረክረው በእምነት ዙሪያ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ ማመን ይሆናል። የክርስቲያን ትልቁ ውድቀት አለማመን ነው። እመን፤ እውነታውም ይረጋገጣል። በእምነት መመል ከት እናም እውነታው በልምምድ ውስጥ ይረጋገጣል።

በእንግሊዝ አገር ውስጥ ኤች ደብልዩ ዌብፒፐሎ *(H.W Webb peploe)* የሚባል የእግዚአብሔር ሰው ነበር። እርሱ ያረጋገጠውን ነገር ስሙ፤

> «ከአራት ቀናት በኋላ በባሕር ዳር ከእኛ ጋር የነበረው ትንሹ ልጃችን ታሞ ሞተ። ትንሹን የሬሳ ሳጥን በእጄቼ ተሸክሜ ወደሚቀበርበት ቦታ መሄድ ነበረብኝ። ከቀብር ተመልሼ ለራሴ እንዲህ አልኩኝ፤ የበአል (የደስታ) ቀንህን አጥተሃል፤ ወደ ቤትህ በችግር ተመልሰሃል፤ ረዳት ቁስህ እንዲናገር ከመፍቀድ ለሕዝብህ ራስህ መናገር አለብህ። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍትሩ ብትነግራቸው የተሻለ ነው። ለእሁድ የተዘጋጀውን ትምህርት ተመለከትኩ፤ ትምህርቱ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12ነበር። ዘጠነኛውን ቁጥር አነበብኩት፤ (ጸጋዬ ይበቃሃል) በዚህ ቁጥር ላይ ለመናገር አሰብኩ። ማስታወሻዬን ለማዘጋጀት ተመለከትኩ፤ ነገር ግን ወዲያውኑ እግዚአብሔር በእኔ ላይ እንድሸከመው ስላመጣብኝ ነገር ማጉረምረም ጀመርኩ። ብእሬን አስቀመጥኩ፤ ራሴን በጉልበቴ ላይ ጫልኩና የሚበቃ አይደለም? አይበቃም? አልኩ። ጌታ ሆይ ጸጋህ እንዲበቃኝ አድርግ አልኩኝ። ቤቴን ከመልቀቂ አንድ ቀን በፊት አንድ የተጻፈ ጥቅስ እናቴ ሰጠችኝ። ስመለስ እንዳገኘው ሠራተኛውን ከጠረጴዛው በላይ

ባለው ግድግዳ ላይ እንዲሰቅለው ጠየኩት። አይኖቹን እንደከ
ፈትኩ፣ ጌታ ሆይ ጸጋህ እንዲበቃኝ አድርግ እያልኩ ነበር።
ግድግዳው ላይም ይህን ተመለከትኩ «ጸጋዬ ይበቃሃል።» ለእኔ
የተነገረ የሚመስል ድምጽ ሰማሁ፣ «አንተ ሞኝ አንዴ የሆነውን
ነገር እግዚአብሔር እንዲያደርግ እንዴት ትጠይቃለህ? ተነስና
ውሰድ፣ እውነትም ሆኖ ታገኘዋለህ። እግዚአብሔር ሆኗል ሲል
አንተ እርሱን እንድታምነው ነው። ስታምነው ለማንኛውም ጊዜ
እውነት ሆኖ ታገኘዋለህ።» ይህ ሕይወቴን ቀየረው። ከዚያን
ጊዜ ጀምሮ እንዲህ ማለት ጀመርኩ፣ ጌታ ሆይ በቃልህ
ያልከውን ሁሉ አምናለሁ፣ እደርስበታለሁም።

ይህ የእግዚአብሔር ባሪያ እግዚአብሔርን በዚህ መንገድ ዳግም
አስከግይጠይቅ ድረስ በደስታና በምስጋና የተሞላ ነበር። በሚቀጥለው
ቀን ሰባኪው የሚቆምበት ቦታ (ፑልፒቱ) ላይ ቆሞ በሕይወቱ ላይ
የተመሠረተውን አስደናቂ መልእክት አቀረበ። ይህን ሰማያዊ ኃይል መቼ
እንደተለማመደው ሰዎች ሲጠይቁት መልሱ ትንሹ ልጄን ቀብሬ
ከተመለስኩ በኋላ ነው የሚል ነበር። ልዩነቱን ያመጣው ነገር ማመንን
መማሩ ነው።

ለረጅም ጊዜ ከተናገርኩ በኋላ እንድ ንግግሬን ያዳመጠ ወንድም
ከንግግሬ ምንም እንዳላገኘ ተናገረኝ። እኔም አንዲህ አልኩት፣ ይህ የሆ
ነው ዝም ብለህ እኔን ስላዳመጥከኝ ነው አልኩት እኔን ከማዳመጡ በተ
ጨማሪ እግዚአብሔር እንዲናገረው መጠየቅ ነበረበት። በዚህም መሠረት
ጸለየ፣ «እግዚአብሔር ሆይ እንዳሸንፍ እርዳኝ፣ እግዚአብሔር ሆይ
ባሕርዬ መጥፎ ነው እንዳሸንፈው እርዳኝ»፣ እየጸለየ እያለ ለኢየሱስ
«ብትወድስ ልታነፃኝ ትችላለህ?» ያለውን የለምፃሙን ሰው ጸሎት አስ
ታወሰ። ይህ ወንድምም እንደዚሁ «ጌታ ሆይ ብትወድስ መጥፎ ባህርዬ
ጥሎኝ እንዲሄድ ማድረግ ትችላለህ» ብሎ ጸለየ። በዚህ ጊዜ በታሪኩ
ውስጥ ኢየሱስ ለምፃሙን እወዳለሁ እንዳለው ሁሉ አሁንም ፈቃዱ እን
ደሆነ ተረዳ። ስለዚህ ለምን ይጸልያል? ጌታ ሁሉንም ነገር ፈጽሞታል፡
ፈቃዱም ስለነበር ሁሉም መልካም ነበር።

አንተ ልታምን ከቻልክ ሁሉም ነገር መልካም ነው። /2ኛ ቆሮ 12:19 /ሉቃ.18:27/ የጌታ ኢየሱስን «እወዳለሁ» የሚል ቃል በግ መን ችግርህ ይፈታል። እምነት እግዚአብሔር አንዴ ቃል የገባውን መጠየቅ አይደለም። እምነት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መተማመን ነው።

አንድ ጊዜ አንድ ወንድም የድልን መድረክ እንዴት ግለፍ እንደሚቻል ተናገረ። ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ ሰጠ። ከታዳሚዎቹ ውስጥ አንዲት ወጣት እህት በጉንጮቿ ላይ እንባ እየወረደ ተመለከትኩኝ። ነገር ግን ተነስታ ቆማ ጥያቄ አልጠየቀችም ነበር። ሌላ በእድሜዋ ጠና ያለች እህት ተነስታ፣ «በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ስለ ድል እጸልያለሁ፣ ነገር ግን ድሉን ፈጽሞ አላገኘሁትም፣ ችግሩ ምንድነው? ብላ ጠየቀች። ተናጋሪው ወንድምም ደግመሽ ከመ ጸለይሽ በስተቀር ምንም ችግር የለብሽም፣ ጸሎትሽን ወደ ምስጋና ብትለ ውጪ ሁሉም ደህና ነው አላት። ይህን በተናገረ ቅጽበት ሌላ ወንድም ተነስቶ፣ ድልን ለማግኘት ለአስራ አንድ ዓመት ያለምንም ውጤት ጸለይኩ። አሁን በዚች ታላቅ እህትና በአንተ መካከል የተደረገውን ጥያ ቄና መልስ በማድመጥ ድልን አግኝቼአለሁ»አለ። የሚያገለግለው ወን ድም ወደ ወጣቷ እህት ሄደና እንዴት እንደነበረች ጠየቃት። እርሷም ጥያቄና መልሱን ላዳምጥ እኔም ድልን አግኝቼአለሁ ስትል መልሳለች። ይህ እምነት ነው።

ከእምነት ውጭ ፈጽሞ የእግዚአብሔርን እውነታዎች ልታረጋግጡ አትችሉም። በሥዕሉ ላይ ያለንን ቀለም ለማረጋገጥ ዓይን፣ የኦርጋኑን ድምጽ ለመለየት ጆሮ፣ የአንድን ነገር ቅርጽ ለማረጋገጥ እጅ እንደሚያ ስፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔርን ተስፋና ቃሉን ለማረጋገጥ እምነት ያስፈ ልጋል። «ጌታ ሆይ ቀስ በቀስ ድሌ ሁን ወይም ጌታ ሆይ ቀስ በቀስ ሕይ ወቴ ሁን ወይም ቀስ በቀስ ቅድስናዬ ሁን»ብለን ፈጽሞ አንጸልይ። የም ንጸልየው «ጌታ ሆይ አንተ ድሌ ነህ፣ አከብርሃለሁ፣ አመሰግንሃለሁ ጌታ ሆይ አንተ ሕይወቴ ነህ፣ አከብርሃለሁ፣ አመሰግንሃለሁ፣ ጌታ ሆይ አንተ ቅድስናዬ ነህ» እያልን ነው።

በሕይወቴ ብዙ ፈተናዎች እንዳለፉ እንድታውቁ እፈልጋለሁ። በመንገዴ ብዙ መከራና ችግሮች ገጥመውኛል፣ ብዙ ጠንካራ ቃላት በጆሮዬ ሰምቻለሁ፣ እነዚህን ለማሸነፍ እግዚአብሔር ኃይል እንዲሰጠኝ የጠየቅኩ አይምሰላችሁ፣ በምትኩ «ጌታ ሆይ ከፍ አደርግሃለሁ፣ አመሰግንሃለሁ፣ አንተ ድሌ ነህና፣ ጌታ ሆይ አንተ ለኔ አሸንፍልኝ፣ እኔም አከብርሃለሁ፣ አመሰግንሃለሁ አንተ ለኔ ተቋቋምክልኝ፣ እኔም አክብርሃለሁ፣ ከፍ አደርግሃለሁ። ጌታ ሆይ አንተ ራሴ ነህ፣ እኔም የአንተ አካል ነኝ። አንተ ግንዱ ነህ እኔም ቅርንጫፍ ነኝ። የሚያስፈልገኝን ሁሉ ትሰጠኛለህ» ብዬ እጸልያለሁ፣ እርሱም ደግሞ እንደ ቃሉ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ሲሰጠኝ አግኝቼዋለሁ።

በመሠረቱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከሚገኙት ብዙ ሺህ ጥቅሶች ውስጥ እያንዳንዳችን የዳንነው በአንድ ጥቅስ ነው። አንዳንዶች በዮሐ 3:16፣ ሌሎች በዮሐ 5:24፣ ሌሎች ደግሞ በሮሚ 10:10 ድነዋል። በአንድ የእግዚአብሔር ቃል አንድ ሰው ይድናል። ይህ እውነት ለድል አድራጊነትም እንዲሁ ነው። ከብዙ የእግዚአብሔር ቃሎች ውስጥ አንዱ ለአንድ አማኝ ድልን ያመጣል። ልክ ያ ወንድም «እወዳለሁ» /ማቴ 8:3/ በሚለው የኢየሱስ ቃል ድልን እንዳገኘ ብዙዎች በ2ኛ ቆሮ 12:9፣ በሮሚ 6:14፣ በ1ኛ ቆሮ 1:30 ወደ ድል አድራጊነት ይገባሉ።

እምነት ተስፋ ማድረግ አይደለም።

እንዲያው በቀላሉ ተስፋ የሚያደርጉ ሁሉ ምናልባት ያላመኑ ይሆናሉ። አንድ ሰው ድል አድርጉ እንደሆነ ስትጠይቁት የሚሰጠው መልስ ድል እንደሚያደርግ ተስፋ አደርጋለሁ ቢል ይህ ሰው እምነት እንደሌለው በእርግጠኝነት ማወቅ ትችላላችሁ። አንድ ሰው ለመዳን ተስፋ አደርጋለሁ ቢላችሁም አለመዳኑን ያሳያል። አንዳንዶች ጌታ ነፃ እንዲያወጣቸውና ድልን እንዲያገኙ እንዲያደርጋቸው ይጠብቃሉ፣ አንዳንዶች ጌታ ድል እንዲሰጣቸው ለረጅም ጊዜ ይጠብቃሉ፣ አንዳንዶች እንዲያውም ራሳቸውን እንደሰጡና እንዳመኑ ያውጃሉ። ነገር ግን ራሳቸውን መስጠታቸውና ማመናቸው ይሰራ እንደሆነ ለማየት ይጠብቃሉ። ብቁ

የሆኑ ወይም ያልሆኑ እንደሆኑ ለሚጠብቁ እምነት ፈጽሞ አይሠራም። ምክንያቱም እምነት ተስፋ ማድረግ አይደለምና።

አንድ ወንድም «አግኝ ድልን ከተለማመደ በኋላ ጌታ ኢየሱስ የእርሱ ድል እንደነበረ ሁልጊዜ ማስታወስ አለበት?» ብሎ ጠየቀኝ። እርሱ በሚሠራበት ፋብሪካ ከሃያ የሚበልጡ ሰራተኞችን ሥራ በበላይነት ይቆጣጠር ነበር። እርሱ እንደነገረኝ ቁጥጥሩ ከጠዋት እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ያለውን ጊዜ ይወስድበት ነበር። እናም እንዲህ ብሎ ጠየቀ፤ ቀኑን ሙሉ ስለ ብዙ ነገሮች ስጠነቀቅ እንዴት አድርጌ ይህን ማስታወስ እችላለሁ? እኔም ስመልስ በፋብሪካ ውስጥ እያለህ ያለማቋረጥ ሁለት ጎይን እንዳለህ ታስባለህን? ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም፣ አላስብም ብሎ መለሰ። «ከሥራ በኋላ አይኖችህ አሁንም በቦታቸው እንደሆኑ ለማረጋገጥ በእጆችህ ትዳብሳቸዋለህን? ብዬም ጠየቅሁት። እርሱም ፈጽሞ አላደርግም» ብሎ መለሰ። እናም እንዲህ አልኩት፣ ማስታወሱ ወይም አለማስታወሱ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ቁም ነገሩ የጎይናቹ በቦታቸው መሆን ነበር። እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን በእኛ ውስጥ ያለው ድል አድራጊ ሕይወት እኛ ጌታን በማስታወሳችን ላይ የተመሠረተ አይደለም። ይልቁን ድላችን የተመሠረተው ጌታ እኛን በማስታወሱ ላይ ነው። ለእኛ ጌታን ሁሌ ማስታወሱ እንዴት አስቸጋሪ ነው? ግን እግዚአብሔር ይመስገን እርሱ ነው እኛን የሚያስታውሰው።

እምነት ስሜት አይደለም።

አንዲት እህት እንደነገረችኝ ምንም እንኳ ራሷን ብትሰጥና ብታምንም አሸናፊ መሆኗን ለመናገር አትደፍርም ነበር። ምክንያቱም የጌታን ድል ከተቀበለችበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ምንም ነገር አይሰማትም። እዚህ ላይ ጠንከር አድርጌ ልናገርና እምነት በእርግጥ በሕይወታችን የምንለማመደው ነው ማመን ከስሜት ጋር የሚያያዝ አይደለም። ስሜት በአንዳንድ ነገሮች ውስጥ ጥቅም ይኖረው ይሆናል፤ ነገር ግን ጌታን በማወቅ ውስጥ ፈጽሞ ጥቅም የሌለው ነው። በእጃችን ዳሰን ቅዝቃዜን ወይም ሙቀትን ልናውቅ እንችላለን። ነገር ግን አንድን ሥዕል እጃችን መመልከት አይችልም። በመንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥም

ለግረጋገጥ የሚጠቅመው እምነት እንጂ ስሜት አይደለም። ድል የተመ ሰረተው የእግ ዚአብሔርን ቃል በማመን ላይ ነው። እግዚአብሔር ስላለ ይሆናል እንጂ ጥንካሬ ወይም ደስታ ስለተሰማችሁ አይሆንም። ድል በአንድ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የቱመሠረተ ነው።

አንድ ጠዋት አንድ ወንድም ችግሩን ሊነግረኝ ወደ እኔ መጣ። ይህ ወንድም ራሱን ሰጥቷል። ነገር ግን ደፍሮ ድል አለኝ ግለት አልቻለም። ሰይጣን ሁልጊዜ ይከሰው ነበር። በሌላ ጊዜ የእርሱ ድል እውነተኛ መሆኑን ያጠራጠረው ነገር ተከሰተ። ለእኔ ግልጽ እንደሆነልኝ ይህ ወንድም ስሜቱን አምኖ ነበር። በምሳሌነትም እንዲህ ብዬ ተናገርኩት፣ «ከቤቴ ጀርባ የአትክልት ቦታ አለ። ይህን የአትክልት ቦታ አንድ ቀን ለአንተ ሸጥኩና የባለቤትነት ማረጋገጫ ውል ጽፌ ሰጠሁህ። አንተ ወደ አትክልቱ ቦታ ስትሄድ አንድ ሰው በዚያ ቆሞ የአትክልቱ ቦታ ግማሹ የእርሱ እንደሆነ ተናገረህ፣ በዚህ ጊዜ ምን ታደርጋለህ? ሁለት አማራ ጮች ይኖሩሃል፣ ወይ የሰውዬውን ቃል ታምናለህ አልያም እኔ የሰጠ ሁህን የአትክልቱን ቦታ ጠቅላላ ይዞታ የሚያመለክተውን ውል ትቀበ ላለህ። የእኔ ውል እውነት ከሆነ ያ ሰው ዋሽ ቶሃል ማለት ነው። ግንን ታምናለህ? የሰውዬውን ቃል የምታምን ከሆነ በአትክልቱ ቦታ እንዲቆይ መፍቀድ ይኖርብሃል። የእኔን ቃል ብታምን ግን ከንብረትህ ለቆ እንዲ ሄድ ታደርጋለህ»።

አሁንም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳንና ቃሉ በአንተ ሁኔታ ላይ ፈጽሞ የተመሠረተ ነው። አንተ ስሜትህን አምነህ ጸባይህና ኩራትህ የግ ይፈቱ ችግሮች እንደሆኑ ትናገር ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ያልታ መነ ይሆናልን? አንተ በእግዚአብሔር ቃል ብታምን ያሉብህ ችግሮች ሁሉ ይፈታሉ።

የዋህነት፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ ፍቅር፣ ራስን መግዛት ሌሎችም በክርስቶስ ያሉ ነገሮች ሁሉ የአንተ እንደሆኑ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቷል። በተቃራኒው ግን አንተ ቁጠኛ ትሆናለህ፣ ከኩራተኛነት ያልነፃህ ትሆናለህ፣ ተሸናፊም ነህ፣ ምን ማድረግ ይኖርብሃል? የእግዚአ ብሔርን ቃል ካመንህ እንዲህ ትላለህ፣ «እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃ ለሁ፣ ከፍ አደርግሃለሁ፣ የዋህና ታጋሽ ቸር አፍቃሪ፣ ራሱን የሚገዛ

መሆን እችላለሁ ምክንያቱም ክርስቶስ በውስጤ እየኖረ ነውና»። በእ ግዚአብሔር ቃል ላይ ስትደላደል አንተ የምትፈራቸው ነገሮች ሁሉ ጥለ ውህ ይሄዳሉ።

አለማመን ትልቁ ኃጢአት ነው

ዛሬ በእግዚአብሔር ልጆች ዘንድ ትልቁ ችግር ቃሉን ለማመን አለመቻል ነው። ለእነርሱ ምናልባት ራሳቸውን መስጠቱ አይከብዳቸ ውም። ራሳቸውን ከመስጠታቸው በተጨማሪም ማመኑ ለእነርሱ ቀላል ሊሆን ይችል ይሆናል። ቁም ነገሩ ግን ይህ አይደለም።

ራሷንና ያላትን ሁሉ ለጌታ የሰጠች አንዲት እህት ድል እንዳላት በጠየቅኋት ጊዜ ለመመለስ አቅማማች። ምክንያቱም ምንም ውጤት ሰላ ላየች ነበር። ስለሆነም እንዲህ ስል በቀጥታ ተናገርኳት፣ «የሰው ልጆች ትልቅ ኃጢአት የሆነው አለማመንን ፈጽመሻል። የአንቺ አለማመን እግ ዚአብሔርን እንደውሸታም አድርጉታል። አንቺ ቅርንጫፍ እንደሆንሽና ራስሽንም ብትሰጪ የእርሱ ሕይወት በአንቺ እንደሚንጸባረቅ ተናግ ሯል። አሁን ግን ምንም እንኳ ራስሽን ብትሰጪም እንዳላደግሽ ትናገ ሪያለሽ። በአጭሩ ድርሻሽን እንዳልተወጣሽ ረስተሽ እግዚአብሔር ኃላ ፊነቱን እንዳልተወጣ እየተናገርሽ ነው። እርሷም እንዲህ ዓይነት ሀሳብ አልነበረኝም ብላ ካደች። ስለዚህም እንዲህ ብዬ ተናገርኳት፣ «ግለት ያለብሽ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ፣ ከፍ አደርግሃለሁ፣ ድልን ሰጥተኸኛልና።» የሚል ነው።

ጌታ ራስ እንደሆነና ሕይወትህም እንደሆነ እንድታምን ይህን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ልትመለከት ይገባሃል። «...እንዳገኛችሁት እመኑ፣ ይሆንላችሁማል።» እመን አስቸጋሪው ነገር ያልፋል፣ እመን እናም ምንም ነገር በድል መንገድህ ላይ አይቆምም። መዳን ይህ ነው። ዛሬ እም ነታችን ሥራ አይደለም፣ እምነታችን የእግዚአብሔርን እውነታ በእርግ ጠኝነት ማወጅ ነው። ጌታ ራስ እንደሆነ እመኑ፣ በውስጣችሁም እንደሚ ኖር እመኑ፣ እርሱ ሕይወታችሁ እንደሆነ እመኑ፣ እርሱ ግንዱ እናንተም ቅርንጫፎች እንደሆናችሁ እመኑ፣ እርሱ ለእናንተ እንደሚያሸንፍም

እመኑ፤ ሁሉም በጌታ እንደተደረገ እመኑ፤ አክብሩት አመስግኑት፤ ሁሉም በእርሱ ተደርጓልና።

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር የታመነ ነው። በስሜቶቻችን ወይም በልምምዳችን አናምንም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል እናምናለን። እግዚአብሔር እንዳለው ጌታ ኢየሱስ ጽድቃችን ይሆን ዘንድ በመስቀል ላይ መሞቱ ብቻ ሳይሆን ቅድስናችንም ይሆን ዘንድ በውስጣችን ይኖራል። ስለሆነም ክርስቶስ ጽድቃችን ነው እንላለን። ክርስቶስ ሕይወታችንና ቅድስናችን እንደሆነ በስሜት አይሰማንም። ነገር ግን እርሱ ሕይወታችንና ቅድስናችን እንደሆነ እናምናለን። እግዚአብሔር ክርስቶስ ሕይወታችን እንደሆነ ተናግሯል፤ እኛም ክርስቶስ ሕይወታችን እንደሆነ እንናገራለን። እግዚአብሔር ክርስቶስ ቅድስናችን እንደሆነ አውጇል፤ ስለሆነም እኛም ክርስቶስ ቅድስናችን እንደሆነ እናውጃለን። እግዚአብሔር ክርስቶስ ድላችን እንደሆነ አውጇል፤ እኛም እንዲሁ ድላችን እንደሆነ እናረጋግጣለን። እግዚአብሔር ተናገረ እኛም የተናገረውን አመንን።

ሌላ እህት ደግሞ «ራስሽን ሰጥተሻል ወይ?» ብዬ ጠየቅኋት፤ እርሷም እግዚአብሔር ስላለ ራሷን እንደሰጠች ተናገረች። ምክንያቱም የእግዚአ ብሔር ቃል እንዲህ ብሏል፤ «እኔ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» ድልን ታውቅ እንደሆን ጠየቅኋት። ለዚህ የሰጠችኝ መልስ እርግጠኛ ስላል ሆነች አለኝ ብላ ለመናገር እንደማትደፍር ነበር። ስለዚህም በግልጽ ከእርሷ ጋር ተነጋገርኩ «እህቴ ክርስቶስ ሕይወትሽ እንደሆነ እግዚአ ብሔር ተናግሯል፤ ነገር ግን አንቺ ክርስቶስ ሕይወትሽ ሊሆንም፤ ላይሆንም እንደሚችል ትናገሪያለሽ። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድስናሽ ነው ብሏል፤ አንቺ ግን ቅድስናዬ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ትያለሽ። እግዚአብሔር ጸጋዬ ይበቃሻል ይላል፤ አንቺ ግን የእግዚአ ብሔር ጸጋ ሊበቃኝም ላይበቃኝም ይችላል ትያለሽ። በእርግጠኝነት አንዳችሁ ዋሽታችኋል። እግዚአብሔር ትክክል ከሆነ አንቺ ዋሽተሻል ማለት ነው። ወይም በተቃራኒው አንቺ ትክክል ከሆንሽ እግዚአብሔር ተሳስቷል ማለት ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ውሸታም ነው ብለሽ ለመናገር ትደፍራለሽ? እንግዲህ አንቺ ባልሽው ስንፈርድ የእግዚአ ብሔር ቃል የማይታመን እንደሆነ የገመትሽ አያስመስልሽምን? ብቅጽ

በት መልኳ ተለዋወጠ። በእግዚአብሔር ቃል ስለግምን እንደዚህ ዓይነት ሀሳብ የለኝም ስትል ካደች። በመጨረሻም ነገሬን ተረዳች።

እናንተንም ይህን እጠይቃችኋለሁ፣ ክርስቶስ ሕይወታችሁና ቅድስ ናችሁ እንደሆነ ባለግመን መወላወላችሁና መጠራጠራችሁ በደል እንደ ሆነ ይሰግችኋል? አጥብቄ አስገንዝባችኋለሁ እግዚአብሔርን ውሸታም እያረጋችሁት ነው።

ሌላዋን እህተም ራሷን ሰጥታ እንደሆነ ጠየቅኋት። መልሷ እንደሰ ጠች ነበር፣ ነገር ግን ድል ነበራትን? ጥቃቅን ችግሮች ስለነበሩባት ድል እንዳላገኘች ታውቅ ነበር።በዚያው ቅጽበት ውስጥ መልስ እንድሰጣት እንዲያስችለኝ እግዚአብሔርን ጠየቅሁ። ያልኳትም ይህንን ነበር። «አንቺ እምነት የለኝም ብለሻል፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ኃጢአት ሰርተሻል፣ ይህም ኃጢአት በቃሉ ያለግመን ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ክርስቶስ ሕይወትሽና ቅድስናሽ፣ ድልሽ ነው ብሏል። በተጨግሪም የእርሱ ጸጋ እንደሚበቃሽ ተናግሯል። ነገር ግን አንቺ አታምኚም፣ እንደ ቀላል ታጠፊዋለሽ። እህቴ እንድናገርሽ ፍቀጂልኝና ከባድ ኃጢአት ሰርተሻል። እንዲህ ብለሽ መጸለይ አለብሽ፣ እግዚአብ ሔር ሆይ በቃልህ አላመንኩም፣ በአንተ ላይ ኃጢአት ሰርቻለሁ፣ ይቅር በለኝ፣ የግያምነውን ደካግውን ልቤን ከእኔ ውሰድ፣ ከዚህ ኃጢአቴም አውጣኝ።»

አንድ ሰው የግያምን ከሆነ ትልቅ ኃጢአት ሰርቷል። የአለግመን ኃጢአት ከዝሙት ወይም ከነፍሰ ገዳይነት የባሰ ነው። ስለዚህም እንዲህ ብሎ መጸለይ አለበት፣ «እግዚአብሔር ሆይ እባክህ ይቅር በለኝ። በአንተ ላይ ኃጢአት ሰርቻለሁ፣ እባክህ ይህን የግያምን ደካግ ልብ ከእኔ ውሰደው።» ግንም ሰው በእግዚአብሔር ቃል ያለግመት ኃጢአት እንደ ሆነ ከተረዳ ፈጥኖ ወደ ድል ይሄዳል። እምነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ነው። እንደዚህ በመሳሰሉት «..ጸጋዬ ይበቃሃል...» /2ኛ ቆሮ 12:9/ ወይም «...ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።» /1ኛ ቆሮ 1:30/ ወይም «ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ...» /ቆላ 3:4/ በሚለው የእግዚአብሔር ቃል ታምናችሁ በእርሱ ተመላለሱ ሁሉም መልካም ይሆናል።

ምዕራፍ 7

የእምነት ፈተና

«በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከ ብር የተፈተነ እምነታችሁ...» 1ጴጥ 1:7

አሁን ደግሞ ወደ እምነት ፈተና እንሔዳለን። የእግዚአብሔር ቃሉች እንደሚነ ግሩን እምነት የሚፈተንበት ጊዜ የለም። እምነት የሚ ፈተንባቸው ምክንያቶች የሚ ከተሉት ናቸው፤

1ኛ እኛ እንድናድግ፡-

እንድናድግ እግዚአብሔር እምነታችንን ይፈትናል። ግንም ክርስቲ ያን እምነቱ ሣይፈተን ግደግ አይችልም። በዓለም ላይ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ እምነታቸው ተፈትኗል እንደዚህ በመናገሬ አልጠራጠርም። ምክ ንያቱም የእምነት ግደጊያው ብቸኛ መንገድ ሲፈተን ብቻ ነው። እኛን ወደ እድገት ለመምራት እግዚአብሔር ያለውን ብቸኛ መንገድ ተጠ ቅሟል። ይሽውም እምነታችን በፈተና ውስጥ እንዲያልፍ ፈቅዷል። ወደ እግዚአብሔር ቀርበን ጸጋን በእምነት እንቀበላለን፤ ስለሆነም እም ነታችን ሲፈተን እያደግን እንሔዳለን።

2ኛ የእግዚአብሔር ልብ እንዲረካ፡-

እግዚአብሔር እምነታችንን በፈተና የሚያስቀመጠው እኛን ለግሳ ደግ ብቻ ሣይሆን የራሱም ልብ እንዲረካ ነው። በዓለም ውስጥ ግንም ሰው በጌታ ካመነና የእግዚአብሔርን ጸጋ ከተቀበለ በኋላ እምነቱ ሳይፈ ተን የቀረ የለም። የፈተናው ምክንያት እምነቱ እውነተኛ እንደሆነ ለግ ረጋገጥ ነው። የእምነታችን እውነተኛነት ደግሞ የእግዚአብሔርን ልብ ያረካዋል። የተፈተነ እምነት የእግዚአብሔርን ስም ያከብራል። በምት

ፈተኑበት ምንም ዓይነት መከራ ስደት ወይም ተቃውሞ ወይም ጨለማ ካለማወላወል ካመናችሁ እግዚአብሔር ይከብራል።

3ኛ የሰይጣን አፍ እንዲዘጋ፡-

እግዚአብሔር እምነታችንን እንዲፈተን የሚያደርገው እንድናድግና የእርሱንም ልብ ለማስደሰት እንድንችል ብቻ ሳይሆን የሰይጣንንም አፍ ለመዝጋት ጭምር ነው። የእግዚአብሔር ጠላት በእግዚአብሔር አምነናል ስንል በጽናት ይቃወማል፣ በእምነት የተቀበልነውን ከመያዝ ሊያስቀረን ይጥራል፣ ሁልጊዜ ችግርንና ጥርጣሬን ወደ እኛ ይወረውራል። ነገር ግን እምነታችንን በመፈተን እግዚአብሔር አፉን ይዘጋዋል። በቀላሉ የምን ታደንለት አለመሆናችንን ሲያውቅ ጥሎ ይሸሻል። ቢቻለው በሰላም እን ዳንኖር የእግዚአብሔርም በረከቶች እንዳይኖሩን ለማድረግ ዘወትር ይሞ ክራል። አፉ እስኪዘጋ ድረስ አርፎ አይቀመጥም። የሰይጣንን አፉን ለመ ዝጋት እግዚአብሔር እምነታችንን መፈተን አለበት።

4ኛ ሌሎችን እንድንረዳ፡-

እግዚአብሔር እምነታችንን የሚፈትንበት ሌላው ምክንያት ሌሎችን ለመርዳት እንድንችል ሊያዘጋጀን ነው። እምነቱ ያልተፈተነ ሌሎችን ለመርዳት አይችልም። ሰዎች እርዳታን ሊያገኙ የሚችሉት እምነቱ ከተፈተነ ሰው ብቻ ነው። አንድ ሰው እንዳመነ ቢናገርም እምነቱ እስካል ተፈተነ ድረስ አስተማማኝ አይደለም። ነገር ግን በእርግጥ የተፈተነ እምነት ሰይጣንን አቅመቢስ አድርጎ ያስቀረዋል። ይህ አይነቱም እምነት ቤተክርስቲያንን ይጠቅማል። የተፈተነና የተረጋገጠ እምነት ከወርቅ የከበረ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። /1ጴጥ 1:7/

በተፈተነ እምነትና በድል መካከል ያለ ግንኙነት፡-

እምነታችን የሚፈተንበት ምክንያት እምነት በእርግጥ ምን እንደሆነ እንድናይ ነው። እውነተኛ እምነት ፀንቶ ይኖራል። ፀንቶ የማይኖረው ግን እምነት አይደለም። እውነተኛ እምነት ከቀናት ወይም ከወራት ወይ ንም ከዓመታት በኋላ እንዳለ ይቆያል። እውነተኛ እምነት ለአንዴም ሆነ

ለተደጋጋሚ ጊዜ እንቅፋቶችን መቋቋም ይችላል፤ ሰባት ጊዜም ቢፈተን እንዳለ ይቆያል። ችግር ሲያጋጥመው ሊቆይ የማይችል እምነት እውነተኛ እምነት አይደለም።

የእግዚአብሔር ቃሎች እንደሚያሳዩን ድል ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል በማመን ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወታችን፣ ራሳችን፣ ቅድስናችንና ኃይላችን እንደሆነ ተናግሯል። እኛም ሸክማችንን ሁሉ እንደተሸከመ ኃላፊነታችንንም ሁሉ እንደወሰደ ታጋሽና ሩኅሩኅ እንዳደረገን በውስጣችንም ድኃፍ እንደሚሆንን እናውቃለን። ጌታን አክብሩት፣ አመስግኑት።

ባሪ ጠዋት አንድ ወንድም እንዲህ አለኝ፣ «ራሴን ሰጥቻለሁ፣ እምኛለሁ ብዙ ድሎችን አግኝቻለሁ፣ ነገር ግን ትላንት ከቤተክርስቲያን ጉባኤ በኋላ ወደ ቤቴ በብስክሌት እየሔድኩ እያለ አንድ ትልቅ ሰው መታኝ፣ ከብስክሌቴም ወደቅኩኝ። በዚያን ጊዜ ምንም እንኳ አንድም ቃል ባልናገርም በውስጤ ግን በጣም ተቆጥቼ ነበር። ስለዚህ ነገር ምን ትላለህ? ራሴን ሰጥቻለሁ አለመቻሌን አምኛለሁ ክርስቶስም ድሌ እንደሆነ አምኛለሁ፣ ነገር ግን እቀጣለሁ ብዬ ባላሰብም ቁጣዬ ነደደ፣ ይህ ምንድነው? በቀላሉ ይህ የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው።

1ኛ ድል አደረግን ማለት ፍጹም ተለውጠናል ማለት አይደለም። ድል ስላለን እንደተለወጥንና እንደተሰጠን፣ ወደፊትም ለጥቂት ሳምንታትም ቢሆን ኃጢአት አንሠራም ብለን እናስብ ይሆናል፣ ባገኘነውም ድል በጣም መደሰትና እንዲያውም ስለተማካልን አዳዲስ ሙከራዎችን እንጀምራለን፣ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሊፈትነን ይፈልጋል፣ አለመለ ወጣችንንም እንድንረዳ እንድንወድቅ ይፈልጋል። ይህ ለተሻለ እድገታችን መጀመሪያ ነው። አዲስ ላገኘነው ታጋሽነት ምክንያቱ መለወጣችን ሳይሆን ከርስቶስ ለእኛ ታጋሽ ስለሆነ ነው። ራሳችንን እንደለወጥን ከቆጠርን ያለ ጥርጥር እንወድቃለን። ማወቅ ያለብን ታጋሽ መሆን የቻልነው ከርስቶስ ትዕግሥታችን ስለሆነ ብቻ ነው፣ ትሑት መሆን የቻልነው ከርስቶስ ትሕትናችን ስለሆነ ብቻ ነው። ቅዱስ መሆን የቻልነውም እርሱ ቅድስናችን ስለሆነ ብቻ ነው። ለብዙ ቀናት አሸናፊ ብንሆን እኛነታችን መቼም እንደበፊቱ ነው። እስከ መጨረሻው ራሳችንን ነን

ለአንድ ሰንበትም ቢሆን አንለወጥም። ዎች ማኒ ለዘለዓለም ዎች ማኒ ነው። ከሀምሣ ዓመት በኋላም እርሱ ዎች ማኒ ነው። ጌታን አመሰግ ነዋለሁ፣ አከብረዋለሁ። ድል ከርስቶስ ነው እንጂ ከእኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እኔ አሁንም ቢሆን ለኃጢአት የምሸነፍ ደካማ ነኝ።

በቺፎ (ቻይና ውስጥ) ያሉ አንዳንድ ሚሲዮናውያን መለወጥ ምንድ ነው ብለው ጠይቀውኝ ነበር። የእኔም መልስ እንዲህ የሚል ነበር፣ «መለወጥ በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ መሆን ነው፣ ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ባዶነት ነው። ይህ እውነት የሚሆነው ለጳውሎስ፣ ለጴጥሮስና ለዮ ሐንስ ብቻ ሳይሆን ለእኛ ለተራዎቹም ሰዎች ነው። ከእግዚአብሔር ጸጋ ከተለየን ከአሕዛብና ኃጢአታቸው ካልተወገደላቸው ሰዎች ያልተለየን ነን። ጸጋ ያገኘነው እኛ ስለተለወጥን ሳይሆን ከርስቶስ በእኛ ምትክ ስለ ሆነ ነው። በመዝሙር መጽሐፋችን ያለው ቃል ምንኛ እውነተኛ ነው፣ «ልቤ ከፍ ከፍ ሲል ለመውደቅ ምንኛ ቀርቢአለሁ» እናንተና እኔ አሁ ንም ቢሆን ያው እንደሆንን እስቲ በአእምሯችን ለዘለዓለም እንጠብቀው ፈጽሞ አልተለወጥንም።

2ኛ የሚታመነው የትኛው ነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ወይስ የእኛ ልምምድ? በልምምዶቻችን ማመኑና መተማመኑ ምንኛ ቀላል ነው። እንደእኛ ደካማ የተሸነፋና ቁጠኛ የሆኑ ሰዎች ድል ሊያገኙ አይችሉም ብለን እናስባለን። የዚህ ምክንያቱ ልምምዳችንን ስለምንመለከት የእግ ዚአብሔር ቃልም ውሸት እንደሆነ ስለምናስብ ነው። ነገር ግን እስቲ ልጠይቃችሁ፣ የሚታመነው የትኛው ነው የእግዚአብሔር ቃል ወይስ የእናንተ ልምምድ?

በቺፎ አንዲት እህት ልታየኝ መጣች። ራሷን እንደሰጠችና ከርስ ቶስም የእርሷ ድል እንደሆነ ማመኗን በእርግጠኝነት ትናገራለች፣ ነገር ግን ድሏ የማይጸና ለአንድ ሣምንት ብቻም የቆየ ነበር። ከአንድ ሣምንት በኋላ ሁለቱ ልጆቿ ተጣሉ። እሷም ልትታገሥ አልቻለችም። ባለፉት ሶስት ቀናት ፈጽሞ ድል እንዳልነበራት ነገረችኝ፣ እኔም ክርስቶስ ተለ ውጦ እንደሆነ ጠየቅኋት፣ አሁንም አልተለወጠም ብላ መለሰች። የእግ ዚአብሔር ቃልም ሆነ ከርስቶስ ሳይለወጡ እንዴት ድል የለኝም ማለት ቻለች? መልሷ ከዚህ በላይ እንደማትችል ነበር።

በዚህ ጊዜ አንድ ምሳሌ ተጠቀምኩ፤ እንበል ልጅሽ መንገድ ላይ ከአንድ ሰው ጋር ተገናኘ። ይህም ሰው እንዲህ አለው፤ «እንተ ወጣት እናትህ አንተን ከመድኃኒት ቤት በሃያ ሳንቲም ገዛችህ እንጂ አል ወለደችህም» እናም ልጅሽ ሮጦ ወደ ቤት መጣና ጠየቀሽ እንበል፤ «እናቴ ከአንቺ ተወልጃለሁ ወይስ ከመድኃኒት ቤት በሃያ ሳንቲም ገዛሽኝ? ይህን የጠየቅኹሽ አንድ እንግዳ ሰው በመንገድ ላይ አግኝቶኝ የተገዛህ ልጅ ነህ ብሎኝ ነው።»አንቺም ለልጅሽ እንዲህ ትይዋለሽ፤ «ልጄ አንተን የወለድኩህ እኔ ነኝ፤ ሰውዬው ያለህን አትመን።»

ልጅሽም ከአንቺ ይለይና እንደገና ሌላ ሰው ተገናኘ። ይህም ሰው ተመሣሣይ ነገር ተናገረው። በተጨማሪም በሽያጩ ጊዜ የኅይን ምስክር እንደነበረ ነገረው። ልጅሽም ስለዚህ ነገር ሊጠይቅሽ ወደ ቤት ተመለሰ። አንቺም ለልጅሽ «እስካሁን ቃሌን አላመንክም ማለት ነው? አሁንም እንደገና ልጅሽ ከቤት ወጣ። ያንኑ ሰው ተገናኘው፤ ሰውዬውም ልጅሽን እናትህን ጠይቀሃታል ወይ ብሎ ይጠይቀዋል፤ በተጨማሪም በመድኅኒት ቤት በተካሄደው ሽያጭ ቆን በሥፍራው እርሱ ብቻ ሣይሆን ሌሎች ወደ ሃያ የሚጠጉ ምስክር መሆን የሚችሉ ሰዎች እንደነበሩ ይነግረዋል። በመቀጠልም እንዲህ ብዬም ጠየቅኋት «በመጨረሻ ልጅሽ ግንን ያምናል? ምስክር የማያስፈልገውን የእናቱን ቃል ወይስ ብዙ ሐሰተኛ ማስረጃዎች ያሉትን የሰው ቃል? እንደገና ተመልሶ ወልደሽኛል ወይስ ገዝተሽኝ ነው ብሎ ቢጠይቅ አንተ ትንሽ ልጅ በእርግጥ ጅል ነህ ትይዋለሽ።

በተመሣሣይ ሁኔታ እህቴ ዛሬ እግዚአብሔር ሞኝ ልጅ ነሽ ይልሻል። ልጁን ለአንቺ የቅድስና ሕይወት መስዋዕት አድርጎታልና ተፈፀ መም ብሏል፤ በተጨማሪም በቃሉ ደግሞ ደጋግሞ ተናግሮታል፤ ነገር ግን አንቺ በተጠራጣሪነት እያደግሽ ሔድሽ እንዲህም ትያለሽ፤ «አንድ ችግር አለ፤ ላለመሽነፈ ማስረጃ ስላለኝ ነው። ምንም እንኳ እግዚአ ብሔር ልጁ ቅድስናዩ እንደሆነ ቢናገርም እኔ ግን ቅድስና እንደሌለኝ አረጋግጫለሁ» ትያለሽ።

እስቲ ልጠይቅሽ በአንቺና በምሳሌ ውስጥ ባነሳሁት ልጅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? አንቺ ብዙ ሐሰተኛ ምስክሮች ባሉት

በሰይጣን ውሸት አምነሻል እናም የእግዚአብሔርን ቃል አታውቂም ። አንድ ሰው በእርግጥ ሊያታልለው ወደ ልጅሽ ቢመጣ በእርግጥ ነው የምናገርሽ፣ ልጅሽ የሚመልሰው መልስ በጣም የሚታመነው በእናቱ ቃል እንደሆነና ሰውዬው ውሸታም እንደሆነ ነበር። ስለዚህ ልጅሽ ጠላቱን ሲያሳፍር አንቺን እናቱን ግን ያከብራል። እናም እነግርሻለሁ ሰይጣን ወዳንቺ ሲመጣና ትዝታዬ ድካምና ተሸናፊነት እንዲሰማሽ ሲያደርግ ግለት ያለብሽ እኔ ባለ ድል ነኝ፣ ክርስቶስ ድሌ ነው የሚለውን ቃል ነው። በውስጥሽ አለመረጋጋትን ለመፍጠር ቢመጣ አሁንም « እኔ ባለ ድል ነኝ፣ ክርስቶስ የኔ ድል ነው» ግለት አለብሽ። ይህን በማድረግ ሰይጣን የሚያደርገውና የሚለው ሁሉ ውሸት መሆኑን ታውጃለሽ፣ ምክንያቱም እውነት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው፣ ይህ እምነት ነው። እንዲህ ያለው የተፈተነ እምነትም የእግዚአብሔርን ስም ያስከብራል።

እግዚአብሔር እንዳለሽ በአፍሽ ብትናገሪ ነገር ግን ቢተፈተንሽ ጊዜ ወደ ቤት እያለቀስሽ ከሔድሽ እምነትሽ ወዴት አለ፣ እንዲህ ያለ እምነት ጊዜያዊ ነው ጥሩ እምነት ግን በፈተና ውስጥም በተሟላ ሁኔታ ያልፋል። ፈተና ባጋጠመሽ ቅጽበት ድል የለኝም ብለሽ ካልሽ አልቆልሻል ማለት ነው።

ፈተና ከፊትሽ በተጋረጠ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል የሚታመን ድጋፍ መሆኑን ብታውጂ በድል ትቆሚያለሽ። እግዚአብሔር የሚለው ሁሉ እውነት ነው፣ ቃሉም በሰማያት ጸንቶ ይኖራል። አሁን አንቺ የማንን ቃል ታምኛለሽ።

እምነት ባለበት ተራራው ይወገዳል

ተመሣሣይ ችግር ላለባት ሌላ እህት እንዲህ አልኋት ለፈተና የሚሸነፍ እምነት ሳይሆን «ተራራውን የሚያስወግድ እምነት ሊኖረን ይገባል።»/ማቴ 17:21: ማር 11:23: 1ኛ ቆሮ 13:2/ ተራራውን የሚያስወግድ እምነት ባለበት ችግር ሁሉ ተወግዶ ይሔዳል። እምነትና ተራራ አብረው አይኖሩም። የምናምነው በእንግዳው ቃል ነው ወይስ

በእግዚአብሔር ቃል፣ በፈተና የሚወድቅ እምነት ጠንካራ እምነት አይደለም።

አንድ ወንድም ድልን እንዳገኘ ያምናል፣ ነገር ግን ድል አይቶ አያውቅም። ሰይጣን ግን ተታለሃል ድል የሚባል ነገር የለም እያለ በሃሳብ ይዋጋዋል፣ ተታልያለሁ ካላችሁ አለቀላችሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚያደርግላችሁ እንደ እምነታችሁ ነውና።

በአንድ ወቅት እንዴት ታምሜ እንደነበር አስታውሳለሁ። አንድ ወንድም ሙቀቴንና የልቤን ምት ለካ። ሙቀቴ የጤነኛ ሰው አልነበረም የልቤም ምት ፈጣን ነበር። ለብዙ ምሽቶች ምንም እንቅልፍ የለኝም ነበር። ወደ ሞት ደጃፍ ተቃርቤ ነበር። በአንድ ምሽት ሰጸልይ ነበር፣ በሚቀጥለው ቀን ጠዋትም የኔታ ቃል መጣልኝ፣ ጸሎቴን ሰማ፣ ሮሜ 8:11ን ሰጠኝ። «ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።» በዚያን ምሽት በሰላም እተኛለሁ ብዬ አሰብኩ፣ ነገር ግን በዚያን ምሽት ብሶብኝ አደርኩ።

በሚቀጥለው ቀን ያው ወንድም የሰውነቴን ሙቀትና የልቤን ምት ሊለካ መጣ። ትኩሳቴ በጣም ጨምሯል፣ ልቤም በፍጥነት ይመታል። ሰይጣን በጣም ትጉህ ነበር። በፍጥነት የተሠጠኝ ቃል ኪዳን ምን እንደነበር ያሳየኛል፣ እግዚአብሔር እንደምድንና በእምነት እንደምነሳ ቢናገረኝም የሰይጣን የፈዝ ቃል ጥርጥር ዘራብኝ ነገር ግን በዚያን ቅጽበት እግዚአብሔር ከሁለት የበለጡ ቃሎችን ሰጠኝ፣ አንደኛው ዮናስ 2:9 «ከንቱነትንና ሐሰትን የሚጠብቁ ምህረታቸውን ትተዋል» ይህን ቃል የተናገረው ዮናስ በአሳ ሆድ ውስጥ እያለ ነበር። ሌላው ጥቅስ ዮሐ 17:17 «ቃልህ እውነት ነው...» እግዚአብሔር ቃሉ እውነት እንደሆነ ተናግሯል። ሌሎች ቃሎች ሁሉ ውሸት ናቸው።

የእግዚአብሔር ቃል እውነት ስለሆነ ኃይለኛ ትኩሣትና የልብ ምት ቢኖርብኝም እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ በኩል ተናግሮኛልና ፈውሴን አጠባበቅ ነበር። ስለዚህ በሮሜ 8፡11 ያለው ቃል አሁንም እውነት ስለሆነ ምንም እንኳን የሕመም ምልክቶች ቢኖሩብኝም እግዚአብሔርን

ስለሰጠኝ ቃልና ስለ ፈዋሽነቱ አመሰገንኩ። ከሰዓት በኋላ ትኩሣቴ ቀነሰ የልብ ምቴም ቀነሰ በዚያን ምሽት መተኛት ቻልኩኝ። ይህ የእምነት ፈተናና የተራራው መወገድ ነው።

ጽኑ የሆነ እምነት የሚደገፈው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው

ጽኑ እምነት ምንድነው? በእግዚአብሔር ቃል ብቻ የሚተማመን በራስ ልምምድ ስሜትና በአካባቢ ሁኔታ የማይደገፍ ነው። ልምም ዳችንና አካባቢያችን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከታረቁ ጌታን እናከ ብራለን፣ እናመሰግናለን። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ካልታረቁ ግን የእግ ዚአብሔር ቃል ብቻውን እውነት ሆኖ ይቆማል፣ ከእግዚአብሔር ቃል የሚቃረን ነገር ሁሉ ውሸት ነው። ሰይጣን እንዲህ እያለ በሐሳብ ሊዋጋን ይችላል። «እንዴት ድል አለኝ ማለት ትችላለህ?» አንተ ከዚህ በፊት ብልሹና ደካማ እንደነበርክ አሁንም ሆነህ ሳለህ ታዲያ ድል ወዴት አለ? ይሁን እንጂ ሰይጣን ወደ እናንተ የሚያሾከሹከው ሁሉ ውሸት ነው፣ የጌታ ቃል ብቻ እውነት ነው።

በቺፎ አንድ ትምህርት ተማርኩኝ፣ አንድ ቀን ከወይዘሮ ኤልሳቤጥ ፊስችባቸር ጋር ሆነን ስለ ስጦታዎች ስንጸልይ ነበር። እኔ ስለእምነት ስጦታ ስጸልይ እርሷ ደግሞ ስለ ፈውስ ስጦታ ስትጸልይ ነበር። ስጦ ታዎቹን እንደተቀበልን በማመን ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች ያህል ብቻ ጸለይን። ምሽት ላይ ወደ ቤተክርስቲያን ስብሰባ ሔድን። እህቴ ከስ ብሰባ አዳራሹ ስር ባለው ቤት ውስጥ የምትኖር አንዲት እህት አእምሮዋ ተናውጦ ማበዷን ነገረችኝ። ከዚህ በፊት በወር አንዴ ወይም ሁለቴ የአእምሮ መረበሽ ሁኔታ ታሳይ እንደነበረና አሁን ግን ለረጅም ጊዜ አእ ምሮዋ መረበሹን ነገረችኝ። ስብሰባው በአራት ተኩል ላይ አበቃ። ወደ ቤት እንደተመለስኩ ለዚያች አእምሮዋ ለተረበሸባት ሴት ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሳስብ ነበር። ከአንድ ወንድም ጋር ተጨዋውተን እንዳበቃን ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ቃል መጣልኝ። «በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ....

1ኛ ጴጥ 1:7 ለራሴ እንዲህ አልኩኝ «እምነቴ እንግዲህ አሁን ይፈተናል።»

በሚቀጥለው ቀን እህቴ ፊሰችባቸርን ለመፈለግ ሔድኩኝ። ነገሩን ብቻዬን ላደርገው እችል ነበር። ነገር ግን ትላንትና እርሷ የፈውስ ስጦታን ስለተቀበለች እኔ ደግሞ የእምነት ስጦታን ስለተቀበልኩ ሁለቱን በአንድ ላይ አድርገን መጠቀም ነበረብን። እህቴ ፈሰችባቸር አብረን እንድንሔድ እንደጋበዝኳት ስትሰማ ለመሔድ አመነታች። ስለዚህ ጉዳይ መጸለይ አለብኝ አለች። ከዳለየች በኋላ ከእኔ ጋር ለመሔድ ወሰነች። ስንደርስ በሽተኛዋ ተኝታ ነበር። ስለዚህ ሐኪሙ ዶርሺ፣ እስከምትነሣ እንድንጠብቅ ነገረን። በተጨማሪም በሰብዓዊ አስተሳሰብ ምንም ተስፋ እንደሌላት ነገረን። እህት ፈሰቺባቸር ደግሞ በአምስት ተኩል የመርከብ ጉዞ አለባት። ጥቂት ደቂቃዎች እስኪቀሩንና ግቡ እስከምንባል ቆየን።

ከበሽተኛዋ ጋር ጥቂት ቃላት ተለዋውጦኩ። ገፅታዋ ላይ የሚነበበው መረበሽ የአእምሮ ህመሟን ያመለክት ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ከጸለይኩ በኋላ ጌታ እምነት ሰጠኝ። በዚያ ቅጽበት እንደምትድን ተገነዘብኩ። እህት ፈሰች ባርም ለጥቂት ደቂቃዎች ከጸለየች በኋላ እሷም እምነት አገኘች። ስለዚህ እሷም ጌታን አከበረች። አብረው ያሉ ሁለት ወንድሞችና አንዲት እህትም ጸለዩ፣ ሆኖም በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ውስጥ አልነበሩም። እህት ፈሰችባር የምትሔድበት ሰዓት በመድረሱ ልንሸኛት ወጣን፣

በሽተኛዋን ልመለከት ከወደብ እንደተመለስኩ እያለቀሰችና እየሳቀች እየጮኸችም ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ራሷን ሳተች። ሁሉም የሚያደርጉት ጠፋባቸው። በዚያን ቅጽበት እምነት ሲፈተን ምን ማለት እንደሆነ ገባኝ። ዶክተር ዶርሺ እንደዶክተርነቱ መጠን ሊያደርግ የሚችለው ነገር ባለመኖሩ ወደ ደጅ ወሰደኝና በፍጥነት መጸለይ እንዳለብኝ አስተያየቱን ሰጠኝ እኔም መጸለዩ አስፈላጊ አይደለም አልኩ፣ ፈገግም እያልኩ ሰይጣን የሚችለውን እንዲሞክር ተፈታተንኩት። በሽተኛዋ አብዳ ነበር። እኔም ያበድኩ እመስል ነበር። እርሷ ለሶስት ሰዓት ተኩል ያህል ስትጮኽ ነበር። እኔም ደግሞ ለሶስት ሰዓት ተኩል ያህል ፈገግ

ስል ነበር። በዚያን ጊዜ በእርግጥ እምነቴ አድጎ ነበር። በአሥር ሰዓት ላይ ስብሰባ ስለነበረኝ መሔድ ነበረብኝ። ልሔድ ስል ለዶክተር ዶርሺ እንዲህ አልኩት፤ «አትፍራ ሌላም ነገር ለማድረግ አትሞክር። ሰይጣን ኃይሉን አስኪጨርስ ጠብቀው። እግዚአብሔር ያለው እርሱ ይከና ወናል፤ እግዚአብሔር እኛን አያታልለንምና።»

ምሽት ላይ ዶክተር ዶርሺ በሽተኛዋ እየተሻላት መሆኑን ነገረኝ። በሚቀጥለውም ጠዋት በፍጹም ጤናማ እየሆነች መምጣቷን ነገረኝ፤ ነገር ግን ደግማ እንደምትጮኽና እንደምትንፈራገጥ ይገባኝ ነበር። ምክን ያቱም የሌሎች ጥቂት ወንድሞችና እህቶች እምነት መፈተን ነበረበት።

ከሰዓት በኋላ በእርግጥም ስትጮኽና ስትንፈራገጥ ነበር። ዶክተር ዶርሺ ወደ እኔ መጣና ምን መደረግ እንዳለበት ጠየቀኝ። ለመጸለይ ተንበረከክኹኝ፤ ነገር ግን አንድም ቃል አልመጣልኝም ነበር። እምነቴም የሚነሣሣ አይመስልም ነበር። በዚያን ቅጽበት ሰይጣን እየተታ ነበር፤ እያፈዘም ጠላት እንዲህ ይለኝ ነበር፤ «ለምን እንደገና አትሥቅም? ትናንት ፈገግ ስትል ነበር፤ ዛሬስ ለምን ፈገግ አትልም?» እምነቴን ያጣሁ ይመስል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይከበር ይመስገን በውስጤ እንዲህ የሚል ድምጽ ነበር «ስሜትህ ከትናንትና ዛሬ ሊለወጥ ይችላል፤ ትናንት ፈገግ ማለት ችለህ ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ቅዝቃዜ ይሰማሃል። ነገር ግን እኔ ጌታ አልተለወጥኩም» የሚል ነበር። ለራሴም እንዲህ አልኩ፤ «በእርግጥ ጌታ አልተለወጠም።» ጌታንም በጣም አከበርኩት። «ጌታ ሆይ አንተ አልተለወጥክም» ትናንትና በእግዚአብሔር ቃል አመንኩኝ ይሁን እንጂ በዚያን ቀን የነበረኝ ፈገግታ እግዚአብሔርን ታማኝ ሊያደርገው አይችልም ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ቀዝቃዛ ስሜት አለኝ፤ ነገር ግን ይህም ቢሆን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ሊቀንሰው አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔርን አከበርኩት። ከዚያ ወዲያም አልጸለይኩም።

ምሽት ላይ ዶክተር ዶርሺ እንደሕክምናው ምርመራ ከሆነ በሽተኛዋ ፍጹም ጤናማ ልትባል እንደሚቻል ነገረኝ። በሚቀጥለው ቀን የፊቷ ገጽታ ሁሉ ጤነኛ እየሆነ ሔደ፤ ሃሌሉያ የእግዚአብሔር ቃል የሚታመን ነው። ይህ የእምነት ፈተና ነው።

ባመንን ቅጽበት ድል እንድናገኝ እንጠብቃለን፣ ነገር ግን እስቲ ልጠይቃችሁ፣ እግዚአብሔርን ለሶስት ሰዓታት ልታምኑት ትችላላችሁ? ለሶስት ሰዓታት ለሶስት ቀናት ለሶስት ወራት ልታምኑት ካለቻላችሁ እምነታችሁ ወዴት አለ? የተፈተነውን፣ የከበረውን፣ መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያ ምን አያፍርም። /ኢሳ 28:16/

አንድ ምሽት ላይ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን የገሊላን ባሕር ተሻግረው እንዲሔዱ አዘዛቸው፣ ድንገት ግን ታላቅ ነፋስ ተነሳ። ማዕበሉ ጀልባዋን ይመታት ስለነበር በመሙላት ላይ ነበረች። ጌታ ግን በጀልባዋ የኋላ ክፍል ተኝቶ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ቀስቅሰው እንዲህ አሉት "መምህር ሆይ ስንጠፋ አይገድህም?» ጌታም ተነስቶ ነፋሱን ገሰጸው ነገር ግን ከዚያን በኋላ ደቀ መዛሙርቱን ጌታ ምን አላቸው? በማርቆስ ወንጌል እንደተጻፈው ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። «እንዴትስ እምነት የላችሁም?» ማር 4-35:41 ይህ እንደሚያመለክተው ጥድፊያ የሞላባቸው ጸሎቶች ሁሉ ያለማመን ምልክቶች ናቸው። እምነት ቢኖራችሁ ጸንታችሁ ትኖራላችሁ። ጌታ ባሕሩን እንድትሻገሩ ያዘል። እርሱ ወደ ባሕሩ ስር ጠልቃችሁ እንድትሔዱ አላዘዘም። ምንም ነፋሱ በኃይል ቢነፍስ ማዕበሉ ምንም ከፍ ቢል ጀልባዋ ልትሰጥም አትችልም። ትን ሽም እምነት የሌላቸው ሰዎች እንቅፋት እንደገጠማቸው ወዲያውኑ ራሳ ቸውን ይደብቃሉ። ነገር ግን ትልቅ እምነት ፈተናውን ተቋቁሞ ይቆ ማል። የውሸት እምነት ሲፈተን ይወድቃል፣ ነገር ግን ቦሩ የሆነ እምነት በፈተና ውስጥ ሁሉ ይጸናል።

ከእምነት ጎን ቁም

በአንድ ወቅት አንድ ሰው እኔን መስደብ ጀመረ። እየታገስኩኝ በሔድኩ መጠን መሳደቡን ቀጠለ። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን እንዲህ ብዬ ጠየቅኹት፣ እግዚአብሔር ሆይ እባክህ ትዕግስትና ጥንካሬ ስጠኝ፣ አለበለዚያ ከቁጥጥሬ ውጭ ሆኜ እናደዳለሁ። ይህ ነገር ዛሬም ቢደገም አልፈራም፣ እንዲያውም እንዲህ እላለሁ፣ «ሰይጣን እኔን በጣም ለማበሳጨት ያንን ሰው ትጠቀምበት ይሆናል፣ ይሁን፣ እንጂ በውስጤ ያለውን ክርስቶስ ታበሳጨው እንደሆን ተመልከት» የሚሰድበኝን ሰው

አልጠላውም፤ እንዲያውም ላፈቅረው እችላለሁ። ይህ ከሆነ ጠላት ምን ሊያደርግ ይችላል? እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ድሉ ክርስቶስ እንጂ እኔ አይደለሁም፤ እኔ ብሆን ናሮ ያንን ያህል አታገሥና በመጨረሻ በንዴት እቀጣጠል ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ከሆነ ምንም ዓይነት ፈተና ለእርሱ አይበዛበትም፤ ምንም ዓይነት መከራ ለእርሱ አስቸጋሪ አይሆንም። በእግዚአብሔር ቃልና በእምነት ቁም፤ ሰይጣን ተሸናፊ ይሆን ልሃል። እግዚአብሔር ወደ ግዶ ተሻገሩ ስላለና ቃሉ ታማኝ ስለሆነ እንሻገራለን፤ እርሱ ለዘለዓለም ታማኝ ነውና።

አስቲ ይህን ጥያቄ በማጠቃለያዬ ላይ ላንሳባችሁ፤ በአንድ ወይም በሁለት ልማድ የሆኑባችሁ ኃጢአቶች ምክንያት ትፈራላችሁ? እንደዚያ ዓይነት ችግር ሊኖርባችሁ እንደሚችል እገምታለሁ። ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ በውስጣችሁ ያለው ክርስቶስ እንድትፈተኑ ሲፈቅድ በእርግጥ ፈተናውን እየተቀበለ ያለው ማነው? ይህን ዕድል ፍቀዱልኝ፤ በመንገዳችሁ ላይ የእምነት ፈተና በመጣባችሁ ቁጥር መገንዘብ ያለባችሁ ነገር በመፈተን ላይ ያላችሁት እናንተ ሳትሆኑ ጌታ ነው። እምነታችሁ ፈተናውን ማለፉ በተረጋገጠ ቁጥር ፈተናውን ማለፉ የሚረጋገጥለት የእግዚአብሔር ልጅ ነው። የተፈተናችሁት እናንተ ሳትሆኑ የእግዚአብሔር ታሪኝነት ነው። በእናንተ ላይ የሚመጣው ፈተና ሁሉ ክርስቶስ ምን ማድረግ እንደሚችል ለማረጋገጥ ነው። በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ቃል አንጻር በመቆም በአካባቢ ሁኔታና በስሜት ተጻራሪ በመቆም እምነት አላችሁ። ይህም ደግሞ በእውነት ድል ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ሰይጣን አንተ አሁንም ንጹሕ አይደለህም ሊል ይችላል፤ እናንተ ግን ክርስቶስ ቅድስ ነው ልትሉት ትችላላችሁ። ሰይጣን አሁንም አንተ ኩራተኛ ነህ ሊል ይችላል፤ እናንተ ግን ክርስቶስ ትሕትናዬ ነው ልትሉት ትችላላችሁ። ሰይጣን አሁንም ቢሆን አንተ ተሸናፊ ነህ ሊል ይችላል፤ እናንተ ግን ክርስቶስ ድሌ ነው ልትሉት ትችላላችሁ። ጠላት ምንም ነገር ቢላችሁ ሁልጊዜ መልሳችሁ ክርስቶስ ታማኝ የእግዚአብሔርም ቃል የሚታመን ነው፤ ይህ እምነት ነው፤ ይህም እምነት የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኝነት ይመሰክራል። ሃሌሉያ ክርስቶስ

አሸንፏል፤ ታማኝ ነው፤ እርሱ ቃሉም ለዘለዓለም የማይለወጥ ሆኖ ይኖራል።

አስታውሱ! የእምነት ፈተና ረጅም አይሆንም። በመጀመሪያ የድ ልን ጎዳና ባለፋችሁ ጊዜ በተለየ ሁኔታ ትፈተናላችሁ፤ አንዴ ግን እም ነታችሁ ከተፈተነ በኋላ ሌሎች ሰዎችን የምትረዱና የምትጠቅሙ ትሆ ናላችሁ። በዚህም የእግዚአብሔር ልብ ደረካል፤ ስሙም ይከብራል፤ የሰይጣን አፍም ይዘጋል፤ እርሱም በእናንተ ላይ ምንም ሊያደርግ አይችልም። እግዚአብሔር ይክበር፤ የእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ነው። እግዚአብሔርን አመስግኑት። እናንተ በእግዚአብሔር ፊት ስትቆሙ በእናንተ ፊት ምንም ነገር ሊቆም አይችልም። በእምነት ስትቆሙ ሊወ ገድ የማይችል ተራራ አይኖርም፤ ምክንያቱም እምነት ተራራን ሊያስ ወግድ ያለ ነገር ነውና። በመንገዳችሁ ላይ ተራራ ቢኖር በእርግጥ መወገድ አለበት።

ምዕራፍ 8

ማደግ

«በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።» ዮሐ 17፡17

በውይይታችን ከመግፋታችን በፊት እስካሁን የተነጋገርናቸውን እንከልስ። እንደተመለከትነው የእኛ ልምድ ተከታታይነት ያለው ሽንፈት ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ ላከርስቲያኖች ያዘጋጀው ሕይወት ከልምዳችን በጣም የራቀ ነው። እግዚአብሔር ያዘጋጀልን አዘናፊ ሕይ ወት ክርስቶስ ነው። የእኛ አዘናፊነት የትግል፣ የጸሎትና የመሳሰሉት መን ገዶቻችን ሁሉ ውጤታማ አይደሉም። በተጨማሪም አምስት የድል ሕይ ወት ባህሪያት ተመልክተናል። ወደዚህ የድል ሕይወት ለመግባት መንገዱ በጣም ቀላል ነው። ይህም ራስን መስጠትና ማመን ነው። እግዚአብሔር የእርሱ ጸጋ ለእኛ በቂ እንደሆነ ተናግሯል፡ ስለሆነም በቂ ነው። እግዚአብሔር ክርስቶስ ሕይወታችን እንደሆነ አውጇልና እርሱ ቅድስናችን ነው። በተጨማሪም እምነት እግዚአብሔር የሠራውን ነገር ለግረጋገጥ እንደሚረዳን ተመልክተናል። ይሁን እንጂ እንደዚህ ያለ እምነት በፈተና ውስጥ ግለፍ አለበት።

አሁን ደግሞ ስለግደግ ከድል ጋር በተገናኘ መልኩ እንመለከ ታለን። በእርግጥ እንዴት እናድጋለን? ምናልባት ከላይ ያሉትን መልእ ክቶች ከተቀበልን በኋላ በድል ጎዳና ካለፍን ሕይወታችን ግደግ ካለበት የመጨረሻው ደረጃ ላይ ደርሷል ብለን እንደመድም ይሆናል። ይህ የተ ሳሳተ አስተሳሰብ ነው። በእርግጥ ድል ውስጥ ከገባን በየዕለቱ ምን ግድ ረግ እንዳለብን መነጋገር አለብን።

1. የሚፈታተነንን ኃጢአት ማሸነፍ

ብዙ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ድላቸው እንደሆነ አውቀው ወደ ድል የሚመራቸውን መንገድ ከጀመሩ በኋላ እንዴት እንደሚጠብቁት

አያውቁም፣ ስለሆነም እንደገና ይወድቃሉ። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ክርስቲያን ድልን ካገኘ በኋላ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከሚፈታተነው ኃጢአት እንዲያወጣው መጠበቅና ሲያወጣውም ማየት አለበት። /ዕብ 12፡1 ተመልከት/

የድልን መንገድ ጀምሮ ኃጢአትን መለማመድን የቀጠለ ግንም የለም። ጌታ እንዴት ነፃ አውጥቶሃል፣ እርሱ አሸናፊ ሕይወታችሁ ነው። ስለዚህ እንዲህ ትጸልዩ ይሆናል፣ «እግዚአብሔር ሆይ አንተን አመሰ ግንሃለሁ አከብርሃለሁ የክርስቶስ ድል ድሌ ነው የክርስቶስ ቅድስናም የእኔ ቅድስና ነውና።» በውስጣችሁ የሚኖረው ክርስቶስ ስለሆነ የቁ ጡነት ባሕሪይ ሊኖራችሁ ቁጡነታችሁ ተወግዷል። ባለማመን ወይም በወረኝነት ወይም በፊት ከጠቀሰናቸው ስምንት ኃጢአቶች በአንዱ ብትቸገሩ እግዚአብሔር እንዲያስወግድላችሁ ጠይቁ። ወደ ድል በገባ ችሁ ቅጽበት ለጌታ እንዲህ ማለት አለባችሁ:- «ጌታ ሆይ ይህን የተለየ ኃጢአት እንደምታሸንፍ እጠብቅብሃለሁ።»

በእርግጥ የተለየ ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ኃጢአቶች አሉ። ለምሳሌ በአንድ ሰው ላይ ኃጢአትን የሠራችሁ ቢሆን ወደ እርሱ ሔዳ ችሁ ይቅርታ መጠየቅ አለባችሁ። በፊት ይቅር በለኝ የማለቱ ድፍረት አልነበራችሁም። አሁን ግን የማለቱ ድፍረት አላችሁ ወይም ቀድሞ በአንድ ነገር ታስራችሁ ይሆን ይሆናል። አሁን ግን ክርስቶስ በውስጣ ችሁ ስላለ ነፃ መውጣት አለባችሁ። ማንኛውም ሰው አሸናፊ ሕይወትን ባገኘ ቅጽበት ከሚለማመደውና ከሚፈታተነው ኃጢአት እግዚአብሔር ነፃ እንዲያደርገው መጠበቅ አለበት።

አሸናፊን ሕይወት ከግማሽ ታችሁ በፊት የመዋጋቱ ብታት አልነበ ራችሁም። አሁን ግን ያንን ሕይወት በመያዛችሁ የማሸነፍ ብቃት አላ ችሁ። አሁን ለማሸነፍ እምነት አላችሁ።

አንዳንድ ሚሲዮናውያን እንዲህ እያሉ ይጠይቁኝ ነበር:- አንድ ሰው አንዴ በድል ውስጥ ከገባ ምንም ኮርነት አይኖርበትም ማለት ነው? የእኔ መልስ እንዲህ ነበር:- ለድል ትዋጋላችሁ ወይስ ከድል በኋላ ተዋ ጋችሁ? ለድል ከተዋጋችሁ ፈጽሞ አይሳካላችሁም። ከድል በኋላ ከተዋ ጋችሁ ግን ትክክለኛ መንገድ ላይ ናችሁ።

ብዙዎች ሁልጊዜ ለድል በከፍተኛ ጥረት ይጋደላሉ ነገር ግን በአብ ዛኛው መጨረሻቸው ሽንፈት ነው። ምክንያቱም ድል በሰዎች ጥረት አይ ገኝም። ድል ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ ላይ የተመሠረተና ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። ጌታ ቅድስናችሁ ትክክለኛነታችሁና ድላ ችሁ እንደሆነ አምናችኋል። በውጤቱም እነዚህ ኃጢአቶች ሁሉ መወ ገድ አለባቸው። «የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል።» ማቴ 15:13

በዚህ ጉዳይ ላይ ከአንድ ወንድም ጋር ስንነጋገር አንድ ምሳሌ ተጠ ቀምኩ:- እንበልና አንተ አንድ መሬት ገዛህ። ሻጩ የመሬቱን ርዝመትና ወርድ የሚያመለክተውን ውል ሰጠህ። ባለንብረትነትህን ልታረጋግጥ ወደ መሬቱ ስትሔድ ያልታወቁ ሰዎች በመሬቱ ላይ የመኖርያ ቤታ ቸውን ሲሰሩ ታገኛቸዋልህ፣ እንግዲህ ምን ታደርጋለህ? በውሉ ላይ በተ ጻፈው መሠረት እነዚህን ያልታወቁ ሰዎች ታስነሳለህ። ከኃጢአት ጋር ያለን ውጊያችንም እንደዚሁ ነው። በራሳችን ኃይል አንዋጋም እግዚ አብሔር በሰጠን ሥልጣን እንዋጋለን። እውነት ነው መጽሐፍ ቅዱስ መዋጋት እንዳለብን ይነግረናል። ነገር ግን የምንዋጋው በእምነት ነው ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ጠላትን ማሸነፍ አለብን ሲል በእምነት እናሸን ፋለን ማለቱ ነው። ጠላትን የምንቋቋመው በእምነት ጋሻ ነው። /ኤፌ 6:6/

እስቲ ልጠይቃችሁ ቁጠኝነታችሁ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ አለን? አለማመናችሁ፣ ወሬኛነታችሁ ወይም ማንኛውም የሚፈታተናችሁ ኃጢ አት በክርስቶስ ውስጥ አለን? እኔና እናንተ እንደምናውቀው ይህ ሁሉ በእርሱ ውስጥ የለም። እነዚህ የክርስቶስ ካልሆኑ እንዲወገዱ ልታዛቸው ትችላለህ። እስከ ድል ድረስ ልትዋጓቸው ካሰባችሁ ያለጥርጥር ትወድቃ ላችሁ። ነገር ግን የምትታወሙትና የምትዋጉት ድልን ስለያዛችሁ ከሆነ ሁልጊዜ ድል ትነሣላችሁ። ስለሆነም ዋናው ጥያቄ ይህ ነው:- ድልን ለማግኘት ትዋጋላችሁ ወይስ ድልን ስላገኛችሁ ትዋጋላችሁ? ድልን ስላገኛችሁ የምትዋጉ ከሆነ እንዲህ ትጸልያላችሁ። «እግዚአብሔር ሆይ አንተን አመሰግንሃለሁ፣ አከብርሃለሁ ክርስቶስ አንድ ጊዜ አሸንፎል ናል፣» እርሱ ስላሸነፈ እነዚህ ኃጢአቶች ሁሉ ይወገዳሉ። ማንኛውም

ክርስቲያን አንድ ጊዜ በድል ጎዳና ካለፈ ክርስቶስ ሕይወቱ ስለሆነ የተለየ ኃጢአቱ እንዲወገድ ማመጅ አለበት። የሚታገላችሁ ኃጢአት በትንሽ የእምነት ግፊት ይወገዳል፤ ይህ ድል ይባላል።

2. ድክመታችንን ተቀብለን ክርስቶስ ሁሉ በሁሉ እንደሆነ ማመን

በየቀኑ ያለው ሕይወታችሁ መጀመሪያ የድልን ጎዳና እንዳለፋችሁ ከክፉራችሁ ሕይወት መመላለስ አለበት። ጠዋት ጠዋት ስትነሱ እንዲህ ትጸልያላችሁ፤ «እግዚአብሔር ሆይ እኔ ምንም የማልችል ልጅህ ነኝ። ራሴን መለወጥም አልችልም። በዚህ ቀን ውስጥም ሁለ ፣ተናዬን አንተ እንድትወርስ አምናለሁ፤ አከብርሃለሁ፤ አመሰግንሃለሁ። የሚደረግልኝ ሁሉ በልጅህ በኩል በተገለጸው ጸጋ ነው።» አሁንም ሌሎች ልትሰ ጪቸው የሚገቡ ጥቂት ነገሮች አሉ። እነዚህን ደግሞ ከዚህ በታች እናያለን።

ሁለት ዓይነት ፈተናዎችና እነርሱን የመወጫ መንገዶች

ከዚህ በፊት በብስክሌት ሲጋልብ ተመቶ ስለወደቀው ወንድም የተነ ጋገርነውን ታሪክ እስቲ እናስታውስ። በንዴት ውስጥ ሆኖ በሚጋልብበት ሰዓት የማሰቢያ ጊዜ አግኝቶ ቢሆን ናሮ ንዴቱን መቆጣጠር ይችል ነበር። ነገር ግን የደረሰበት ነገር ለማሰቢያ ጊዜ አልሰጠውም። በየቀኑ የሚያጋጥሙን ፈተናዎች ሁለት ዓይነት ናቸው አንደኛው ዓይነት ፈተና የሚመጣብን ድንገት ሲሆን ለማሰቢያም ጊዜ አይሰጠንም። ሌላኛው ዓይነት ፈተና የሚመጣብን ቀስ ብሎ ሲሆን እያደገም ይሔዳል። ጊዜ የማይሰጠንን ፈተና ከመወጣት ጊዜ የሚሰጠንን ፈተና መወጣት እንደ ሚቀል እንስማማለን። ይህን በተመለከተ አንድ ጊዜ የድልን ጎዳና ካለ ፍን እነዚህን ሁለት ነገሮች በሚመለከት ሁልጊዜ ጠዋት መጸለይ ይገባ ናል፤ አለበለዚያ ልንወድቅ እንችላለን።

በመጀመሪያ ለጌታ እንዲህ ማለት አለብን:- «ጌታ ሆይ ለማሰቢያ ጊዜ በማይሰጡኝ ፈተናዎች በምፈተንበት ጊዜ እባክህን ኃጢአት እንዳ ልሠራ አድነኝ።» ጌታም ከእንደዚህ ዓይነት ድንገተኛ ፈተናዎች አንድን ወጣ ይረዳናል። እንደዚህ ዓይነት ጸሎት ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነው። ብዙ ነፍሳትንም አድኗል።

ሮሜ ምዕራፍ አምስትን በሙሉ ለመመልከት ጊዜ አይኖረንም። በዚህ ቦታ በክፍሉ ላይ ጥቂት አስተያየቴን እሰጣለሁ። ሮሜ 5:12–19 ከክርስቶስ ጋር ያለን ሕብረት ከአዳም ጋር ካለን ሕብረት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ያስተምረናል።

ቀድሞ ኃጢአት ሠራን ምክንያቱም ከአዳም ጋር አንድነት ስላለን ነው፤ አሁን ግን ጽድቅን እንለማመዳለን ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር በሕብረት ተገናኝተናልና። እንደምናውቀው በትንሽ ጸብ የብዙዎች ቁጣ ይነዳል። ከአዳም ጋር ባለን አንድነት ምክንያት ትዕግሥታችንን የማጣቱ ነገር በአብዛኛው ተፈጥሮዓዊ ነው። ከአዳም ጋር ባለን ሕብረት በበኩላ ችን ምንም ጥረት ወይም ድካም ሳናደርግ ኃጢአትን ለንድንሠራ ያደርገ ናል። ይህ እግዚአብሔር በክርስቶስ ቃል ከገባልን ሕይወት ጋር ተመሳ ሳይነት አለው። ለጌታ እንዲህ ማለት አለባችሁ:- «በፊት ከአዳም ጋር ሕብረት ስለነበረኝ ምንም ጥረት ሳላደርግና ብዙም ሳልጨነቅበት ኃጢ አት አደርግ ነበር። ዛሬ ደግሞ ያለ ብዙ ድካም ታጋሽ፣ ትሑት፣ ሌላም ነገር መሆን እችል ዘንድ በክርስቶስ ውስጥ አለሁ። ጌታ ሆይ እንዳስበው ጊዜ ባይኖረኝም እንኳ ከክርስቶስ ጋር ያለኝ ሕብረት ጥልቅ ስለሆነ አመሰግንሃልሁ፤ አከብርሃለሁ፤ ስለሆነም ዛሬ ወደ እኔ ፈተና ሲመጣ እንዳስብበትም ሆነ እንድቃወመው ጊዜ ባይሰጠኝም አንተ አንድ ጊዜ ከብርህን፣ ቅድስናህን፣ ድልህን በውስጤ ገልጸሃል።»

በዚህ መልኩ በእግዚአብሔር ፊት ብትቆሙ ያህን የመጀመርያውን ዓይነት ፈተና ትወጣላችሁ። ጠዋት ስትነሱ ለማሰቢያ ጊዜ ከማይሰጣችሁ ፈተና እንደሚያድናችሁ በእግዚአብሔር ታመኑ። በጠዋት ስትነሱ እና ንተ ባታውቁትም እንኳ የክርስቶስ ሕይወት በውስጣችሁ ድልን እንደሚ ያስቀምጥ እመኑት። ስለዚህ ዋናው ጥያቄ የእምነት ጉዳይ ይሆናል።

እናንተ ካመናችሁ የእግዚአብሔር እውነታዎች በሕይወታችሁ ይፈጸማሉ።

በድንገት የማይመጣውንና ይልቁንም ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደ የሚመጣባችሁን ፈተና በሚመለከት ምን ማድረግ አለባችሁ? ውስጣችሁ ሳይቆጣ በቀላሉ እርሱት። ሁሉም ነገር በክርስቶስ ላይ አማክሉ የሚመጣ ነው። በራሳችሁ ደካሞችና ሁለተናችሁን መለወጥ የማትችሉ ናችሁ። ለመቋቋምም ኃይሉ የላችሁም፤ ወደፊትም አትችሉም፤ በፊትም እንደ ማትችሉ ሁሉ አሁንም አትችሉም። ዝም ብላችሁ ራሳችሁን ቀና አድርጉና በጸሎት ጌታን ተመልከቱት፤ እርሱ እንደሚችል አስቡ ምክንያቱም እርሱ ደካማ አይደለም፤ በእናንተ ውስጥም ኃያል ነው። በዚህ አቋም ሁኑ፤ ፈተናውም ይወገድላችኋል፤ ለመቃወምና ለመቋቋም ብትሞክሩ ፈተናው ሊወገድላችሁ የማይፈልግ ይመስላል። ነገር ግን እኔ አልችልም እግዚአብሔር ግን ይችላል ብትሉና እናንተ ደካማ ጌታ ግን ኃያል መሆኑን ብታምኑ ፈተናው በፍጥነት ይወገዳል።

ጻድቅ በእምነት ይኖራል

አንዳንድ ወንድሞች ወደ ድል የሚያመራውን ጎዳና ካለፍን ኃጢአት እንሠራለን ወይ ብለው ሰለቀኝ። የእኔ መልስ ቀስ በቀስ ወደዚያ ደረጃ መድረስ እንዳለብን ነው ይሁን እንጂ በኃጢአት የመውደቁ አጋጣሚ ሊኖረን ይችላል። ምን ዓይነት ኑሮ ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የሚያመለክቱን? የክርስቲያን ሕይወት በእምነት እንደሆነ ይገልጽልናል። «ጻድቅ በእምነት ይኖራል።» ሮሜ 1:17

በፊታችን ሁለት መንግሥታት አሉ። አንደኛው ቁሳዊ ዓለም ሲሆን ሌላው ደግሞ መንፈሳዊው ዓለም ነው። በአምስቱ ሕዋሳቶቻችን በመጀመሪያው ዓለም ውስጥ እንኖራለን በእምነታችን ግን በሁለተኛው ዓለም ውስጥ እንኖራለን። ራሳችሁን ስራሳችሁ መስፈርት ብትመለከቱት ወኒያውኑ የምታዩት ሌላው ዓለም እንደሆነ ሁሉ ኃጢአተኛ መሆናችሁን፤ ኩራተኛ መሆናችሁን፤ ያልክዳችሁ መሆናችሁን ትመለከታላችሁ። ነገር ግን ራሳችሁን በእምነት በክርስቶስ ውስጥ ስትመለከቱት ተናዳጅነታችሁና አስቸጋሪነታችሁ ሁሉ እንደተወገደ ትገነዘባላችሁ። ዛሬ ችግሩ

በየቀኑ ከሁለቱ ዓለማት መምረጡ ነው። እኛ ሰዎች ሁለንተናችን ተጠራ ጣሪዎች፣ ስሜታውያን፣ በራሳችን መወሰን የምንፈልግ ነን። ፈቃዳችን ከሁለቱ አንዱን ዓለም ለመምረጥ ነፃ ነው፣ እናም በመረጥነው በአንዱ ዓለም ውስጥ እንኖራለን። በአምስቱ ስሜቶቻችሁ ላይ ከተማመ ናችሁና በቁሳዊው ዓለም ከኖራችሁ ይህንን ዓለም በሕይወታችሁ ውስጥ ታንጸባርቃላችሁ፣ ነገር ግን በእምነት በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ከሆና ችሁ መንፈሳዊውን ዓለም በሕይወታችሁ ታንጸባርቃላችሁ። በሌላ አነጋ ገር የምትመሩት በአእምሮዓችሁ፣ በስሜታችሁና በራሳችሁ ፈቃድ ከሆነ በቀጥታ በአዳም ውስጥ ትኖራላችሁ፣ ነገር ግን በእምነት ከተመራችሁ ፈጥናችሁ በክርስቶስ ትኖራላችሁ፣ በክርስቶስም ብትኖሩ በእርሱ ውስጥ ያለው ሁሉ የእናንተም ልምምድ ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ግጥሩትን ዶክትሪን አያስተምርም። ይሁን እንጂ እንደ እግዚአብሔር ሥራ፣ ደንብና ትእዛዝ ማንኛውም አማኝ ኃጢአት መሥራት የለበትም። በየቀኑ ክርስቶስን ማዛየት ይገባ ናል፣ እናም በየቀኑ ከአሸናፊዎች በላይ መሆን አለብን። ምንም ይሁን በስሜታችን በኖርን ቅጽበት እንወድቃለን። በምትኩ በየቀኑ በእምነት ስንኖር በክርስቶስ ያለውን ሁሉ በእኛም እናረጋግጣለን።

ከውድቀት በኋላ በፍጥነት በደሙ መታደስ

ሳናስበው ብንወድቅ ምን ማድረግ ይገባናል? በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን በአንድ ጊዜ ኃጢአታችንን በክርስቶስ ውድ ደም ስር ጥለን ይሆናል። በመቀጠልም ምናልባት ወደ ሰማያት እያየን እንዲህ ብለናል:- «እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሐለሁ:- አከብርሃለሁ:- የአንተ ልጅ አሁንም ሕይወቴነው። ቅድስናዬም ነው፣ እናም ልጅህ የድል ሕይወቱን በውስጤ ማሳለፍ አለበት።» በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ መታደስ እንች ላለን። ለአምስት ደቂቃ ሆነ ለአንድ ሰዓት መቆየት አያስፈልገንም። እግ ዚአብሔር አንዴ ይቅር ብሎናል። ከኃጢአታችንም አንጽቶናል፣ ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ትንሽ መሰቃየትና መቀጣት እንዳለብንና ኃጢአታችንም ከዚያ በኋላ ምናልባት ይቅር ይባል ይሆናል ብለን እናሰባለን፣ ይህ

በራሳችን ላይ ችግር መፍጠር ነው። ይህ አሁን ዘለሚት መኖር ነው፤ ደግሞም በአዳም ውስጥ መኖር ነው።

ከድል በኋላ የክብሩን ደም ግንጻት የሚጠይቁ ውድቀቶች ይኖራሉን? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። ይህን ጥያቄ በሚመለከት በመጀመሪያ ከድል በኋላና ከድል በፊት ባሉት ጊዜያት መካከል ያለውን ልዩነት ምን እንደሆነ መጠየቅ አለብን። ይህን ግለት እወዳለሁ፤ የኃላ ልዩነት አለ የድልን ጎዳና ከግለፋችን በፊት ሕይወታችሁ የተሸነፈ ነበር። ያኔ አልፎ አልፎ አሸናፊዎች ሆናችሁ ይሆን ይሆናል፤ ነገር ግን ሽንፈት ወጋችሁ ነበር። ነገር ግን የድልን ጎዳና ካለፋችሁ በኋላ ሕይወታችሁ ባለ ድል ሆኗል። ዛሬ በእርግጥ አንዳንዴ ትወድቁ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ እናንተ ሁልጊዜ አሸናፊ ናችሁ። ቀድሞ ብዙ ጊዜ ሽንፈቶች ነበሩ፤ ድሎች ግን በጣም ጥቂት ናቸው። አሁን ግን ጥቂት ሽንፈቶች ቢኖሩ ብዙ ድሎች ይኖሩናል። በፊት ሽንፈት ሕግ ነበር። ሁልጊዜ ቁጡ ነበራችሁ፤ ሀሳባችሁ ሁልጊዜ ያልነፃ ነበር። አመለካከታችሁ ሁልጊዜ የከፉ ነበር፤ ተፈጥሮአችሁ ሁልጊዜ ቀናተኛ ነበረ። በአብዛኛው በእነዚህ ኃጢአቶች ታስራችሁ ነበር፤ አልፎ አልፎ ከምታገኙት ድል በስተቀር። ነገር ግን አሁን ድልን አግኝታችኋል፤ ውድቀታችሁ በተደጋጋሚ አይደለም። ዛሬ ብትወድቁም በቋሚነት የኃጢአት ቀንበር የታሠራችሁ አይደላችሁም።

ከድል በፊት ውድቀት ሲያጋጥማችሁ ትደናገሩ ነበር። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ሕብረትና ብርሃን ባላችሁ ሕብረት እንዴት እንደምትታደሱ አታውቁም ነበርና ነው። ለመውጣት የማትችሉት ታላቅ ተራራ እንደ መውጣት ያህል ይታያችሁ ነበር። ከድል በኋላ ግን ከውድቀታችሁ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ልትታደሱ ትችላላችሁ። ፈተናችሁ ኃጢአታችሁን ትናዘዛላችሁ፤ ወዲያው በውድ ደሙ በአንዴም ትነፃላችሁ፤ እግዚአብሔርን ማመስገንና ማክበር ትችላላችሁ ምክንያቱም ክርስ

ቶስ የራሱን ድል በሙስጣችሁ እንደገና ስለሚያስቀምጥ ነው። ይህ ነው በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት።

በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር ትክክለኛ ሕብረትን መጠበቅ

«....ምስክሩ ይህ ነው፣ ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።» /1ዮሐ 5:12/ ይህ አሸናፊ ሕይወት ለእኛ እንዴት ተሰጠን? ይህ የሆነልን በልጁ ነው። ከልጁ ውጭ ምንም ዓይነት አሸናፊ ሕይወት አይኖረንም። ልጁ ያለው ሁሉ ሕይወት አለው፣ ልጁ የሌለው ሁሉ ግን ሕይወት የለውም፤ እግዚአብሔር ሕይወቱን የሰጠን በቀጥታ አይደለም። ይህን አሸናፊ ሕይወት ለመቀበል የቻልነው በልጁ ነው። ስለዚህም ሕይወቱን ለማግኘት የእግዚአብሔርን ልጅ መቀበል አለብን። ከክርስቶስ ጋር ያለው ሕብረት በደከመ ጊዜ ሕይወታችንን ችግር ያጋጥመዋል። በክርስቶስና በተሰፋው ቃል ታማኝነት ላይ በተጠራጠርን ቅጽበት በሕይወታችን ውድቀት ያጋጥመናል። እግዚአብሔር ትዕግሥትን፣ ክብርን፣ ታዛዥነትን አልሰጠንም፣ ነገር ግን ይህን ሁሉ በልጁ ውስጥ ሰጥቶናል። ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ያለን ሕብረት ጤናማ ካልሆነ፣ ድላችንን በፍጥነት እናጣለን። ስለዚህ በየቀኑ ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት መጠበቅ አለብን።

በየቀኑ ለጌታ እንዲህ እንበለው:- «ጌታ ሆይ አንተ አውንም የእኔ ራስ ነህ፤ እኔም የአንተ የአካል ክፍል ነኝ:- አንተ ሕይወቴና ቅድስናዬ ነህ።» ዓይኖቻችሁን ከክርስቶስ ላይ አንስታችሁ ወደ ራሳችሁ ከተመለከታችሁ እነዚህ እውነታዎች ይጠፉባችኋል። ነገር ግን ዓይኖቻችሁ በክርስቶስ ላይ ከተጣበቁ እነዚህን እውነታዎች በሕይወታችሁ ትለማመዳላችሁ፤ እምነት ማለትም ይህ ነው። ከክርስቶስ ውጭ ቅድስና፣ ድል፣ ታጋሽነት፣ ትሕትና ሊኖራችሁ አይችልም ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ካላችሁ ቅድስና፣ ድል፣ ታጋሽነት ታገኛላችሁ። አንድ የቻይናዎች ምሳሌ እንዲህ ይላል:- «ለአረንጓዴው ተራራ ተጠንቀቁለት፣ እንዲህ ከሆነ ለማገዶ የሚሆን እንጨት አታጡም።» በምሳሌው አነጋገር እግዚአብሔር እንጨት አልሰጠንም፣ እርሱ አረንጓዴውን ተራራ ሰጥቶናል፣ እርሱ ክርስቶስ ነው። ይህ ተራራ እስካለ ድረስ የቅድስና፣ የታጋሽነቱ፣

የትሕትናው የሌሎቹም ስጦታዎች ይኖራሉ፤ የእኛም ይሆናሉ፤ በየቀኑ ሕይወታችንም እንለማመዳቸዋለን። ለብዙ ክርስቲያኖች ውድቀት ምክንያቱ በእምነት ከመኖር ይልቅ በስሜት ስለሚኖሩ ነው።

ሽንፈት የሚከሰተው የቀድሞው ልምዳችን የማይታመን ስለሆኖ ሳይ ሆን እምነት ሲጠፉ ነው። ክድል በኋላም መውደቅ አለብን የሚለውን አስተሳሰብ አትቀበሉ። ከድል በፊት በእርግጥ መውደቅ ይኖርብናል እግዚአብሔር እንድንወድቅ እንዲያውም ጠለቅ ብለን እንድንወድቅ ይፈትዳል ይህም የእኛን ደካማነት እንድናውቅ ነው። ነገር ግን ድልን ካወቅን በኋላ ውድቀት አስፈላጊ አይደለም፤ እናም ውድቀት በተከሰተ ጊዜ ያልተለመደ ይሆናል። በእዳም ውስጥ ትዝታዜ፤ ሕይወተ ቢስነት፤ ችግረኛነት፤ ቆሻሻነት ይሰማናል፤ በዚህም ምክንያት የሚሰማንን እንሆና ለን። ዛሬ ግን በክርስቶስ ቅድስና ክብርና ድል እንዳለን እናውጃለን። ስለሆነም እነዚህን ነገሮች በሕይወታችን እንለማመዳለን።

እውነትን እያያችሁ ጸጋን በመቀበል እደጉ

እስቲ አሁን እውነተኛ እድገት ምን እንደሆነ እንመልከት። ድልን ካገኘን በኋላ ቀጣዩ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ግደግ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንዶች ድልን ካገኘሁ በቂ ነው በማለት እድገትን ሳይፈልጉ ዝም ብለው ይኖራሉ። በእርግጥ ድልን አግኝተው ይሆናል። በበሩ ሳይገባ ግንም ሰው መንገዱን ቁልቁል ሊራመድ አይችልም ነገር ግን ግወቅ ያለ ባችሁ የድሉን ጉዳና ብቻ ነው። ግደግ ያለው ከድል በኋላ ብቻ ነውና። እስከ አሁን ድልን ያግየሁት በምናውቃቸው ኃጢአቶች አቅጣጫ ነው። በምናውቀው ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ለእድገት በተሠወረውም ጭምር ድል ያስፈልገናል።

የምታውቋቸውን ኃጢአቶች በሚመለከት እንደምሳሌ እስቲ ንዴ ትን እንውሰድ። በክርስቶስ ያለውን ድል ካወቃችሁ ትዕግሥታችሁ መሻ ሻል እስከግያስፈልገው ድረስ ፍጹም ሆኖ ይሆናል። ለምን? ምክንያ ቱም ይህ ፍጹም የሆነ ትዕግሥት ክርስቶስ ራሱ ለእናንተ የሰጠው ነውና። እናንተ አሁን ያላችሁ ትዕግሥት ጌታ በምድር ላይ ለሠላሳ

ሦስት ዓመት ተኩል ሲመላለስ ከነበረው ትዕግሥት ጋር አንድ ነው፤ ስለዚህ ዛሬ እናንተ ያላችሁ ትዕግሥት ከዚህ የበለጠ ሊሻሻል አይችልም። ይህም ማለት በምታውቁት ኃጢአት ላይ የክርስቶስን አሸናፊነት አንጸባረቃችሁ ማለት ነው።

ይሁን እንጂ ትኩረት ያልሰጠናቸው ኃጢአቶች አሉ። የክርስቶስም ድል በእነዚህ ኃጢአቶች ላይ አልተንጸባረቀባቸውም ስለዚህ እነዚህን ኃጢአቶች በሚመለከት ዮሐንስ ወንጌል ምዕ.17 ላይ አንድ ቃል እንይ «በእውነትህ ቀድሳቸው...» /ዮሐ 17:17/ በአንድ ወገን 1ኛ ቆሮ 1:30 እንዲህ ይለናል– «እግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ፣ ቅድስናም፣ ቤዛነትም በተደረገልን፣ በክርስቶስ ኢየሱስም የሆናችሁ ከእርሱ ነው።» በሌላ በኩል ዮሐ 17:17 እንዲህ ይላል:– «በእውነትህ ቀድሳቸው» በእውነት በቅድስና የሚያነጻን ክርስቶስ ነው። ለቅድስና ያለንን ብቃት የሚያሰፋው እውነቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ በሙሉ የሚረዳው ማን ነው? ማንም አይችልም። ሁላችንም ልንረዳው የምንችለው ቀስ በቀስ ነው። እውነቱ፣ ትክክለኛው የቱ እንደሆነና ስሕ ተቱ የቱ እንደሆነ ይነግረናል፣ ስለሆነም ከዚህ በፊት ኃጢአት እንደሆኑ የማናውቃቸውን ብዙ ነገሮች አሁን ኃጢአት እንደሆኑ እንረዳለን። ከሁለት ሳምንት በፊት ሕይወታችን እንደ ኃጢአት የማይቆጥራቸው ነገሮች አሁን ግን ኃጢአት መሆናቸውን እንገነዘባለን።

ለምንድነው በአሁኑና በአለፈው መካከል እንዲህ ያለ ልዩነት ያለው? ምክንያቱ የበለጠ የእግዚአብሔርን ቃል በተረዳን መጠን ብዙ ኃጢአቶች እየተገለጡ ስለሚሄዱ ነው። የበለጠ ኃጢአቶች እየተገለጡልን በሄዱ መጠንም ክርስቶስ ይበልጡን በሕይወታችን እያስፈለገን ይመጣል፣ ስለሆነም ኃጢአቶችን የመግለጡ አቅም እያደገ በመጣ መጠን ክርስቶስ አንዲኖረን ማስፈለጉ የበለጠ እያደገ ይሄዳል። እስቲ ዕለት በዕለት የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ እናንብብ፣ በዚህ ጊዜ ኃጢአተኝነት ምን እንደሆነ እያወቅን እንሄዳለን። የበለጠ ስለኃጢአት ባወቅን መጠን ክርስቶስ እንዴት ድላችን እንደሆነና እንዴትም ድልን እንደሚሰጠን እንዲያሳየን እግዚአብሔርን የበለጠ እንጠይቀዋለን።

ስለዚህ የእውነቱ ብርሃን በእርግጥ ለማደጋችን አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ይህ የእውነት ብርሃን ብዙ ስህተቶችንና ጥቅመቢስነታችንን ስለሚያሣየን ነው። የእውነቱ ብርሃን ያለንበትን እርግጠኛ ሁኔታ ስለሚገልጽ ብቃታ ችንም እንዲሁ እያደገ ይሄዳል። ብቃታችንም የበለጠ እያደገ ሲሄድ ክርስቶስም የበለጠ ሕይወታችን እየሆነ ይሄዳል።

በሁለተኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ ሦስት ውስጥ ያለውን ቃል በጣም እወደዋለሁ:- «... በጌታችንና በመድኅኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ።» 2ኛ ጴጥ 3:18 እድገቱ በጸጋ ነው። በጸጋ እንጂ ወደጸጋ ውስጥ የሚያድግ ማንም አማኝ የለም።

ጸጋ ማለት እግዚአብሔር ለእኔ ያደረገው ማለት ነው። ስለሆነም «በጸጋ ማደግ» ማለት እግዚአብሔር ለእኔ ብዙ እንዲያደርግልኝ ያስፈልጋል ማለት ነው። ያ ነው በጸጋና በእውነቱ መካከል ያለው ግንኙነት። እውነቱ የሚነድለኝን ነገር ሲጠቁም ጸጋ ደግሞ የሚያስፈልገኝን ነገር ይሞላል። ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር እውነት ብቻ ሳይሆን እርሱ ጸጋውም ጭምር ነው። በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበሩት ሰዎች ሁልጊዜ ይወድቁ ነበር። ምክንያቱም እነርሱ እውነቱ ቢኖራቸውም ጸጋው ስላልነበራቸው ነው። እነርሱ ሕጉ ነበራቸው ነገር ግን ሕጉን ለመጠበቅ ኃይል አልነበራቸውም። ሕጉ በሙሴ በኩል ቢመጣም ጸጋና እውነቱ ግን በክርስቶስ በኩል ስለመጣልን እግዚአብሔርን እናከብረዋለን፣ እናመሰግነዋለን። ዛሬ እውነት የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለመግለጽ ጸጋው ደግሞ የጐደለንን ለመሙላት አሉልን።

ከእንግዲህ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ቀርባችሁ እንዲህ ትጸልዩ ይሆናል:- «እግዚአብሔር ሆይ እኔ ለዘለዓለም ርዳታ የሚያስፈልገኝ ምስ ኪን ነኝ፣ ዛሬ ለርዳታ መጥቻለሁ ነገና ከነገ ወዲያም እንደገና እመጣለሁ በየቀኑ ልግስናህ አለኝና ተመስገን» ብላችሁ በዚህ ሁኔታ ወደ እርሱ ከቀረባችሁ በጸጋ እያደጋችሁ ትሄዳላችሁ። ስለሆነም እርሱ ለእናንተ ኃላፊ እንዲሆን ትፈልጋላችሁ ስለዚህም ስህተታችሁን በተረዳችሁ ቅጽበት መጀመሪያ የምታደርጉት ነገር መፀለይ ነው። በዚህ ጊዜ አንድ ትምህርት ደግሞ ትማራላችሁ:- «እኔ በራሴ ልለወጥ አልችልም፣ ራሴንም ለመለወጥ ፈጣሪም እግዚአብሔር ሆየ

ስለድክመቴ አመሰግንሐለሁ አከብርሃለሁ አንተ ሽንፈቴን ሁሉ ልታስወ ግድልኝ ትችላለህ» ብላችሁ በየጊዜው ድክመታችሁ እየታወቃችሁ በመጣ ቁጥር የክርስቶስ ኃይል እየሸፈናችሁ ይሄዳል። አልችልም ባላ ችሁ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነቱን እየገለፀላችሁ ይሄዳል። ያለማቋረጥ ይህን ብታደ ርጉ በማያቋርጥ እድገት ታድጋላችሁ።

እንደተነጋገርነው የማናስተውላቸው ብዙ ኃጢአቶች አሉ፣ በቃሉ መሠረት ካስተዋልናቸው ግን በፍጥነት ኃጢአታችንን መናዘዝና ክርስቶ ስም በውስጣችን የእርሱን ሕይወት እንዲያስቀምጥ መጸለይ አለብን። እዚህ ላይ አንድ ምስክርነት እንድናገር ፍቀዱልኝ፣ አንድ ሰው የማይገባ ነገር አደረገብኝና እኔም ጥቂት የቁጣ ቃላት ተናገርኩት። እነዚህን ቃላት መናገር እንዳልነበረብኝ አውቃለሁ፣ ይሁን እንጂ እንዲህ ብዬ ተጯገ ትኩኝ፣ እርሱ ሆን ብሎ መጥፎ ነገር ሰርቶብኛል፣ ይቅርታም አልጠየ ቀኝም፣ ታዲያ እኔ በእርሱ ላይ ብቀጣ ስህተቴ ምንድነው? ብዬ አሰብ ኩኝ። ሆኖም እግዚአብሔር እኔ ይቅርታ እንዳደርግ ጠየቀኝ ታዛዥነቴን ለመፈፀም ይቅርታ አድርጌለት ነበር። ይሁን እንጂ አሁንም መጥፎ ሰው እንዳልሆንኩ አሰብ ነበር። ነገር ግን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት የእውነት ብርሃን ለእኔ የገለጸውን ማድረግ አቅቶኝ ነበር። ማድረግ ያለብኝ «ጠላትህን ውደድ» /ማቴ 5:44/ የሚለውን ነበር። እርሱን መውደድ ከቻልኩ ማንንም ሰው መውደድ እንደምችል አሰብኩ። በእውነቱ ለተናገርኳቸው መጥፎ ቃላት ይቅርታ የጠየቅኩበትን ደብዳቤ አዘጋጅቼ ነበር። ነገር ግን እንደተገነዘብኩት ልወደው አልቻልኩም። ስለሆነም ደብዳቤውን ልልክለት አቃተኝ። ምንም እንኳ ይቅር ብለውም ልወደው ግን አልቻልኩም። ይህን ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር እውነት ነው ስላለ አለማፍቀር ኃጢአት ነው። የእምነት ውጊያ ተዋግቼም ማሸነፍ ፈለግኩኝ። ስለሆነም አምላኬ ራሱ የማፈቅርበትን ፀጋ እስካላበዛልኝ ድረስ ለራሴ እንደማልችል ተናገር ኩኝ። በዚያን ቀን ጠላቴን ለመውደድ ቻልኩኝ። ያም ማለት በአንድ ወገን እውነት መውደድ እንዳለብን ሲነግረን በሌላ ወገን ደግሞ ጸጋው እንድንችል ይረዳናል። እንደ እኔ ሁሉ አንዳንዴ በጥቂት ሴኮንዶች

ውስጥ ጠላታችሁን መውደድ ትችሉ ይሆናል። አንዳንዱ ደግሞ ብዙ ጊዜ ይወስድባችኋል።

ወይዘሪት ፊስች ባቸር በብዙ መልክ የምታስቸግራት አንድ የሥራ ባልደረባ ነበረቻት። በንግግርም የሚግባቡ አልነበሩም። ሁልጊዜም የህ ሳቧ ተቃራኒ ሆና ታስቸግራታለች። ይህች ሴት ወይዘሪት ፊስች ባቸርን በሰዎች ፊት ለማቃለል የምትፈልግ ትመስል ነበር። እህት ፊስች ባቸር ይህችን ባልደረባዋን ልትታገሳት ሞክራ ነበር፣ ነገር ግን ይህን ሁኔታ እን ዴት እንደምትቋቋመው ጨንቋት ነበር። ይህች ባልደረባዋን ባየቻት ቁጥር ጥሩ ሰላምታ እየሰጠቻት ትህትናዋን ለማሳየት ትሞክር ነበር። በው ጫዊ ሁኔታ ሁሉም ነገር ደህና ይመስል ነበር። ነገር ግን በውስጥ አንድ የተበላሸ ነገር ነበር።

አንድ ቀን እህት ፈስችባቸር በ1ኛ ጴጥ 1:22 ላይ ያለውን እው ነት አነበበች፣ «ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማ ማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በእርሳችሁ ከልባችሁ አጥብ ቃችሁ ተዋደዱ»። ለራሷም እንዲህ አለች፣ ይህችን የሥራ ጓደኛዬን እስከዛሬ እንደሚገባው አልወደድኳትም፣ ከአሁን በኋላ በፍጹም ልቤ ልወዳት እችላለሁን? ብላ ራሷን ጠየቀች፣ እንዲህም ጸለየች፣ «እግዚአ ብሔር ሆይ በዚህ ነገር ላይ ምንም ድል የለኝም፣ ኃጢአት መሆኑን ተገንዝቤአለሁ፣ አንተ ወንድሞችን ሁሉ ከልቤ አጥብቄ እንድወድ ተናግ ረሃል፣ ነገር ግን እኔ አልቻልኩም» በማለት እግዚአብሔር ከዚህ ኃጢ አት እንዲያወጣት ጠየቀች፣ ሰዎችን አትጠላም ነበር ነገር ግን ለማፍቀር አልቻለችም። ያቺን የሥራ ባልደረባዋን ባገኘች ቁጥር እሷን ለማፍቀር የምትችለውን አደረገች፣ ነገር ግን ይህ የማይቻል ሆነባት። አንድ ቀን ወደ ቤቷ ገብታ በሯን ዘጋች ንስሐም ገባች፣ እግዚአብሔር ሆይ እሷን ማፍቀር አለብኝ፣ ነገር ግን አልቻልኩም። ይህ ኃጢአት ነው። ዛሬ እኔ እሷን ለማፍቀር ካልቻልኩ ምን ሊመጣብኝ ነው? የክርስቶስ ፍቅር ልቧን እስኪሞላው ድረስ ለሦስት ሰዓት ያህል ጸለየች። በዚያ ቅጽበት ለዚያች እህት ቢያስፈልግ ለሞት እንኳ ዝግጁ ሆነች። መውደድ ብቻ ሳይሆን በፍጹም ልቧ ወደደቻት። በዚያ በልቧ ባለው ፍጹም ፍቅር ለዚያች ለሥራ ባልደረባዋ ሌሊቱን ሙሉ ጸለየች። በሚቀጥለው ቀን

ከሰዓት በኋላ ሥራዋን ስትጨርስ እህት ፈስችባቸር እንደገና ለዚያች እህት ጻለየች። በውጤቱም በዚያች ባልደረባዋ ላይ ድልንና ኃይልን አገኘች።

አዎን ይህ በዮሐንስ 17 ላይ ላለው ቃል ምሳሌ ነው። «በእውነትህ ቀድሳቸው» ዮሐ 17:17። ይህ ነው በጸጋ ግደግ ግለት። እውነት ኃጢአትን እንድንመለከት ያደርገናል፣ ጸጋ ደግሞ ያንን ኃጢአት የምናሸንፍበትን ኃይል ይሰጠናል። እያወቃችሁ ወደ ውድቀት እንድትገቡ አትፍቀዱ፣ በየእለቱ በጸጋ ግደግ አለባችሁና።

ቻይና ውስጥ ጌታን የሚያገለግሉ ሦስት እንግሊዛውያን ወጣት ሴቶች ነበሩ። አንዷ እጮኛ ያላት ስትሆን ሌሎች ሁለቱ ግን ሳያገቡ ለመኖር ወስነው ነበር። ነገር ግን የታጨችው እህት ከሁሉ ይልቅ ደስተኛ ያልሆነች ነበረች። ምንም እንኳ እጮኛዋ አዘውትሮ ደብዳቤ እየፃፈ ሊያረጋጋት ቢሞክርም እሷ ግን ሐዘን ይሰማት ነበር። የማትረካ ሰው ነበረች።

አንድ ቀን በክፍሏ ውስጥ ሆና ብቸኝነት ከፉኛ ስለተሰማት አለቀሰች። ሌሎች እህቶችም ለምን ብቸኝነት ይሰማሻል ብለው ጠየቋት። እጮኛዋ አዘውትሮ አይጽፍላትም ብለው አሰቡም። ቀጠሉና ሰው ሁሉ ብቸኝነት የሚሰማው ቢሆን ኖሮ የእኛን ያህል ብቸኝነት የሚሰማው አይኖርም ብለው ገመቱ። እነዚህን ቃላት ከተናገሩ በኋላ ወደ ክፍላቸው ተመለሱ። ከዚያም እነርሱ ራሳቸውም ብቸኝነት ተሰማቸው። ለራሳቸውም እንዲህ አሰቡ፣ ብቸኝነት ሊሰማን ይገባል ምክንያቱም ያለጥሩ ምግብና ያለጥሩ መኖሪያ ቦታ በቻይና ውስጥ ለጌታ እየደከምን ነውና አሉ። በጣም ይገርማል፣ ኃጢአት ምንኛ ተላላፊ በሽታ ነው።

መረበሻቸው እየቀጠለ ሲሄድ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ያላቸውን ቃል አሰቡ። «እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ማቴ 28:20። በተጨማሪም የዘማሪውን ቃል አስታወሱ፣ «የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፣ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠግበኸኝ፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስሐ አለ።» መዝ (16)11 ተንበርክከውም ሲጸልዩ ጌታ ሆይ ብቸኛ እንደሆንን ግሰባችን ኃጢአት ነው። አንተ እስከ ዓለም ፍፃሜ ከእናንተ

ጋር ነኝ ብለሃል፣ ስለሆነም የብቸኝነትን ስሜት ኃጢአት መሆኑን እናምናለን፣ አንተ ተናግረሃል፣ አንተ ከእኛ ጋር ስትሆን ሙሉ ደስታ አለን፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስሃ አለ አሉ። በእርግጠኝነት ይህን ኃጢአት ከተገነዘቡት በኋላ ብቸኝነት ፈጽሞ ወደ እነርሱ አልተመለ ሰም፣ ሃሌ ሉያ!

በየቀኑ በሕይወታችን ውስጥ አዲስ ኃጢአት ወይም አዲስ ውድቀት እናይ ይሆናል። ይሁን እንጂ በየቀኑ አዲስ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦ ታው ሊኖር ይችላል። እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል፣... ዮሐ 1:16 ደጋግመን ጸጋውን መቀበል አለብን።

አንድ በሕንድ ውስጥ ለጌታ የምትሠራ እህት በጣም ትጨነቅ ነበር። አንድ ቀን ፊሊጲስዩስ 4:6ን አነበበች፣ « በነገር ሁሉ በፀሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።» መጨነቅና ምስጋና አለ ማቅረብም ኃጢአት መሆኑን ተመለከተች። ኃጢአት የሆነን ነገር በተገነ ዘብን ጊዜ ወደ ጌታ ቀርበን እስቲ እንናዘዝ፣ በተጨማሪም ጌታ በውስ ጣችን መኖሩን እንተማመን፣ ይህ ለሕይወታችን እድገት ይሆንልናል።

በክርስቶስ ያለ ድል ፍፁም የሆነ ሲሆን ምንም ዓይነት መሻሻልም አያስፈልገውም። ነገር ግን የድሉ አድማስ ያለማቋረጥ እያደገ የሚሄድ ነው። እያንዳንዱ የሚቀበለው ብርሃን የተለያየ ነው። ብዙ ብርሃን የተቀ በለ የበለጠ ያድጋል፣ በአንጻሩ ያነሰ ብርሃን የተቀበለው አነስተኛ እድገት ይኖረዋል። ኃጢአት ምን እንደሆነ የበለጠ የሚያውቀው የበለጠ ከእግዚ አብሔር ይቀበላል፣ በአንጻሩ ኃጢአት ምን እንደሆነ አነስተኛ እውቀት ያለው አነስተኛ ስጦታን ከእግዚአብሔር ይቀበላል።

እውነትና ጸጋ በእኛ ላይ ያላቸውን ግንኙነት መረዳት ይኖርብናል። በየቀኑ በእግዚአብሔር ፊት እየተገኘን እንዲህ በማለት እንፀልይ። «ጌታ ሆይ ምስጋናና ክብር ላንተ ይሁን። እኔ በራሴ የምችለው አንድም ነገር የለም። ደካማና የማልችል ሰው ነኝ። በየቀኑ ጸጋህንአብዛልኝ ብርሃንህን

አብራልኝ።» በእንዲህ ዓይነቱ ሕይወት ውስጥ ስናልፍ ብንወድቅም እንነሣለን፣ ከድልም ወደ ድል እንሸጋገራለን። በየቀኑ በዚህ ሁኔታ ከተ ራመድን በሕይወታችን እያደግን እንሄዳለን። ሁሉ በክርስቶስ ለክርስቶስ ሆኗልና።

ሃሌሉያ! ይህ ፍፁም መዳን ነው። እግዚአብሔር እያደግንና ከጊዜ ወደጊዜም የበለጠ ወደፍፁምነት እየተሸጋገርን እንድንሄድ ይመራናል። ሠይጣን ምንምሊያደርግ አይችልም። ክርስቶስ አንዴ ይህን ባላጋራችንን ስላሸነፈልን እግዚአብሔር ይክበር።

ምዕራፍ 9

የድል ድምፀት

«ዘግዳንህ ደስ ይለናል፣ በአምላካችንም ስም ከፍ ከፍ እንላለን።»

«እንዲህም ሆነ፣ ከዚህ በኋላ በሞዓብና የአሞን ልጆች ከእነርሱም ጋር ምዑናው ያን ኢዮሣፍጥን ሊወጉ መጡ።»

...ኢዮሣፍጥም ፈራ፣ እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ፊቱን አቀና፣ በይሁዳም ሁሉ ጾም አወጀ።

...አምላካችን ሆይ፣ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣ ብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፣ የምናደርገ ውንም አናውቅም፣ ነገር ግን አይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው።

...ይሁዳ ሁሉ፣ በኢየሩሳሌም የምትኖሩ፣ አንተም ንጉሡ ኢዮ ሣፍጥ፣ ስሙ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኋል:- ሰልፉ የእግዚ አብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና ከዚህ ታላቅ ወገን የተነሣ አትፍሩ፣ አትደንግጡም።

...የይሁዳ ሰዎች ወደ ምድረ በዳ ግንብ በመጡ ጊዜ ሕዝቡን አዩ፣ እነሆም በምድሩ ሁሉ ሬሳ ሞልቶ ነበር፣ ያመለጠም ሰው አልነበረም።

...በአራተኛውም ቀን በበረከት ሸለቆ ውስጥ ተሰበሰቡ፣ በዚ ያም እግዚአብሔርን ባረኩ፣ ስለዚህም ያስፍራ እስከ ዛሬ ድረስ የበረከት ሸለቆ ተባለ። የይሁዳና የኢየሩሳ ሌም ሰዎች፣ በፊታ ቸውም ኢዮሣፍጥ፣ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ደስ አሰኝ ቶአቸዋልና በደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ዘንድ ተመለሱ። በበገናና በመሰንቆ በመለከትም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ እግዚ አብሔር ቤት ገቡ። 2ኛ ዜና 20:1.3.12. 15. 24. 26–28

የአሸናፊነት ሕይወት ራሱን የቻለ ድምፀት እና «ቃል» አለው። በመዝ 20:5 «በግዳንህ» የሚለው ሐረግ «በድልህ፣» ደስ ይለናል» የሚለው ደግሞ «እናውጃለን» ተብሎ ሊተረጉም ይቻላል። ስለዚህ ድልህን እናውጃልን ግለት ይቻላል። ደህንነት እና ድል አይነጣጠሉም። ድል እንዳገኘህ በምን ታውቃለህ? መልሱ በመዝ 20:5 ላይ ተቀምጧል «ድልህን እናውጃለን»

ድልና ድልን ማወጅ የተለያዩ ነገሮች ናቸው

ድል በክርስቶስ ብቻ የሚሰጥና የሚደረግ ሲሆን «ድልን ማወጅ»

ግን የእኛ ሥራ ነው። «ድል» የማሸነፍ ሥራ ሲሆን «ድል ማወጅ» ግን ከድል በኋላ የሚወጣ ቃል ነው። ለምሳሌ:- ድሮ የኳስ ጨዋታ ተጫውተን ስናሸንፍ የእኛ ትምህርት ቤት ደጋፊዎች በደስታ ይጮሃሉ፣ በሌላ አነጋገር እኛ ድል ስንቀዳጅ ደጋፊዎቻችን ድሉን ያውጃሉ ማለት ነው።

ማንኛውም ክርስቲያን በክርስቶስ ያገኘውን ድል ሊያውጅ ይገባል፣ ማለትም በጌታ ማዳን ምክንያት የደስታችን ማስተጋባት ማለት ነው። «ሃሌ ሉያ» ብለን እንጩህ ክርስቶስ አሸናፊ ነው። ሃሌሉያ ያላለ ተሸናፊ ነው ማለቴ አይደለም ነገር ግን የድል ብስራት ማወጃችን እጅግ አስፈላጊ ነው። ያለዚያ ሰዎች ያገኘነውን ድል ሊጠራጠሩት ይችላሉ። ጴጥሮስአነጋገሩ ገሊላዊ ነበር፣ በዚህም ገረዲቷ ልትለየው ችላለች። የእኛም አነጋገር ገሊላዊ ሆኖ ሰዎች የገሊላውን ኢየሱስ እንደምንከተል ይወቁልን።

የኢዮሣፍጥ አዋጅ

በብሉይ ኪዳን ዘመን ይሁዳ ኢዮሣፍጥ የሚባል ንጉሥ ነበረው። እስቲ በሁለተኛ ዜና 20 ላይ ያለውን ታሪክ እንመልከት። «እንዲህም ሆነ፣ ከዚህ በኋላ የሞዓብና የአሞን ልጆች ከእነርሱም ጋር ምዑናውያን ኢዮሣፍጥን ሊወጉ መጡ።» /ቁ.1/

በዚያን ጊዜ የይሁዳ መንግሥት እጅግ ደከማ ነበር። እርዳታንም የምትሻና በሐላት የተወረረች ነበረች። ኢዮሣፍጥ ወደራሱ ሲመለከት በተፈጥሮውም በፍርሃት የተሞላ ነበር። ምን ማድረግ ነበረበት? ምንም ቢፈራ ከሕዝቡ ጋር እግዚአብሔርን ሊፈልግ ፈቱን አቀና። እንዲህም ብሎ ጸለየ፣ «እግዚአብሔር ሆይ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣብንን ታላቅ ሠራዊት እንቃወም ዘንድ አንችልም ነገር ግን አይናቻችን ወደ አንተ ናቸው።» ከራሳቸው የሆነ ኃይልና ብርታት ምንም እንደሌላቸው መለከረ። ኢዮሣፍጥ የተሻለ እርምጃ ወሰዷል። ይህም በአምልኮ ብእግዚአብሔር ፊት መውደቅ ነው። ይሁዳ እና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ወደቁ። ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም በጠላት ሲከበቡ ኢዮሣፍጥ ሌዋውያንን ጠርቶ አቆማቸውና እግዚአብሔርን እንዲያ መሰግኑ አደረገ፣ በቅዱስ ዝማሬ ከጦሩ ፊት አስለፋቸው። ይህን ሲያደርግ ኢዮሳፍጥ አብዶ ይሆን? አይደለም። ሌዋውያንም ጦሩንና ድንጋዩን ሳይፈሩ እግዚአብሔርን በማመስገን ዘመሩ። ይህ ታዲያ የድል ብሥራት ነው። ይህ የድል ድምፅ የሚወጣው እግዚአብሔር ድል ሰጥቶህ ጠላቶችህን እንዳሸነፍህ ስታውቅ ወይም ስትረዳ ነው።

ፈተና ወዳንተ በሚመጣበት ጊዜ ሰዎች እንድትታገለው ይመክሩሃል። እግዚአብሔር ግን ለእኛ ግልፅ ያደረገው ነገር በቁ.22 እርሱን መባረከና ማመስገን ነው። ጌታን መባረከና ማመስገን በሚኖርበት ጊዜ የጠላት መሸነፍና መውደቅ አለ። ይሁዳ ሁሉ ወደምድረበዳው ግንብ በመጡ ጊዜ ውጤቱ ምን ነበር? የይሁዳም ሰዎች ወደ ምድረበዳ ግንብ በመጡ ጊዜ ሕዝቡን አዩ። እነሆም በምድሩ ሁሉ ሬሳ ሞልቶ ነበር። ያመለጠም ሰው አልነበረም። /ቁ.24/ እግዚአብሔር ድልን ሲሰጥ አንድም የሚያመልጥ ጠላት አይኖርም።

«ዝማሬውንና ምስጋናውንም በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞአብ ልጆች በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦርን አመጣባቸው።» የሚለው ቃል እጅግ ታላቅ የሆነ ምስጢር አለው። እግዚአብሔር ሊሠራ የሚችለው አንተ ማመስገን ስትጀምር ነው። አንተ ስታመሰግን እርሱ ድልን ይሰጥሃል።

የተለያዩ ፈተናዎች ሊናሩብህ ይችላሉ፤ ይህም በሥጋህ መድከም፣ የግይመች ሁኔታ ውስጥ መሆን፣ የኑሮ ቀውስ ሊሆን ይችላል። አንተም ምን ላደርግ እችላለሁ? እንዴትስ ልቋቋመው እችላለሁ? እያልክ በጥያቄ ትወጠር ይሆናል።

ስለድል ልታውቅ ትችላለህ ቢሆንም ግን ይህን ጥያቄ በመጠየቅ ብቻ ድምፅህ ትክክል እንዳልሆነ ተረዳ። ፈተና ወዳንተ ሲመጣ ወይም አስቸጋሪ ነገር ሲገጥምህ ሃሌ ሉያ! በል። ሃሌ ሉያ ስትል ጠላት ይሸነፋል። አምላክህ እግዚአብሔር አንተ ስታመሰግን መሥራት ይጀምራል። ስትዘምር ድሉ የአንተ ነው። የአንተን አለመቻል የእግዚአብሔርንም ሁሉን ቻይነት ብቻ መመስከር በቂ አይደለም። ከልብህ ሃሌ ሉያ ብለህ ዘምር! «እግዚአብሔር ሆይ ይህ ፈተና ወደ እኔ ስለመጣ እና እኔም ደካማ ስለሆንኩ አመሰግንሃለሁ፣ ምክንያቱም የአንተ ድል የእኔ ነውና» በል። አዮሣፍጥን አስብ! የዘመረውና ያመሰገነው ድሉ የእርሱ መሆኑን ስላመነ ነው። በኢዮሣፍጥ ዓይን ጠላቶቹ ሁሉ የሞቱ ሬሳዎች ነበሩ። ስለዚህም በማመስገኑ እና በመዘመሩ ገፋ። ድንጋዩንና ጦሩንም አልፈራም፣ ምክንያቱም ጠላቶቹ «እንደሞቱ» ቆጠሯቸዋልና ነው። የእሥራኤል ልጆች ግን ወደ ምድረ በዳው በመጡ ጊዜ ያዩት የጠላቶቻቸውን ሬሳ ነበር።

ምስጋናና ዝማሬ፣ ሁለት ደረጃዎች

«በአራተኛው ቀን በበረከት ሸለቆ ውስጥ ተሰበሰቡ፤ በዚህም እግዚአብሔርን ባረኩ፤ ስለዚህም ያ ሰፈር እስከ ዛሬ ድረስ የበረከት ሸለቆ ተባለ። የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች በፊታቸውም ኢዮሣፍጥ፤ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ ደስ አሰኝቷቸዋልና በደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ተመለሱ።» 2ኛ ዜና 20:26–28

ምስጋናና ዝማሬ ሁለት ደረጃዎች አሏቸው፤

* የመጀመሪያው ከመከናወን በፊት (ከድል በፊት)
* ሁለተኛው ከመከናወን በኋላ (ከድል በኋላ)

በአሁኑ ጊዜ ያለው ትልቁ ስህተት ከድል በፊት አለማመስገናችን ነው። ብዙ ወንድሞችና እህቶች ድካማቸውን ያውቃሉ፣ በራሳቸው ችሎታ እንደሌላቸው ይረዳሉ፣ ክርስቶስም ድላቸው እንደሆነ ያውቃሉ፣ ነገር ግን ሃሌ ሉያ አሸንፋለሁ፣ አይሉም።

አንዳንድ ወገኖች «እግዚአብሔር እንደሚሠራ ማየት እፈልጋለሁ እግዚአብሔር በዚህ ሥራዬ ውጤታማ ነገር ሲያደርግ ማየት አሻለሁ» ይላሉ። የሚያመሰግኑት ነገ መሥራቱን ካዩና ካረጋገጡ በኋላ ነው። ኢዮ ሣፍጥ ያመሰገነው ሁለት ጊዜ ነው። አሸናፊ ሁልጊዜ እጥፍ ምስጋና ይና ረዋል። ይህም ሥጋዊ ዓይኖቹ ከማየታቸው በፊት እና በኋላ ነው። ይህም የድል ድምፅ ወይም ቃና ነው። ነገር ግን ምስጋናና ዝማሬ በማይኖርበት ወቅት ተጋድሎ ኖጋ ቢስ ይሆናል።

አንተ ስለ ድል መገኘት ትናገር ይሆናል፣ እኔ ግን በሃሌ ሉያ ስለመ ሞላትህ እጠይቅሃለሁ። ምክንያቱም ሃሌ ሉያ የድል ድምፅ ነውና።

ትክክለኛ ድምፅ እውነተኛ ድልን ይገልፃል። ያሸነፈ ሁሉ ያሸናፊ ነትን ቃል ያወጣል፣ ደስተኛና አመስጋኝ ነው።

የአንድን ሰው የአነጋገር ሁኔታ በማየት የየት አገር ሰው እንደሆነ መለየት ይቻላል። በተመሳሳይ ሁኔታ የአንድን ክርስቲያን ቃል በማዳ መጥ እንዳሸነፈና እንደተሸነፈ መለየት ይቻላል። የመንፈሳዊ ድል ነጥቡ ያለው ሃሌ ሉያ! በማለት ላይ ነው። ምንጊዜም ወደ ራስህ ብቻ ከተመ ለከትህ አሸናፊ አትሆንም። ነገር ግን ክርስቶስን ከተመለከትህ ወዲያውኑ አየሩን በሃሌ ሉያ ትሞላዋለህ። ጌታ ይመስገን! ፈተናው ሲበረታ፣ የሞዓብና የአሞን ልጆች እጅግ ብዙ ቢሆኑም ውጊያው የእግዚአብሔር ነውና ኃላፊነቱን ሁሉ እርሱ ይወስዳል። የድል ድምፅ ደስታ፣ ምስጋናና ዝማሬ በሕይወትህ ከሌሉ እየተሸነፍህ ነውና አስብበት።

ድልን በደስታ ውስጥ ጠብቅ

በነህምያ 8:10 ላይ «የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ አላቸው።» የሚል ጥቅስ እናገኛለን። እግዚአብሔር የሰጠን ሕይ

ወት የሚገለጠው ከደስታ ውስጥ ነው። ጌታ ኢየሱስ ይተነፍሰው የነበረው አየር በደስታና በበረከት የተሞላ ነው።

ጌታ ይመስገን ማለት ካልቻልን ያለነው በተሸነፈ ሕይወት ውስጥ ነው ማለት ነው። ስለዚህም ድላችን በጌታ ደስታ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። የጌታ ደስታ በውስጥህ ክሌል ተሸናፊ ሆነሃል ማለት ነው። በመሆኑም አሣ በውሃ ውስጥ እንደሚኖር ድላችንም በጌታ ደስታ ውስጥ ሊሆን ይገባል።

በመከራ ውስጥ መደሰት

ደስተኞች ለመሆን የምንችለው እንዴት ነው? አስደሳች ነገሮች ሲገጥሙንና ድልን ስንቀዳጅ መደሰትና ማመስገን ቀላልና የተለመደም ነው። ነገር ግን ታሉ ደስ ቦሚያሰኙ ነገሮች ውስጥ እንድንደሰት ይነግረናል።

«...በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና...» /2ኛ ቆሮ 8:2/

በዚህ ቃል ላይ የመቄዶንያ አማኞች በብዙ መከራ ውስጥ ሆነው ደስ ታቸው ግን የበዛና የተትረፈረፈ እንደነበር ያሳየናል። የክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወት የአሸናፊነት ሕይወት ነው። እስቲ ጠላትም እያጠቃን እንኳ እግዚአብሔርን በታላቅ ደስታ እናመሰግነው እንባርከው። «ወንድሞች ሆይ! ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት።» ያዕ 1:2 «በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ እጅግ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፣ ለምስጋናና ለክብር ውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል።» 1ኛ ጴጥ 1:6–7

እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፣ አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አምናችሁ፣ የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ፣ በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ይላችኋል።» 1ኛ ጴጥ 1:8–9

«ወዳጆች ሆይ፣ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚ ሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ አትደነቁ፣ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ፣ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ። ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ።1ኛ ጴጥ 4:12–15

እነዚህ ጥቅሶች በፈተና ውስጥ እንዴት ማለፍ እንዳለብን ያሳዩናል። ያዕቆብ ስለ ልዩ ልዩ ፈተና ወይም መከራ ይነግረናል። የተጠበቀ ይሁን ያልተጠበቀ፣ ከጠላት ይምጣ ከወዳጅ፣ ከዓለማውያን ወይም ከወንድ ሞች በትክክለኛ ወይም ያለምክንያት የተለያዩ ዓይነት ፈተናዎች ቢመጡ ብንም በደስታ ከምንጓዘው ጉዞ ሊያደናቅፉን እንደማይችሉ ተገልጧል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደስታ ሲናገር «ታላቅ ደስታ»፣ «የተትረፈረፈ ደስታ»፣ «ሙሉ ደስታ» ሊገለጽ የማይቻል ደስታ እያለ ነው የሚገ ልጸው። ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ስጦታ ታላቅ ደስታ ሲሆን ሐዘን ቢኖር በት እንኳ ለጥቂት ጊዜ ነው። ለመሆኑ ሐዘን ተፈቅዶዓል? በሐዘን ውስጥ ሆነን ከዓይናችን እንባ እየወረደና እየፈሰሰ በዚህ ውስጥ ደስታ ይኖራል? 1ኛ ጴጥ 1:8 ላይ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያሳየው «የእምነታ ችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ በማይነገር ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ ይላችኋል»። ይህ ደስታ ሊነገር የማይችል ነው። ስንት ጊዜ ይሆን እንባችን ሳይደርቅ ሃሌ ሉያ ብለን የጮህነው? ስንቴስ እንባችን እየፈሰሰ አፋችን ተከፍቶ እግዚአብሔር ይመስገን ብለናል? በአንድ በኩልእንባቸውን ሲያወርዱ በሌላ በኩል እግዚአብ ሔርን የሚያመሰግኑ ብዙ ሰዎች አሉ። በ1ኛ ጴጥ 4:12 መሠረት የምንደ ሰተው በፈተና ውስጥ ሆነን ብቻ ሳይሆን ገና ፈተናው ወደ እኛ ሲመጣ ነው በሌላ አነጋገር ፈተና ሲመጣ በደስታ ልንቀበለው ይገባል። ስለዚህ ፈተና ወደ አንተ ሲመጣ ጌታን ልታመሰግን ይገባል። አንዳንድ ወገኖች ፈተና ገና ሲመጣባቸው ዓይናቸውን ይጨፍናሉ። ነገር ግን ጴጥሮስ የሚለን ፈተና እንደመጣ ስታዩ እግዚአብሔርን አመስግኑ ነው።

ቸር በምትባለው ቦታ አንዲት እህት ባሏ ከቤት እንደወጣ የሚወዱት ሴት ልጃቸው ሞቷችባቸው። ብዙ ወንድሞችና እህቶች ሊያፅናኗት መጥተው ነበር፤ አይናቿ በሐዘን የእንባ ፈሳሽ ቢያፈልቁም ፊቷ ግን በፈገግታ እና በብሩህነት ተሞልቶ ነበር። ስትመለከርም፣ የልጇ መሞት እጅግ ቢያሳዝናትም ልትረዳው በማትችለው መንገድ ውስጧ በደስታ እና በሐሴት እንደተሞላ ተናግራለች፤ እግዚአብሔርንም ታመሰግንና ትባርክ ነበር። ሊያፅናኗት የመጡ ወንድሞችና እህቶች ጭራሽ ተፅናንተው ይመለሱ ነበር።

ዛሬ እኛ በምድር ላይ ያለን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ምሳሌዎች ነን። ምሳሌነታችን ውብ ነውን? ከዓለም የተለየን ነን? ዓለም ሲያሳትስ የምናሳትስ ሲስትም የምንስት ከሆነ ድላችን እምኑ ላይ ነው? ለዓለም ደስታችንና ጥንካሬያችንን ልናሳይ ይገባል። ምንም ዓለም እንደ እብድ ብትቆጥረንና ለዚህም ምክንያት የሆንንን ክርስቶስን ልታደንቀው ባትችልም በመከራችን የክርስቶስን ድል እናረጋግጣለን፤ እግዚአብሔርም በዚህ ይከብራል።

«ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፋውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።» ማቴ 5:12

ሰዎች ሲነቅፉአችሁ እንታገ ሳለን ትሉ ይሆናል፤ ሲሰድቡአችሁም መልስ አንሰጥም ትሉ ይሆናል። ትዕግስተኛ መሆንና መልስ አለመስጠት በቂ ነው ብላችሁ አታስቡ። ግሽንፋችሁ እርግጥነው። ዓለም ሊያደርገው የሚችል ነገር ነውና፤ የቡድሀና የኮንፊሺየስ እምነት ተከታዮች ሊያደርጉት ይችላሉ። እናንተ ከእነርሱ የተለያችሁ መሆን አለባችሁ። የሰዎችን ነቀፌታ ለራሳችሁ እንደ አስደሳች ነገር ቁጠሩት። ሰዎች በሚያሳድዱአችሁ ጊዜ በክርስቶስ ደስታ «ጌታ ሆይ አመሰግንሃለሁ፤ አባርከሃለሁ» ማለት አለብን። ምክን ያቱም ስደቱን እንደ አንድ አስደሳች ነገር ወስዳችሁ ድላችሁ እውነተኛ ነውና ደስ ይላችኋል፤ ሐሴትንም ታደርጋላችሁ። ዓለም ሊከፍለው የሚች ለውን ዋጋ በመክፈል ብቻ የምንቀዳጀው ድል እውነተኛ ድል ሳይሆን የይስሙላ

ድል ነው። እግዚአብሔር ሲሠራ በውጤቱ ሁልጊዜ ትደሰታ ላችሁ ነገር ግን ተቃዋሚዎች በሚነቅፉአችሁ ጊዜ ደስተኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ? ወይስ በቅላሉ አንገታችሁን ደፍታችሁ ፀጥ ትላላችሁ? ብዙዎች ይሰደዳሉ፣ ብዙ እህቶች በባሎቻቸው መከራ ይቀበላሉ፣ ብዙዎች በሐሰት ክፉ ይነገርባቸዋል፣ እናንተ እንዲህ ያለው መከራ ቢደርስባችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች ሲላኩላችሁ ድል እንዳደረጋችሁ ታስቡ ይሆናል፣ ሆኖም ከጌታ የተሰጠ ድል ላይሆን ይችላል የእርሱ ድል በነቀፈታና በስደት ውስጥ ሆናችሁ እርሱን እጅግ እንድትባርኩና እንድ ታመሰግኑ የሚያስችላችሁ ነው። ደግሚ ልንገራችሁ፣ እግዚአብሔርን ባትባርኩና ባታመሰግኑትም አሸናፊዎች ናችሁ። ድል አድራጊነት የሚገ ለፀው ግን በማመስገንና በመባረክ ነው።

አንድ ጊዜ በጌታ ያለ ወንድም አውቶቡስ ውስጥ በአጋጣሚ ከ አንድ ጠላቱ ጉን ተቀምጦ ያገኘዋል። ድል ለማግኘት የጠላቱን ከመኪና መውረድ እንዲያፋጥንለት እግዚአብሔርን ይለምን ነበር። በመውረጃው ቦታም በደረሰ ጊዜ «እርይ ይህንን ድል ማግኘት ቀላል አይደለም» አለ። ነገር ግን ይህ ድል እውነተኛ የእግዚአብሔር ድል ነውን? በግል ፀነት እንድናገር ይፈቀድልኝ፣ ይህ ድል የውሸት ድል ነው፣ ሰው ሠራሽ ድል ነው፣ ባዶ ድል ነው። እግዚአብሔር የሰጠው ድል ቢሆን ኖሮ ትዕግሥት እንዲሰጠው እግዚአብሔርን መለመን አያስፈልገውም ነበር። በዚህ ፈንታ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፍ ያደረገውን እግዚአብሔርን ያመሰግንና ይባርክ ነበር። ጉዞው ረጅም ቢሆንም እንኳ ምንም አይመስለውም ነበር።

«ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ» ፊሊጵ 4:4 ምንጊዜም የእግዚ አብሔር ቃል ደስታን ሲገልጽ «ታላቅ ደስታ ወይም ሙሉ ደስታ ወይም የሁልጊዜ ደስታ ማለቱ የተለመደ ነው። እዚህ ጋ ሁልጊዜ ማለት ዘለቄታ ያለው ማለት ነው። ሰምታችኋልን? አልሰማችሁ እንደሆነ «ደግሚ እላለሁ ደስ ይበላችሁ» ፊሊጵ 4:4 ጳውሎስ ሊለው የፈለገው ይህንን ነው። ቀደም ብዬ ያልኩትን ካላስተዋላችሁት እንደገና እላለሁ ደስ ይበላችሁ ማለቱ ነው። እግዚአብሔር የሚሰጠው ሕይወት ደስታ

የሞላበት ነው። ደስታ የክርስቲያን የየዕለት እርምጃ መግለጫ ነው። ስቃይና ደስታ ቢኖርም ደስታ አለ። የዚህ ተቃራኒ መጨነቅ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በፊሊጵ 4:6 ላይ «በአንዳች አትጨነቁ» ይለናል። እኛ የምንጨነቅበት ምክንያት እንዳለ እናስባለን። የእግዚአብሔር ቃል ግን በአንዳች አትጨነቁ ይለናል። ስለዚህ ሁልጊዜ ደስ ይበለን። ለአንድ ቀን እንኳ ደስ ሳንሰኝ ስንውል በደለኞች እንሆ ናለን። በአንድ ስብሰባ ላይ አንድ ጊዜ አንድ ወንድም ለጎብረቱ «በአ ንዳች አትጨነቁ» ሲል ተናገረ። ይህንን መልእክት ስትሰማ ደስ ያልተ ሰኘች አንዲት እህት ሁሉም ሰው እንዴት የማይጨነቁ ሊሆኑ ይችላሉ? አለች። ወንድሞች ከእህቶች ይበልጥ የሚጨነቁ ከሆነ እህቶች ከወን ድሞች የተሻለ ነገር ስላገኙ ይሆናል ብላ አሰበች። ይህንን ያለችበት ምክንያት ደግሞ በዚያን ዕለት ወንድሞች ስለ ዕለቱ ምግብ ተሰግሚነት ተጠይቀው ስለነበር ነው። ይሁን እንጂ መጨነቅ በእርግጥ ኃጢአት እንደሆነ ሳትረዳ ጌታ አልተዋትም። ምስጢሩ ሲገባትም ድልን ልትጨብጥ ቻለች።

«ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤ ስደክም ያንጊዜ ኃይለኛ ነኝና። 2ኛቆሮ 12:10 ሐዋርያው ድካምን፣ መንገላታትን፣ ችግርና ስደትን እንዲሁም ጭንቀትን የወሰዳቸው እንደ ደስታ ነው። ማናችሁም ምን እንደሚደርስባችሁ ልታውቁ አትችሉም። በምድር ላይ ጉዞአችሁ ሙሉ ለሙሉ ችግር የሌለበት እንደሆነ ትገነዘባላችሁ። ጥቂቶቻችሁ የታመሙ ዘመዶች ሊኖሩአችሁ ይችላል፣ ጥቂቶቻችሁ በጣም የምትወዱት ወዳጅ ሞቶባችሁ ይሆናል፣ ምን ታደርጋላችሁ? ታጋሽ መሆናችሁን ለጌታ ብትነግሩ ይህ ቃላችሁ ተሸናፊነታችሁን ያረጋግጣል። ነገር ግን ጌታ ሆይ እባርክሃለሁ፣ አመሰግንሃለሁ ብትሉ ድል ትቀዳ ጀላችሁ። በዚህ ክርስ ቶስ በእናንተ ይገለጣል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃይሉን እንዲያሳይ እድል ሰጥታችሁታል፣ ደስተኞችም ትሆናላችሁ። የየቀኑ ምድራዊ ሕይ ወታችሁ እንዲህ ሊሆን ይገባል። በጌታ ደስ ይበላችሁ፣ ምስጋናና ክብር ለስሙ ስጡ።

«በሁሉ አመስግኑ» ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና» 1ኛ ተሰ 5:18 «እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያ መሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ሰም አድርጉት።» ቆላስ 3:17 እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ሐሳቡን ያጠቃልላሉ። እግዚአብሔርን እናመሰግን ሃሌ ሉያ እንበል። በዓለም ያሉ ሰዎች በእኛ ሁኔታ ግራ ሊጋቡ ይችላሉ። ሆኖም እኛ በሁሉ እናመሰግናለን። በሁኔታዎች ሁሉ የምናመሰግን ብንሆን ምንም መከራና ፈታኝ ነገር ሊቋቋመን አይችልም። ምንም ሊነካን አይችልም። የሚያ ስተንን ለመቋቋም እምነት አለንና በፈተና እግዚአብሔርን እንባርካለን፣ እናመሰግናለን፣ ምክንያቱም ታዛዦች ነንና።

አንዳንዶች ትዕግሥትን እንደምቃወም አድርገው ተረድተውኝ ይሆናል። በነገራችን ላይ ትዕግስት እጅግ ውድ ነገር መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ፣ ትዕግሥት እንዲኖረን ያስፈልጋል። ነገር ግን የሚለያየን ሳይሆን እንደ ሠንሠለት እርስ በርሳችን የሚያያይዘን ሊሆን ይገባል። 1ኛ ቆሮ 1:10 ይህ ትዕግሥት በሐዘን ወይም ያለፈቃደኝነት በፍርሃት የሆነ ትዕግሥት ሳይሆን በደስታ ላይ የተመሠረተ ትዕግሥት ነው። በሁሉ ማመስገን ከደስታ ጋር መከራን መቀበል ሁሉ በሁሉ ትዕግሥተኛ በመ ሆን የክርስቲያን እለታዊ ኑሮ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት ደግሞ የሦስተኛው ሰማይ ሕይወት ነው።

ከአሸናፊዎች በላይ

ሕይወት ደስታ ከሌለበት የድል ሕይወት አይባልም የምንልበት ምክንያት ምንድነው? ለምንስ ነው የአሸናፊነትን ሕይወት ለመግለጥ ደስታ የሚያስፈልገው? «በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» ሮሜ 8:37 እግዚአብሔር የሚሰጠን ድል ከአሸናፊ ዎች በላይ ነው።

እግዚአብሔር የሚሰጠንን ድል «እንደተትረፈረፈ ጽዋ» ልናስበው ይገባል። እግዚአብሔር የሚሰጠን ድል ከተፈጥሮ ወሰን ያለፈና የተረፈ ነው። ያዘዘንም የድል ትዕዛዝ «እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉውን አትቃወሙ

ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙ
ርለት፤ እንዲከስህም እጀ ጠባብህን እንዲወስድ ለሚወድ መጐናጸፊያህን
ደግሞ ተውለት። ግንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ
ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ፤ ለሚለምንህ ስጥ ከአንተም ይበደር ዘንድ
ከሚወደው ፈቀቅ አትበል።» ማቴ 5: 39–41 የሚል ነው።

የመተው ሕይወት ትከክለኛው የእግዚአብሔር ድል ነው። ክርስቶስ
በእኛ ከኖረ በሁሉ ነገር ውስጥ ልንደሰት እና ልናመሰግን እንችላለን።
ከዚህም የተነሣ ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር ይመስገን! እያልን ከአሁን እስከ
ዘለዓለም ልንኖር እንችላለን።

ምዕራፍ 10

መለየት

«ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ በሕይወትም ያሉት ስለእነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዲኖሩ ስለሁሉ ሞተ» 2ኛ ቆሮ 5:14:15

«ብልቶቻችሁንም የዓመጻ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደም ትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ» ሮሜ 6:13

«ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።» ሮሜ 6:16

«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራሄ አለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለኢአ ምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነውን ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» ሮሜ 12:1–2

«ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልግድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኩሰትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳ ቀረባችሁ፣ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ።» ሮሜ 6:19

«አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔር ተገዝታችሁ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፣ መጨረሻውም የዘለዓለም ሕይወት ነው።»

መለየት የድል ነሽ ሕይወት ከተቀዳጀን በኋላ የሚሆን ነው፣ ይህም ደኅንነትን ከተቀበልን በኋላ ይቀጥላል። ጌታ ስለኔ ከሞተ እና ከተነሣ በኋላ እኔ መጀመሪያ ላደርገው የሚገባኝ ራሴን ለእርሱ መስጠት ነው። አንዳንዶች ራስን መስጠት ከድል በፊት ነው ይላሉ ማለትም «ራስህን ከሰጠህ በኋላ ታሸንፋለህ።» ነገር ግን በሮሜ 6:13 ላይ ራስን ከመ ስጠት በፊት የድል ነሽ ሕይወት ውስጥ መግባት እንዳለብን ያመለ ክታል። አንድ ነገር ግልፅ ሊሆንልህ የሚገባው «በሞት እና በትንሣኤ» ካልሆነ አንድ ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር ሊያቀርብና ሊሰጥ አይች ልም። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር የሞተና የተነሣ ራሱን ቅዱስ መስዋዕት አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል።

ቀደም ሲል ከክርስቶስ ጋር ስለመሞታችን ተነጋግረናል፣ በመሆኑም አሁን ሞተን በክርስቶስ ሕያዋን ሆነን እንኖራለን። « እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆና ችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ ሮሜ፥ 6፥11

በመሆኑም በሮሜ 6:13 ክርስቲያን ራሱን የሚሰጠው የድል ነሽ ሕይወት ውስጥ ከገባ በኋላ ነው። ከዚህ ሕይወት ውጭ ግንም ራሱን ቢሰጥ እግዚአብሔር ይህንን ሕይወት አይቀበለውም። ምክንያቱም እርሱ (እግዚአብሔር) የአዳምና የሞት የሆነውን ነገር አይፈልግምና ነው።

የድል ነሽ ሕይወት ሳይኖር የአንድ ሰው ራስን መለየት ወይም መስጠት አስተማማኝ አይሆንም። ምክንያቱም አንድ ቀን ራስን መስጠት በተከታዩ ቀን ለሥጋ መኖር ሌላ ጊዜ ለጌታ ፈቃድን ማስገዛት በሌላ ቀን በራስ ፈቃድ መሄድ ይሆናል።

የመለየት መሠረትና ምክንያቱ

ሮሜ 6 እና ሮሜ 12 ስለ መለየት ይናገራሉ። ለምንድነው ሰውነ ታችንን ለእግዚአብሔር ሕያው መስዋዕት አድርገን የምናቀርበው? ጳውሎስም በእግዚአብሔር ርኅራሄ (ምሕረት) እለምናችኋለሁ ይላል። የእግዚአብሔር ርኅራሄ ምንድነው? ሮሜ 1–8 ያሉት ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ይናገራሉ። ከ9–11 ባሉት ምዕራፎች ደግሞ ጳውሎስ ለአይሁድንና ደኅንነትን በሚመለከት ይናገራል።

ቀደም ሲል እኛ ኃጢአተኞች ነበርን ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር መጥቶ ደሙን በማፍሰስ ዋጀን። ምዕራፍ 3 እና 4 ስለ «ደሙ» እና ስለ «እምነት» ሲናገር ምዕራፍ 5 ስለ «ይቅርታ» እና ስለ «ጽድቅ» እንዲሁም ከ6–8 ያለው ምዕራፍ ስለ «መስቀሉ» ይገልጣል። በአንድ በኩል ደሙ ለኃጢአታችን ስርየት ስለፈሰሰ ይቅርታን ስንቀበል መስቀሉ ደግሞ የአሮጌውን ሰው መሞትና ከኃጢአት ኃይል መዳናችንን ያሳያል።

«ክርስቶስ በመስቀል ስለ እኛ ሞተ ስለ እኛም ሕያው ሆኖ ይኖራል በእኛም ውስጥ ይኖራል ለዚህም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።» በመ ሆኑም በዚህ የእግዚአብሔር ምሕረት መሠረት በጳውሎስ ውስጥ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንድናቀርብ ይለምነናል። እግዚአብሔር ሲፈጥረንና ሲዋጀን ዓላማውን ልንረዳ ያስፈልጋል። ይህም ልጁን በእኛ ሊገልጥና የልጁም ክብር ተካፋዮች ሊያደርገን ነውና።

ዓለም ሳይፈጠር በፊት እንኳ እግዚአብሔር አንድ ዓላማ ነበረው። ይህም የልጁን መልክ የሚመስሉ ብዙ ልጆች ማግኘት ነው ሮሜ 8:29 እንዲህ ይላል፣ ልጁ «በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስ ቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአልና» ይህንን ነገር እግዚአብሔር ለምን አደረገ? ምክንያቱም አስቀድሞ የል ጁን መልክ እንዲመስሉ ስለወሰነ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅዱ ነው። «የገዛንና የዋጀን የራሱ ሊያደርገን ነው።» እግዚአብሔር

የራሱ ሊያደርገን ሁለት ዓይነት መንገድ አለው፤ አንደኛው ከእርሱ በኩል ሲሆን ሁለተኛው ከእኛ በኩል ባለው መሰጠት ነው። በክርስቶስ በኩል ልጁን ለእኛ እንዲሞት ላከና ዋጀን፤ በመሆኑም በመግዛት ደንብ መሠረት እኛ የእርሱ ባሪያዎች ነን፤ እግዚአብሔር ስለገዛን የተመሰገነ ይሁን።

አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ አለው፤ «በቤትህ የተወለደ በብርህም የተገዛ ፈጽሞ ይገረዝ» ዘፍ 17፥13 ሃሌ ሉያ! እኛ ከእግዚአብሔር መወለድ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም ተገዝተናል። በእግዚአብሔር ተገዝተናልና የእርሱ ነን፤ እግዚአብሔርም ነፃ አውጥቶ ናል። በመዋጀት ደንብ እኛ የእግዚአብሔር ነን ቢሆንም የግድ እንድናገለግለውና እንድንከተለው አያደርግም።

ሰይጣንን፣ ዓለምን፣ ሆዳችንን፣ ጣዖታትን በማምለክ ልንበድል እንችላለን። በዚህ ጊዜ ታዲያ የእርሱ ዝምታ አንድ ቀን «አምላኬ ሆይ እኔ የአንተ ባሪያ ነኝ፤ የማገለግልህም ስለገዛኸኝ ብቻ ሳይሆን አንተን ማገለገል ደስ ስለሚለኝ ነው» ብለን በኛ በኩል ወደ እርሱ እስክንመጣ ነው። በሮሜ 6:16 ራስን ስለ መስጠት ድንቅ የሆነ ሐሳብ ያቀርባል። እኛ የእግዚአብሔር ባሪያዎች የሆንነው ስለገዛን ብቻ ሳይሆን «ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ» ስለሚል ነው።

ስለዚህም በአጠቃላይ እግዚአብሔር የእርሱ ያደረገን በሁለት ዓይ ነት ሁኔታ እንደሆነ እናያለን። አንደኛው የእርሱ ባሪያዎች ነን ምክንያ ቱም በልጁ ደም ገዝቶናልና ነው። ሁለተኛው በፈቃደኝነትና በደስታ ለእርሱ ራሳችንን ባሮች አድርገን እናቀርባለን።

በሕጋዊ መብትና ባለቤትነት አንጻር ስናየው እኛ እግዚአብሔር በዋጀን ዕለት የእርሱ ባሪያዎች እንሆናለን ነገር ግን ከልምምድ አንጻር ስናየው ግን በእውነት እኛ የእርሱ ባሪያዎች የምንሆነው በደስታ ራሳችንን ለእርሱ ስንሰጥ (ስንለይ) ነው።

ማንም መቼስ የእግዚአብሔር ባሪያ እንደሆነ ያውቃል። ግን የእርሱ ባሪያ ለመሆን አማኝ ሁልጊዜ በፈቃደኝነት ራሱን ሊሰጥ ይገባል። በመ ሆኑም ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ልብ በመረዳቱ «እንደማያስገድድ»

ነገር ግን «ፈቃድን እንደሚፈልግ» ይናገራል /ሮሜ 12:1/ እግዚአ ብሔር የሚደሰተው ሕዝቡ በደስታ ራሱን ሲሰጠው ነው።

የድል ሕይወትና ደኅንነት በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ቤዳንን ወቅት ለመለየት (ለመሰጠት) እንሞክር ይሆናል። ምክንያቱም የተ ቀበልነው አዲስ ሕይወት ይህን እንድናደርግ ይገፋናልና ነው። የጸን ሰው ሁሉ ለጌታ መኖር እንዳለበት ያውቃል፣ ነገር ግን ኃይል (ጉልበት) እናጣለን። ለጌታ እንዳንኖር በብዙ ዓይነት ተግራሪ ነገሮች እንከበባለን፣ ቢሆንም እግዚአብሔር ይመስገን አርሱ ክርስቶስን ሰጠን። ይህም ራሳችንን ለእርሱ እንድንሰጥ ነው። በኃጢአት ሞተን ሕያው መስዋዕት ልንሆን አንችልም። ድነን እንኳ በኃጢአት ውስጥ እየኖርን ራስን መስጠት አይቻልም። ነገር ግን አሁን የድልን ጎዳና እንሂድ፣ ክርስቶስ ሕይወታችንና ቅድስናችን ነው። ከዚህ በኋላ ራሳችንን በፈቃደኝነትና በደስታ እንሰጣለን።

ሮሜ 6 ራስን ስለማቅረብ ይናገራል። በተለይ «ብልቶቻችንን ለእግዚአብሔር የጽድቅ የሙር ዕቃ» አድርገን ማቅረብ እንደሚናርብን እንዲሁም ሮሜ 12 «ሰውነትን» ሕያው መስዋዕት አድርጎ ስለማቅረብ ይናገራል። የእግዚአብሔር ፍላጎት ሁለንተናችንን ለእርሱ እንድንሰጥ ነው። ይህ በራሳችን አይሆንም ነገር ግን በክርስቶስ ሁሉን እንችላለን።

በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ዕብራዊ ባሪያ ጌታውን ስድስት ዓመት ያገልግላል፣ በሰባተኛው ዓመት በነፃ ሊሄድ (ሊወጣ) ይችላል። ነገር ግን ጌታውን ከወደደና ነፃ መውጣት ካልፈለገ ጌታው ወደ ፈራጆች ያመጣውና ወደ ደጁና መቃኑ አቅርቦ በወስፌ ጆሮውን ይበሳዋል፣ ለዘለዓለምም ጌታውን እያገለገለ ይኖራል። /ዘፀ 21:2–6/

እግዚአብሔር አድኖን በደሙ ገዝቶናል። በሚጠፋ ብርና ወርቅ ሳይሆን በውድ ልጁ ደም ገዝቶናል 1ኛ ጴጥ 1:–18–19። በመሆኑም ብዙዎች ጌታን የሚወዱ እስከ መጨረሻው ባሪያዎች ሆነውለት፣ ደግ ቸውን አፍስሰውለት አልፈዋል። እንደነዚህ ክርስቲያኖች መሆን ከፈለ ግህ እንዲህ ብለህ ጸልይ፣ «አ ጌታ ሆይ አንተ ትወደኛለህ፣ አድነኛ ኛል፣ ነፃም አውጥተኸኛል፣ እኔም እወድሃለሁ። በመሆኑም ለዘለዓለም አገለግልሃለሁ»።

የምንሰጣቸው ነገሮች

1. ሰዎችን:-

መጀመሪያ ልንሰጥ የሚገባን «የምንወዳቸውን» ነው። ጌታን ከወላጆችህ፣ ከሚስትህ፣ ከልጆችህና ከጓደኞችህ በላይ ካልወደድህ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀመዝሙር አይደለህም። እግዚአብሔር ያዳነህ አንተ ነትህን ሁሉ የራሱ ሊያደርግህ ነው። ብዙ ዕንባ፣ ስቃይና ሐዘን ልብህን ከጌታ ሊመልሱህ ይታገላሉና ጸንተህ ቁም። እግዚአብሔር የአሸና ፈነት ሕይወት እንድንኖር ሊያደርግ እንድንታዘዘው፣ ፈቃዱን እንድና ደርግና እንድናውቀው ነው።

ሰዎችንና ጓደኞቻችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሳንሰጥ እግዚአብሔርን ማስደሰት አንችልም። «በሰማይ ያለኝ ምንድነው? በምድርስ ውስጥ ከአንተ ዘንድ ምን እሻለሁ?» መዝ /73/:25 እንዲህ ማለት አለብን፣ «ጌታ አምላኬን በፍጹም ልቤ፣ በፍጹም ነፍሴ፣ በፍጹም ኃይሌ እወድዳለሁ» ማቴ 22:37 ይስሐቅን ከያዝክ በመስዋዕቱ ላይ ኢጋድ መው። በአሁኑ ጊዜ የብዙ ክርስቲያኖች ውድቀት ከሰዎች ጋር መጣበቃቸው ነው።

2. ጉዳዮችን:-

ብዙ ጉዳዮቻችንን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳንጠይቅ በራሳችን እናደርጋለን። በአንድ ሥራ ላይ ጊዜን ማዋል ጥሩ ሊመስል ይችላል፣ ነገር ግን ያን የምንሠራውን ሥራ ለጌታ ካላስረከብን ውጤቱ አያምርም። አገልግሎታችንን ሁሉ ለእርሱ ልንሰጠው ያስፈልጋል።

3. ነገሮችን:-

ሰዎችንና ጉዳዮችን ብቻ ሳይሆን ያለንን ነገር ሁሉ ለጌታ ልንሰጥ ይገባል፣ ማለት ጊጣችንን፣ ንብረታችንን፣ ወይም ልብሳችንን ሊሆን ይችላል። በሕይወታችን ትንሽ መስሎን ለጌታ ያልሰጠነው ነገር የተባረከ ሕይወት እንዳንኖር ሊያግድብን ይችላል። አንዳንዶች ገንዘብ ያባክናሉ፣

ሌሎች ደግሞ ሀብታቸውን ይጠብቃሉ። እነዚህ ሁለቱም ግን በእግዚ አብሔር ፊት ተቀባይነት የላቸውም። ስለዚህ ገንዘብ ስናገኝ እንዲህ ብለን እንጸልይ፣ አ ጌታ ሆይ ይህ ገንዘብ ሁሉ ያንተ ነው፣ በዚህ ውስጥ ለቤቴ ወጪ ስለምትሰጠኝ አመሰግንሃለሁ፣ ነገር ግን እኔ ከተጠቀም ኩበት በኋላ የተረፈኝን ልሰጥህ አይገባም።

እግዚአብሔር ከዓለም እኛነታችንን ብቻ ሳይሆን ንብረታችንንም አውጥቷል። የእሥራኤል ልጆች ከግብጽ ሲወጡ አንድ ሰኮና ትተው አልወጡም። ስለዚህ እኛ አንድ ሰኮና እንኳ ለዓለም መተው አይገባንም። በራሳችን ይህን አንችልም፣ ነገር ግን በእርሱ ይቻላል። ቃሉ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» ይላልና ነው። ይህ ማለት በጌታ ኃይል ስሞላ ሁሉን እችላለሁ ማለት ነው። በሚያስፈልጉኝ ቁሳዊ በረከቶችም እባረካለሁ፣ እነርሱንም ለእርሱ እሰጣለሁ።

4. ራሳችንን :-

ሰዎችን ነገሮችንና ጉዳዮችን ብቻ ሳይሆን በመጨረሻ ራሳችንን ልንሰ ጠው ይገባል። ወደፊት ምን እንደሚጠብቅህ አላውቅም። በብልጽግና መንገድ ላትሄድ ትችላለህ። ወይም ደግሞ በስቃይ መንገድ ላትጓዝ ትችላለህ። ያም ሆነ ይህ በረከትም ይሁን መከራ ራስህን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ልታቀርብ ይገባል። እግዚአብሔር እንዲጠቀምባቸው ፈቃደኞች የሆኑ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው የድል ሕይወት ኖረዋል፣ ምክንያቱም ራሳቸውን ሰጥተዋልና ነው።

ለመሆኑ የምንሰጠው ምናችንን ነው? የምንሰጠው ሰውነታችንን ሕያው መስዋዕት አድርገን ነው። ምክንያቱም ራሱን ለእግዚአብሔር ለይቶ ሰውነቱን የማይሰጥ የለምና። ስለሆነም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መላ እኛ ነታችንን ለጌታ ልንሰጥ ይገባል፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አፋችን፣ ጆሮአ ችን፣ አይናችን፣ እጃችን፣ የውስጥ አካል ክፍሎቻችን ሁሉ የራሳችን አይደሉም።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሁለት እጆቻችን፣ ሁለት እግሮቻችን፣ ሌሎችም ሁሉ የጌታ ናቸው። በእነርሱም ላይ ምንም መብትና ሥልጣን የለንም።

1ቆሮ 6:19 ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ አይደለምን? ይላል።

ራስን የመስጠት ውጤት

ራስን የመስጠት ውጤት ምንድነው? በሮሜ 6እና12 ሁለት ውጤቶች ተገልጠዋል። በሮሜ 6:22 ውጤቱ የጽድቅ (የቅድስና) ፍሬ ማፍራት ሲሆን በሮሜ 12 ግን ራስን የመስጠት ውጤቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዲከናወን ያደርጋል።

በሮሜ 6 ላይ ራስን የመስጠት ውጤቱ ከኃጢአት በመንፃት የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆነን የጽድቅ ፍሬ እንድናፈራ ነው። /ቁ.22/ ቀን በቀን በድል ሕይወት ልንመላለስ እንችላለን። በሮሜ 12 ራስን የመስጠቱ ውጤት ደግሞ ፍጹምና በጎ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ምን እንደሆነ ፈትነን እናውቅ ዘንድ ነው።

በሕይወት ዘመንህ ማመንና ማመስገን ብቻ በቂ አይደለም። የመጨረሻው ደረጃ በሰውነትህ እግዚአብሔር የራሱን ቅድስና እንዲገልጥ ራስህን አሳልፈህ መስጠት ነው። ቀድሞ ራስህን ለመስጠት ጉልበትና ኃይል የለህም ነበር። አሁን ግን የድልን ሕይወት ስለተቀዳጀህ ራስህን መስጠት ትችላለህ። ልታስተውለው የሚገባ ነገር ቀድሞ ራስህን ለእግዚአብሔር መስጠት አትችልም ነበር፣ አሁን ግን የችሎታ ጥያቄ ሳይሆን የፈቃደኝነት ጥያቄ ነው።

አንድ በአውስትራሊያ ያለ ራሱን በሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጠ ወንድም ነበር። አንድ ጊዜ በባቡር ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር ሲሄድ ካርታ እንዲጫወት ጠየቁት። ነገር ግን ለጓደኞቹ የመለሰላቸው መልስ እንዲህ ነበር፣ «አዝናለሁ፣ አልጫወትም ምክንያቱም እጅ የለኝም። እነዚህ እጆቼ ቀደም ብለው በክርስቶስ ደም ተገዝተዋል» የሚል ነበር። ምክንያቱም ሰውነቱ ሁሉ የጌታ ነውና።

በየጊዜው ከኃጢአትና ከፈተና ጋር ትጋጠማለህ፣ ስለዚህም እጅ እንደሌለህ ልትናገር ይቻላል። ይህ ታዲያ በሮሜ 6 መሠረት ራስን መስጠት ነው። እንዲህ ዓይነት ራስን መስጠት አንተን ከመቀደሱም በላይ

የቅድስና ፍሬ እንድታፈራ ያደርግሃል። በዚህ ምክንያት ራስን መስጠት ከድል በኋላ የመጀመሪያ ፍሬ ነው ማለት ነው። በሮሜ 12 መሠረት ደግሞ ለእግዚአብሔር ሰውነታችንን ሕያው መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ ነው። ይህ ዓይነት ራስን መስጠት ቅዱስና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው።

ከሞት ድነን ሁላችንም የእግዚአብሔርን ምሕረት ተቀብለናል። ስለዚህም ራሳችንን መስጠታችን በእርሱ ፊት ተቀባይነት አለው። ይህም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችን ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ ራሳቸውን ሊሰጡ ይገባል። በጌታ ደም ተጋዝተናል፤ ስለዚህም የእርሱ ነን፤ ፍቅሩ በውስጣችን ፈሷል፤ ስለዚህም ለእርሱ እንኖራለን «ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና ለራሱም የሚሞት የለም በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን።» ሮሜ 14፥7፥8 በደሙ ተዋጅተናል።

በመሆኑም ምን ዓይነት መስዋዕት ነው ለጌታ የምናቀርበው? በቃሉ መሠረት እኛ ሕያዋን ድንጋዮች ሆነን ስለምንኖር ሕያው መስዋዕት ነን ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን መስዋዕት «የሞተ» ነው። በአዲስ ኪዳን ግን መስዋዕት «ሕያው» ነው።

ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርገን ስናቀርብ የመጨረሻው ውጤት «በልባችሁ» መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ የሚለው ነው። ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም የሆነውን ፈትነን እናውቅ ዘንድ ነው።

ብዙዎቻችን ስለእግዚአብሔር ፈቃድ ሲነግ እንፈራለን። ነገር ግን ጳውሎስ ፈቃዱን እንድናውቅ ራሳችንን ልንሰጥ እንደሚገባ ይነግረናል። እስቲ ስለመልካምነቱና ስለፈቃዱ እናመስግነው። ሃሌ ሉያ! እንበል፤ በእውነት ፈቃዱ መልካም ናት፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከፋ ሐሳብ የለውም።

አንድ ወንድም ሲጸልይ፤ «ጌታ ሆይ ዳቦ እንጠይቅሃለን ነገር ግን ድንጋይ እንደምትሰጠን እናስባለን፤ አሣ እንለምንሃለን ነገር ግን እባብ

እንደምትሰጠን እናስባለን፣ እንቁላል ስንጠይቅህ ጊንጥ እንደምትሰጠን እናስባለን። ነገር ግን ጌታ ሆይ ድንቃይ ስንለምንህ ሁለጊዜ ዳቦ ትሰጠናለህ። /ሉቃ 11:11–12/ ብሎ አለ። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድና ፍቅር አይገባንም። እርሱ ለእኛ ያለው ሐሳብ የሰላም፣ የመልካም፣ እጅግ በጣም መልካም እንደሆነ አንገነዘብም።

የእግዚአብሔር ፈቃድ መልካም ብቻ ሳይሆን ፍጹምም ነው። እርሱን ለሚወዱት ሁሉ የእርሱ ፈቃድ መልካም ነው። እንዲህ እንበል፣ «ጌታ ሆይ መላ እኔነቴ የአንተ ነውና ወደፊት ለራሴ አልኖርም»

« ሞቀህም ቀዘቀዘህም ራስህን ለጌታ ከሰጠህ ሁሉ መልካም ነው።

ምስጋና

በዚህ የትርጉም ሥራ ጊዜ በተለያየ ሁኔታ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለአቶ ሚልዩን ቸርነት፣ ጽሑፍን በማረም፣ አስተያየት በመስጠትና በማስተካከል ለረዱኝ ለአቶ ደረጅ አበበ እና አዲስ አግዶ እንዲሁም ይህን ጽሑፍ በኮምፒተር በመጻፍ የረዱኝን ወ/ሪት መሠረት ሐብቴን እና የኬሚ ቢዝነስ ድርጅትን ከልብ አመሰግናለሁ።



ስለደራሲው

ዎች ማን ኒ እ.ኤ.አ. 1920 የኮሌጅ ተማሪ ሆነው ሳሉ በትውልድ አገራቸው በፋችው ኩተማ አንድ ቻይናዊ ወንጌላዊ ተማሪዎችን ሊንበኛቸው መጥቶ በሰበከው ስብከት ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው ተቀበሉ። ዎች ማን ኒ በቱ ሼንግ በራሳቸው ሕዝብ መካከል ጌታን ለማገልገል አንዳች ሳይቆጠቡ ራሳቸውን የሰጡ ታላቅ አገልጋይ ነበሩ። በዓመታት መካከል በቻይና በተለያዩ ታላላቅ ክርስቲያናዊ ጉባኤዎች፣ በቡድኖችና ግለሰቦች ላይ አገልግሎታቸው አስደናቂ ፍሬ የሰጠ፣ ታዋቂ የወንጌል ሰባኪና ቃሉን በአዲስና በትክክለኛ መልኩ የገለጡ መሆኑ በስፋት የታወቀላቸው የተከበሩ የእግዚአብሔር ሰው ናቸው።

የዎች ማን ኒ ታላላቅ ክርስቲያናዊ ሰሃ ፅሑፎች ፋይዳ ያላቸው ክርስቲያናዊ የሕይወት ገፅታዎችን፣ በእምነት የምንደርስባቸውን አዳዲስ የእድገት እርከኖች የሚያስጨብጡ፣ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ዕቅድ በቀላል መንገድ በማቅረብ የሚያስተምሩ አስተማማኝ ሥራዎች ናቸው። የጽሑፋቸው ሁሉ መካከለኛ ሃሳብ «ክርስቶስ ሕይወታችን ነው» የሚለው ነው።

የዎች ማን ኒ መጽሐፍት የክርስትናን አዲስና ደስ የሚያሰኝ መንገድ ጠቋሚዎች፣ መሠረታዊውን የእምነት መርሆ አሳማኝ በሆኑ አነሣሽ ሐሳቦች አመልካቾች እንዲሁም እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት የሚጠቀምባቸውን የእግዚአብሔርን ብቸኛ መንገዶችን በሚገባ የገለፁ ናቸው።

ታላቁ ቻይናዊ ፀሐፊና ሰባኪ ዎች ማን ኒ በቻይና የአብዮት መሪዎች የደረሰባቸውን ከፍተኛ መከራ በእግዚአብሔር ጸጋ በትዕግስት ተቋቁመው ከዚህ ዓለም ብፁዕ መሰናበትን አግኝተው በድል ነሽነት ወደ አምላካቸው የሄዱ፣ በምዕራብም ዓለም በክርስቲያናዊ ፅናታቸው መልካም ምስክርነት የሰበራቸው ወንድም ናቸው። በዚህ መጽሐፍም ለጌታ ባላቸው ያልተቆጠበ አገልግሎት ድል ነሽ ሕይወት ምን ዓይነት እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል ያገኙትን መረዳት ግልጽ በሆነ አቀራረብ አስቀምጠውልናል።